


ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

# የተቀናጀ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህር መምሪያ

# ደረጃ ሶስት

# የተቀናጀ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህር መምሪያ

## ደረጃ ሶስት

2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

**FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**
**MINISTRY OF EDUCATION**

# የተቀናጀ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህር መምሪያ ደረጃ ሶስት

አዘጋጅ፡-

መ/ርት መቅደስ ጌታቸው

መ/ር አባይነህ ሙላት

መ/ርት የኔነሽ ፍቃዱ

መ/ርት ትዕግስት አለምጸሀይ

አቶ ሰሎሞን ወንድሙ

አቶ ሰይድ ሁሴን

አቶ አሰግድ አሳሂል

አርታኢ፡-

አቶ ጥላሁን በየነ

አቶ ሽመልስ መሀመድ

ዲዛይነር፡-

ሲሳይ ደገ

አስተባባሪ፡-

አቶ ኡመር ኢማም

ወ/ሮ ሂሩት ወ/ሚካኤል

**FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**
**MINISTRY OF EDUCATION**

የባለቤትነት መብት

የአዘጋጅው ባለቤትነት መብት የተረጋገጠ ነው።

ያለትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ በባለቤትነት መብት ህግ ከተፈቀደው ውጪ የመምህሩን መምሪያ የተወሰነ ክፍል ወይም ሙሉ በሙሉ መልሶ ማሳተም፣ ማባዛት፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸት እና መልሶ በማንኛውም መንገድና ሁኔታ መጨቀም ለሚደርሰው የመንግስትና የህዝብ ጉዳት በወንጀል ህግ ተጠያቂ ያደርጋል።

የመጀመሪያ ህትመት 2017 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ምስጋና

ይህ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህር መምሪያ ለክልሎች ዝግጅት በናሙናነት እንዲያገለግል ታስቦ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ከክልሎች ጋር በጋራ የተዘጋጀ ነው። በዚህ የመምህር መምሪያ ዝግጅት ላይ ውድ ግዜያቸውን ለዝግጅቱ ጥራት ትኩረት በመስጠት በአዘጋጅነት፣ ገምጋሚነት፣ በአስተባባሪነት፣ በጥራት አስጠባቂነት እና በዲዛይን አዘጋጅነት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን። በመቀጠል ስራው በጥራት እና በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛውን ድርሻ ቢወስድም በገንዘብ ድጋፍ እና በማማከር ያላሰለሰ ጥረት የደረጉ የሁል ግዜ አጋር የሆኑት አለም አቀፍ እና ሀገር በቀል ተቋማት ለሆኑት የአለም አቀፍ የህፃናት ተራድኦ ድርጅት (UNICEF)፣ አለም ባንክ (World Bank)፣ የኢትዮጵያ ስኩል ሬዲነስ ኢኒሸቲቭ (ESRI) እና ኢዱኬሽን ሰስተኔብል ድቨሎፐመንት (ESD) ያለንን ልባዊ ምስጋና በኢትዮጵያ ህፃናት ስም ማቅረብ እንወዳለን።

# ማውጫ

## ክፍል አንድ

1.1. መግቢያ ....1
1.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት ....2
1.2.1. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነት ....2
1.2.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊነት ....2
1.3. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሆዎች ....3
1.3.1. ሕጻናት-ተኮር አቀራረብ ....3
1.3.2. ጨዋታ-ተኮር ትምህርት ....3
1.3.3. የተቀናጀ ሥርዓተ-ትምህርት ....3
1.3.4. አካቶ ትምህርት ....3
1.3.5. ሀገር በቀል እውቀት ....3
1.3.6. ከእድገታቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ ተግባራት ....3
1.3.7. የወላጆች/አሳዳጊዎችና ማህበረሰብ ተሳትፎ ....4
1.3.8. ጤናማና ምቹ የትምህርት አከባቢ ....4
1.3.9. ሁለንተናዊና ቀጣይነት ያለው እድገት ....4
1.3.10. የተመጣጠነ አቀራረብ ....4
1.3.11. የህፃናት ተከታታይ ምዘና ....4
1.4. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት አጠቃላይ ዳሰሳ ....4
1.5. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ-ትምህርት ....5
1.6. የዕድገትና መማር መስኮች ....5
1.6.1. የቋንቋ መዳበርና ተግባቦት ....5
1.6.2. የቅድመ-ሂሳብ መዳበር ....5
1.6.3. አካባቢ ሳይንስ ....5
1.6.4. የግልና ማህበረ-ስሜታዊ መዳበር ....6
1.6.5. አካላዊ መዳበርና ጤና ....6
1.6.6. የክወናና የእይታ ጥበባት ....6
1.7. የዕድገትና የመማር ብቃቶች ....6
1.8. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት የባህርይ ገጽታ ....7
1.9. ሀገር በቀል (አካባቢያዊ) እውቀትን መሠረት ያደረገ ትምህርት ....7
1.10. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት (PPE Integration) ....8
1.11. የህጻናት ንቁ ተሳትፎ በትምህርት ....9
1.12. ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ....9
1.13. ህጻናትን ማዕከል ያደረገ ትምህርት ላይ የመምህራን ሚና ....10
1.14. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሀ-ግብር የዕለት ተዕለት ተግባራት ....11
1.15. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህሪያት ....14
1.15.1. የመማሪያ አካባቢ አደረጃጀት ....14
1.15.2. ሀ. የክፍል ውስጥ አደረጃጀት ....14
1.16. የህጻናት እድገትና ትምህርት ምዘና ....15
1.17. የወላጅና አሳዳጊ ተሳትፎ በህጻናት ትምህርትና እንክብካቤ ....16
1.18. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህር መምሪያ አጠቃቀም ....17
1.19. የክፍለ ጊዜ ድልድል ....17

# ክፍል ሁለት

ዐውድ አንድ፡- ተክሎች ..... 18

1.1. መግቢያ ..... 18
1.2. ከዐውዱ የሚጠበቁ ውጤቶች ..... 18
1.3. ዐበይት ይዘቶች ..... 19
አንደኛ ሳምንት ..... 19
ሁለተኛ ሳምንት ..... 25
ሦስተኛ ሳምንት ..... 29
አራተኛ ሳምንት ..... 35
አምስተኛ ሳምንት ..... 39
ስድስተኛ ሳምንት ..... 45

አውድ ሁለት፡- ሠላም ..... 51

2.1. መግቢያ ..... 51
አንደኛ ሳምንት ..... 52
ሁለተኛ ሳምንት ..... 60
ሦስተኛ ሳምንት ..... 66
አምስተኛ ሳምንት ..... 81

አዉድ ሶስት - ቴክኖሎጅ ..... 89

3.1. መግቢያ ..... 89
3.2. የሚጠበቁ ውጤቶች ..... 89
3.3. አበይት ይዘቶች ..... 89
አንደኛ ሳምንት ..... 90
ሁለተኛ ሳምንት ..... 94
ሦስተኛ ሳምንት ..... 102
አራተኛ ሳምንት ..... 108
አምስተኛ ሳምንት ..... 112

ዐውድ አራት - እርሻ ..... 120

4.1. መግቢያ ..... 120
4.2. የሚጠበቁ ውጤቶች ..... 120
4.3. ዐበይት ይዘቶች ..... 120
አንደኛ ሳምንት ..... 121
ሁለተኛ ሳምንት ..... 129
ሶስተኛ ሳምንት ..... 135
አራተኛ ሳምንት ..... 142

አምስተኛ ሳምንት ........ 150
ስድስተኛ ሳምንት ........ 151

## ዐውድ አምስት፡- መጓጓዣ ........ 158

5.1. መግቢያ ........ 158
5.2. የሚጠበቁ ውጤቶች ........ 158
5.3. ዐበይት ይዘቶች ........ 159
5.4. የማስተማሪያ ዘዴዎች ........ 159
5.5. የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁሶች ........ 159
5.6. የምዘና ስልቶች ........ 160
አንደኛ ሳምንት ........ 160
ሁለተኛ ሳምንት ........ 165
ሦስተኛ ሳምንት ........ 171
አራተኛ ሳምንት ........ 176
አምስተኛ ሳምንት ........ 180
ስድስተኛ ሳምንት ........ 184

## ዐውድ ስድስት፡- ባህል ........ 190

6.1. መግቢያ ........ 190
6.2. የሚጠበቁ ውጤቶች ........ 190
6.3. አበይት ይዘቶች ........ 190
6.4. የማስተማሪያ ዘዴዎች ........ 191
6.5. የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁሶች ........ 191
6.6. የምዘና ስልቶች ........ 191
አንደኛ ሳምንት ........ 192
ሁለተኛ ሳምንት ........ 197
ሦስተኛ ሳምንት ........ 204
አራተኛ ሳምንት ........ 207
አምስተኛ ሳምንት ........ 211

# የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የዕለት ዕቅድ ናሙና

የት/ቤቱ ስም፡ባህርዳር ቅድመ-አንደኛ ደረጃ

የመ/ር ስም፡ አዲስ ዓለም ወዳጆ

ደረጃ፡ 3

አውድ፡ ተክሎች ሳምንት፡1

የህጻናት ብዛት፡ ወ፡ 16 ሴ፡ 25 ድ፡ 41

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ፡ 30 ደቂቃ

ዓላማዎች፦ ህጻናት ከዕለቱ ተግባራት በኋላ

- ሠላምታይለዋወጣሉ፤
- ራሳቸውንናችሎታቸውንበተህትናይገልጻሉ፤
- በአካላዊገጽታቸውእራሳቸውንይገልፃሉ፤
- የዕፅዋትን የአካል ክፍሎችይለያሉ፤
- የግልንጽህናቸውንይጠብቃሉ፤
- የተለያዩ ዕፅዋትን ስለው ቀለም ይቀባሉ

| ጊዜ | የተግባራት ርዕስ | የመምህር ሚና | የህጻናት ሚና | የትምህርት አቀራረብ ዘዴ | መማሪያና መጫዎቻ ቁሳቁስ | ምዘና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2:00-2:30 | የመቀበያ ጊዜ | ህጻናትን ጤንነታቸውንና ስሜታቸውን እያዩ ከመግቢያ በር አቀባበል ማድረግ፤ የህዝብ መዝሙር እየዘመሩ የባንዲራ ሥነ-ሥርዓት እንዲያከብሩ ማድረግ፤ ነጻ ጨዋታ እንዲጫወቱ ማበረታታትወደ መማሪያ ክፍል ማስገባት | ነጻ ጨዋታዎችን መጫዎት፣ የህዝብ መዝሙር መዘመርና ባንዲራ መስቀል፣ ወደ ክፍል መግባት | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2:30-4:00 | ክፍለ ጊዜ 1-3፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ ርዕስ፦ ራስን ማስተዋወቅ | ሰላምታ መለዋወጥ፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ ህፃናት በየተራ እየተነሱ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ማገዝ፣ ህፃናትን ወደ ውጭ ይዞ መውጣት፣ ክብ እንዲሰሩ ማድረግ፣ በክቡ ውስጥ አሻንጉሊት ወይም ኳስ በመያዝ በክቡ ውስጥ በመግባት እንዴት ራሳቸውን እንደሚያስተዋውቁ ማሳየት፣ ህፃናት ተራ በተራ ክብ ውስጥ በመግባት በጨዋታው አማካኝነት ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ መርዳት | ለጨዋታው ዝግጁ መሁን፣ መምህሯ ቸዋታውን ስትጫወት መከታተል፣ በክብ ውስጥ ገብቶ ጨዋታውን በመጫወት ራስን ማስተዋወቅ፣ ማጨብጨብ | -መንገር<br>-ማሳየት<br>-መጫወት | - አሻልጉሊት፣ ኳስ፣ የተለያዩ የአትክልትና ፍራፍሬ ስዕሎች | -ጨዋታውን ሲጫወቱ መመልከት<br>- የቃል ጥያቄ |
| 4:00-4:15 | የእረፍት ሰዓት | ህጻናት አየር እንዲወስዱ ማድረግ | ወደ ውጭ ወጥተው ተንፈስ ብለው መመለስ | | | |
| 4:15-4:45 | ክፍለ ጊዜ 4፡ መዝሙር ርዕስ፦ እንቡጥ ነኝ እኔ | ህጻናትን ለመዝሙር ማነሳሳት፣ የመዝሙሩን አቀራረብ ዘዴን ተከትለው ማዘመር፣ የመዝሙሩን ፍሬ ነገር መንገር | ለመዝሙር ዝግጁ መሆን፣ መዝሙሩን መስማት፣ ተከትለው መዘመር፣ለብቻ መዘመር፣ የመዝሙሩን ፍሬ ሲጠየቁ መንገር | -መንገር<br>-ማሳየት<br>-መዘመር | - የተፈጥሮ አበባ<br>-የንፅህና አጠባበቅን የሚያሳዩ መግለጫዎች | - የቃል ጥያቄ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4:45- 5:15 | ክፍለ ጊዜ 5፡ የግል ተግባር<br><br>ርዕስ፡ የተክሎችን የአካ ክፍሎች መለየት | የተክሎችን የአካል ክፍል የሚያሳይ ስዕል፣ የተለያዩ ተገጣጣሚ የተክል ክፍሎችን የያዘ ፐዝል ይዞ በመግባትሁሉም ህፃናት በሚያዩበት ቡታ ማድረግና የዕለቱን የትምህርት ርዕስ ማስተዋወቅ፣ በመጀመሪያ የተክሎችን የአካል ክፍሎች ስዕሉን በመመልከት እንዲናገሩ ማበረታታት፣ ጠገጣጣሚ የሆኑትን ፐዝሎች እንዲገጣጥሙ ማድረግ፣ ማገዝና ማበረታታት፣ መጠየቅ | የሚቀርበውን ስዕል መመልከት፣ የዕለቱን ተግባር ርዕስ መተዋወቅ፣ ስዕሉን በመመልከት የተክሎችን የአካል ክፍሎች መናገር፣ ፐዝሉን መገጣጠም፣ ምላሽ መስጠት | - ገለጻ<br><br>- ማሳየት<br><br>- መገጣጠም | - የተክሎችን የአካል ክፍል የሚያሳይ ስዕል<br><br>- የተለያዩ ተገጣጣሚ የተክል ክፍሎችን የያዘ ፐዝል | - ምልከታ<br><br>- የቃል ጥያቄ |
| 5:15- 5:45 | ክፍለ ጊዜ 6፡ በተግባር መማር<br><br>ርዕስ፡ ስዕል መሳል | የተለያዩ ስዕል ለመሳል የሚያፈልግሉ ቁሳቁሶችን ማቅረበረ፣ የተለያዩ ዕፅዋትን እንዲስሉና የሚመሳሰለውን ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ፣ እየተዘዋወሩ መከታተልና ማገዝ፣ ምን ምን አይነት ቀለም እንደተጠቀሙና የሳሏቸውን ዕፅዋት ብዛት መጠየቅ | የዕፅዋትን ስዕል ለመሳል መዘጋጀት፣ መምህሯ ያቀረበችላቸውን ቁሳቁስ በመጠቀም መሳል፣ የሚመሳሰላቸውን ቀለም መቀባት፣ የሳሏቸውን ስዕሎች ብዛት መቁጠርና ሲጠየቁ ምላሽ መስጠት | - መንገር<br><br>- ማሳል | • እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት፣ የተለያዩ ዕፅዋትን የያዙ ካርዶች | ስዕላቸውን መመልከት፣ የቃል ጥያቄ መጠየቅ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5:45-6:00 | የመሸኛ ጊዜ | ህጻናት ቁሳቁሳቸውን መያዛቸውን ማረጋገጥ፣በተራ ከክፍል እንዲወጡ ማድረግ፣ እስከበር ድረስ መውሰድና ከወላጅ ወይም አሳዳጊ ጋር ማገናኘት | ቁሳቁሳቸውን መሰብሰብ፣ በሥርዓት ከክፍል መውጣት፣ ከወላጅ ጋር መገናኘትና መምህራቸውን መሰናበት | | | |

የር/መ/C አስተያየት: ________________________________

ስም:____________________ፊርማ: ____________ቀን:__________

የራስ ግምገማ:

ጠንካራ ጎኖቼ: ________________________________

________________________________

ማሻሻል ያለብኝ: ________________________________

________________________________

# ክፍል አንድ

## አጠቃላይ መረጃ

### 1.1. መግቢያ

የቀዳማይ ልጅነት ጊዜ የሰው ልጅ የዕድገት መሰረት የሚጣልበት ወሳኝ ወቅት ነው:: የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ስኬት የሚጀመረው በዚህ ጊዜ ነው:: የዘርፉ ምሁራን እድሜያቸው ከ4 እስከ 6 ዓመት ክልል ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጠት አጠቃላይ እድገታቸውን ለማጎልበት አስፈላጊ መሆኑን ይስማማሉ:: በኢትዮጵያ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ለረጅም ጊዜ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን ዘመናዊው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከመምጣቱ በፊትም በአብነት እና ቁርዓን ትምህርት ቤቶች አማካይነት ህፃናት መሰረታዊ የንባብና የህይወት ክህሎቶችን እንዲማሩ ይደረግ እንደነበር ድርሳናት ይነግሩናል:: በሀገራችን ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ (ከ1908 ዓ.ም) በፊት ለኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ሥራ የመጡ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ዜጎች ህጻናትን የሚያገለግል የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት በድሬዳዋ ከተማ ይሰጥ እንደነበረም ታርክ ያሳያል። በ1960ዎቹም ከአውሮፓ የተቀዱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት በሀገራችን እንዲተገበሩ የተደረገ ሲሆን ህፃናት የትምህርት እድል እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: ይሁን እንጂ አሁንም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተደራሽነት፣ ተገቢነትና ጥራት ጉዳይ ፈተና ሆኖ ይገኛል::

የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ችግር ለመፍታት በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል:: ከእነዚህ እርምጃዎች መካከል ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የኦ-ክፍል (የአንድ ዓመት መርሃ ግብር ) ፣ የህፃን ለህፃን ትምህርት፣ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የተፋጠነ የትምህርት ቤት ዝግጁነት እና የሶስት ዓ መት መደበኛ የህፃናት ትምህርት ተግባራዊ ተደርጓል::

የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ግኝትም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የአጠቃላይ ትምህርት አካል አለመሆኑን፣ ለግልና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት የተተወ መሆኑን፣ መደበኛ ትምህርት ራሱን ችሎ ሳይሆን እንደ ተጨማሪ መርሃ-ግብር መታየቱን፣ በየደረጃው በባለድርሻ አካላት በቂ ትኩረት አለማግኘቱን እና ራሱን የቻለ አስተዳደር የሌለው መሆኑን አመላክቷል::

ከዚህ በተጨማሪ ፕሮግራሙ ከአንደኛ ደረጃ ጋር ያለው ትስስር በግልጽ አለመቀመጡ የተጠያቂነት ችግር ማስከተሉን፣ ሥርዓተ ትምህርቱ አምዳዊና የጎንዮሽ ትስስሩ በሚገባ የጠበቀ አለመሆኑን፣ በህጻናቱ ሁለተናዊ ዕድገት ላይ ትኩረት ያላደረገ መሆኑን እና ሥርዓተ ትምህርቱ የተቀናጀ ሳይሆን በአብዛኛው ለተወሰኑ የመማር ይዘቶች ማለትም ቁጥርና ቋንቋ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ጥናቱ በግልጽ አሳይቷል::

ሌላው የመማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁሶችና ተግባራት የህጻናትን የዕድገት ደረጃ እና ባህል ያገናዘቡ አለመሆናቸው፣ በዘርፉ በቂ የሰለጠኑ መምህራን አለመኖራቸው፣ መምህራን በቂ የሆነ ስልጠና አለማግኘታቸው፣ መምህራን በሚያስተምሩበት ቋንቋ ቅድመ ስልጠናው አለመሰጠቱ እንድሁም መምህራን የሚያገኙት ደመወዝ አነስተኛ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ፍልሰት መታየቱ ተግዳሮት መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል::

አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ግብረ-ገብን፣ ሀገር በቀል ዕውቀቶችንና የ21ኛ ክፍለ ዘመን ክህሎቶችንና ሀገራዊ ጉዳዮችን የፕሮግራሙ አካል በማድረግ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ህጻናት የሙያ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት እንዲተዋወቁ ይጋብዛል፡፡ ፖሊሲው የፈጠራ ሥራዎች እንዲበረታቱ፣ ቅንጅታዊ ውህደትና ጨዋታ-መር የማስተማርያ ዘዴ እንዲኖር፣ የመማር ውጤቶች ብቃት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ይደነግጋል፡፡ በ2015 ዓ.ም በተከለሰው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እድሜያቸው ከ5 እስከ 6 ዓመት ለሆናቸው ሕጻናት የ2 ዓመት ትምህርት የነጻና የግዴታ እንዲሆን እና እድሜያቸው 4 ዓመት የሞላቸው ህጻናት ደግሞ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርትን በሌሎች አማራጮች እንደሚማሩ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ እድሜያቸው 4 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የሥርዓተ-ትምህርት ሰነዶች ባለመኖራቸው ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የ3 ዓመት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ከፍተኛ ፍላጎትና ጥያቄ ቀርበዋል፡፡ ከዚህ መነሻ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመከተል የ4 ዓመት ህፃናትን ያካተተ የ3 ዓመት መርሀ-ግብር መርሀ-ትምህርት ተዘጋጅቷል፡፡ ይህንን መርሀ-ትምህርት መሰረት በማድረግ የ4 ዓመት ህፃናትን ታሳቢ ያደረገ፣ ተግባር-ተኮር/ህጻን-ተኮር እና ጨዋታ ላይ የተመሰረተ፣ ስድስቱን የእድገትና የመማር መስኮችን በአውድ ያቀናጀ፣ ሀገር በቀል እውቀቶችን ያካተተ፣ ንቁ ተሳትፎን የሚያበረታቱ የማስተማርያ ዘዴዎችን እና ህፃን-ተኮር የምዘና ስልቶችን ያካተተ የተቀናጀ የመምህር መምሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

ህጻናት እጅግ የተለያዩ የትምህርትና የዕድገት ፍላጎቶች ያሏቸው በመሆናቸው ለዚህ ደረጃ የተቀመጡ የመማርና የዕድገት ውጤቶችን ታሳቢ ያደረገ ትምህርት ያስፈልጋል፡፡ ይህ የመምህር መምሪያም ዕድሜያቸው 6 ዓመት (ከ5 ዓመት ከ9 ወር እስከ 6 ዓመት ከ8 ወር) ለሆናቸው ህጻናት የተዘጋጅ ስሆን ስያሜውም የተቀናጀ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃ ሶስት የመምህር መምሪያ ይባላል፡፡

## 1.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት

### 1.2.1. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዕድሜያቸው ከ4 እስክ 6 ዓመት ለሚሆናቸው ህጻናት የሚደረግ እንክብካቤንና የሚሰጡ መሰረታዊ እውቀትና ክህሎቶችን ያካተተ የትምህርት እርከን ነው፡፡ መርሀ-ግብሩ ጨዋታ ተኮር በሆነ የአቀራረብ ዘዴ የህፃናቱን ሁለተናዊ እድገት (አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜት፣ ስነ-ምግባር) በማጎልበት የተሟላ የስብዕና እድገት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህፃናት የህይወት ዘመን ውጤታማነት የሚጀምርበት እና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሚሆኑበት ወሳኝ ምዕራፍ ነው፡፡

### 1.2.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊነት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም የትምህርት እርከን መሰረት ነው፡፡ የዚህ እርከን ትምህርት የሚያስፈልግበት ዋነኛ ምክንያት የህፃናትን ሁለንተናዊ (አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማህበረ-ስሜታዊ፣ የቋንቋና ሞራላዊ) ዕድገት ማረጋገጥ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በተጨማሪ ህጻናት ዛሬን መኖርና ዓለም የራሳቸው እንደሆነች መገንዘብ መቻል አለባቸው፡፡ ይህ ማለት ህጻናት አስፈላጊ እንክብካቤና ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው ማለት ነው፡፡ ነገ የተሻለና የበለጸገ ማህበረሰብ እንዲኖር ከተፈለገም ዛሬ ለህጻናት የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤና ትምህርት

መስጠት ያስፈልጋል። ጥራት ያለው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሌላይኛው አስፈላጊነት ህጻናትን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

## 1.3. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሆዎች

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሕጻናት ዘላቂ ትምህርትና እድገት መሠረት የሚጣልበት ደረጃ ነው። መርሃ-ግብሩ ጥራት ያለውና ተደራሽነትን ያረጋገጠ መሆን ይጠበቅበታል።ጥሩ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚከተሉት ቁልፍ መርሆዎች ይኖሩታል፡ ህጻናትን በተገቢው ለመንከባከብና ለማስተማር እነዚህን መርሆዎች ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊነው፡

### 1.3.1. ሕጻናት-ተኮር አቀራረብ

የሕጻናት ፍላጎትና ችሎታ ሊያሟሉ የሚችሉ ተግባራትን ማደራጀት ያስፈልጋል። ለህጻናት አካባቢያቸውን በማሰስ እንዲሁም በመሞከርና ንቁ ተሳታፊ በመሆን ተግባራትን በግል፣ በጥንድና በቡድን በማከናወን የሚማሩበትን ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል። ይህም የፈጠራ ችሎታቸውንና የመማር ፍላጎታቸውን ለማሳደግ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል።

### 1.3.2. ጨዋታ-ተኮር ትምህርት

ጨዋታ የሕጻናት ቋንቋ ነው። ህጻናት ካልተጫወቱ በተገቢ ሁኔታ መማርና ማደግ አይችሉም። በመሆኑም አእምሯዊና ማህበራዊ እድገታቸውን ለማዳበር ያለውን ሚና በመረዳት ነጻ፣ መምህር መርና የተደራጁ/የተዋቀሩ ጨዋታዎችን በመጠቀም የሕጻትን የመማር ፍላጎት ሊያሳካ በሚችል መልኩ መተግበር ያስፈልጋል።

### 1.3.3. የተቀናጀ ሥርዓተ-ትምህርት

ለቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተመረጡ ስድስት (6) የእድገትና የመማር መስኮችን (ቋንቋና ተግባቦት፣ መሠረታዊ ሂሳብ፣ አካባቢ ሳይንስ፣ ማህበረ-ስሜታዊ ዕድገት፣ ጤናና የአካል መዳበር እና ስነ-ጥበባት) ተቀናጅተው በቀረቡበት አውድ ከነባራዊ የሕይወት ልምድና ተሞክሮ ጋር በማዛመድ የሚማሩበትን እድል መፍጠር ያስፈልጋል።

### 1.3.4. አካቶ ትምህርት

ሁሉም ሕጻናት ያለምንም ልዩነት ጥራት ያለው የቅድመ-አንደኛ ትምህርት በእኩል ደረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥና ብዝሃነት (ከባህል፣ ከቋንቋ፣ ግለሰባዊ ልዩነትና ወዘተ.) በክፍልና ከክፍል ውጪ እንደሚኖር በመረዳት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

### 1.3.5. ሀገር በቀል እውቀት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ እና ከራስ ወደ ቤት/አከባቢ የሚዘጋጅና የሚቀርብ ሂደትን ይከተላል። የሚቀርቡ ይዘቶች ህፃናቱ በአከባቢያቸው በሚያውቁት እና ቅርብ በሆኑ ቅድመ እውቀቶች ላይ በመመስረት የተቀመጠውን ብቃት መላበስ እንዲችሉ መደረግ አለበት።

### 1.3.6. ከእድገታቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ ተግባራት

ከሕጻናት የእድሜና የእድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣሙ ተግባራትን በማዘጋጀት ሁለንተናዊ እድገታቸውን ማለትም አእምሯዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊና አካላዊ እድገታቸውን ሊያዳብሩ

በሚችሉ ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረግ።

### 1.3.7. የወላጆች/አሳዳጊዎችና ማህበረሰብ ተሳትፎ

ወላጆች የህጻናት የመጀመሪያዎቹ የህይወት መምህራን በመሆናቸው የዚህ ደረጃ ትምህርት ያለእነርሱ ንቁ ተሳትፎ ዋጋ አይኖረውም። ስለዚህ በመማር ማስተማር ሂደት ወላጆች/አሳዲጊዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታትና ከማህበረሰቡ ጋር የሕጻናቱን ትምህርትና እድገት ለመደገፍ የሚያስችል ጤናማ ግንኙነትን ከማህበረሰቡ ጋር መፍጠር ያስፈልጋል።

### 1.3.8. ጤናማና ምቹ የትምህርት አከባቢ

ለሕጻናት ምቹ፣ ንጹህና ጤናማ የመማር አካባቢ እንዲኖር በማድረግ ደህንነትና ምቾት እንዲሰማቸው የሚያስችል የትምህርት አከባቢ መፍጠር ያስፈልጋል። የክፍል ውስጥ አደረጃጀቱ ጣሪያ፣ ግድግዳዎቹና ወለሉ በመማሪያ መጫወቻ ቁሳቁሶች የበለጸጉ መሆን አለባቸው። የክፍል ውጭ አደረጃጀትም ለህጻናት አስፈላጊ ሁሉ ሁኔታዎች የተሟሉበት መሆን ያስፈልጋል።

### 1.3.9. ሁለንተናዊና ቀጣይነት ያለው እድገት

የልጆች ሁለንተናዊ እድገትና ትምህርት የሚጀምረው ከማህፀን ውስጥ ጀምሮ ሲሆን ይህም በሕይወት ዘመናቸውም ቀጣይነት ያለው መሆኑን በመረዳት የልዩ ፍላጎትን ጨምሮ በቀዳማይ የልጅነት ጊዜ ጥሩ የስሜት ማነቃቂያና የቅድመ እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል።

### 1.3.10. የተመጣጠነ አቀራረብ

በእውቀት፣ በአመለካከት እና በችሎታ እንዲሁም በንድፈ ሀሳብ እና በተግባር መካከል የተመጣጠነ አቀራረብ መከተል እና በተጨማሪም የክፍል ውስጥና የክፍል ውጭ ተግባራትን ለሕጻናቱ መማር በሚጠቀም መልኩ አመጣጥኖ ማቅረብ ያስፈልጋል።

### 1.3.11. የህፃናት ተከታታይ ምዘና

የሕጻናትን ሁለንተናዊ እድገታቸውንና የመማር ሂደትን በምልከታና መደበኛ ባልሆነ የምዘና ስልት በመጠቀም መከታተል፣ እንደማህደረ-ተግባር፣ የመከታተያ ቅጾችና የመሳሰሉትን በመጠቀም ለውጣቸውን መመዝገብ፣ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው-ግብረ-መልስ መስጠት የሚያስችል የግንኙነት ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

## 1.4. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት አጠቃላይ ዳሰሳ

አዲሱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት በ3 የትምህርት ደረጃዎች የተዋቀረ ነው። ደረጃ አንድ እድሜያቸው ከ3 ዓመት ከ 9 ወር እስከ 4 ዓመት ከ8 ወር ለሆናቸው ህጻናት የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ለቀጣይ የልጆች እድገትና የመማር ደረጃዎች መሠረት ሆኖ ያገለግላል። በዚህ ደረጃ " ስለ እኔ"፣ "ቤቴ እና ቤተሰቦቼ"፣ "ጎረቤቶቹ እና ትምህርት ቤቴ"፣ "ቀለማት"፣ "ጓደኝነት" እና "ጊዜ" የሚሉ የትምህርት አውዶች ተካተዋል። ደረጃ 2 ዕድሜያቸው ከ 4 ዓመት ከ9 ወር እስከ 5 ዓመት ከ8 ወር ላሉ ሕፃናት የተዘጋጀ ሲሆን "ማኅበረሰብ"፣ "እንስሳት"፣ "ሥራ"፣ "ውኃ"፣ "ጠፈር" እና "ወቅቶች" በሚባሉ ስድስት የትምህርት አውዶች የተዘጋጀ ነው። ደረጃ 3 ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት ከ9 ወር እስከ 6 ዓመት ከ8 ወር ለሆናቸው ህጻናትን የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ ደረጃ "ተክሎች"፣ "ቴክኖሎጂ"፣ "ባህል"፣ "ትራንስፖርት"፣ "ግብርና" እና "ሰላም" የሚባሉ ስድስት አውዶች ተካተዋል።

## 1.5. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ-ትምህርት

መርሀ-ትምህርት በአንድ የትምህርት ዓይነት ወይም መርሃ-ግብር የሚሰጡ ይዘቶችን፣ ዓላማዎችንና የማስተማር ዘዴዎችን ያካተተ ዝርዝር የይዘት ሠንጠረዥ የያዘ ሰነድ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በዚህ ደረጃ የተዘጋጀው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ መርሃ-ትምህርት ለየደረጃው የተለዩ ስድስት አውዶች፣ ስድስት የትምህርት መስኮችን፣ በየአውዱ መጨረሻ ከህፃናት የሚጠበቁ ውጤቶች፣ በሳምንት የተለዩ የትምህርት ይዘቶች፣ ሳምንታዊ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፣ የተቀናጁ ተግባራት፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የመማሪያና መጫወቻ ቁሳቁሶችና በመጨረሻም የምዘና ስልቶች በዝርዝር የቀረቡበት ሀገራዊ ሰነድ ነው፡፡ ሰነዱም የመምህር መምሪያና የህፃናት መለማመጃ ደብተር ለማዘጋጀት መሠረትና መሪ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡

## 1.6. የዕድገትና መማር መስኮች

ለቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተቀናጅተው የሚሰጡ ስድስት የእድገትና የመማር መስኮች ተለይተዋል፡፡ እነዚህ መስኮች የሕጻናትን ሁለንተናዊ እድገት ለማበልጸግ የሚያስችሉ ሲሆን እንደእድሜ ደረጃቸው ህጻናት አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ የቋንቋ፣ ግብረ-ገባዊ እና ስነ-ጥበባዊ ክህሎታቸውን ለማዳበር በማቀናጀት እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የዕድገትና የመማር መስኮችን እንደሚከተለው ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

### 1.6.1. የቋንቋ መዳበርና ተግባቦት

ህጻናት ቋንቋን በመጠቀም ተሞክሮዎቻቸውንና ስሜቶቻቸውን መግለጽ እንዲሁም እርስ በርስ መግባባት ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህጻናት በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍም የማዳመጥ፣ የመናገር እና የቅድመ ንባብ ክህሎቶቻቸውን ያዳብራሉ፡፡ ስለሆነም ይህ የዕድገትና የመማር መስክ በዋናነት የሚያተኩረው ማዳመጥና መናገር፣ ፊደላትን ማወቅ፣ የመጽሐፍ እውቀት፣ የህትመት ግንዛቤ፣ ድምጾችን መለየትና የተግባቦት ሥርዓት የሚሉት ላይ ነው፡፡

### 1.6.2. የቅድመ-ሂሳብ መዳበር

ህጻናት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የሂሳብ ፅንሰ ሐሳቦችን ይማራሉ፤ የሂሳብ ሀሳቦችን እና ሂደቶችን ይመረምራሉ፡፡ አካላዊና ማህበራዊ አካባቢያቸውን በመመርመር ከቀዳሚ ልምዶቻቸው አዲስ ዕውቀትን በንቃት ይገነባሉ፡፡ ስለዚህ ይህ የመማር መስክ ቁጥሮችን በመቁጠር፣ በመጻፍ፣ በማወዳደር፣ በቅደም ተከተል በመደርደርና በመመደብ እንዲሁም በመለካት፣ ቀላል የማመዛዘን (ጊዜን፣ ገንዘብንና ቅርጾችን) ችሎታዎችን እና ቀላል የሂሳብ ስሌቶችን (መደመርና መቀነስ) ያሉ ክህሎትን ማዳበር ላይ ያተኩራል፡፡

### 1.6.3. አካባቢ ሳይንስ

ህጻናት በዚህ የዕድገትና የመማር መስክ ስለአምስቱ የስሜት ሕዋሶቻቸውና ስለሰውነት ክፍሎቻቸው መማርና ግንዛቤ ማዳበር ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ህፃናት ስለተክሎች፣ እንስሳትና በአካባቢያቸው ስለሚሆኑ ቀላል ክስተቶች በዕይታና በቀላል እንቅስቃሴዎች በመማር አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩና በዕለት ተዕለት ህይወታቸው የቴክኖሎጂን አስፈላጊነት ለመማር እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ስለዚህ ይህ የዕድገትና መማር መስክ በሰው አካል ክፍሎች፣ በአካባቢያቸው በሚገኙ እንስሳት፣ እጽዋት፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ክስተቶች፣ ራስንና አካባቢን በመንከባከብ፣

በጥንቃቄና ደህንነት ጉዳዮች፣ ቀላል ቴክኖሎጂን በማስገንዘብ ማህበራዊ ግንኙነቶች በመረዳት ዙሪያ ያተኩራል ።

### 1.6.4. የግልና ማህበረ-ስሜታዊ መዳበር

በዚህ የዕድገትና የመማር መስክ ህጻናት ራስን በመገንዘብ የራስን ማንነት መገንባት፣ ራሳቸው ለመቻል ጥረት ማድረግ እና ስሜቶቻቸውን መቆጣጠር የሚጀምሩ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ከሌሎች ጋር ውጤታማ በሆነ መንገድ መግባባትን፣ ሌሎችን ማክበርና መንከባከብን ይማራሉ። ስለዚህ ይህ የዕድገትና የመማር መስክ የራስ ግንዛቤ፣ የግል ነፃነት፣ የማህበራዊ ግንዛቤ፣ የሞራል እሴቶችን መገንዘብ፣ የተግባቦት ችሎታ፣ ለደንብ መገዛት፣ ውሳኔ የመስጠት ክህሎትና የሀገር ፍቅር ስሜት ለማዳበር የሚረዱ ዕውቀትና ክህሎቶች እንደ የደረጃቸውና እድሜያቸው ተካተው ቀርበዋል።

### 1.6.5. አካላዊ መዳበርና ጤና

ህጻናት ጥሩ ልማዶችን በማዳበር ንቁና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ማዳበር እንዲሁም መሠረታዊ የጤናና የደህንነት ጉዳዮችን በመረዳት ራሳቸውን መጠበቅን ይማራሉ። በተጨማሪም ስለስሜቶቻቸውና አካባቢያቸውን ለመመርመር የስሜት ህዋሳቶቻቸውን የመጠቀም ችሎታን ያዳብራሉ። ይህ የዕድገትና የመማር መስክ በጤና፣ በአመጋገብ፣ በአካላዊ ቅልጥፍና እድገት፣በቦታ ግንዛቤ፣ በአካል ብቃት እና በአካላዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኩራል።

### 1.6.6. የክወናና የእይታ ጥበባት

ይህ የዕድገትና የመማር መስክ ህጻናት የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና አከባቢያቸውን እንዲመረምሩና እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም ህጻናት በዚህ ደረጃ የተለያዩ የኪነ-ጥበባት፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሙዚቃ፣ የታሪክ፣ ተረት እና እንቅስቃሴን በመጠቀም ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን ለመግለጽ የፈጠራ ችሎታቸውን ይጠቀማሉ፤ እንዲሁም የሥነ-ጥበብ ተሞክሮዎችንና ሰብዓዊ እሴቶችን ያደንቃሉ። ስለሆነም ይህ የዕድገትና መማር መስክ በኪነ-ጥበባዊ ግንዛቤ፣ በፈጠራ አገላለጽ፣ በባህላዊ ቅርስ፣ ውበትን ማድነቅና ተገቢውን ዋጋ መስጠት ላይ ያተኩራል።

## 1.7. የዕድገትና የመማር ብቃቶች

የእድገትና የመማር ብቃቶች በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንደሚያመላክተው ልጆች በሶስቱም ደረጃዎች በእድገትና የመማር ተግባራት ላይ ማግኘት የሚገባቸውን ተፈላጊ እውቀትን፣ አመለካከትን እና ክህሎቶችን ያመላክታል። እንደየደረጃውና አውዱ በዋና ዋና የብቃት ዘርፎች ሊደራጁ ይገባል። ስኬታማነት፣ ጥልቅ አሳቢነትና ችግር ፈቺነት፣ተግባቦት፣ የመማር ቀጣይነትና የምዘና መሳሪያነት የአጥጋቢ የመማር ብቃቶች መሰረታዊ ባህሪያት ናቸው። በተጨማሪም በዚህ የትምህርት ደረጃ ህጻናት መሠረታዊ የግል ክህሎቶች፣ የመማር ዝግጁነት፣ ችግር የመፍታት ክህሎት፣ በጥልቀት ማሰብና መመራመር፤ ተግባቦት፣ የፈጠራ ክህሎት፣ ትብብርን፣ በጋራ የመማርና የመስራት ክሂል፤ አመራርና ውሳኔ ሰጭነት፣ መሠረታዊ የዲጂታል ዕውቀትና ክህሎት፣ የአመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ፣ ባህላዊ ማንነትና ዓለም አቀፋዊ ዜግነት ብቃቶችን ያዳብራሉ።

## 1.8. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት የባህርይ ገጽታ

የህጻናት የባህርይ ገጽታ የሶስቱም ዓመታት ቆይታ ውጤት ነው። ይህም ህጻናት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ መሆናቸውን የሚለኩበት መነጽር ነው። በእያንዳንዱ ደረጃ ህጻናት የሚጠበቅባቸውን ብቃትና የዕድገትና የትምህርት ውጤት በማሟላት የራሳቸውን የባህርይ ገጽታ ይገነባሉ ተብለው ይጠበቃል። ስለሆነም ይህ የ3 ዓመት ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ሲጠናቀቅ ህፃናት፦

- የቅድመ ስሌት፣ የቅድመ ንባብና ጽህፈት ክህሎቶችን ማዳበር፣
- መሰረታዊ የቴክኖሎጂ ክህሎቶችን መጠቀም፣
- ከተፈጥሮ እና ከማህበረ-ኢኮኖሚ አከባቢዎች ጋር ጤናማ መስተጋብር መፍጠር፣
- የአከባቢያቸውን ባህላዊ ልምዶችን መገንዘብ፣ ማድነቅ እና መስተጋብር መፍጠር፣
- ከሌሎች ጋር ለመገናኘትና ለመተባበር የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ክህሎትን መጠቀም፣
- መሰረታዊ የሥነ-ምግባር መገለጫዎችን ማለትም ታዛዥነት፣ ታማኝነት (ሀቀኝነት፣ መልካምነት፣ እውነተኝነት)፣ እራሳቸውንና ሌሎችን መንከባከብና አክብሮትን ማሳደግ፣
- ሀሳቦችንና ስሜቶችን በኪነጥበብ፣ በሙዚቃ እና በእንቅስቃሴ መግለፅ፣
- የግል ንጽህና ደህንነት እና የአከባቢ ጽዳት ለመጠበቅ መሰረታዊ የጤና ህግጋትን ማወቅ
- በዝቅተኛ ደረጃ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ማከናወን፣
- የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ዕውቀትንና ክህሎትን መጠቀም።

## 1.9. ሀገር በቀል (አካባቢያዊ) እውቀትን መሠረት ያደረገ ትምህርት

የሀገር በቀል ዕውቀት እንደየአውዱና ደረጃው የተመጠኑ ባህላዊ ዕውቀቶች፣ ክህሎቶች፣ አመለካከቶች፣ ልምዶች እና እሴቶች ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው የሚተላለፉ ናቸው። ይህ እንደ ተረት፣ ባህላዊ ዘፈኖች፣ እንቆቅልሾች፣ የቃል ጨዋታዎች፣ እሴቶች፣ ደንቦች፣ ቁሳዊ ባህሎችና ስለተፈጥሮአዊ አካባቢዎች ዕውቀትን ጨምሮ የአገር በቀል የጨዋታ ልምዶችን ያጠቃልላል። እነዚህ የተዘረዘሩት ሀገር በቀል እውቀቶች በአምስት ሰፋፊ ምድቦች (በቃል የሚተላለፍ የሀገር በቀል ዕውቀት፣ በባህላዊ ልምዶች የሚተላለፍ የሀገር በቀል ዕውቀት፣ ቁሳዊ ባህል፣ የህዝብ ጥበባትና ሙዚቃ እና የአኗኗር ዘይቤ ወይም ትውፊት) ይመደባሉ። እነዚህ ዕውቀቶች ለህጻናት ተመጥነው ከቀረቡ የሚኖራቸው ዋና ዋና ጥቅሞች የሚከተሉትን ይጠቀሳሉ፡-

- ✓ የሀገር በቀል እውቀት ወጪ ቆጣቢ የመማር ዘዴዎችን ያረጋግጣል፤
- ✓ እውቀትን ተደራሽ፣ ተገቢና ውጤታማ ያደርጋል፤
- ✓ የልጆችን ማህበራዊና ተፈጥሯዊ አካባቢን በተመለከተ ያላቸውን እውቀት ያሻሽላል፤
- ✓ ሕጻናትን ስለልዩነት ወይም ብዝሀነት አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ይረዳል፤
- ✓ በአካባቢው ተቀባይነትን ያገኙአዎንታዊ እሴቶችን እንዲያከብሩ ያደርጋል።

ስለሆነም ከላይ የተገለጹትን የተለያዩ የሀገር በቀል ዕውቀት ዓይነቶችን በመጠቀም ተቀናጅተው

የቀረቡ የትምህርት መስኮችን በማስተማሪያ ዘዴነት መገልገል ከመምህራን ይጠበቃል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን አቀራረቦች ማየት ይቻላል፡፡

- ✓ ከወላጆቻቸው ያዩዋቸውን ባህላዊ ጥበቦችንና እደ-ጥበባት ሥራዎችን እንዲሠሩ በማበረታታት፤
- ✓ በባህላቸው የሚገኙትንና በንድፍ የተዘጋጁ የእደ-ጥበብ ውጤቶች እንዲያቀርቡ በማድረግ፤
- ✓ በአካባቢው በሚከበሩ በዓላት ወቅት የሠሯቸውን በስጦታ መልክ እንዲሰጡ በማመቻቸት መከባበርን እንዲማሩ በማድረግ፤
- ✓ በአካባቢው ያሉ ታሪኮችን፣ አፈ-ታሪኮችን መምህራን፣ ወላጆች፣ የአካባቢው አርቲስቶች፣ ሽማግሌዎች እንዲነግሩዋቸው በማድረግ፤
- ✓ የአካባቢውን መዝሙሮች እንዲዘምሩ በማድረግና፤ቀላል የሆኑ የአካባቢ የሙዚቃ መሳሪያዎችን (ለምሳሌ ከበሮ) እንዲጫወቱ በማድረግ፤
- ✓ በአከባቢያው የሚዘወተሩ ልዩ ልዩ ውድድሮችን በጋራ እንዲጫወቱ በማድረግ መምህራን የህፃናቱን ትምህርት ተጨባጭ (Authentic) በማድረግ ማቅረብ ሳቢ እንደሚያደርገውና የክፍል ውስጥና ውጭ ተግባራትን አመጣጥነው ለማስተማር የሚኖረውን ፋይዳ በመረዳት እንደሚጠቀሙት ይጠበቃል፡፡

## 1.10. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት (PPE Integration)

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት የተለያዩ ይዘቶችን አንድ ላይ በማቀናጀት የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚደግፍ የተቀናጀ አቀራረብ ነው፡፡ ውህደት የህጻናትን አዕምሯዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ እድገትን ጨምሮ የትምህርት ቤት ዝግጁነትን እውን የሚያደርግ ተመራጭ ሂደት ነው፡፡ በውህደት የማስተማር ሂደት የትምህርት ይዘቶች በተግባራት ውስጥ ተቀናጅተውና በአቀራረብ ዘዴዎች፣ ግብዓቶችና ምዘናዎች ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥተው ይቀርባሉ፡፡ ይህም ህጻናት በመዳሰስ፣ በመሞከር፣ በማብራራት እና በተግባር ልምምዶችን በአንድ ተግባር ውስጥ ልዩ ልዩ እውቀት፣ክህሎትና ልምድ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

የተቀናጀ አቀራረብ ለህፃናት ሰፊ ክህሎቶችን እና ችሎታን እንዲያዳብሩ ከመርዳት ባሻገር የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ ግብር ብዝሃነትን እንዲያስተናግድ ይረዳል፡፡ ህጻናት ይዘቶቹ ተቀናጅተው በሚማሩበት ጊዜ የችግር መፍታት፣ ፈጠራ እና ወሳኝ የማሰብ ችሎታን በቀላሉ ያዳብራሉ፡፡ የተቀናጀ የትምህርት አቀራረብ ህጻናት በልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉ፣ እንዲመራመሩ፣ ሀሳብ እንዲገልጹ፣ እንዲያብራሩና እንዲገመግሙ ማድረግን ይጠይቃል፡፡

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚቀርብባቸው ሁለት የውህደት ዘዴዎች አሉ፡፡ እነሱም በአውድ ላይ የተመሠረተ ውህደት (Theme-based Integration) እና ሁለገብ ውሂደት (Interdisciplinary Integration for Standalone Competencies) በመባል ይታወቃሉ፡፡ የእኛ ሀገር የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ ግብር የሚከተለው በዓለም ላይ ብዙ ሀገራት የሚተገብሩትን በአውድ ላይ የተመሰረተ ውህደት ነው፡፡ ይህ የውህደት ዓይነት መሰረት የሚያደርገው የተለያዩ የእድገትና የትምህርት መስኮችን በአንድ አቀናጅተው ማቅረብን ነው፡፡ አውድ በተለያዩ ብቃቶች ላይ የተመሰረቱ ይዘቶችን አቀናጅተው ለማቀፍ ያገለግላል፡፡ ለአብነት፣ 'ሁሉም ስለ እኔ' የሚለው አውድ ለዚህ ደረጃ ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከቀረቡ አውዶች አንዱ ነው፡፡ መምህራን

ይህንን አውድ እንደ አቃፊ በመጠቀም የተቀናጁ ይዘቶችን እንዲያስተምሩ ይጠበቃል፡፡ ሳምንታዊ ብቃቶችን ለመተግበር እንደ ተረት፣ መዝሙር፣ እንቆቅልሽ፣ ጨዋታ፣ ጉብኝት፣ ሥራ፣ ውይይት፣ ፕሮጀክት እና የመሳሰሉት ዘዴዎች ይዘቶችን አቀናጅተው ለማቅረብ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

**ለአብነት፦**

- በአንድ መዝሙር፣ ተረት፣ ጨዋታ ወይም ሌላ ተግባር ውስጥ ሶስትና ከዚያ በላይ (ቋንቋና ተግባቦት፣ ቅድመ ሂሳብ፣ አከባቢን መገንዘብና ሌሎች) ይዘቶችን በማቀናጀት ህጻናት እየተጫወቱ እንደሆነ ብቻ እየተሰማቸው እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

## 1.11. የህጻናት ንቁ ተሳትፎ በትምህርት

በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት ንቁ ተሳትፎ የህጻናትን የመማር ፍላጎትና ጉጉት ደረጃን የሚያመላክት ሲሆን የትምህርት አቀባበላቸውንና ዕድገታቸውን ለማፋጠን ይረዳል፡፡ የህጻናት ንቁ የትምህርት ተሳትፎ ለተሻለ አዕምሯዊ፣ አካላዊ፣ ቋንቋ፣ ሞራላዊ፣ ማህበራዊና ስሜት ዕድገት ወሳኝ ነው፡፡ ተሳትፏቸውን ከፍ ከሚያደርጉ ዘዴዎች ወሳኝ የሚባሉት ተግባር-ተኮር ትምህርት መስጠት፣ በጨዋታ ማስተማር፣ ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠር፣ ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን መረዳት፣ አርአያ መሆንና ምቹና ሳቢ የመማሪያ አከባቢን መፍጠር ናቸው፡፡

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዋና ዋና ዓላማዎች የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ማረጋገጥ፣ ህጻናት ዛሬን መኖር እንዲችሉ ማድረግና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማዘጋጀት ናቸው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት የህጻናትና የመምህራን ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ በጨዋታ መማር ዓላማዎቹን ለማሳካት ከሚረዱ ዘዴዎች አንዱ ከመሆኑም ባሻገር የህጻናትን አዕምሯዊ ዕድገት (የማወቅ ጉጉት፣ የፈጠራ ችሎታና ችግር የመፍታት ክህሎት መዳበር) ይደግፋል፡፡ ይህም ህጻናት ተጨማሪ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ፣ በርካታ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ፣ እንዲተነብዩ፣ መላምቶችን እንዲያዳብሩ፣ መረጃን እንዲተረጉሙና ችግሮችን እንዲፈቱ እድሎችን ይፈጥርላቸዋል፡፡

## 1.12. ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት

ጨዋታ ለህጻናት ቋንቋ፣ ልማድ፣ መብት፣ አሰራርና ተፈጥሮአዊ ስጦታ ነው፡፡ ህጻናት በጨዋታ አማካኝነት አካባቢያቸውን ይፈትሻሉ፤ ይረዳሉ፤ እንዲሁም ይተረጉማሉ፡፡ ጨዋታ በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የህጻናትን ሁለንተናዊ እድገት እውን ለማድረግ ወሳኝ የማስተማርያ ዘዴ ነው፡፡ አንዳንዶች ጨዋታ የህጻናትን አካዳሚክ ክህሎቶች ሊያሻሽል እንደማይችል በስህተት በመገንዘብ ከእድገት ጋር ብቻ ያያይዙታል፡፡ ህጻናት ለመግባባት፣ ለመተርጎም፣ ትርጉም ያላቸውን ፅንሰ-ሀሳቦች ለመፍጠር፣ መረጃን ለማደራጀት፣ አዳዲስ ሀሳቦችን ለመገንባትና ለማስተናገድ የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡

በጨዋታ ጊዜ የህጻናት እና የመምህራን ንቁ ተሳታፊ መሆን ውጤታማ መማርንና እድገትን እውን ለማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ ህጻናት ራሳቸውን የመምራት እና በራሳቸው የመማር ተግበራትን (ነፃ ጨዋታ) የመጀመር እድል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ መምህራን ደግሞ ህጻናት በራሳቸው ተነሳሽነት በሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ውስጥ የመሳተፍ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በህጻናት ትምህርት የታቀዱ፣ ነጻና ድንገተኛ ጨዋታዎችንና ተግባራትን ማጣጣም ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ደረጃ ሊተገበሩ የሚችሉ የተለያዩ ህጻን-ተኮር ጨዋታዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አዕምሯዊ ጨዋታዎች (ተግባራዊ ጨዋታ፣ እና የመርህ ጨዋታ) እና ማህበራዊ ጨዋታዎች (እንቅስቃሴ አልባ ጨዋታ፣ ለብቻ ጨዋታ፣ ትይዩ ጨዋታ፣ የቡድን ጨዋታ እና የትብብር ጨዋታ) በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ህጻናትን እያዝናኑ ለማስተማር ወሳኝ ናቸው፡፡

የግል ሙከራዎች፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታዎችና ተግባራት (መዝሙር፣ ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ ውይይት)፣ ከክፍል ውጭ የሚደረጉ ጨዋታዎች፣ ጉብኝት፣ በፕሮጀክት ላይ የተመሰረቱ ተግበራት፣ በሥራ ላይ የተመሰረተ ትምህርት እና በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ ተግበራት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ዋና ዋና ህጻን-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ሁሉ ተግበራት ህጻናት በራሳቸው ችግር እንዲፈቱና ተሳትፎዎቻቸውን እንዲያሳድጉ ተግባራትን እንዲያከውኑ ብቻ ሳይሆን ሀሳብም እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት የሚከተሉት ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ተብለው ይታሰባል፡፡


- በህጻናት የሚመሩ ተግባራት፡- ህጻናት የራሳቸውን ተግባራት ሲመሩና ሲወስኑ የተሻለ ትምህርት ያገኛሉ፡፡ ስለዚህ መምህራን የሚያቀርቧቸው ተግባራት በህጻናት የሚተገበሩና የሚመሩ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ አካሄድ የህጻናትን ፍላጎት ለማሟላትና ተግባሮቻቸውን ትርጉም ባለው መንገድ እንዲከታተሉ ለማድረግ ይረዳል፡፡
- ምርጫ፡- ምንም እንኳን በተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት በአብዛኛው የታቀዱ ተግባራት የሚከናወኑ ቢሆንም የህጻናትን ተሳትፎ ለማሳደግ በጨዋታና በተግባራት ወቅት ፍላጎታቸውንና ምርጫቸውም ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- የህጻናት ቋንቋና አስተሳሰብ፡- ህጻናት ሀሳባቸውን በቃልም ሆነ በምልክት ወይም በተግባር ሊገልጹ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ህጻናት ሀሳባቸውንና እይታቸውን በመረጡት ቋንቋና ተግባር መግለጽ እንዲችሉ የሚያግዙ ህጻን ተኮር ጨዋታዎችንና ተግባራትን ይሻሉ፡፡
- ማስተዋል እና መጠቀም፡- በተግባር ተኮር ዘዴ ስናስተምር የሚንጠቀማቸው የመጫዎቻ ቁሳቁሶች ህጻናት አዳዲስ ሀሳቦችንና ክህሎቶችን እንዲማሩ የሚያግዙ መሆን አለባቸው፡፡
- መልሰን ልንጠቀማቸው የምንችላቸው ቁሳቁሶች፡- ህጻናት በመነካካት የሚማሩባቸው የመጫወቻ ቁሳቁሶች ያስፈልጓቸዋል፡፡ ቁሳቁሶቹ በአካባቢያቸው የሚገኙ፣ ከህጻናት ባህልና ዕድሜ ጋር የሚጣጣሙ እና መልሰው መጠቀም የሚችሏቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የመምህራን/የወላጆች ድጋፍ፡- በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህራንና የወላጆች ሚና ተግባራትን መምራትን፣ ማበረታታትን፣ ማመቻቸትንና መከታተልን ያካትታል፡፡ ይህንን በምናደርግበት ጊዜ የህጻናትን የማሰብ፣ የመፍጠርና የመመራመር ፍላጎቻቸውንና ችሎታቸውን በማይገድብ መልኩ መሆን አለበት፡፡

## 1.13. ህጻናትን ማዕከል ያደረገ ትምህርት ላይ የመምህራን ሚና

ህጻናት አዲስ ነገር የሚማሩት በመፍጠር፣ በመዳሰስ፣ በመሳተፍ፣ በመሞከር፣ በመመራመር እና በማሰላሰል ነው፡፡ በዚህ ሂደት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ንቁ የመማር አካባቢን ማዘጋጀት፣ መደገፍና መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ህጻናት በንቃት እየተሳተፉ እንደሆነ ማረጋገጥ፣ ምን እያደረጉ እንደሆነና እንዴት እየተማሩ እንደሆነ መከታተል እና ህጻናት ለራሳቸው ትምህርት ሀላፊነት እንዲወስዱ መምህራን ህጻናትን በማነሳሳትና አቅም በማሳደግ አጠቃላይ የትምህርት እንቅስቃሴውን መምራት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ህጻናት ተሳትፎቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ፣ እንቅስቃሴዎቻቸውን በመመልከት፣ ተግባራቸዉን በመመዝገብ እና እንዲያንፀባርቁ በማድረግ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለባቸው፡፡ ህጻናት ራሳቸው በመረጡት እና በራሳቸው የሚመሩ የጨዋታ ተግበራትን መመልከት እንዲሁም በነዚህ የጨዋታ ተግበራት ውስጥ መምህራን በንቃት መሳተፍ፣መምራትና ማገዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን የመማሪያ አካባቢዎችን ማደራጀት (የተለያዩ ማዕዘናትን ማደራጀት)፤ የዕለት ተዕለት ተግባራትን በቅደም ተከተል ማደራጀት፤ ምቹና ደጋፊ የመማር አከባቢን ማደራጀት ፤ከህፃናት ጋር አዎንታዊ ግንኙነቶችን ማጎልበት፤ የህጻናትን ተሳትፎ እና ጽብረቃን ለማጎልበት አቅዶ መስራት፤ ህጻናት ያላቸውን ልምዶች በተለያዩ የዕለት ተዕለት ተግባራት ለማጠናከር መምህራን አቅደው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 1.14. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሀ-ግብር የዕለት ተዕለት ተግባራት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት በይዘት የተጨናነቀና በትምህርት ዓይነት የተደራጀ ባለመሆኑ የተለያዩ የዕለት ተዕለት ተግባራትን ያካትታል፡፡ ተግባራቶቹ ህጻን-ተኮር የማስተማር ዘዴን መሰረት ያደረጉ ሆነው በሁሉም ተግባራት ውስጥ የህጻናትና የመምህራን ሚና የጎላ ነው፡፡ ህጻናትን ከመቀበል እስከ መሸኘት ድረስ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት (የቁርስ፣ የመተኛትና የእረፍት ጊዜን ሳያካትት) የሚከተሉት ናቸው፡፡




ህጻናትን መቀበልና መሸኘት የሁል ጊዜ ተግባራት ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ቀሪዎቹ የዕለት ተዕለት ተግባራት እንደየአስፍላጊነታቸው በቀን ውስጥ ስድስቱ ብቻ) እየተመረጡ ይቀርባሉ፡፡ የእያንዳንዱ ተግባር ምንነትና ዝርዝር መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. ህጻናትን መቀበል፦

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህርያት ውስጥ አንዱ የመምህራንና የህጻናት ግንኙነት ነው። በዚህ ፕሮግራም የታቀፉ ህጻናት በራሳቸው ክፍል መጥተው ቁጭ ብለው የሚማሩ ባለመሆናቸው የወላጅና የመምህራን ቅብብሎሽ ያስፈልጋቸዋል። ለደህንነታቸው ሲባል ህጻናቱ ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡት በወላጅ ወይም በአሳዳጊ እገዛ ሲሆን መምህራን እስከ ት/ቤቱ በር ድረስ ቀርበው ሊቀበሏቸው ይገባል። ይህ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ለሚያስተምሩ መምህራን ዋነኛና ቀዳሚ ተግባር ተደርገው ይወሰዳል። የመቀበያ ጊዜ ህጻናት ነጻ ጨዋታዎችን የሚጫወቱበት፣ የባንዲራ ሥነ-ሥርዓት የሚያከብሩበትና ብሔራዊ የህዝብ መዝሙር የሚዘምሩበት እንዲሁም መምህራን የህጻናትን ጤንነትና ስሜት የሚከታተሉበት ነው።

2. የመዝሙር ጊዜ፦

ይህ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተለያዩ ይዘቶች በዜማ ታጅበውና ተቀናጅተው ለህጻናት መንፈሳቸውንና ፍላጎታቸውን መቀስቀስ በሚያስችል መልኩ የሚቀርቡበት ጊዜ ነው። በዚህ ተግባር ህጻናት በሳምንት ውስጥ የተማሩትን የተቀናጀ ይዘት ሳይረሱ ለረጅም ጊዜ ማስታወስ ይችላሉ። በዚህ መምሪያ ውስጥ የተዘረዘሩ የሳምንት መዝሙሮች የሚቀርቡት የሚከተሉትን የድርጊት ቅደም ተከተል መሰረት ይሆናል።

- በቅድሚያ የህጻናትን የመዘመር ፍላጎት በማነቃቂያ ጥያቄዎች መቀስቀስ
- በመቀጠል ሁል ጊዜ የዕለቱን መዝሙር ርዕስ ማስተዋወቅ
- አስቀድመው መዝመሩን ዘምረው አሊያም በቴፕ/ሲ.ፓስ/ሞባይል ከፍተው ማሰማት
- ህጻናት ስንኝ በስንኝ ተከትለው እንዲዘምሩ ማበረታታት
- ከህጻናት ጋር አብረው መዘመር ከዚያም ህጻናት ለብቻቸው በጋራ እንዲዘምሩ ማድረግ
- ሁሉም ህጻናት በትክክል መዘመር መቻላቸውን ማረጋገጥ
- በመጨረሻም የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና መንገር ያስፈልጋል።

3. የተረት ጊዜ፦

ተረት የፈጠራ ሥራ ሆነው የአንድን ማህበረሰብ አኗኗር፣ ባህል፣ ወግና እሴት ለትውልድ ማሻገር የሚያስችል ዘዴ ነው። በዚህ ዘዴ ሲማሩ ህጻናት የጊዜ ሂደትን፣ ታሪክን፣ የምክንያትና ውጤት ትስስርን እንዲሁም የተቀናጁ የትምህርት ይዘቶችን በቀላሉ ይገነዘባሉ፤ ያስታውሳሉም። ተረት በቃል፣ በንባብና በድራማ መልክ መቅረብ የሚችል ሲሆን የራሱ የሆነ ባህላዊ አተራረክ ዘዴ ያለው ነው። ዘዴው እንደየማህበረሰቡ ባህል የሚለያይ ቢሆንም ለምሳሌ በአማርኛ የሚቀርብ ተረት ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ይከተላል።

| አቅራቢ | ተቀባይ |
|---|---|
| o ህጻናትዬ ተረት እንስማ አይደል? | አዎ! |
| o እሺ! ተረት! ተረት! | የላም በረት ወይም የመሰረት! |
| o በድሮ ጊዜ አንድ....... ነበር። | እሺ! |
| ከዚያ.............. | እሺ! |
| ተረቴን መልሱ! አፌን በዳቦ አብሱ! | |

4. የክፍል ውጭ ጨዋታ ጊዜ፦

ይህ ከክፍል ውጭ ደጅ ወይም ሜዳ ላይ የሚደረጉ አካላዊ እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ነጻና የታቀዱ ተግባራትን የሚያካትት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ህጻናት በግል፣ በጥንድና በትንሽና በትልቅ ቡድኖች እየተደራጁ ልዩ ልዩ የትንንሽና የትልልቅ ጡንቻዎች እንቅስቃሴን የሚፈልጉ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፤ ተግባራትን ያከናውናሉ። እንደ ጭቃ ማቡካት፣ አባሮሽና ሌሎች ጨዋታዎች የዚህ ክፍለ ጊዜ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ።

5. የክፍል ውስጥ ጨዋታ ጊዜ፦

ይህ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ በአብዛኛው የታቀዱ ትምህርታዊ ጨዋታዎችንና ተግባራትን የሚያካትት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ህጻናት በግል፣ በጥንድና በትንሽና በመጠነኛ ቡድኖች እየተደራጁ ልዩ ልዩ የትንንሽና የትልልቅ ጡንቻዎች እንቅስቃሴን፣ አዕምሯዊ ዝግጁነትንና ትኩረትን የሚፈልጉ ጨዋታዎችን ይጫዎታሉ፤ ተግባራትን ያከናውናሉ። እንደእንቆቅልሽ ያሉ ጨዋታዎች የዚህ ጊዜ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ።

6. የተግባር ልምምድ ጊዜ፦

ህጻናት አዲስ ነገር ለማወቅ ካላቸው ጉጉት የተነሳ መጠየቅን፣ መመራመርን፣ መሞከርን፣ መነካካትን፣ ማዋሄድንና መለያየትን፣ መስበርና መጠገንን እንድሁም ሀሳባቸውን በቃልና በተግባር መግለጽን ዋነኛ ምርጫቸው ያደጋሉ። ከዚህ መነሻ በዚህ ጊዜ ለህጻናት ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በማቅረብ በግል፣ በጥንድ፣ በትንሽና በትልቅ ቡድን እየሆኑ እንዲተገብሩ ይደረጋል።

7. የውይይት ጊዜ፦

ውይይት ሀሳብ መለዋወጥንና መነጋገርን ያካትታል። ህጻናት በዚህ ጊዜ በተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በሰፊው ይነጋገራሉ። ይህ ተግባር የህጻናትን በራስ የመተማመን፣ የንግግር፣ ለአንድ ነገር ትኩረት መስጠትን፣ የማዳመጥና ሀሳብ የማፍለቅ ችሎታቸውን ያዳብራል።

8. በሥራ የመማር ጊዜ፦

ለህጻናት ትምህርት ቤት ሌላኛው ቤታቸው ተደርጎ ይወሰዳል። በመሆኑም ህጻናት በዚህ ጊዜ በቤተሰባቸውና በማህበረሰባቸው ዘንድ የሚዘወተሩ የሥራ ዓይነቶችን መሰረት ያደረጉ ሥራዎችን በመስራት ልዩ ልዩ ክህሎቶቻቸውንና ችሎታቸውን ያሳድጋሉ ተብለው ይታመናል።

9. በፕሮጀክት የመማር ጊዜ፦

ፕሮጀክት ታቅደውና ታስበው ረዘም ላለ ጊዜ ህጻናት ፈትሸው፣ ጠይቀው፣ ተመራምረው፣ ሠርተውና አስተካክለው የሚያመጧቸው የግል፣ የጥንድና የቡድን ሥራዎችን ያካትታል። መምህራን የህጻናትን ሥራ የሚከታተሉ ሲሆን ህጻናት ግን በስተመጨረሻ ሥራቸውን ለክፍሉ አቅርበው ማብራሪያና መግለጫ እንዲሰጡ ይደረጋል።

10. የመስክ ጉብኝት ጊዜ፦

ይህ ወደ ክፍል በቀላሉ ማምጣት የማንችላቸውንና ህጻናት ትምህርት ያገኙባቸዋል ብለን የምናስባቸውን ቅርሶች፣ ታሪካዊ ቦታዎችና ኩነቶችን የምናስቃኝበት ሌላኛው በክፍል ውጭ የታቀደ ምልከታ የምናደግበት ጊዜ ነው።

### 11. ህጻናትን መሸኘት፦

ህጻናት በራሳቸው ወደቤታቸው መሄድ ላይችሉ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን ደህንነታቸውን፣ ቁሳቁሶቻቸውን (የምሳ ዕቃ፣ መለማመጃ ደብተርና ወዘተ) በተገቢው መያዛቸውንና ለመሄድ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠው ከወላጆቻቸው ወይም ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር ያገናኟቸዋል፡፡

## 1.15. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህሪያት


የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተቀናጅተው በሚቀርቡ ይዘቶች፣ በአቀራረብ ዘዴ፣ በመማሪያ አካባቢ አደረጃጀት፣ በመጫወቻ ቁሳቁሶች፣ በህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ስልት፣ በቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ፣ በህጻናትና መምህራን ግንኙነት እንዲሁም በመምህራን አቅም ማጎልበት ረገድ ከሌላው የትምህርት እርከን እጅግ ለየት ይላል፡፡ ተቀናጅተው የሚቀርቡ ይዘቶችና የአቀራረብ ዘዴዎች ከላይ በዝርዝር የቀረቡ በመሆናቸው ቀሪ መገለጫዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

### 1.15.1. የመማሪያ አካባቢ አደረጃጀት

የዚህ ደረጃ ትምህርት ህጻናት በክፍል ውስጥ ብቻ ቁጭ ብለው የሚማሩ ባለመሆናቸው የመማሪያ አከባቢያቸውን ለሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡

### 1.15.2. ሀ. የክፍል ውስጥ አደረጃጀት

የክፍል ውስጥ አደረጃጀት የተለየ ሆነው የክፍሉ ጣሪያና ግድግዳ ጭምር ሳይቀር ትምህርታዊ ቁሳቁስን ያሉበት መሆን አለበት፡፡ የምከተለው በአውድ ላይ የተመሰረተ ውህደት ሥርዓት በመሆኑ የመማሪያ ክፍሎቻችንም በዚሁ ልክ የተደራጁ ይሆናሉ፡፡ የህጻናት ትምህርት ክፍል ሳቢ፣ ማራኪ፣ በመጫወቻ ቁሳቁስ የበለጸገና በማዕዘናት የተደራጀ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም የዚህ ደረጃ ትምህርት የሚማሩ ህጻናት የሚማሩበት ክፍል በዋና ዋና እድገት ዘርፎች የተደረጁ ማዕዘናት ያሉት ክፍል ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡




**አእምሯዊ መዳበር:** ቁጥር፣ ፊደላት፣ አከባቢ ሳይንስ፣ የማሰብ፣ ማሰላሰል፣ ምክንያታዊነትና ሌሎች ክህሎቶችን የሚዳብሩበት ማዕዘን ነው፡፡

**አካላዊ መዳር:** ጤና፣ የተመጣጠነ ምግብ አይነቶች፣ከአደጋ መጠበቅ፣ ጥራጥሬዎች፣ ፍራፍሬዎች የትልልቅ እና ትንንሽ ጡንቻዎች ዕድገትና መዳበርን እንዲሁም ጤናን የሚደግፉ ቁሳቁሶች በዚህ ማዕዘን ይደራጃሉ፡፡

**ማህበረ ስሜታዊ መዳበር:** ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ተግባቦት፣ የማህበራዊ መስተጋብር፣ስሜትን መረዳት እን ሌሎች ክህሎቶች እንዲዳብሩ የሚያስችሉ ቁሳቁሶች ይደራጃሉ፡፡

**ቋንቋ መዳበር:** ፊደላት፣ቃላት፣ የንግግር፣የተግባቦትና ሌሎች የቋንቋ ክህሎቶችን የሚዳብሩበት ማዕዘን ነው፡፡

### ለ. የክፍል ውጭ አደረጃጀት

ይህ ሌላይኛው የመማሪያ አከባቢ ሲሆን ብዙ ጊዜ ለታቀዱና ለነጻ ጨዋታዎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይደራጁበታል፡፡ መጫወቻ አካባቢው ከጎጂ ነገሮች የጸዳ መሆን አለበት፡፡ ውጭ መደራጀት ካለባቸው የመማሪያና መጫወቻ ቁሳቁሶች የተፈጥሮ (ሳር፣ አሸዋ፣ ቅጠል፣ ጠጠር፣ ፍሬ፣ ጭቃ፣ እጽዋት፣ ነፍሳትና ወዘተ) እና ሰው ሰራሽ (ብሎኮች፣ መሹለኪያዎች፣ ሸርተቴዎች፣ ዡዋዡዌዎች፣ ጎማዎች፣ ኳሶች፣ ገመድ፣ መወጣጫዎችና ወዘተ) ይጠቀሳሉ፡፡

## 1.16. የህጻናት እድገትና ትምህርት ምዘና

የህጻናትን የመማር እና የእድገት ደረጃ ምዘና በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ መምህራን ስለህጻናት ጥንካሬ፣ ችሎታ እና ፍላጎቶች መረጃን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና ከእሱ በመነሳት ለህጻናት በየቀኑ የጫወታና የትምህርት መርሀ-ግብሮችን በተመለከተ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ የሚረዳቸውን መደምደሚያዎችን ያካትታል፡፡ በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ የህጻናት መማር እና እድገት ምዘና ውስብስብ ቢሆንም የውጤታማ ማስተማርያ ዘዴና እድገት ልምዶች አካል ተደርገው ይወሰዳል፡፡

የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ቀጥተኛ ምልከታን፣ ቃለ-መጠይቆችን፣ ስታንዳርድ ፈተናዎችን፣ የደረጃ አሰጣጥ መለኪያዎችን እና ቼክ-ሊስቶችን፣ የህጻናትን የክፍል ሥራ ናሙናዎች መሰብሰብን እና የወላጅ አስተያየቶችን ያጠቃልላል፡፡ የምዘና ሂደቱ በቀጥታ ከሥርዓተ ትምህርት ይዘት እና በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከሚጠቀሙት የማስተማሪያ ስልቶች ጋር የሚያገናኝ ሰፊ አቀራረቦችን ይይዛል፡፡

የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ሶስት ዓላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም አንድ ልጅ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለመሳተፍ ብቁ መሆኑን ለመወሰን፣ ለዚያ ልጅ በክፍል ውስጥ ባለው አፈፃፀም ላይ በመመርኮዝ የግል የትምህርትና የእንክብካቤ እቅድ ለማዘጋጀት እና በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የልጁን መሻሻል ለመገምገም ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህጻናትን ለመለየትና አስፈላጊ ሁሉ ድጋፍና እገዛ ለማድረግ ልዩ ምዘና በባለሙያ ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል በቅድመ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ህጻናት እድገትና ትምህርት ደረጃ ለመለካት የተደራጁና ስታንዳርድ ቴስቶችን በአመቱ አጋማሽ ወይም መጨረሻ መስጠት ይቻላል፡፡ የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ዘዴዎች በጨዋታ በፕሮጀክት እና ማህደረ ተግባር ላይ የተመሠረተ ምዘናን ያካትታል፡፡

በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ምዘና ህጻናት ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን እየተጫወቱ ሳሉና ከተጫወቱ በኋላ የሚደረጉ ምልከታዎችንና የቃል ጥያቄዎችን ያካትታል፡፡ መምህራን ህጻናት ሲጫወቱ በስርዓት በመመልከት ስለእድገትና ስለትምህርት ብቃት ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ማግኘት ይችላሉ፡፡

በፕሮጀክት ላይ የተመሠረተ ምዘና የህጻናትን የትምህርት እድገት ለመመዘን የሚያገለግል ሌላ ዓይነት አማራጭ ምዘና ሲሆን ይህም በእውቀታቸው፣ በፈጠራ ክህሎታቸው እና ችግር በመፍታት ችሎታቸው ላይ በማተኮር የህጻናትን አቅም መፈተሽን ያካትታል፡፡ ይህ የምዘና ሂደት መካከል የሚታየውን የአረዳድ ልዩነት ለማጥበብና በተቻለ መጠን ሁሉም ህጻናት አቅማቸውን እንዲያወጡ ይረዳቸዋል፡፡

በማህደረ-ተግባር ላይ የተመሰረተ ምዘና የህጻናትን የዕለት ተዕለት ተግባራትን አደራጅተው መያዝንና ከዚያ መነሻ ህጻናቱ ያሉበትን ደረጃ የማየትና የማወቅ ሂደትን ያካትታል፡፡ ማህደረ-ተግባር ህጻናት በትምህርታዊ ተግባራት ላይ በሚሳተፉበት ጊዜ የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች የያዘ ስልታዊ እና የተደራጀ ስብስብ ነው፡፡ በማህደረ-ተግባሩ ውስጥ የተወከሉት የህጻናት ስራዎች የህጻናትን የመማር ብቃት ያለበት ደረጃን፣ የቀረቡ ይዘቶችን እና ስልቶችን ያንፀባርቃሉ፡፡ ማህደረ-ተግባሮች በራሳቸው የግምገማ መሳሪያ አይደሉም፡፡ ስለህጻናት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በአግባቡ ማደራጀትና ተንትነው ለህጻናት አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ይጠበቃል፡፡

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን የህጻናትን እድገትና ትምህርት ሲመዘኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች መርሳት የለባቸውም፡፡

- ✓ የተለያዩ የምዘና ስልቶችን (ምልከታ፣ የቃል ጥያቄ፣ መህደረ-ተግባር፣ ቼክ-ሊስት) መጠቀም
- ✓ ምዘናው ተግባር-ተኮርና ከህጻናት ዕድሜ፣ ባህልና ቋንቋ ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ማድረግ
- ✓ አወንታዊና መማርንና እድገትን የሚደግፍ አካባቢ መፍጠር
- ✓ በምዘናው ሂደት ውስጥ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ያለውን ሚና መረዳትና ማሳተፍ
- ✓ በህጻናት ሁለንተናዊ ዕድገትና የመማር ብቃቶች ላይ ትኩረት ማድረግ
- ✓ የምዘናን ውጤት ለህጻናት እድገትና ትምህርት መሻሻል መጠቀም
- ✓ የህጻናትን ደህንነትና ሚስጥር መጠበቅና ልጆቻቸው በተለይ በስታንዳርድ ፈተናዎች ሲመዘኑ ለወላጆች ወይም ለአሳዲጊዎች ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

## 1.17. የወላጅና አሳዳጊ ተሳትፎ በህጻናት ትምህርትና እንክብካቤ

የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ለህፃናት አጠቃላይ ስኬት መሠረት እንደመሆኑ መጠን ትኩረት መስጠቱ አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ሕጻን ከሰዎች ጋር የሚኖረው መስተጋብር የሚጀምረው ከቤተሰብ አባላትና በቅርብ ከሚንከባከቡት ጋር ነው፡፡ እነዚህ የመጀመሪያ ግኑኝነቶች የማህበራዊ ግንኙነት ክህሎቶች እድገትና ልጆች ስለራሳቸው እና በዙሪያቸው ስላሉት ሰዎች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስተማር ወሳኝ ጊዜያት ናቸው፡፡ ቤተሰቦች የልጆቻቸው የመጀመሪያ አስተማሪዎች በመሆናቸው በእድገታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፉ መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የቤተሰብ ተሳትፎ በልጆች ትምህርት ላይ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡

ቤተሰቦች ለልጆቻቸው እድገትና መዳበር የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤና ግብዓቶች ያቀርባሉ፡፡ በዚህም የህጻናትን ጤና እና እድገት በማረጋገጥ ረገድ ቀዳሚ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ሌላው በቤተሰብ እና በትምህርት ቤቶች መካከል ቀጣይነት ያለው፣ በጋራ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተና፣ ጠንካራ አጋርነት ሲኖር የቤተሰብ ተሳትፎን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የቤተሰብ ተሳትፎ በትምህርት ቤትና በቤተሰብ መካከል በሁለትዮሽ መተማመንና መከባበር ላይ የተመሠረተ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ በማድረግና ኃላፊነትን በመከፋፈል በቁርጠኝነት በመሥራት የልጆቻቸውን ትምህርትና እድገትን

በንቃት መደገፍ ይገባል፡፡ ይህ በትብብር ላይ የተመሰረተ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ግንኙነት ወላጆች እና አስተማሪዎች የልጆችን ብቃት ለማሳደግ፣ በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ የሚያጋጥማቸውን ችግሮቻቸውን ለመፍታት እና ግብዓትን በማሟላት በጋራ ጥረት እንዲያደርጉ መሰረት ይሰጣል፡፡

## 1.18. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህር መምሪያ አጠቃቀም

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን የመግቢያውን ክፍል፣ ስለ ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት የተጻፉትን ጉዳዮች፣ የመመሪያዎቹን አተገባበር ቅደም ተከተል፣ የትምህርቱን ዓላማዎች እና መርሆዎችን በጥልቀት እንዲያነቡ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተጠቆሙትን ንቁ የመማር ዘዴዎች፣ ግብአቶች፣ በልጆች ላይ ያተኮረና በጨዋታ ላይ የተመሠረተ ትምህርት አጠቃቀም፣ የእድገት እና የመማር ዘርፎች፣ የልጆች እድገት እና የመማር ውጤቶች እና የተጠቆሙ መደበኛ የሆኑና ያልሆኑ የግምገማ ቴክኒኮችን ማወቅ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም መምህራን አካባዊ የመማር አካባቢዎችን እንዴት ማደራጀት እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው፤ የአከባቢ ቁሳቁሶችን የመጠቀም፣ የተለያዩ ማዕዘኖችን (የክፍል ውስጥ እና የውጭ ማዕዘኖችን) የማደራጀት እና ቤተሰብንና ማህበረሰብን የማሳተፍ ስልቶችን ተግባራዊ የማድረግ አስፈላጊነትን በመገንዘብ በስራ ሊያውሉት ይገባል፡፡ ከዚህም ጋር መምህራን የዕለት ተዕለት ተግባራትን እንዴት እንደሚያከናውኑ መረዳትና ዕለታዊ፣ ሳምንታዊ እና ዓመታዊ የትምህርት እቅዶችን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪም መምህራን ይህን የመምህር መምሪያ ከህጻናት መለማመጃ ደብተር ጋር ትኩረት ሰጥተው በማቀናጀት መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

## 1.19. የክፍለ ጊዜ ድልድል

ይህ የ6 ዓመት ህጻናት ማስተማሪያ፣ ማሳደጊያና ማዘጋጃ የመምህር መምሪያ እንደመሆኑ መጠን ከህጻናት እድሜና የእድገት ደረጃ ጋር የሚቀራረብ ድርጊት የያዘ የጊዜ ድልድል ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህጻናት በአንድ ነገር ላይ የሚኖራቸው የትኩረት ደረጃ መካከለኛ በመሆኑ የሚከናወኑ ተግባራት አሰልቺና ጊዜ የሚፈጁ መሆን እንደሌለባቸው ይታመናል፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደማስተማሪያ ዘዴዎች የተዘረዘሩ ተግባራት የሚከተሉት የጊዜ ድልድል ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የዚህ ደረጃ ትምህርት የተደራጀው በቀን 6 ክፍለ ጊዜ ኖሮት አንዱ ክፍለ ጊዜ ከ30 ደቂቃ በማይበልጥ ሁኔታ ነው፡፡ ተረት፣ መዝሙር፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታና ውይይት እያንዳንዳቸው በቀን 30 ደቂቃ ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን የመስክ ጉብኝት፣ በሥራ መማርና በፕሮጀክት መማር እንደየተግባራቱ ስፋትና ጥልቀት እስከ አንድ ሰዓት ሊዘልቁ ይችላሉ፡፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ ግን ህጻናትን ወደ ውጭ ይዘው መውጣትን፣ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግንና ነጻ ጨዋታዎችን የሚያካትት በመሆኑ በልዩነት የሁለት ክፍለ ጊዜያት ቆይታ ይኖረዋል፡፡ ይህም ማለት የክፍል ውጭ ጨዋታ በሚኖርበት ጊዜ 1 ሰዓት ያክል ሊፈጅ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንድ ተግባር በሳምንት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚቀርብ ከሆነ ተግባሩ አንድ አይነት ቢሆንም በተሰጠው ክፍለ ጊዜ መሠረት የማስተማር፣ የአቀራረብና ምዘና ስልትን በመቀያየር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የመማር ዐውዶች
# ዐውድ አንድ፡ ተክሎች

አጠቃላይ ለዐውዱ የተቀመጠው ሳምንትና ሰዓት 6 ሳምንት/180 ክፍለ ጊዜ

## 2.1. መግቢያ

በቅድመ አንደኛ ደረጃ ሦስት ለሚገኙ ሕፃናት "ተክሎች" የሚለው የመማር ዐውድ ሕፃናት ተፈጥሮን እንዲያደንቁና ስለዕፅዋት የሕይወት ዑደት እንዲማሩ ይረዳቸዋል።ስለዕፅዋት የዕድገት ደረጃዎች መመልከትም ያስደስታቸዋል። ዐውዱ በዙሪያቸው የሚገኙ ተክሎችን አገልግሎት በመለየት መትከልና መንከባከብ እንደሚገባቸው ይገነዘቡበታል። በዚህም አንድ ትንሽ ዘር እንዴት ተክል ሆኖ እንደሚያድግ ያውቃሉ። ዕፅዋት የምግብ፣ የመጠለያ፣ የአልባሳትና የውበት ምንጭ እንደሆኑም ይረዳሉ። በተጨማሪም ዐውዱ ለልጆች ስለ ተክሎች ሕይወት እንዲማሩ ብዙ ዕድሎችን ይሰጣል፤ እንዲሁም መጠንን፣ ቀለማትን፣ ሸካራነትን ይለዩበታል፤ በማያያዝም ቁጥርንና ቅርፅን የመሳሰሉ ፅንሰ ሐሳቦችንም ያውቃሉ። ስለራሳቸው እንዲያውቁ፣ ራሳቸውን ከተለያዩ የንጽሕና ጉድለትና የደኅንነት ችግሮች ሊጠብቁ ስለሚችሉበት ሁኔታም ግንዛቤ ያገኛሉ።

በአጠቃላይ በዐውዱ ሕፃናትን የሚመጥኑ አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ብቃቶች ተካተዋል። ለእያንዳንዱ ሳምንትም አጥጋቢ የመማር ብቃቶችና ዝርዝር የአተገባበር ስልቶች ቀርበዋል ።

## 2.2. ከዐውዱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ሕፃናቱ ይህንን ዐውድ ከተማሩ በኋላ ፡

- ✓ በውይይት በንቃት በመሳተፍ ተገቢ ምላሽ ይሰጣሉ።
- ✓ የሰዎችን ስሜት በመገንዘብ ውጤታማ ማኅበራዊ ተግባቦት ይፈጥራሉ።
- ✓ የመኖሪያ አካባቢያቸውን ይጠብቃሉ።
- ✓ በመቆምና በመንቀሳቀስ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ።
- ✓ ቁጥሮችን በማወዳደር በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ።
- ✓ የድግግሞሽ/ቅጥ/ሥርዓተ ጥለትን (Pattern) ይገነዘባሉ፤ቅደም ተከተሉን ይገልጻሉ።
- ✓ የተለያዩ ጥበባዊ እሴቶችን ይተገብራሉ።
- ✓ ማኅበራዊና ስሜታዊ ክህሎትን ያዳብራሉ።
- ✓ የግብረገብ እሴቶችን በተግባር ያሳያሉ።
- ✓ አናባቢ እና ተነባቢዎችን ማንበብና መፃፍ ይችላሉ።
- ✓ የባህል ብዝኃነትን ያደንቃሉ።

## 2.3. ዐበይት ይዘቶች

ተክሎች በሚለው የመማር ዐውድ ውስጥ የሚከተሉት ዐበይት የትምህርት ይዘቶች ተካተዋል፡፡

- ራስን ማስተዋወቅ፣ ማወቅና መግለጽ
- ራስን መምራት፣ ራስን መቻል
- የአካል ክፍሎችና ጤና፣
- ድምፅን መለየት፣
- አካባቢን መገንዘብ፣
- ራስን ከአደጋ መጠበቅ
- ትክክለኛ የአመጋገብ ስልትን መከተል፣
- ራስንና አካባቢን መንከባከብ፣
- የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣
- ቁጥሮችን መቁጠር፣ መጻፍ፣ ማነጻጸርና ማወዳደር፣ መደመርና መቀነስ
- ድግግሞሽ/ቅጥ/ሥርዓተ ጥለት (Pattern) ቅርጾችን ማወቅ፣ ጥበባዊ ግንዛቤ፣ የራስን ፈጠራ መግለጽ
- ማኅበረሰብን መገንዘብ፣ የሥነ ምግባር ዕሴቶችን መገንዘብ፣
- ሥነ ልሳንን መገንዘብ፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ አካባቢን መለየት፣
- ነገሮችን መመደብና ማዛመድ፣
- ባህላዊ ቅርሶች
- ሀገር መውደድ
- የፊደላት ቅርጽ መለየት፣ ቃላትን ማወቅ፣ መጻፍና ማንበብ

## አንደኛ ሳምንት

**ለሳምንቱ የተሰጠው፡ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት**

**አጥጋቢ የመማር ብቃት ፡**

- ✓ ስለራሳቸው፣ ቤተሰቦቻቸውና ማኅበረሰቦቻቸው ልምዶቻቸውን ያካፍላሉ፡፡
- ✓ በራስ የመተማመን ስሜታቸውን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ የገመድ ዝላይ ጨዋታን ይጫወታሉ፡፡
- ✓ ከዕፅዋት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መዝሙሮች ይዘምራሉ፡፡
- ✓ የሚወዱትን እና የሚጠሉትን ነገር ይገልጻሉ፡፡
- ✓ በአካባቢያቸው የሚገኙ አትክልት እና ፍራፍሬዎችን ስም ይጠራሉ፡፡
- ✓ በአካባቢያቸው የሚገኙ የዕፅዋትን የአካል ክፍሎች ይለያሉ፡፡
- ✓ መሠረታዊ የንጽሕና አጠባበቅ መርሖዎችን ይተገብራሉ፡፡
- ✓ እስከ 15 ያሉ ቁጥሮችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ሥዕሎችን ሥለው ይቀባሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን ማስተዋወቅ፣ ራስን መግለጽ፣ ራስን ማወቅ፣ የአካል ክፍሎች፣ ጤና፣ ቁጥር መቁጠር፣ ጥበባዊ ግንዛቤ

## ተግባር አንድ: የክፍል ውጭ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ስም፣ እድሜ፣ ፆታ፣ ፍራፍሬ፣ እንቅስቃሴ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በተግባር

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! ይህ ክፍለ ጊዜ የዓመቱ ትምህርት የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ስለሆነ በክፍል ውስጥ ከሕፃናቱ ጋር በመጀመሪያ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ስምዎን፣ ዕድሜዎን፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ የሚሠሩበትን አካባቢና ትምህርት ቤት እና የሚወዱትን የአትክልትና ፍራፍሬ ዓይነት መሠረት በማድረግ ራስዎን ለሕፃናት ያስተዋውቋቸው፡፡

ሕፃናቱን ለማነቃቃት በአካባቢያቸቸው የተለመደ ሁሉም ሊያውቁት የሚችል መዝሙር ያዘምሯቸው፡፡ በመቀጠልም ከተለያየ ትምህርት ቤት እና አካባቢ የመጡ ሕፃናቶች ስለሚኖሩ ተራ በተራ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ልጆችን ከክፍል ውጭ ይዘዋቸው በመውጣትና ክብ በማሠራት በክቡ ውስጥ ተራ በተራ አሻንጉሊት ወይም ኳስ በመቀባበል ተራ የደረሰው/ሳት ሕፃን በክቡ ውስጥ እንዲሮጥ/እንድትሮጥ ሌሎች ደግሞ በማጨብጨብ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ እና የሚያውቁትን የአትክልትና እና የፍራፍሬ ዓይነቶች እንዲያስተዋውቁ ዕድል ይስጧቸው፡፡ በመቀጠለም በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን (ስም፣ ዕድሜ፣ ፆታ...) ተግባር እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ኳስ፣ አሻንጉሊት፣ የተለያዩ የአትክልት እና ፍራፍሬ ሥዕሎችን የያዙ ካርዶች

**የምዘና ስልት:** የፍራፍሬ ዓይነቶችን ስም እንዲናገሩ በቃል መጠየቅ፣ ስለ አትክልትና ፍራፍሬ ሲዘምሩ (ሲጫወቱ) በማየት ለውጣቸውን መመዝገብ፤

### የክፍል ውጭ ጨዋታ ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የሰውነት ክፍሎች፣ ፍራፍሬ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በተግባር

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! ሕፃናቶቹን ወደ ውጭ በማስወጣት ለማነቃቂያ የሚሆን ነጻ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ለአምስት ደቂቃ ያህል ይፍቀዱላቸው፤ ከዚያም የፓፓያ፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ አናናስ ሥዕሎችን የያዙ የሥዕል ካርዶችን በማሳየት እንደ ሕፃናቱ ብዛት በአራት ረድፍ እንዲሰለፉ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል ለህፃናቶች የስምምነት ጨዋታ እንደሚጫወቱ ይንገሯቸዉ(የስምምነት ጨዋታ ለጨዋታዉ መግባቢያ ብቻ በስምምነት የሚወጣ ህግ ነዉ እንጅ የእዉነተኛዉን የእለትከእለት የህይወት እንቅስቃሴ የሚወክል አለመሆኑን ለህፃናቶች ማስገንዘብዎን አይዘንጉ) ከዚያም የሰውነት ክፍላቸውን አናናስን በራሳቸው (ጭንቅላታቸው)፣ ማንጎን በጉልበታቸው፣ ሙዝን በወገባቸው፣ ፓፓያን በትከሻቸው እንደሚወክል ይግለጹላቸው፡፡ ከዚያም አናናስ ሲባል ራሳቸውን፣ ማንጎ ሲባል ጉልበታቸውን፣ ሙዝ ሲባል ወገባቸውን፣ ፓፓያ ሲባል ትካሻቸውን እየነኩ አብረው ከእርስዎ ጋር እንዲጠሩ ያድርጓቸው፤ “ምን እንብላ?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡ ከዚያም የመረጡትን በፍራፍሬ የተሰየመውን አካላቸውን በመንካት በሀሳባቸው በድርጊት እያሳዩ እንዲበሉ ያድርጓቸው፡፡ የተበላውን ፍራፍሬ በአፍ እንቅስቃሴ ብቻ ስሙን

ይጠሩታል እንጂ እንዳልተበሉት ፍራፍሬ ስሙን በቃል አይጠሩትም። በመጨረሻም ህፃናቱን በቡድን በመከፋፈልና ለመዝለያ ገመድ በመስጠት በየተራ እየቆጠሩ ገመድ እንዲዘሉ ያድርጓቸው፡

**የመማርያ እና የመጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ፍራፍሬዎችን የያዙ ካርዶች፣ የሰው የአካል ክፍሎችን የያዘ ሥዕል

**የምዘና ስልት:** የሚወዱትን እና የሚጠሉትን ፍራፍሬ እንዲናገሩ መጠየቅ፣ የሰውነት ክፍሎችን በትክክል መለየታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ

## ተግባር ሁለት: መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ንፅህና፣ ራስን ማስተዋወቅና መግለፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ፣

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! ሕፃናቱ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡ ሁለት መዝሙሮችን እየዘመሩ እንዲማሩ ያድርጉ።

### መዝሙር: አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**የመዝሙር ርዕስ እንቡጥ ነኝ እኔ**

እንቡጥ ነኝ እኔ እንቡጥ አበባ፣
በጣም ቀንጆ ቀንጆ ሆድ እማባባ።
ያየኝ ሁሉ ይወደኛል፣
እደጊ ተመንደጊ ይሉኛል፣
ጠዋት በማለዳ ከእንቅልፌ ነቅቼ፣
ፊቴንም ታጥቤ ቁርሴንም በልቼ።
ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ
እኔ መማር እወዳለሁ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተፈጥሮ አበባ፣ የንፅህና አጠባበቅን የሚያሳዩ ስዕላዊ መግለጫዎች

**የምዘና ስልት፣** ሕፃናት በጋራና በግል ሲዘምሩ ተሳትፏቸውን በትኩረት መመልከት፣ ስለምን እንደ ዘመሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣ ስለ መሠረታዊ የንጽሕና አጠባበቅ መርሖዎች እንዲናገሩ ዕድል መስጠት፤

### መዝሙር፣ ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጤና፣ እንቅስቃሴ፣ ቁጥር፣ ፊደል

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ፣

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! ሕፃናቱ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር እየዘመሩ እንዲማሩ ያድርጉ።

**ጤናማ ለመሆን**

ጤናማ ለመሆን በጣም እጥራለሁ፣
ጠዋት ተነስቼ እጄን እታጠባለሁ፣
ከፍራፍሬ አይነት ሁሌ እመገባለሁ፣
አካላቴ ብርቱ ጤናዬም ጥሩ ነው፣
ስለዚህ ሁልጊዜ ስፖርት እሰራለሁ፣
አንድ ሁለት ሶስት አራት ገመድ እዘላለሁ፣
ተ - ተክል ዕ - ዕፅዋት ዛ   ዛፍ፣
እያልኩ ቃላት እጠራለሁ፣

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** መዝሙሩ ዉስጥ ያሉ ቃላቶችን የያዙ ካርዶች፣ስዕላዊ መግለጫዎች

**የምዘና ስልት፣** ሕፃናት በጋራና በግል ሲዘምሩ ተሳትፏቸውን በትኩረት መመልከት፣ ስለምን እንደ ዘመሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣ ስለ መሠረታዊ የንጽሕና አጠባበቅ መርሖዎች እንዲናገሩ ዕድል መስጠት

## ተግባር ሦስት: የመስክ ጉብኝት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** አትክልት፣ ለስላሳና ሸካራ፣ የተክል ክፍሎች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመስክ ጉብኝት ፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ በተግባር

**የመምህር ሚና :** ውድ መምህር! በመጀመሪያ እንደማነቃቂያም የሚያገለግል ሕፃናቶች ማነቃቂያ መዝሙር ያዘሙሯቸው፤ በዙሪያቸው የሚያዩዋቸውን ተክሎች በመዘዋወር እንደሚመለከቱና እንዲሚቆጥሩ ይንገሯቸዉ፤ በመስክ ጉብኝቱ ሊያደርጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄና ደኅንነቶች ግንዛቤ ያስጨብጧቸው፡፡ በትምህርት ቤት ግቢያቸው ወይም በአካባቢያቸው ወደሚገኝ የአትክልት ቦታ ይዘዋቸው በመሄድ እንዴት እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው፤ ጤንነታቸው እንደሚጠበቅና አጠቃላይ ሁኔታዎችን እንዲመለከቱ ዕድል ይስጧቸው፡፡ የተክሎችን ክፍሎች ሥር፤ ግንድ፤ ቅጠልና አበባ በተግባር ተክሎችን ልብ ብለው  በመመልከትና በመነካካት ቅጠላቸውን ለስላሳና ሸካራ መሆኑን በመዳሰስ እንዲለዩ  ይርዷቸዉ፡፡ እርሳስና  ወረቀት ተጠቅመው ያዩትን ተክል ሥለው እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡ ስለሣሉት ሥዕልም እንዲናገሩ ዕድሉን በየተራ ይስጧቸው፡፡ ከጉብኝቱ በኋላ ሕፃናቱ  እጃቸውን  በውሃና በሳሙና እንዲታጠቡ ያድርጓቸዉ፡፡ በመጨረሻም ውድ መምህር! ሁሉም ሕፃናት በመማሪያ ክፍላቸው ፊት ለፊት /በመኖሪያ ቤታቸው/አካባቢ አንድ አትክልት በዕቃ ተክለው እንዲንከባከቡና እንዲያሳድጉ የፕሮጀክት ሥራ ይስጧቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ችግኝ፣ ተክሎች፣ የፕላስቲክ ተክሎች፤

**የምዘና ስልት:** የተክል ሥዕል በማሳየት ክፍሎቻቸውን እንዲናገሩ በቃል መጠየቅ፣ ለስላሳና ሸካራ በትክክል መለየታቸውን መመልከት፣ ለተክሎች ስለሚደረገው እንክብካቤ እንዲናገሩ ዕድል መስጠት፣ የሣሉትንና ቀለም የቀቡትን ሥዕል በማረም በማጎደረ ተግባር ማስቀመጥ

## ተግባር አራት፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ስም፣ እድሜ፣ አካባቢ፣ ፆታ፣ ቁጥር፣ ፍራፍሬ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና፡** መምህር! ሕፃናት እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁ በክፍል ውስጥ በሁለት ወይም በሦስት ቡድን በመክፈል ለጨዋታው እጅ በእጅ በማያያዝ በክብ ያዘጋጇቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ሕፃን እስከ 15 መጠሪያ ቁጥር የተጻፈበትን የቁጥር ካርድ/የውሃ ፕላስቲክ በመስጠት ቁጥራቸውን እንዳይረሱ ያሳስቧቸው፡፡ እርስዎ በክቡ መሀል ቆመው የቁጥር ካርድ/የውሃ ፕላስቲኮች በመያዝ ስምዎን፣ ዕድሜዎን፣ የት ሰፈር እንደሚኖሩና ከፍራፍሬ ምን እንደሚወዱ ለሕፃናቱ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ይንገሯቸው፡፡ በመጀመሪያ ፈቃደኛ የሆኑ ሕፃናትን ቁጥር በመጥራት በክቡ ውስጥ የቁጥር ካርድ/የውሃ ፕላስቲክ ይዘዉ በመግባት እራሳቸውን እንዲገልጹ ያበረቷቷቸው፡፡ በመቀጠልም ሕፃናቱ ቁጥራቸው ሲጠራ ክቡ መሀል በመግባት ስማቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ የት ሰፈር እንደሚኖሩና ምን ዓይነት ፍራፍሬ እንደሚወዱ ያለፍርሃት እንዲናገሩ ዕድሉን ይስጧቸው፡፡ ከትምህርቱ በኋላ ሕፃናቱ የተሰጣቸውን ቁጥር እንዲጠሩ ያድርጓቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** እስከ 15 ቁጥር የተጻፈባቸው የቁጥር ካርዶች ወይም የውሃ ሃይላንድ ፕላስቲኮች

**የምዘና ስልት፡** ምልከታ፣ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣ (ምን አይነት ፍራፍሬ ትወዳለህ/ትወጃለሽ፣ስንት ዓይነት ፍራፍሬዎችን ታውቃላችሁ)፣ ሲናገሩ ማድመጥ፣

## ተግባር አምስት፡ የግል ተግባር (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ቁጥር፣ የተክሎች አካል ክፍል፣ ቃላት

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና፡** ውድ መምህር! የተክሎችን የአካል ክፍሎች የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫና የተለያዩ ተጋጣጣሚ የተክል ክፍሎች የሚያሳይ ፐዝል ወደ ክፍል ይዘው በመግባት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውኑ፡፡

የተክሎችን የአካል ክፍል የሚያሳይ ሥዕላዊውን መግለጫ በመጠቀምና ለሁሉም ሕፃናቶች የሚታይ ቦታ ላይ በማስቀመጥ የአካል ክፍሎቹን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፤ ተክሎች እንደ ሰዎች የአካል ክፍል እንዳላቸው ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡

የተክል ሥዕል በጠንካራ ካርቶን ላይ በመሣል ከ4 5 ቦታ በመቆራረጥ ሕፃናትን በትናንሽ ቡድን በማስቀመጥ የተቆራረጡ የተክሎች የአካል ክፍሎችን የያዙ ፐዝል በመስጠት የአካል ክፍሎቻቸውን በተገቢ ሁኔታ በመገጣጠም እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡ የፐዝሉ ቁርጥራጭ ብዛትን በአኃዝ እንዲገልጹ ይርዷቸው፡፡ ሌሎች የፍራፍሬ፣ አትክልቶችና ተክሎችን ናሙና በማሳየት በክፍል ውስጥ ፐዝል እንዲሠሩ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም በመለማመጃ ደብተራቸዉ ገፅ ላይ ያለዉን የእፅዋት የአካል ክፍሎችን በመመልከት ስማቸዉን እንዲፅፉ ያድርጓቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፤ ቀለም፤ ካርቶን፤ ላጲስ፤ ወረቀት መቁረጫ፤ የተክሎችን የአካል ክፍሎች የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫና የተቆራረጠ የተክል ክፍሎች፤ የፍራፍሬ ሞዴል (ፐዝል)፣ የመለማመጃ ደብተር

ማስታወሻ: ሕፃናቱ የፕላስቲክ መቁረጫዎችን ብቻ በጥንቃቄ እንዲጠቀሙ ይጠብቋቸው፤

**የምዘና ስልት፤** የተቆራረጡ የተክል ክፍሎችን በትክክል መለየታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣ የተክል ክፍሎችን በቁጥር እንዲገልጹ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣ የተክል ክፍሎችን የተለያየ ቀለም ቀብተው እንዲያሳዩ መጠየቅና ያሳዩትን ብቃት በውጤት መመዝገቢያ ላይ/በማህደረ ተግባራቸው/ ማስፈር

## ተግባር ስድስት ፡ በሥራ መማር (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቀለም፣ ጤና፣ ቁጥር፣ ተክሎች፣ ራስን መግለፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር! ለሕፃናቱ እርሳስ እና ባለቀለም እርሳስ በመስጠት/በማቅረብ/ የተለያዩ ዕፅዋትን፣ የፍራፍሬዎችና የአትክልት ሥዕሎችን በመሣል ትክክለኛ ቀለም እንዲቀቡ አድርጓቸው:: የቀቡትን ዕፅዋት፣ ፍራፍሬዎች እና አትክልቶች ብዛት በመጠየቅ የቁጥር ዕውቀታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጓቸው። የቀቡት ቀለም ምን ዓይነት እንደሆነ በመጠየቅ የቀለም ዓይነቶችን እንዲለዩ ያበረታቷቸው። በመቀጠል ከቀቡት ውስጥ አዘውትረው የሚመገቡትን የፍራፍሬ ዓይነት እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው። ዕፅዋትን፣ ፍራፍሬዎችንና አትክልቶችን መመገብ ለጤና የሚሰጡትን ጥቅም ይግለጹላቸው። ሕፃናቱ ከፍራፍሬ የሚወዱትንና የሚጠሉትን ራሳቸው እንዲገልጹ ይጠይቋቸው:: በአካባቢው የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የሚወዱትን የፍራፍሬ ሞዴል እንዲሠሩ ያድርጓቸው። በማያያዝም የተለያዩ ዕፅዋትን፣ ፍራፍሬዎችና የአትክልቶችን ሥዕሎች በመሣል እንዲለማመዱ በማድረግ የእጅና የአእምሮ ቅንጅትን እንዲያዳብሩ ያግዟቸው። በመጨረሻም በመልማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ የቀቡትን የዕፅዋት፣ የፍራፍሬና የአትክልት ዓይነቶች እንዲጽፉ አደርጓቸው።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፣ የተለያዩ ቀለሞች፣ ወረቀት፣ የተለያዩ ዕፅዋትን የያዙ የሥዕል ካርዶች፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ ለኮላዥ ሥራ የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ቁርጥራጭ ቁሳቁሶች፣ በአካባቢው የሚገኙ ለማጣበቂያ የሚያገለግሉ ማጣበቂያዎች፣ መቀስ፤

**የምዘና ስልት:** የተለያዩ ተክሎችንና ፍራፍሬዎች ሲሥሉና ቀለም ሲቀቡ በምልከታ ማረጋገጥ፣ ለማስተማሪያነት የቀረቡ የፍራፍሬዎችና አትክልቶችን ብዛት መጠየቅ፤ የሚወዱትንና የሚጠሉትን ፍራፍሬ በቁጥር እንዲገልጹ የቃል ጥያቄ መጠየቅ

# ሁለተኛ ሳምንት

**ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ 30 ክፍለ ጊዜ3/15 ሰዓት**

**አጥጋቢ የመማር ብቃት ፡**

- ✓ በማኅበራዊ ግንኙነታቸው የራሳቸውን ባሕርይና ስሜታቸውን ይመራሉ፡፡
- ✓ በአካባቢያቸው የሚገኙ የሚበሉና የማይበሉ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ በአካባቢያቸው የሚሰሙ ድምፆችን ምንነት ይለያሉ፡፡
- ✓ በትምህርት ቤት የሚገኙ ተክሎችን ይንከባከባሉ፡፡
- ✓ በቤተሰብ ውስጥ የሚከናወኑ የቤት ውስጥ ሥራዎችን በመዝሙርና በማስመሰል ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ቢያንስ እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ይጽፋሉ፡፡
- ✓ ሥዕሎችን ሥለው ቀለም ይቀባሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን መቆጣጠር፣ ድምፅን መለየት፣ አካባቢን ማወቅ፣ ሥርዓተ ምግብ፣ ቁጥር መጻፍ፣ የራስን ፈጠራ መግለፅ

## ተግባር አንድ: የተግባር ሥራ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ምርጫ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር! የተለያዩ የፍራፍሬ ሥዕሎችን የያዘ ቻርት ለሁሉም በሚታይ ቦታ በመለጠፍ ያሳዩአቸው፤ በመቀጠልም ከሥዕሎቹ መርጠው በመልመጃ ደብተራቸው ወይም በወረቀት ላይ የመረጡትን የአንድ ፍራፍሬ ሥዕል በመሳል የፍራፍሬውን ተፈጥሮአዊ ቀለም ጠብቀው እንዲቀቡ ያድርጉዋቸው፡፡ ሁሉም እኩል እየተገበሩ መሆናቸውን በመከታተል ደከም ያሉትን ያግዟቸው፡፡ በአካባቢያቸው የሚገኙ የፍራፍሬዎችን ስምና ብዛት እንዲገልጹ ዕድል ይስጧቸው፡፡ በጣም የሚወዱትን የፍራፍሬ ዓይነት ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** እርሳስ፣ ላጲስ፤ ቀለም፤ የተለያዩ የአትክልት እና ፍራፍሬ ሥዕሎችን የያዘ ቻርት፣ የሥዕል ካርድ፣ ልሙጥ ወረቀት

**የምዘና ስልት፡** የፍራፍሬ ሥዕል ሲሥሉ በምልከታ ማረጋገጥ፣ የሳሉትን ትክክለኛ ተፈጥሯዊ ቀለማቸውን የሚመስል ቀለም መቀባታቸውን ማረጋገጥ፣ በአካባቢያቸው የሚገኙ የፍራፍሬዎችን ስምና ብዛት እንዲገልጹ በቃል በመጠየቅ፣

## ተግባር ሁለት: በሥራ መማር: (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ፍራፍሬ፣ ቀለም፣ ጣዕም፣ ጭማቂ፣ ቅርፅ፣ ገንዘብ፣ ግብይት

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህሩ ሚና:** መምህር! ሕፃናቶቹን በጥንድ በጥንድ በማድረግ ለተግባር ሥራው ማዘጋጀት፤

ለጥንዶቹ የፍራፍሬ ዓይነቶችን በስም ለይቶ መስጠት፣ ፍራፍሬዎቹን መስለው እንዲጫወቱ በመጀመሪያ እርስዎ ከአንድ ተማሪ ጋር አብረው በመሥራት ያሳዩቸው፣ "እኔ ብርቱካን ነኝ፣ ቢጫ ቀለም አለኝ፣ ድቡልቡል ቅርፅ አለኝ፣ ጣፋጭ ጣዕም አለኝ፣ ሰዎች በእኔ ጭማቂ ይዝናናሉ።" በማለት ሌላው ደግሞ "እኔ አቦካዶ ነኝ፣ አረንጓዴ ቀለም አለኝ፣ ሞላላ ቅርፅ አለኝ፣ ጣፋጭ ጣዕም አለኝ፣ በእኔ ጭማቂ ሰዎች ይዝናናሉ፣" በማለት በምሳሌ ያስረዷቸው። ፍራፍሬዎች ለጤንነት ያላቸዉን ጥቅም፣ ጣዕም፣ ቅርፅና ቀለም በየተራ እንዲናገሩ ያበረቷቷቸው።

የፍራፍሬና የብር ሞዴሎችን በማዘጋጀት ገዥና ሻጪ ሆነው ቁጥር መቁጠርን እንዲለማመዱ ያድርጓቸው። ህጻናቱ ሻጪና ገዥ በመሆን የመገበያያ ሥርዓትን ጠብቀው እንዲገበያዩ ያድርጉ። በተግባር ልምምድ የገንዘብ ልውውጥ እንዲያደርጉ ዕድል በመስጠት ቁጥር መቁጠርን እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ፍራፍሬዎችን የያዙ ሞዴሎች፣ እውነተኛ ወይም የወረቀት የብር ኖት፣ ፍራፍሬ የያዙ የሥዕል ካርድ

**የምዘና ስልት:** ቢያንስ እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በትክክል መቁጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ፣ የፍራፍሬዎችን ጥቅም እንዲናገሩ መጠየቅ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር የሚያደርጉትን የገበያ ድርድር ምልከታ ማድረግ፣ በተግባር ሂደት የሚያሳዩትን ብቃት መዝግቦ በማሕደር ተግባር መያዝ፣

## ተግባር ሦስት: እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ መድኃኒቶች፣ ጤናዳም/ዳማከሴ/የምች መድሃኒት ፣ ራስ ምታት፣እንስሳት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህሩ ሚና:** መምህር! ሕፃናት ከዚህ ቀጥሎ ለቀረበው እንቆቅልሽ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

**እንቆቅልሽ ፡ 1**

እኔ ትንንሽና ቀጭን አረንጓዴ ቅጠሎች አሉኝ፣ የሰው ልጆች ከቡና ጋር ለባህላዊ መድኃኒትነት ይገለገሉብኛል፡፡ የሆድ ሕመምና የራስ ምታት ሕመምን እፈውሳለሁ፣ እኔ ማነኝ?

**መልሱ:** ጤናዳም/ዳማከሴ/የምች መድሀኒት ነው፡፡ መልሱን ካልመለሱ ሀገር ስጡኝ በማለት ይጠይቋቸዉ በመቀጠል የሰጧቸዉን ሀገር በመጠቀም በአካባቢዉ ያሉትን ፀጋዎችን በመጥቀስ መልሱን ይንገሯቸዉ፡፡

**እንቆቅልሽ 2**

የቤት እንስሳ ነኝ፣ ሌባ ሲመጣ ው ው ው እያልኩ እጮሀለሁ፣ ስጋ በጣም እወዳለሁ፣ ቤት እጠብቃለሁ፣ አራት እግር አለኝ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** ዉሻ

መምህር! ሕፃናት እየወጡ ወይም ባሉበት ቆመው ሌሎች የሚያዉቋቸዉን እንቆቅልሾችን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያበረቷቷቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** በቅርብ ከተገኘ የጤናዳም/ዳማከሴ/የምች መድሀኒት ተክልን ካልተገኘ ሥዕል፣ የዉሻ ሥዕል

**የምዘና ስልት፤** የሚያውቋቸውን ባህላዊ መድኃኒቶችን እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣ የጤናዳም/ዳማከሴ/የምች መድሀኒት ጥቅምን መጠየቅ ፣ የዉሻን ተፈጥሯዊ ባህሪይ መጠየቅ

**ማስታወሻ፤** በተገኘው አጋጣሚ ሕፃናት የሚያውቋቸውን እንቅቅልሾችን እንዲናገሩ ይጋብዟቸው፡፡

## ተግባር አራት: የግል ተግባር አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የተክሎች ጥቅም፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ስሞች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! አትክልትና ፍራፍሬ የያዘ ስዕል በማቅረብ ለሁሉም ሕፃናት የሚታይ ቦታ ላይ በማስቀመጥ የሚበሉና የማይበሉትን እንዲለዩ ያድርጓቸው፤የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬን የያዘ ካርድ በማዘጋጀትና በየግላቸዉ በመስጠት ከስዕሉ ጋር እያዩ ለይተው እንዲመድቡና ብዛታቸዉን እንዲናገሩ ያድርጓቸዉ፤ የፍራፍሬ ቅርጽና ጥቅማቸውን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠልም ስማቸውን በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ላይ ደጋግመው እንዲጽፉ ያለማምዷቸው፡፡ በአካባቢያቸው/በቤታቸው የሚያውቋቸውን የሚበሉና የማይበሉ ተክሎችን እንዲናገሩ ዕድሉን ይስጧቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** አትክልትና ፍራፍሬ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ እና የሥዕል ካርድ

**የምዘና ስልት፤** አትክልትና ፍራፍሬ ለይተው መመደባቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣ የተክሎችን ጥቅም እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፤ የአትክልትና ፍራፍሬ ስሞችን በትክክል መጻፋቸውን ማረጋገጥ፣ የሚበሉና የማይበሉ ተክሎችን ስም እንዲናገሩ መጠየቅ

## የግል ተግባር: ሁለት (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የእርሳስ አያያዝ፣ ፣ ቁጥር፣ ፍራፍሬ፣ መመገብ፣ ስዕል፣ ቃላት፣ ቀለም

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ

**የመምህር ሚና :** መምህር! ለሕፃናት ቀለምና እርሳስ ይስጣቸው ተገቢውን የእርሳስ አያያዝ ተጠቅመው በፍላጎታቸው የተለያዩ አትክልቶችና ፍርፍሬዎችን መርጠው በተቆራረጡ ወረቀቶች ላይ እንዲሥሉና ትክክለኛ ቀለም እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡ የቀቡት የዕፅዋት፣ ፍራፍሬዎች እና አትክልቶች ብዛት ስንት እንደሆነ በመጠየቅ የቁጥር ዕውቀታቸውን እንዲያሳድጉ አድርጓቸው፡፡ የቀቡት ቀለም ምን ዓይነት እንደሆነ በመጠየቅ የቀለም ዓይነቶችን እንዲለዩ ያበረታቷቸው፡፡ ከቀቡት ውስጥ አዘውትረው የሚመገቡትን እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ የቀቡትን የዕፅዋትን፣ የፍራፍሬና የአትክልት ዓይነቶች በመለማመጃ ደብተር ላይ እንዲጽፉ አደርጓቸው፡፡ በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን ተጠቅመው የተለያዩ ዕፅዋትን፣ ፍራፍሬዎችና የአትክልቶች ሥዕሎች ሞዴል በመሥራት እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** መቀስ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ላጲስ፣ ቦርድ እውነተኛ ሞዴል አትክልቶችና ፍራፍሬዎች፣ የአትክልት ቦታዎች፣ ፕላስቲክ፣ችግኝ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ፣ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ፣ የተሠሩትን ማየት:

## ተግባር አምስት: መዝሙር (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** እንስሳት፣ ድምፅ፣ እንቅስቃሴ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር! ሕፃናት ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር እንዲዘመሩ ያድርጉ።

**የመዝሙሩ ርዕስ: የቤት እንስሳት**

የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ/2/
አዎ ምን ምን ይላሉ
ድመት ትዘምራለች፣ ትደንሳለች፣
ሚያው ሚያው ትላለች፣
የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ፣
አዎ አዎ ምን ምን እያሉ፣
ውሻ ምን ይላል ምን ምን ይላል፣
ው ው ው ይላል አጥንት ይግጣል፣
የቤት እንስሳት መዘመር ይችላሉ፣
አዎ አዎ ምን ምን እያሉ፣
ዶሮስ ምን አለ ምን ምን አለ፣
ኩኩሉ ኩኩሉ አለ በአጥር ላይ ዘለለ።
ምንጭ፣ ከኦ ክፍል የመምህሩ መምሪያ የተወሰደ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ውድ መምህር! ከሰው ልጆች ጋር አብረው የሚኖሩ እንስሳትን የያዘ ሥዕል /ፎቶ/ ከሞባይል ወይም ከሌላ በማሳየት ይጠቀሙ

**የምዘና ስልት፤**በትክክል መዘመራቸውን ማዳመጥና እንቅስቃሴያቸውን መመልከት፣ የቃል ጥያቄ

## ተግባር ስድስት: የፕሮጀክት ሥራ (8 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** እንቅስቃሴ፣ ዘር፣ ማህበራዊ ግንኙነት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በፕሮጀክት፣

**የመምህር ሚና :** ውድ መምህር!፣ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የአትክልት ቦታ ይምረጡ፤ ህጻናቱን በቡድን በቡድን ይመድቧቸውና እያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ የአትክልት መትከያ እቃ አፈር ጨምረዉ ይዘዉ እንዲመጡ ያድርጓቸዉ፤ ተማሪዎችን ከክፍል ውጪ ይዘዋቸው በመውጣት በየቡድናቸው የሚሠሩትን ይግለፁላቸው። በእቃቻው ዘር ከዘሩ በኋላ በየዕለቱም ውሃ በማጠጣት፤ በመኮትኮትና በመንከባከብ እንዲከታተሉ ያድርጓቸዉ። ተክሎችን ለመንከባከብ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በተግባር እንዲያውቋቸው ዕድሉን ይስጧቸው።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የአትክልት መትከያ እቃ፣ የዉሀ ማጠጫ እቃ፣ መኮትኮቻ፣ አፈር፣ ውሀ፣ የተለያዩ ዘሮች

**የምዘና ስልት:** ተክሎች ለመብቀል የሚያስፈልጋቸዉን ነገሮች መጠየቅ፣ በተግባር ሲሠሩ መመልከት

## ሦስተኛ ሳምንት

### ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት

**አጥጋቢ የመማር ብቃት :**

- ✓ የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን ያከናዉናሉ፡፡
- ✓ ለሌሎች ጥንቃቄ በማድረግ ማህበራዊ ግንኙነታቸዉን ያሳድጋሉ፡፡
- ✓ ለራሳቸው እንክብካቤ የማድረግ ልምድን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ የተለመዱ ቃላቶችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችንና ቁሶችን  ያወዳድራሉ፡፡
- ✓ ቁሶችንና ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ ቁሶችን በዓይነት በዓይነታቸዉ ይመድባሉ፡፡
- ✓ ባህላዊ ቅርሶችን በመንከባከብ ዋጋ ይሰጣሉ፡፡
- ✓ ቀላል የጣትና የእጅ እንቅስቃሴ ተግባራትን ያከናዉናሉ፡

**ንዑስ ይዘቶች:** ራስን መቻል፣ ራስንና አካባቢን መንከባከብ፣ ቃላት፣ የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደምተከተል ማስቀመጥ፣ ባህላዊ ቅርሶች

**ተግባር አንድ: የተግባር ሥራ (5 ክፍለ ጊዜ)**

**ቁልፍ ቃላት:** አካባቢን መንከባከብ ፣ቁጥር፣ እፅዋት፣ንግግር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር ሥራ ፣ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ፣በገለፃ

**የመምህር ሚና:** መምህር! እባክዎትን በቅድሚያ ከዚህ በፊት ህፃናት ተክለዋቸዉ የነበረዉን የተለያዩ ችግኞች ከህፃናቱ ጋር በመጎብኘት እድገታቸውን እንዲገመግሙ በማድረግ ያልበቀሉ ካሉ በሌላ ዘር በመተካት፣ አፈር ያነሳቸዉን በመጨመር፣ የፀሀይ ብርሀን ያላገኙትን እንዲያገኙ ቦታ በመቀየር፣ ከአካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን የመጨመር፣ የበቀሉትን እና የጠወለጉ ዕፅዋትን ብዛት መቁጠር እና የመሳሰሉትን ተግባራት እንዲያከናዉኑ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ወደ ክፍል ዉስጥ በመመለስ የገመገሙትን፣ የተሰማቸዉን ስሜትና የጠወለጉ ዕፅዋቶችን ብዛት በቃል ዘገባ እንዲያቀርቡና ያዩትን አትክልቶች በስዕል ስለዉ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ችግኝ፣ ውሃ፣ አፈር፣ ዘር፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ሲሠሩ በማየት)፣ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ፣ ዘገባቸዉን በማዳመጥ

## የተግባር ሥራ: ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ባህላዊ ቅርሶች፣ ቃላት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር ሥራ ፣ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ፣በገለፃ

**የመምህሩ ተግባር:** መምህር! የተለያዩ ባህላዊ ቅርሶችን በስዕል፣ በሞዴል፣ በቅርፅ በማዘጋጀት በክፍል ዉስጥ ጥግ/ማዕዘን በማስቀመጥ ለሕፃናት ያሳዩአቸዉ፤ በመቀጠልም ስማቸዉን እንዲናገሩና እንዴትመንከባከብ እንዳለባቸው በተግባር እንዲያሳዩ ያድርጓቸዉ፤ በመጨረሻም እያንዳንዳቸዉ ምን አይነት ባህላዊ ቅርሶች እንደተንከባከቡና ብዛታቸው ስንት እንደሆነ እንዲናገሩ እንዳደረጉ በመጨረሻ በሕፃናት መለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን ሥዕላዊ መግለጫ እንዲያዩ ያድርጓቸው::

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ባህላዊ ቅርሶች ስዕል፣ሞዴል፣ቅርፅ





**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ሲንከባከቡ በማየት)፣ የቃል ጥያቄ

**ተግባር ሁለት:** የግል ሥራ (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** አኃዝ፣ፊደል፣ተክል፣ቁጥር መቁጠር ፣ቀለም

**የማስተማሪያ ዘዴ:** ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ ፣በጥያቄና መልስ፣ በተግባር

**የመምህር ሚና:** እባክዎትን መምህር! የቁጥር ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ቁጥሮች የሚወክሉትን ብዛት ከአትክልትና ፍራፍሬ ሥዕል ጋር በማቀናጀት ቁጥሮችን መቁጠር ያሳዩቸው:: የሥዕል፣ የአኃዝና የፊደል ውክልናን ያለማምዷቸው:: በመቀጠልም እንዲጽፉና እንዲገልጹ ያድርጓቸው::

| ምስል | ጎመን | ሎሚ | ማንጎ | ሙዝ | ቃሪያ | ቲማቲም | እንጆሪ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| |  |  |  |  |  |  |  |
| አህዝ | 1 | 3 | 5 | 8 | 10 | 15 | 20 |
| ፊደል | አንድ | ሶስት | አምስት | ስምንት | አስር | አሥራ አምስት | ሃያ |

ከላይ የተቀመጠዉን ሰንጠረዥ በመመልከት ቁጥሮችን፣ የጓሮ አትክልት እና ፍራፍሬዎችን በማዛመድ እስከ 20 ያሉትን ቁጥሮች በአኃዝና በፊደል ሥዕሉን አስመስለዉ በመሳልና በመቁጠር እንዲለማመዱ ይርዷቸው:: መሥራታቸውን ይከታተሏቸውና ያጠናቀቁትን በመመልከት ደብተራቸውን ያርሙላቸዉ:: ተጨማሪ መልመጃዎችን ከመለማመጃ ደብተራቸው ላይ እንዲሠሩ

ያድርጓቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቁጥር ሰንጠረዥ፣ እርሳስ፣ አባከስ፣ የሥዕል ካርድ፣ ጠጠር፣ የተክል ፍሬ፣ ቆርኪ፣ የፕላስቲክ ክዳን

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(ሲሠሩ በማየት)፣የቃል ጥያቄ ( በቃል በመጠየቅ ፣ደብተራቸዉን ማረም

## ተግባር ሦስት: መስሎ ጨዋታ (3 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ደመና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር! እባክዎትን ይህ ክፍለ ጊዜ የመስሎ ጨዋታ መሆኑን ነግረው መሰሎ መጫወትን የሚተገብሩ ሁለት ሕፃናት በፈቃደኝነት ይምረጡ፡፡ የተመረጡትን ሕፃናት እንዲዘጋጁና ጭውውቱን በመደጋገም በቃላቸው እንዲይዙት ያለማምዷቸው፡፡ በደንብ መረዳታቸውን ሲያረጋግጡ ለክፍል አቻዎቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡በቀጣይ ሁሉም ህፃናት በየተራ እንዲሰሩ እድሉን ይስጡ፡፡

**ጭውውት:** ጽጌረዳና ደመና

**ጽጌረዳ:** አንደምን ዋልክ? ደመና

**ደመና:** እንደምን ውለሻል? ጽጌረዳ

**ጽጌረዳ:** እኔ ቀይ ቀለም ያለኝ ቆንጆ እንቡጥ አበባ ነኝ፤ ከተንከባከቡኝ የበለጠ እየተዋብኩ አድጋለሁ፤ አሁን ግን ውሃ ካገኘሁ አምስት ቀን ሆኖኛል በጥም ልደርቅ ነው፤ ትንሽ ብታካፋልኝ ፈልጌ ነው!

**ደመና:** አሁን ወደሌላ አካባቢ እየሄድኩ ነው ቸኩያለሁ ስመለስ አዘንብልሻለሁ፡፡

**ጽጌረዳ:** ብትረዳኝ አሁን ብትጥልልኝ መዳን እችል ነበር፤ ግን ከቸኮልክ ምንም ማድረግ

አልችልም በማለት ጽጌረዳ በጣም አዘነች፡፡

**ደመና:** ተመልሼ መጥቻለሁ አሁን በቃሌ መሠረት ውሃውን ላዝንብልሽ በማለት ብዙ ዝናብ አዘነበላት፡፡ ግን ጽጌረዳ በጣም ተጠምታ ስለነበር ደርቃ አገኛት፡፡

**መምህር!** እባክዎትን ከታሪኩ ምን እንደተገነዘቡ ይጠይቋቸው፡፡ ከዚህ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ታሪክ እንዲናገሩ ዕድሉን ይስጧቸው፡፡ ታሪኩን በሥዕላዊ መግለጫ እንዲገልጹት/እንዲሥሉት ያበረታቷቸውና በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን ተግባር እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የፅጌረዳና የደመና ሥዕል፣ እርሳስ፣ ልሙጥ ወረቀት፣ ላጲስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ሲጫወቱ በማየት)፣ የቃል ጥያቄ : በጭውውቱ ውስጥ ያሉት ባላታሪኮች እነማን ነበሩ፣ ውሃ በጣም የተጠማው ማነው...

## ተግባር አራት: መዝሙር (4 ክፍለጊዜ)

### መዝሙር አንድ ( 2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ መጠን፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር! ቀጥሎ የቀረበዉን መዝሙር ሕፃናቱ እንዲዘመሩ ያድርጓቸዉ፤ በመጨረሻም ሕፃናት መለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን ተግባር ያሠሯቸዉ።

**ትንሽ ትንሽ ወፎች**

አንድ ሁለት ሦስት ትንሽ ትንሽ ወፎች
አራት አምስት ስድስት ትንሽ ትንሽ ወፎች
ሰባት ስምንት ዘጠኝ ትንሽ ትንሽ ወፎች

አሥር ትናንሽ ወፎች

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ቴፕ ፣ፍላሽ፣ ጂፓስ፣ ስልክ፣ የወፍ ምስል ፣የቁጥር ካርድ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ሲዘምሩ በማየት)፣ የቃል ጥያቄ ስንት ወፎች ነበሩ፣ መጠናቸው ምን ያክላል፣

### መዝሙር ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መቀነስ፣ ማካፈል፣ጓደኝነት፣ ንጽህና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ቀጥሎ የቀረበዉን መዝሙር ሕፃናቱ እንዲዘመሩ ያድርጓቸዉ፤ በመጨረሻም ሕፃናት መለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን ተግባር ያሠሯቸዉ።

**ሶስት ሙዞች አሉኝ**

እኔ እኔ ሶስት ሙዞች አሉኝ
ለጓደኛዬ አንዱን ስሰጠዉ ስንት ይቀረኛል
ለአንች ለአንች ሁለት ቀርቶሻል
እኔ እኔ ሁለት ሙዞች አሉኝ
ለጓደኛዬ አንዱን ስሰጠዉ ስንት ይቀረኛል
ለአንች ለአንች አንድ ቀርቶሻል
እኔ እኔ አንድ ሙዝ አሉኝ
ለራሴ ስንት ወሰድኩኝ
ለአንች ለአንች አንድ ወስደሻል
በሉ ልጆች እጅን እጥብ እጥብ
ሙዝን እጥብ እጥብ
በጋራ ብልት ብልት

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የሙዝ ስዕል/ሞዴል፣ የቁጥር ካርድ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ሲዘምሩ በማድመጥ)፣ የቃል ጥያቄ ፡ በመጀመሪያ ፣ስንት ሙዝ ነበረኝ፣ ለጓደኛዬ ስንት ሰጠው ፣ስንት ሙዝ ቀረኝ ሙዙን ከመብላታችን በፊት ምን አደረግነው፣ እጃችንስ...

## ተግባር አምስት: ተረት (5 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መልካም ባህል፣ ማኅበራዊ ግንኙነት ፣እሴት፣መጠን

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ በማስመሰል

**የመምህር ሚና ፡** መምህር! ይህ ክፍለ ጊዜ የተረት መሆኑን ለሕፃናቱ ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም ተረቱን ካዳመጡ በኋላ ገፀባህሪውን ተላብሰው እንዲጫውቱ ያድርጓቸው፡፡

### አቶ ዳውድና ሁለት ልጆቹ

በአንድ ሰፈር የሚኖሩ በጣም ጨዋና የተከበሩ አቶ ዳውድ የሚባሉ ግለሰብ ነበሩ፡፡ ሁለት ልጆችም አሏቸው፡፡ እነሱም ሙሳና አብርሀም ይባላሉ፡፡ እርሳቸውም የሌሉበት ሽምግልና በሰፈሩ የለም፡፡ ሽምግልና የሚቀመጡት ትልቁ ዛፍ ስር ነበር፡ ማኅበረሰቡም በሀቅ ስለሚፈርዱ በሽምግልና እንዲገቡላቸው ይወዳሉ፡፡ ከሽምግልና ሲመለሱ ምንጊዜም ጊዜ ማታ ማታ ስለውሏቸው ለልጆቻቸው ያወጋሉ፡፡ በወጋቸውም መሀል ማኅበረሰቡ ካለው መልካም ዕሴት በማፈንገጥ የሚፈጠር አለመግባባት መሆኑን ለልጆቻቸው ይመክራሉ፡፡ ቀደምት የነበሩን ደንን የመትክል፣ የመንከባከብ፣ አብሮ በጋራ የመጠቀም፣ የመብላትና አብሮ የመሥራት ባህሎቻችንን ወደጎን በመተው የሚፈጠር ማኅበራዊ ቀውስ ጠብ እንደሚባል ያስረዳሉ፡፡ ጠብንም ለመፍታት ቤተሰባዊ የሽምግልና ደንቦች አሉን፡፡ እነዚህን ከተከተልን ራስ ወዳድነትን፣ ጥላቻን፣ ስስታምነትን፣ ብቸኝነትን ማስቀረት እንደሚቻል ይመክራሉ፡፡ ልጆቻቸውም ያልገባቸውን በመጠየቅ ከአባታቸው ጋር በነጻነት ይወያያሉ፡፡ በመጨረሻም በማኅበረሰቡ እንድትወደዱ ከፈለጋችሁ መልካም ባህሎቻችሁንና ቅርሶቻችሁን አውቃችሁ እንድታከብሩና ለማስከበር እንድትተጉ አደራ እሰጣችኋለሁ በማለት ይመክሯቸው ነበር፡፡

መምህር! እባክዎትን ሕፃናቱን በተረቱ መሠረት ያዘጋጇቸው፤ አንዱ ሕፃን እንደ አቶ ዳውድ ሌሎቹ ሁለቱ ሕፃናት እንደ ሙሳና አብርሃም ሆነው እንዲሠሩና እርስዎም በማለማመድ ሐሳቡን ያስረዷቸው፡፡ በመጨረሻም በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ባህላዊ አልባሳት፣ ጋቢ፣ ጥላ፣ ከዘራ፣ባርኔጣ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ ሲናገሩ እና ሲተውኑ በማየት፣

**የቃል ጥያቄ:** ሽምግልና የሚቀመጡት ማን ነበሩ፣ ልጆቻቸውን ምን በማለት ይመክሩ ነበር፣ ሽምግልና የሚቀመጡት የትኛው ዛፍ ስር ነው...

## ተግባር ስድስት: የክፍል ውጪ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ እንቅስቃሴ፣ ጤና ፣ቁጭ ብድግ፣ ዱብዱብ፣ ዘለል ዘለል፣ፍራፍሬ፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ለሕፃናት ክፍለ ጊዜዉ የክፍል ዉጭ ጨዋታ እንደሆነ በመንገር ይዘዋቸዉ ይዉጡ፤ በመቀጠልም ቀላል የሰውነት እንቅስቃሴዎችን እንዲሰሩ እና ለማነቃቂያነት የሚከተለውን መዝሙር በተግባር እየዘመሩ እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡፡

**የመዝሙሩ ርዕስ : ስፖርት ለሁላችን**

ስፖርት ስፖርት ስፖርት ለሁላችን
ይጠበቅ ጤናችን/2/

ዱብዱብ
አንድ ሁለት ሦስት አራት

ቁጭ ብድግ
አምስት ስድስት ሰባት ስምንት

ዘለል ዘለል
ዘጠኝ አስር አሥራ አንድ አሥራ ሁለት

እናጨብጭብ
አሥራ ሶስት አሥራ አራት አሥራ አምስት አሥራ ስድስት

እንደገና
አሥራ ሰባት አሥራ ስምንት አሥራ ዘጠኝ ሀያ

መምህር! ከሰውነት ማነቃቂያ እንቅስቃሴው በኋላ የሥዕል ካርዶችን በማዘጋጀት ከ1 20 ቁጥር ይጻፉባቸው፡፡ በጀርባቸው ደግሞ የፍራፍሬና አትክልት ምስሎችን ይሣሉባቸው፡፡ ቁጥር የተጻፈባቸውን የሥዕል ካርዶች አዘበራርቀው መሬት ላይ በአንድ ረድፍ ይደርድሯቸው፡፡ በመቀጠል ሕፃናቱ የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ይርዷቸው፡

ቁጥር እንዲጠሩና የጠሩትን ቁጥር እንዳይረሱ ይንገሯቸው፤ የመዝለያ ቦታ ታሳቢ በማድረግ በቁጥራቸው ላይ እንዲሚዘሉ ያስረዷቸው፤ የተጠራው ሕፃን በራሱ ቁጥር ላይ መዝለል ይኖርበታል፤ በሌላ ቁጥር ላይ ከዘለለ ከጨዋታው ይወጣል፡፡ ለተግባር ሥራው በመጀመሪያ እርስዎ በተግባር ያሳዩአቸው፡፡ የቁጥሩን ጀርባ በመመልከት ምን ዓይነት ፍራፍሬ /አትክልት/ እንደ ደረሳቸው እንደ ሎተሪ በማውጣት ይጫወታሉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የሥዕል ካርድ፣ የቁጥር ካርድ፣ በድምፅ የተቀረፀ መዝሙር

**የምዘና ስልት:** የመዝለያ ቦታ ታሳቢ በማድረግ በቁጥራቸው ላይ ሲጫወቱ በማየት፣ የቃል በስንት ቁጥር ላይ ዘለልክ/ሽ፣ የዘለልሽው/ከው ቁጥር ላይ ምን አይነት ፍራፍሬ ነበር፣ ምን አይነት፣ ምን አይነት እንቅስቃሴዎችን ሰራችሁ፣

# አራተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ 30 ክፍለ ጊዜ/ 15 ሰዓት

### አጥጋቢ የመማር ብቃት:

- ✓ ሕፃናቱ ይህንን ይዘት ከተማሩ በኋላ:
- ✓ ለሌሎች ያላቸውን ግንዛቤ ያሳድጋሉ፡፡
- ✓ የቅርብ አካባቢያቸዉን የመንከባከብ ሀላፊነታቸዉን ይወጣሉ፡፡
- ✓ ከሌሎች ጋር በመከባበር ይጫወታሉ፡፡
- ✓ አካላዊ እንቅስቃሴ ይሰራሉ፡፡
- ✓ ሥዕሎችን በመሳል ይቀባሉ፡፡
- ✓ እጆቻውንና ጣቶቻቸውን በመጠቀም የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡
- ✓ ቅርፅና ቅጥን/ድግግሞሽን/ሥርዓተ ጥለትን ይለያሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች:** ማኅበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን መግለጽ፣ ቅጥ፣ ቅርፅ፣ ጥበባዊ ግንዛቤ፣ የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር የሚሉ የትምህርት ይዘቶች ተካተዋል:

### ተግባር አንድ: መዝሙር (5 ክፍለ ጊዜ )

**ቁልፍ ቃላት:** አካላዊ ዕድገት፣ አካባቢን መንከባከብ፣ ተክሎች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣በገለፃ፣በጥያቄና መልስ፣

**የመምህሩ ሚና:** መምህር! ከዚህ ትምህርት በፊት የተማሩትን ሕፃናት እንዲያስተውሱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ዋና ነጥቦችን በማስታወስ ወደ ዛሬው ትምህርት ይግቡ፡፡ ለሕፃናት ዕፅዋትን እንዴት እንደሚንከባከቡ የሚገልጽ መዝሙር በማዘጋጀት/በማቅረብ ያሰሟቸው:

መምህር! ለሕፃናት ድጋፍ በማድረግ እንዴት ሐላፊነት ወስደው ዕፅዋትን እንደሚንከባከቡ ተራ በተራ ወጥተው እንዲለማመዱና እንዲሁም ለዕፅዋት የሚደረገውን እንክብካቤ ጥቅም እንዲያውቁ ያድርጓቸው፡፡ ሁሉም ሕፃናት ተራ በተራ እንዲሳተፉ ያድርጉ፤ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ ለሕፃናት ችግኞችን ስለመትከልና ውሃ ስለማጠጣት ግንዛቤ ይስጧቸው፡፡

የሚከተለውን መዝሙር ሕፃናት በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጓቸው፡፡

<u>መዝሙር 1</u>

ጎበዝ ችግኝ እንትከል (2 ጊዜ)፤
ተክለን እንከባከብ (2 ጊዜ)፤
አንድ ስንቆርጥ ሁለት ብንተክል፣
ጤናማ ይሆናል አካባቢያችን፣
በእድገት ከፍ ይላል ሀገራችን፣
ስለዚህ እንትከል በጋራ ሁነን፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የዕፅዋት ሥዕሎች፣ የዕፅዋት ቅጠሎችን፣ በክፍል ውስጥ በጣሳ (በባልዲ) የተተከሉትን ዕፅዋት/ተክሎች/

**የምዘና ስልት:** ለዕፅዋት የሚደረጉትን እንክብካቤዎች በምልከታ መከታተል፣ የቃል ጥያቄ መዝሙሩ ስለምን ይነግረናል፣ ለተክሎች ምን አይነት እንክብከቤ ማድረግ አለብን፣

## ተግባር ሁለት: የክፍል ውጭ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ )

### የክፍል ውጭ ጨዋታ አንድ

**ቁልፍ ቃላት:** አካላዊ እንቅስቃሴ፣ መንሸራተት፣ ገመድ ዝላይ፣ዕለታት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**መምህር ሚና:** ውድ መምህር! ለአካላዊ የእንቅስቃሴ ጨዋታ ሕፃናት ከክፍል ውጪ እንዲወጡ በማድረግ ለ5 ደቂቃ ያህል ሕፃናት የሚያውቁትን ቀላል አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲሠሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ለሕፃናት ምቹና ሳቢ የሆነ ቦታ መርጦ ማዘጋጀት፤ ሕፃናት ክብ ሠርተው እንዲቀመጡ በማድረግ ስለሚሠሩትን/ስለሚያከናውኑት/ አካላዊ እንቅስቃሴ በገለጻ ያስረዷቸው፡፡ በተግባር ሠርተው ያሳዩቸው፡፡ **ለምሳሌ:** መዝለል፣ መዘርጋት ወዘተ. በመቀጠል ሕፃናቱ በፍቃደኝነት ወጥተው እንዲያሠሩ ያድርጉ፡፡

አካላዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንደ መዝለል፣ መዘርጋት፣ መታጠፍ የመሳሰሉትን በእርምጃ ወይንም ንድፍን ተከትለው እንዲሠሩ እገዛ ማድረግ፤ ቀላል እንቅስቃሴውን ደጋግመው እንዲሠሩ ያበረታቷቸው፤ የውጪ መጫዎቻዎችን በመጠቀም በመንሸራተት፣ በገመድ ዝላይ፣ በማምለጥና በዱብ ዱብ ለሕፃናት በማሳየት እንዲሠሩ ይርዷቸው፡፡

### በመቀጠልም ሰኞ ማክሰኞ ማጫወት

በየተግባሩ መሐል ስሜታቸውን መጠየቅ፤

የሕፃናቱን ሙከራ ማበረታታት፤

ተግባራቱ ላይ ሁሉም ሕፃናት እንዲሳተፉ መከታተል፤ ማገዝና ማበረታታት፡፡

**መምህር!** ለሕፃናቱ ሰፊ ቦታ በመፈለግ ተቀምጠው እንዲጫወቱ ለምሳሌ፣ ዛፍ ጥላ ሥር በመቀመጥ እንዲዘምሩ ወይንም የፈለጉትን ተረት እንዲናገሩ በማድረግ እርስ በርሳቸው እንዲማማሩ ያድርጓቸው፡፡

ከሰሙት ተረት ምን እንደተማሩ መጠየቅ ለምሳሌ፣ እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ? ወይንም ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም ሕፃናት አካላዊ እንቅስቃሴን ማድረግ ጤናማ፤ የተስተካከለና ጠንካራ ሰውነት እንዲኖራቸው እንደሚያደርግ ይግለጹላቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ገመድ፣ የተለያዩ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** የተለያዩ እንቅስቃሴችን ሲያደርጉ በምልከታ መከታተል፣ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ለምን እንደሚጠቅም የቃል ጥያቄ ፡ ምን አይነት እንቅስቃሴ ሰራችሁ፣የሳምንቱን ዕለታት ጥራልኝ/ጥሪልኝ፣ከተረቱ ምን ተማራችሁ

## ተግባር ሶስት: የፕሮጀክት ሥራ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ዘር፣ አፈር፣ ጥራጥሬ

**የማስተማሪያ ዘዴ** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! ለህፃናት ከክፍል ዉጭ ወጥተዉ የፕሮጀክት ሥራ (ተክሎችን መትከል) እንደሚሰሩና ማድረግ ስላለባቸዉ ጥንቃቄና ደህንነት እንዲሁም የአሰራር ቅደም ተከተሎችን በማስገንዘብ ወደ ቦታዉ ይዘዋቸዉ ይሂዱ፡፡

### የአሰራር ቅደም ተከተል

- ✓ አፈር፣ ውሃ እና የፀሐይ ብርሃንን በመጠቀም በፕላስቲክ/በጣሳ ተክሎችን በሚከተለው ቅደም ተከተል እንዲተክሉ ያግዟቸው፡፡

1. አፈር፤ ፕላስቲክ (ጣሳ) እና ውሃ ማዘጋጀት፤
2. የተዘጋጀውን አፈር ፕላስቲክ /ጣሳ/ ውስጥ መጨመር
3. የጥራጥሬ ዘር **ለምሳሌ:** በቆሎ፣ ባቄላ ወዘተ መጨመር እና አፈሩን ብርሃን የሚያገኝበት ቦታ ማስቀመጥ
4. በየዕለቱ ውሃ እያጠጡ በመንከባከብ ዕድገቱን መከታተል
5. በመጨረሻ የተከሉዋቸውን እንዲጎበኙ በማድረግ እንዲማማሩ ይርዷቸው፡፡

በቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ሕፃናት በቤታቸው/በጓሮአቸው ውስጥ ችግኞችን/የአትክልት ዘርን በመትከል እንዲንከባከቧቸው ያድርጓቸው፡፡ ከተከሉ በኋላ ውሃ ማጠጣት፣ በየጊዜው ክትትል ማድረግ፤ አረሞችን ማስወገድና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን እንደሚያስፈልጋቸው ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን ተግባራት ያሠሯቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ውሃ፣ የውሃ ማርከፊከፊያ፣ ችግኝ/ዘር አፈር፣ ባልዲ፤

**የምዘና ስልት:** ሕፃናቱ ከጓደኞቻቸው ጋር አብረው በተራ ሲሰሩ፣ ቁሳቁሶችንም በጋራ ሲጠቀሙ በምልከታ ማረጋገጥ፣ የተለያዩ የተክል መንከባከቢያ መሣሪያዎችን እንዲለዩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፡፡ ምን ተክል ተከልክ፣ ለመብቅ ምን ምን ይፈልጋል፣፣ ከወላጆች ጋር በጋራ ተግባራቸውን መገምገም

## ተግባር አራት: የግል ተግባር (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቅርፅ ፣ፈጠራ፣ አበባ፣ ዛፍ፣ ፍራፍሬ፣ ቀለም

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** ውድ መምህር! የተለያዩ የዕፅዋት ዓይነቶችን ምስሎች(ፖስተሮችን) በማዘጋጀት፤ በክፍል ውስጥ በሚታይ ቦታ ላይ ያስቀምጡ/ይስቀሉ፤ በትምህርት ቤት እና በቤታቸው ውስጥ ስላሉ የዕፅዋት ዓይነቶች በክፍል ውስጥ ለሕፃናት ያስተዋውቁ፤ ካዳመጡት ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ምላሾቻቸውን ይቀበሉ፤ ሕፃናት በክፍል ውስጥ ሰፊ ቦታ እንዲያገኙ ክፍሉን በተገቢው መልኩ ያደራጁን፤ ሕፃናት የዕፅዋት የቅርጽ አካልን በፈጠራ ሲሠሩ የሚያሳይ ስዕል ወይም ቪዲዮ ያሳዩ፡፡ ውድ መምህር! በመቀጠልም የዕፅዋትን (ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ ዛፍ፣

አበባ ወዘተ) ቅርፅ እንዲሠሉና እንዲቀቡ ማድረግ፤ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሠሩ ዕድል መስጠት፤ ለሕፃናቱ ሥራና ሙከራ ማበረታታት፤ በየተግባሩ መሐል ስሜታቸውን መከታተል አይዘንጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የዕፅዋት ቅጠል፣ ወረቀት፣ ደብተር፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ማጥፊያ (ላጲስ) መቅረጫ፤

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ሲሠሉና ሲቀቡ በማየት)፣ የቃልጥያቄ ፡ ምን አይነት ቅርፅ ሰራህ፣ የሰራኸውን ቅርጽ ምን አይነት ቀለም ቀባህ

## ተግባር አምስት: በሥራ መማር (10 ክፍለ ጊዜ)

በሥራ መማር አንድ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ተግባር:** ዕፅዋት፣ ዛፍ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ቁሳቁሶችንም በጋራ መጠቀም፣ በጋራ መጫወት፣ ሌሎችን መንከባከብ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና :** ውድ መምህር! ለሕፃናቱ ዕፅዋትን አስመልክቶ አንድ ማነቃቂያ መዝሙር በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጓቸው፡፡ የተለያዩ የዕፅዋት ቅርጾችን የሚያሳዩ ምስሎች (ፖስተሮችን)፣ ሞዴሎችን በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ በሚታይ ቦታ ላይ ያስቀምጡ/ይደርድሩ፤ የተለያዩ የዛፍ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ የዕፅዋት ቅርጾችን (**ለምሳሌ:** በካርቶን፣ በወረቀት ወዘተ) በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ያቅርቡ፤ በመቀስ የተለያዩ የዕፅዋት ቅርጾችን እንዲቆራርጡ ያድርጉ፤ ሥራውንም ሕፃናት በራሳቸው ደጋግመው እንዲሠሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡

ውድ መምህር! በክፍል ውስጥ ጭቃ በማምጣት ሕፃናት እንዲያቦኩ፣ እንዲጠፈጥፉ፣ እንዲቆራርጡ ያድርጓቸው፡፡ ሕፃናቱ በተሰጣቸው ጭቃ አማካይነት የሚወዱትን ዕፅዋት ማለትም ዛፍ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሠሩ ይደግፏቸው፡፡ ሁሉም ሕፃናት እንዲሳተፉ በመከታተልና በማገዝ ያበረታቷቸው ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** መቀስ፣ጭቃ፤ የተለያዩ የዕፅዋት ቅርጾች

**የምዘና ስልት:** ሕፃናት የዕፅዋት የዛፍ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ቅርጾችን ሲቆራርጡ በተሰጣቸው ጭቃ ዛፍ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ሲሠሩ በምልከታ መከታተል፤ የቃል ጥያቄ ምን አይነት እፅዋት ሰራችሁ፣

## በሥራ መማር: ሁለት (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ገመድ፣ መከባበር፣ እንቅስቃሴ፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህሩ ሚና:** ውድ መምህር! ሕፃናቱን ወደ ውጭ በማስወጣት ለማነቃቂያ የሚሆን ነፃ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ለአምስት ደቂቃ ያህል ይፍቀዱላቸው፤ ሕፃናት ባሉበት ቦታ ሆነው ለመጫወት እርስ በእርስ እንዲከባበሩ በአካባቢያቸው ያለውን ዕውቀት እንዲያሳድጉ አጠር ያለ ግንዛቤ መስጠት /ለሕፃናት ማስተዋወቅ/፤ ሕፃናት ገለጻው ሲነገር በማዳመጥ ለሚጠየቁት

ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤

መምህር! ሕፃናቱ አብረው ተራ በተራ እንዲጫወቱ፣ ቁሳቁሶችንም በጋራ እንዲቀባበሉ/እንዲዋዋሱ እንዲሁም ተከባብረው እንዲጫወቱ ያግዟቸው፤

በተጨማሪም ሕፃናትን የችግኝ መትከያ ቦታ በመውሰድ የተለያዩ ዕቃዎችን ለምሳሌ፡ ውሃ ማጠጫ፣ ማርከፊከፊያ፣ ገመድ፣ መቆፈሪያ፣ ወዘተ ማሳየት ይችላሉ:: በእርስዎ ድጋፍ ሕፃናት በየተራ ውሃ እንዲያጠጡ፣ ለችግኙ አፈር እንዲጨምሩና መኮትኮት እንዲለማመዱ ያድርጓቸው:: ይህንንም ተግባር በተደጋጋሚ እንዲያከናውኑ፤ ለሕፃናቱ ምላሽ ማስተካከያ በመስጠትና ሙከራቸውን በማድነቅ፤ በየተግባሩ መሐል ስሜታቸውን በመጠየቅ ያበረታቷቸው::

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ውሃ ማጠጫ፣ ማርከፊከፊያ፣ ገመድ፣ መቆፈሪያ፣ ወዘተ

**የምዘና ስልት:** በተግባር ውሃ ሲያጠጡ፣ ለችግኙ አፈር ሲጨምሩና ሲኮተኩቱ መመልከት፣ የቃል ጥያቄ፡ ህፅዋትን ለመንከባከብ ምን ምን መሳሪያዎች ያስፈልጉናል፣ከጓደኞቻችን ጋር ለመጫወት እርስ በእርስ ምን ማድረግ ያስፈልገናል

# አምስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት

## አጥጋቢ የመማር ብቃት :

- ✓ ጥሩና መጥፎ ባህሪያቶችን ይለያሉ::
- ✓ የቦታዎችን መገኛ ይገልጻሉ::
- ✓ ነገሮችን መለየትና መመደብ ይችላሉ::
- ✓ የፊደላትን ድምፅ ከቃላትና ከሥዕል ጋር ያዛምዳሉ::
- ✓ በአካባቢያቸው ያሉ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ቁሶችን ይለያሉ::
- ✓ የተለያዩ ቅርጽ ያላቸውን ንድፎች የመሥራትን ልምድ ያሳድጋሉ::

**ንዑስ ይዘቶች:** የግብረ ገብ ዕሴቶች፣ የፊደላት ድምፅ፣ እሴቶች፣ የንግግር ድምፅ፣ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አካባቢ፣ የቦታ ግንዛቤ፣ መለየትና መመደብ፣ (ማያያዝ፣ ማገናኘት እና ትግበራ)

### ተግባር አንድ: ውይይት (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጥሩ ፣መጥፎ፣ ተክሎች፣ እንክብካቤ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በውይይት፣ በበገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር! ሕፃናቱን በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድን ይክፈሏቸው:: በመቀጠልም በየቡድናቸዉ አትክልቶችን ከመንከባከብ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ጥሩና መጥፎ ባህሪያቶችን እንዲዘረዝሩ ያድርጓቸዉ፤ በመጨረሻም በየቡድናቸዉ ምን ያክል እንደዘረዘሩ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ ካደረጓቸዉ በኂላ በክፍል ዉስጥ ግድግዳ ላይ ከተለጠፉት ስዕላዊ መግለጫዎች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸዉ::

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** አትክልቶች ላይ የሚደረጉ ጥሩና መጥፎ ባህሪያቶችን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት:** የዘረዘሯቸዉን ጥሩና መጥፎ ባህሪያቶች ሪፖርት ሲያቀርቡ በማዳመጥ፣ የዘረዘሯቸዉን ጥሩና መጥፎ ባህሪያቶች ከስዕላዊ መግለጫዉ ጋር ሲያዛምዱ በመመልከት፣የቃል ጥያቄ: እፅዋትን ስንከባከብ ጥሩ ተግባር ምንላቸው ምን ምን ናቸው‹ መጥፎ የምንላቸው ተግባራትስ፣ እናንተ የትኛውን ተግባር ታከናውናላችሁ

## ተግባር ሁለት: የመስክ ጉብኝት (5 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጥላና ማረፊያ፣ ማገዶ፣ የግንባታ ሥራ፣ ውበትና ጌጥ፣ የገቢ ምንጭ፣ እቅድ፣ አቅጣጫ፣ የሚበላና የማይበላ ተክል፣ ለመድሀኒት የሚጠቅም ተክል

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመስክ ጉብኝት፣ በትረካ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር! ሕፃናቱን ከክፍል በማውጣት በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ወዳለው የአትክልት ቦታ ይውሰዷቸው፡፡ ዛፎችንም ሆነ ቅጠላቸውን መነካካትና መቁረጥ እንደሌለባቸው በጥብቅ ያስረዷቸው፡፡ የትምህርት ቤቱን አትክልተኛ በመጋበዝ ተክሎችን እንዴት መትከል እንዳለብን፤ ለሰው ልጅ የሚሰጡትን ጥቅም፤ ለምን ለምን አግልግሎት እንደሚውሉና ስማቸውን በማስተዋወቅ እንዲገልጹላቸው ሕፃናቱም ታሪካቸውን በጸጥታ እንዲያዳምጡ ያድርጓቸው፡፡

እኔ አቶ ዘገየ ዋሲሁን እባላለሁ፡፡ የዚህ ትምህርት ቤት አትክልተኛ ነኝ፡፡ በትምህርት ቤቱ በአትክልተኝነት ለ20 ዓመት አገልግያለሁ፡፡ ይህ ትምህርት ቤት ከዛሬ 20 ዓመት በፊት እንደዚህ የሚያማምሩ ትልልቅ ዛፎች፣ ተክሎችና ፍራፍሬ አልነበሩትም፡፡ እኔም ለሥራዬ በመትጋት ከግንባታ ውጪ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በመምረጥና ንድፍ በማውጣት ሥራዬን ጀመርኩ፡፡ በመግቢያ በኩል ግራና ቀኝ የምታዩት ትልልቅ ዛፎች ለጥላና ለማረፊያ እንዲያገለግሉ ታቅደው የተተከሉ ችግኞች ነበሩ፡፡ ከማገዶና ግንባታ ሥራ ውጪ ለምግብነት አያገለግሉም፡፡ ከፊት ለፊት የምታያቸው አበቦች ለውበትና ጌጥ የሚጠቅሙ መንፈስን የሚያድሱ ለፎቶ ለዝግጅት የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ በዚህ በኩል ያሉት ደግሞ ለምግብነት የሚጠቅሙ ተክሎች ናቸው፡፡ ለትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ተሸጠው የገቢ ምንጭ ያስገኛሉ:(ለምሳሌ: ሰላጣ፣ ቆስጣ፣ ቲማቲም፣ ቃሪያ፣ ቀይሥር፣ ካሮት፣ ጎመን፣ አቡካዶ፣ ማንጎ፣ ሎሚ ናቸው)፡፡

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚገኙት ተክሎችን በመንከባከብ ከችግኝ መትከል ትልቅ እስከሚሆኑ ድረስ ማረም፣ መኮትኮት፣ ውሃ ማጠጣትና የመሳሰሉትን ተግባራት አከናውናለሁ፡፡ ተክሎች በዙሪያችን መኖራቸው ለዝናብ መገኘት፣ ንጹህ አየር ለመተነፍስ፣ በረሀነትን ለመከላከል፣ ለሰው ልጅ ምግብነት፣ ለመድኃኒትነት፣ ለእንስሳት ምግብነት፣ ለማገዶነትና ለቤት ቁሳቁስ መሥሪያነት አገልግሎት ይውላሉ፡፡ ስለአዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

**መምህር!** ሕፃናት አቶ ዘገየን ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው፡፡ ሕፃናቱን ወደ ክፍል ይመልሷቸው:: ክፍል ውስጥ እንደገቡ ስለመስክ ጉብኝቱ በቃላቸው ያዩትን (የተመለከቱትን) እንዲናገሩ በየተራ ይጠይቋቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ተክሎች፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ

**የምዘና ስልት :** ታሪክ ሲነገራቸው በጸጥታ ማዳመጣቸውን በምልከታ መከታተል፣ ከታሪኩ በመነሣት የቃል ጥያቄ: ተክሎች ለምን ለምን ይጠቅሙናል፣ ለተክሎች እድገት ምን ማድረግ አለብን

## ተግባር ሦስት: የክፍል ዉጭ ጨዋታ (5 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መጠን፣ ይዘት፣ ቅርጽ፣ ለስላሳነት፣ ሸካራነት፣ስም

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በቡድን ሥራ መማር

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናቱን ከክፍል ውጪ ይዟዋቸው በመውጣት በሦስት ቡድን ይክፈሏቸው፡፡ በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ተክሎችን (አትክልትና ፍራፍሬ፣ ዛፎች፣ አበባ፣ የመሳሰሉትን) እንዲመለከቱና የቅጠሎቻቸውን ልዩነት በመጠን፣ በይዘትና በቅርጽ በማሳየትና በመዳሰስ እንዲለዩ በምልከታው በንቃት እንዲሳተፉ ይርዷቸው፡፡ ቅጠሎች በቅርጽ አንዱ ከአንዱ መለያየታቸውን ከየተክሎቹ አንድ አንድ ቅጠል በጥንቃቄ በመቁረጥ እንዲሰበስቡ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠልም የሰበሰቧቸውን የተክሎቹን ቅጠል ሰፋፊነት፣ ትንንሽነት፣ ለስላሳነት፣ ሸካራነት ስማቸውን ጭምር እንዲለዩ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ጥያቄውን የመለሱትን በክፍሉ ፊት ለፊት በማቆም በጭብጨባ እንዲወደሱ ያድርጓቸው፡፡ የተሰበሰቡትን ቅጠሎች ሦስቱም ቡድን ለየራሱ በአንድ ሰፊና ጠንካራ ወረቀት ላይ በማጣበቂያ በመጠቀም እንዲለጥፉ ያድርጓቸው፡፡ ከቅጠሉ ግርጌ የተክሎቹን ስም እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡ በወረቀቱ ላይ የቡድን አባላትን ስም በመጻፍ ሥራቸውን ለመማሪያነት እንዲያገለግል ለእይታ ምቹ በሆነ የክፍሉ ግድግዳ ላይ ያንጠልጥሉት፡፡ በመቀጠልም ካዩአቸው ውስጥ 3 ቅጠሎችን በመምረጥ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ በእርሳስ እንዲስሉና ስማቸውን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች**</u>

1. በጣም ሰፋፊ ቅጠል ያላቸውን ተክሎችን ስም ዘርዝሩ?
2. ትንንሽ ቅጠል ያላቸውን ተክሎች ስም ግለጹ?
3. ለስላሳ ቅጠል ያላቸው ተክሎች ስም ጥቀሱ?
4. ሸካራ ቅጠል ያላቸውን ተክሎች ስም ተናገሩ?

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተክሎች ቅጠል፣ ቅጠሎችን የሚያሳይ ሥዕል፣ እርሳስ፣ ማጣበቂያ፣ ሰፊና ጠንካራ ወረቀት፣ ላጲስ፣ መቀስ

**የምዘና ስልት:** ቅጠሎችን በመጠን፤ በይዘት፤ በቅርጽ በማሳየትና በመዳሰስ እንዲለዩ መጠየቅ፤ የቡድን ሥራቸውን በመመልከት ተግባራቸውን መመዝገብ፣

## ተግባር አራት: የግል ሥራ (5 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ስም፣ ቀለም ፣መሳል፣ ማድነቅ፣ ብድፍ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በግል ሥራ፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! ይህ ክፍለ ጊዜ ባለፉት ከተማሯቸው የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ጋር ተመሳሰይ መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡ በመቀጠልም የተወሰኑትን እንዲያስታውሱ ይጠይቋቸው፡፡ (ለምሳሌ፡ ሰላጣ፤ ቀይሥር፣ ካሮት፣ ጎመን፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም) በተጨማሪም አሁንም የፍራፍሬ ዓይነቶችን እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ (ለምሳሌ፡ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ማንጎ፣ መንደሪን፣ ዘይቱን፣ ሙዝ) እርስዎም ምን ያህሉን ስማቸውን እንዳስታወሷቸው ይገነዘባሉ፡፡ በመቀጠል የተክሎቹን/ የፍራፍሬዎችን የቀለም ዓይነታቸውን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፤ በመቀጠል የቀለም ዓይነቶችን የያዘ የሥዕል ካርድ (ባለቀለም ወረቀት) በማዘጋጀት አንድ በአንድ ያሳዩአቸው፤ የቀለም ዓይነቱን ስም እንዲናገሩ ዕድሉን ይስጧቸው፡፡ከዚያም ሰፊ ጨርቅ በመጠቀም ለሁሉም ሕፃናት በሚታይ ቦታ የሥዕል ካርዶቹን በግድግዳ ላይ ይስቀሏቸው፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሙባቸውን የአትክልትና ፍራፍሬ የሥዕል ካርዶች በመጠቀም እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡ (ሙዝ ቢጫ፤ ማንጎ አረንጓዴ/ ቢጫ፤ ቲማቲም ቀይ፤ ቃሪያ አረንጓዴ፤ አቡካዶ አረንጓዴ፤ ፓፓያ ቢጫ) በመቀጠል ሕፃናቱ የሚያውቋቸውን ሁለት/ሦስት/ አትክልት (ፍራፍሬ) በመምረጥ ነጭ ወረቀት ይስጧቸውና እርሳስ በመጠቀም አስመስለው ይሳሉሲስሉም ይከታተሏቸው፡፡ ለሳሉት ስእላቸውን እውነተኛ ቀለም እንዲይዝ እንዲቀቡት ይርዷቸው፡፡ በመጨረሻም ስለሳሉት ስእል እንዲያብራሩ እድል ይስጡ ቀጥሎ በንድፍና በቅብ የተሻለውን ሥዕል በመምረጥ በክፍሉ ውስጥ በሚታይ ቦታ በመስቀል ሕፃናቱን እንዲያደንቁ ያድርጉ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን ተግባር እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡

**ለማበረታታት ምሳሌ፡** አቢ ጎበዙ የሚወደውን ፍራፍሬ ይናገራል፤ ለምስሌ፡ አናናስ ካለ…

አናናስ አናናስ የዛፍ ፍሬ

ማነው ጎበዝ ንገሩኝ ዛሬ

አቢ በማለት ያጨበጭባሉ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** ሎቶ፣ አትክል፣ፍራፍሬ፣ የሥዕል ካርድ፣ ጨርቅ፣ ማጣበቂያ፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ (ማርከር)፣ ወረቀት፣ ባለቀለም ወረቀት

**የምዘና ስልት፡** ምልከታ፡ ህፃናቱ በተቀመጠው ክፍለ ጊዜ ተግባራቱን ሲያከናውኑ በመመልከት፣የቃል ጥያቄ፡ ቲማቲም ምን አይነት ቀለም አለው፣ ብርትኳንስ፣ ፍራፍሬዎች ምን ላይ ይበቅላሉ፣ ምን ሳልክ/ሽ፣ ምን አይነት ቀለም ቀባህ/ሽ…

## ተግባር አምስት፡ እንቆቅልሽ (5 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡ ፊደል ቃላት:** የተክል ክፍል፣ ድምፅ፣ የአካል ክፍል፣ ምግብ፣ ጤና፣ ተፈጥሮ፣ ሻካራ እና ለስላሳ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ…

**የመምህር ሚና፡** መምህር! ሕፃናቱን ለማነቃቃት ቀደም ሲል ከተማሯቸው አትክልትና ፍራፍሬ ስም በመነሣት የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

**ምሳሌ1፡** በ “ከ” ዘር የሚጀምር የአትክልት ዓይነት ስም ጻፉ? **መልሱ** ካሮት

**ምሳሌ 2፡** በ “ቀ” ዘር የሚጀምር የአትክልት ዓይነት ስም ጻፉ? **መልሱ** ቀይሥር

በመቀጠልም ሁሉንም ሕፃናት እኩል በሚያሳትፍ መልኩ በንቃት ማዳመጥ፣ በደንብ ማሰብ፣መመራመርና የእንቆቅልሹን መልስ ለመመለስ ዝግጁ መሆን አንዳለባቸው ትዕዛዝ ይስጡ፡፡

- ከሰው አካል ክፍል ውስጥ ከአንገት በላይ እገኛለሁ ቅርፄም የጥያቄ ምልክት ይመስላል ጥሩና ጥሩ ያልሆኑ ድምፆችን እሰማለሁ ስሜ የሚጀምርበት ፊደል ጆ ነው እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** ጆሮ

- ተክሎችን ለመኮትኮት፣ ውሃ ለማጠጣት ፊደሎችን፣ ቃላትን፣ ቁጥሮችን ለመፃፍ ና የተለያዩ ሸካራና ለስላሳ ነገሮችን ለመለየት እንዲሁም ለጤናዬ ተስማሚ ምግቦችን በእኔ ተጠቅመው ይመገቡብኛል እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** እጅ

- ከተፈጥሮ ውስጥ እመደባለሁ ስር፣ግንድ፣ቅጠልና አበባ የሚባሉ ክፍሎች አሉኝ የስሜ ፊደል የሚጀምረው በተ ፊደል ነው ቆንጆ አድርገው ሲስሉኝ በጣም አምራለሁ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** ተክል

**መምህር!** እንዲህ እያሉ እርስዎ ከጠየቁ በኋላ በእርስዎ መሰረት እንዲጠይቁ እድሉን ለሕፃናት ይስጡ፡፡ በመቀጠልም በመለማመጃ ደብተሩ ላይ ያሉትን ፊደላት በመውሰድ ቃላት ምሥረታ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ በነጠብጣብ የተቀመጡ ሆሄያትን በማገጣጠም እንዲጽፉ ይደግፏቸው:: በአካባቢያቸው ያሉትን የአትክልት፣ የፍራፍሬ፣ የዛፎችን ስም ሆሄያትን በመጠቀም ስማቸውን እንዲጽፉ ይርዷቸው፡፡

ሕፃናቱ የሚያውቋቸውን ቃላት በመጠየቅና በመቀበል በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በየተራ እየወጡ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ በመደጋገምም ካነበቡት በኋላ በመልመጃ ደብተራቸው ላይ በአግባቡ እንዲጽፉ ይርዷቸው፡፡ **ለምሳሌ:** ቃላትን በ "ቀ" የሚጀምር (ቀበሌ) በ "ት" የሚጨርስ (ትምህርት)፤ በ "ተ" የሚጀምር (ተማሪ)፤ በ "ል" የሚጨርስ (ትል)፤ በጥያቄያዊ መልክ በማጫወት ቃላትን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም በጥቁር ሰሌዳ ላይ የተጻፉትን ቃላቶች እንዲገለብጡ ካደረጓቸዉ በኋላ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን ተግባር እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡

**ማስታወሻ:** ይህንን ተግባር በተገቢ እያዩ በተቀመጠለጥ ክፍለ ጊዜ ተግባሩን እየለዩ በአግባቡ እንዲለማመዱ ያርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የፊደል ገበታ፣ የአትክልት ስም፣ የፍራፍሬ ስም የያዘ የሥዕል ካርድ፣

**የምዘና ስልት:** ቃላት ምሥረታ፣ የቃል ጥያቄ፣ አሁን ምን ጨዋታ ተጫወትን፣ ስንት ቃላት መሰረታቹ፣ እነማን ናቸው፣ በእንቆቅልሹ ውስጥ በእጃችን ምን ነገሮችን እንደምናከናውን ተነገረን....እያሉ መጠየቅ ፣ የፁሁፍ ምዘናም መስጠት...

## ተግባር ስድስት: የመስክ ጉብኝት (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** አካባቢን ማወቅ፣ የተፈጥሮ ቁሶች፣ ሰው ሠራሽ ቁሶች፣ አቅጣጫ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በገለፃ፣ ጉብኝት ፣ በጠያቂና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናቱን በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያሉትን ነገሮች እንዲመለከቱ ከክፍል ውጪ ይዘዋቸው ይውጡ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ስለሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ቁሶች ጽንስ ሐሳቡን ይግለጹላቸው፡፡ በደንብ መረዳታቸውን ከአረጋገጡ በኋላ የመስክ ጉብኝቱን ዓላማ ያስረዷቸው፡፡ቀጥሎ በሁለት ቡድን ይክፈሏቸው ቡድን አንድ ሰው ሠራሽ፤ ቡድን ሁለት የተፈጥሮ ቁሶች ከዚያም በጉብኝታቸው ወቅት ቡድናቸውን የሚመለከተውን እየለዩ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል በግቢውም ውስጥ እየተዘዋወሩ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ቁሶች የሚባሉትን እየለዩ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ የለዩዋቸውንና መዘገቡዋቸውን በዘገባ መልክ ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው እርሶም እየተከታተሉ ማስተካከያ ይስጡ፡፡

**ለምሳሌ:** (የተፈጥሮ ቁሶች: እንስሳትና ተክሎች፤ ሰው ሠራሽ: ቤት፣ መኪና፣ ወንበር… ወዘተ)፡፡ በሕፃናቱ ደረጃ ማወቅ ያለባቸው እንስሳት የቤት ድመት፣ ውሻ፣ ዶሮ፣ ፍየል፣ በግ፣ ፈረስ…ሰው ሠራሽ መኪና፣ ብረት፣ እርሳስ…) በማለት እርሰዎ ከዘረዘሩ በኋላ ሕፃናትም በቅርብ አካባቢያቸው የሚያውቋቸውን እንዲናገሩ እድል በመስጠት መልሶቻቸውን ያዳምጧቸው፡፡ በመቀጠልም የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቁሶች በየትኛው የትምህርት ቤቱ አቅጣጫ እንደሚገኙ ይግለጹላቸው፡፡ አንደኛው ከአንደኛው ቁስ በየት በኩል እንደሚገኝ ሕፃናቱ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

(**ለምሳሌ:** በቀኝ፣ በግራ፣ ከፊት፣ ከጀርባ፣ ከጎን፣ ከላይ፣ ከታች፣ ከውስጥ)የመሳሰሉትን እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ ከራሳቸውና ከጓደኞቻቸው አቅጣጫ በመነሣት ያሉበትን አቀማመጥ እንዲያውቁ ይርዷቸውና መለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን ተግባር እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቤታችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ነገሮችን ዘርዝሩ?
2. ሰው ሠራሽ የሚባሉት ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. ከፊትህ የተቀመጠው ሕፃን ማን ይባላል?
4. ከጎንህ የተቀመጠችው ሕፃን ማን ትባላለች?

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቁሶችን የያዘ ሥዕል፤

**የምዘና ስልት:** በጉብኝቱ ወቅት በአግባቡ ተግባሩን እያከናወኑ መሆኑን በምልታ ያረጋግጡ፣ ያቃል እና የፁፍ ጥያቄዎችን ይጠይቁ ለምሳሌ ምን ነገሮችን ተመለከትክ/ሽ ፣ የተፈጥሮ የሆነው የትኞቹ ናቸው፣ ሰው ሰራሽ የሆኑት የትኞቹ ናቸው፣በመፀዳጃ ቤታችሁ አቅጣጫ የነበረው ተፈጥሮአዊ ነገር ምን ነበር…የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቁሶችን በስም ዘርዝራችሁ ፃፍ/ፊ….

# ስድስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት

### አጥጋቢ የመማር ብቃት ፡

- ✓ ከሌሎች ጋር ያላቸዉን የግንኙነት ክህሎታቸውን ያዳብራሉ።
- ✓ የሀገር ወዳድነት መዝሙሮችን ይዘምራሉ።
- ✓ የጤናማ አካባቢ መንፈስን ያዳብራሉ።
- ✓ በአካባቢያቸዉ ከተለያዩ ነገሮች ራሳቸዉን ይጠብቃሉ።
- ✓ ቀላል ቃላቶችን ማንበብና መፃፍ ይችላሉ።
- ✓ ትላልቅ ጡንቻዎቻቸዉን በመቆጣጠር ሚዛናቸዉን ይጠብቃሉ።
- ✓ ቀላል ስሌቶችን ያሰላሉ።
- ✓ የተለያዩ ሥዕሎችን ይስላሉ።

**ንዑስ ይዘቶች:** ሀገር ወዳድነት፣ ማንበብና መጻፍ፣ መደመርና መቀነስ፣ ራስን መጠበቅና መንከባከብ፣ ጥበባዊ ግንዛቤ

### ተግባር አንድ: መዝሙር (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ሀገር ወዳድነት፣ ጤናና አካላዊ መዳበር፣ መኖሪያ አካባቢን መጠበቅ፣ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናቱ የሚያውቁት በአካባቢያቸው የተለመደ ስለ ተክሎች የሚያወራ አንድ መዝሙር በጋራ እንዲመርጡ ያድርጓቸው። ቀጥሎ ከታች የቀረበውን መዝሙር እና ተግባር በተቀመጠለት ክፍለ ጊዜ ደጋግመው ያሰሩ።

**ተክሎችን መንከባከብ**

የተክል ክፍሎችን እንወቅ ሕፃናት፣
ሥር፣ግንድ፣ ቅጠልና አበባ በማለት፣
እንከባከብ ውሀ በማጠጣት፣
እንቁጠር የፍራፍሬ አይነት፣
አንድ ሁለት ሶስት አራት።
ሙዝእናብርቱካን፣ፓፓያእና ማንጎ፣
በሽታን ሲያርቁ እንሆናለን በጎ
ሀገሬ ኢትዮጲያ እኔ እወድሻለሁ፣
ተክሎችን በመትከል አለማሻለሁ

**መምህር:** ለሕፃናት ድጋፍ በማድረግ እንዴት ሐላፊነት ወስደው ዕፅዋትን እንደሚንከባከቡ ተራ በተራ ወጥተው እንዲለማመዱና እንዲሁም ስለ ዕፅዋት አካል ክፍሎች የሚደረገውን እንክብካቤ ጥቅም እንዲያውቁ ያድርጓቸው። በተጨማሪም በክፍል ውስጥ ለሕፃናቱ አንድ ችግኝ ከሥሩ

ነቅሎ በማምጣት የተክል ክፍሎቹን በተግባር መለየት እንዲለማመዱ ፣በመኖሪያ አካባቢያችን የሚገኙ ተክሎችን መንከባከብ የዜግነት ግዴታችን መሆኑን ለሕፃናቱ እንዲረዱ ያድርጓቸው፤ ሀገራዊ ስሜትን፤ ሀገር ወዳድነትን እንዲያዳብሩ ያለማምዷቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የተክል ክፍሎች የያዙ ሥዕሎች፣ ተክል፣የተለያዩ የፍራፍሬ አይነቶችን የያዘ የስዕል ካርድ እና የቁጥር ካርድ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ ሲዘምሩ ፣ተግባራትን ሲያከናውኑ በአግባቡ መከታተል የቃል ጥያቄ፣ በአከባቢያችሁ ምን አይነት ተክሎች አሉ፣ተክል ስንተክል ሀገራችን ምን ትሆናለች፣ ፈራፍሬዎችን መመገብ ምን ይተቀመናል…

## ተግባር ሁለት: የክፍል ውስጥ ጨዋታ (8 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ፍራፍሬ፣እህል፣ዘር፣ቁጥር፣አቅጣጫ፣ ገንዘብ፣ስሌት፣ጤና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናቱ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን መመገብ ለአእምሮቸውና ለአካላዊ እድገታቸው ወሳኝ እንደሆኑ ከራሳቸው አካላዊ አወቃቀር ጋር እያስተሳሰሩ ያስረዷቸው፡፡ ለሰው ልጅ ለምግብነት ሲያገለግሉም ለሰውነታችን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳሚሰጡ በምሳሌ ያብራሩላቸው፡፡ በመቀጠልም የእእምሮና እጅ ቅንጅታቸውን እንዲያዳብሩ ጹሁፍ እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡ በጥቁር ሰሌዳ ላይ የሚያውቋቸውን ፍራፍሬና የእህል ዘሮች እየወጡ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

ውድ መምህር! በቀጣዩ ክፍል ጊዜ ከቤታቸው የተለያዩ ችግኞች ወደ ክፍል እንዲያመጡ ይዘዟቸው፡፡ ያመጧቸውን የዕፅዋት ዘሮች በመቀበል በጠረጴዛው ላይ ለየብቻ ያስቀምጧቸው፡፡ ሕፃናቱን አንድ በአንድ በማስወጣት ዘሮቹንን እስከቻሉት ቁጥር ድረስ እንዲቆጥሩ ያድርጓቸው፡፡ ተመሳሳይ ዘሮቹን በማንሣትና በመጨመር የመቀነስና መደመር የሂሳብ ስሌትን እንዲለማመዱ ይርዷቸው፡፡ በተክሎቹ ዘሮች በመጠቀም ደጋግመው እንዲደምሩና እንዲቀንሱ ያሠሯቸው፡፡ ስማቸውንም እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

መምህር! በጥቁር ሰሌዳው ላይ ባለ አንድ አኃዝ ቁጥሮችን በመጻፍ የመደመርና የመቀነስ ምልክትን በመጠቀም መልመጃዎች እንዲሠሩ ይስጧቸው፡፡ ስሌቱን እንዲሠሩ ምሳሌ በመስጠት ያስረዷቸው፡፡ መሥራታቸውን በመዘዋወር ይከታተሏቸው፡፡ ለምሳሌ፣ አቶ አለሙ ሁለት ሴት ልጆች ሲኖሩት እድሜያቸው 5 እና 6ዓመት ነው፡፡ ቤታቸውም የሚገኘው ከትምህርት ቤታቸው በስተቀኝ አቅጣጫ ራቅ ብሎ ነው፡፡ ሁለቱም ልጆች ለእያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ብርቱካን በአሥራ አምስት ብር ቢገዛላቸው የሁለቱንም ልጆች ብርቱካን በአንድ እቃ ቢያደርጉት ስንት ብርቱካን ይሆንላቸዋል? እንዲህ ያሉ ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ በመስጠት ስለመደመር፣ ብር ኖቶች፣ በሽታ ተከላካይ የሚባሉትንና አቅጣጫ መለያዎችን አያይዘው ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም መቀነስን ለማስተማር አምስት ዳክዬዎች ጨዋታ ሔዱ የሚለውን መዝሙር የእጅ ጣታቸውን በመጠቀም ቆመው እንዲዘምሩ ያድረጉ፡

**መዝሙር:**

አምስት ዳክዬዎች ጨዋታ ሔዱ፣
በአትክልቱ ውስጥ ወደ ሩቅ ስፍራ፣
እናትየዋ ዳክየ ቋቋ አለች፣
አንዷ ዳክየ ወደ እሷ ሮጠች።
አራት ዳክየወች ጨዋታ ሔዱ፣
በአትክልቱ ውስጥ ወደ ሩቅ ስፍራ፣
እናትየዋ ዳክየ ቋቋ አለች፣
አንዷ ዳክየ ወደ እሷ ሮጠች።

**መምህር!** እንዲህ እንዲህ እያለ መዝሙሩ አንድ ዳክዬ እስኪቀር ድረስ ይቀጥላል። በዚህ መሰረት መቀነስን ማስተማር ይችላሉ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ እህል ዘሮች፤ ቁጥሮችን የያዙ የሥዕል ካርዶች፣ የተክል ክፍሎችን የያዘ ሥዕል፣ የዳክዬ ሥዕል

**የምዘና ስልት:** ባለ አንድ አኃዝ ቁጥሮችን በመጻፍ የመደመርና የመቀነስ ምልክትን በመጠቀም መልመጃዎች እንዲሠሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣ መዝሙሩን ሲዘምሩ በደንብ ማየትና ማዳመጥ፣ጥቁር ሰሌዳ ላይ ባለ አንድ አሀዝ ቁጥሮችን በመፃፍ ሕፃናት እየወጡ ተራ በተራ እንዲያሰሉና እንዲፅፉ ያድርጉ።

## ተግባር ሦስት: የግል ሥራ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የተክሎች የአካል ክፍሎች፣ ቃላት፣ ንባብ፣ ቴምር፣ ማሽላ፣ ጤፍ፣ ባቄላ፣አተር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር! ለሕፃናቱ የተክል ክፍሎችን ቃላት የያዙ ካርዶችን ማዘጋጀት፤ አንድ የዕፅዋት ሥዕል በጠንካራ ወረቀት ላይ በመሣል ቃላቶቹን ከሥዕሉ ክፍሎች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው። (ለምሳሌ: ግንድ፣ ቅጠል፣ ሥር፣ አበባ፣ ዘር ባቄላ፣ አተር፣ማሽላ፣ ቴምር፣ ጤፍና የመሳሰሉትን ቃላት በካርዶቹ ላይ ይጻፉላቸው) በመቀጠል የቃላት ካርዶቹን ለሕፃናቱ በየተራ በመስጠት ከቁስ/ከሥዕል ጋር እያዛመዱ እንዲለማመዱ ያድርጓቸው። በመጨረሻም የተክሎቹን ክፍሎችና እህል ዓይነቶችን ስም በቃላት እንዲያነቡና እንዲጽፉ ያድርጓቸው። ሕፃናቱን በየተራ በማስወጣት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማንበብን እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው። በመጨረሻም እንዲጽፉ ጊዜ ይስጧቸው።

ተጨማሪ ተግባር የተክሎቹን የአካል ክፍሎች መጀመሪያ ፊደል በመጻፍ ሌላውን (ጎደለውን) እንዲሞሉ ያድርጓቸው። (ለምሳሌ: ቅ <u>መልሱ</u> ቅጠል፤ ግ <u>መልስ</u> ግንድ)። በመደጋገም እንዲያነቡና እንዲጽፉም ያበረታቷቸው።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የተክል ክፍል የያዙ የሥዕል ካርዶች፣ የተክል ክፍሎችን የያዘ ሥዕል

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ፣ በ ስ የሚጀምር የተክል ክፍል ምንድን ነው፣ የተክሎችን ነገረኝ/ኝ.... የፁሁፍ መጠይቅ የተክል ክፍሎችና ፊደላትን/ቃላትን እንዲያዛምዱ ማድረግ ምልከታ፣

## ተግባር አራት: በሥራ መማር (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የግብረገብ እሴት፣ የብር ኖት፣ ገዢ ፣ሻጭ፣ፍራፍሬ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና:** መምህር! ወደ ዕለቱ ክፍለ ጊዜ ከመግባትዎ በፊት ቀደም ባሉት ክፍለ ጊዜዎች የተማሯቸውን የፍራፍሬዎች ስም በማስታወስ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። የተናገሯቸውን የፍራፍሬ ስሞች እንዲጽፉ ያድርጓቸው። (ለምሳሌ: ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ማንጎ፣ ፖም፣ አናናስ፣ አቮካዶ፣ ወይን፣ እንጆሪ፣ ፓፓያ ወ.ዘ.ተ)

በመቀጠል የመስሎ ጨዋታ ሁለት ሕፃናትን ይምረጡ፤ የጨዋታው ይዘት ሻጪና ገዥ መሆኑን ለሕፃናቱ ያስረዷቸው። ለጨዋታው የሚሆን የብር ኖቶች ያዘጋጁ። የሱቅ ማዕዘኑን ለጨዋታው ይምረጡ።ሁሉምህፃናትን የገዢና ሻጭ ቦታን እያተቀያየሩ እንዲሰሩ ያድርጉ

### ሻጪና ገዥ

**ገዥ:** እባክህ/ሽ የአንድ ሙዝ ዋጋ ስንት ነው?

**ሻጪ:** እሺ ዋጋው አስር ብር ነው።

**ገዥ:** አቡካዶስ ዋጋው ስንት ነው?

**ሻጪ:** አንዱ አምስት ብር ነው ።

**ገዥ:** ይቅርታ ወደሜ/እህቴ የአንድ ማንጎ ዋጋ ንገረኝና/ሪኝና ሙዙንም፣ አቮካዶውንም፣ ማንጎውንም ሶስቱንም ስጠኝ/ስጭኝ?

**ሻጭ:** እንዴ ችግር የለውም ዋጋው አምስት ብር ነው።

**ገዥ:** የሶስቱም ፍራፍሬዎች ድምር ስንት ነው?

**ሻጭ:** አስር ብር፣ አምሰት ብርና አምስት ብር በድምሩ ሀያ ብር ነው።

**ገዥ:** ይኸው ሂሳቡ ልክ ነው?

**ሻጭ:** አዎ ልክ ነው ስለገዛኸን/ሽኝ አመሰግናለሁ።

**ገዢ:** እኔም በአግባቡ ስላስተናገድከኝ አመሰግናለሁ

**መምህር!** በግብይቱ ውስጥ የተጠቀሙትን የብር ኖቶች ዓይነት እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡ ፍራፍሬዎችን እና የብር ኖቶችን ስለው እንዲያሳዩ ያበረታቱ፣የብር መጠንን እንዲለዩ ዕድሉን ይስጧቸው፣ መልካም የግብረገብ እሴቶችን በማንኛውም ጊዜ መተግበር እንዳለባቸው ያስረዷቸው።

**መወያያ ጥያቄዎች**

ገዥ ስንት ሙዝ ገዛ?

የማንጎ ዋጋ ስንት ብር ነበር?

ገዥ በጠቅላላ ስንት ብር ከፈለ?

ገዥ ስንት አቦካዶ ገዛ?

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የፍራፍሬ ሞዴሎች፣ የብር ኖቶች፣ ሚዛን

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ፣ በመስሎ ጨዋታው ምን ተግባር ተከናወና፣ የግብረገብ እሴት የሆኑት የትህትና ቃላት ይኞቹ ናቸው፣ እናንተስ ሱቅ ስትሁዱ እንዴት ትገበያያላቹ...ምልከታ

**ማስታወሻ:** ይህን ተግባር ከበቃ+ ጋር ተያያዥ እንዲሆን በማድረግ በተቀመጠለት ክፍለ ጊዜ ከፋፍለው ያሰሩ

## ተግባር አምስት: የክፍል ውጭ ጨዋታ (7 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የተክል ክፍል፣ፍራፍሬ ፣ እንቅስቃሴ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ክፍለ ጊዜው የውጭ ጨዋታ እንደሆነ ለሕፃናቱ በመንገር ከክፍል ውጪ ይዟዋቸው ይውጡ፡፡ በመቀጠልም ወደ ጨዋታው ከመግባታቸው በፊት መጠነኛ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ይፍቀዱላቸው፡፡ ለማነቃቂያ “ማንበብ እወዳለሁ” የሚለውን መዝሙር ያዘምሯቸው ፡፡ ከዚያም ያዘጋጁትን የፓፓያ፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ አናናስ ሥዕሎችን የያዙ ካርዶችን በማሳየት እንደ ሕፃናቱ ብዛት በአራት ረድፍ እንዲሰለፉ ያድርጓቸው፤ በመቀጠል የሰውነት ክፍላቸውን አናናስን (እራስ/ጭንቅላታቸው)፣ ማንጎን በጉልበታቸው፣ ሙዝን በወገባቸው፣ ፓፓያን በትከሻቸው እንደሚወከል ይግለጹላቸው፤ አናናስ አናናስ ሲባል ራሳቸውን፣ ማንጎ ሲባል ጉልበታቸውን፣ ሙዝ ሲባል ወገባቸውን፣ ፓፓያ ሲባል ትካሻቸውን እየነኩ አብረው ከእርስዎ ጋር እንዲጠሩ ያድርጓቸው፤ ምን እንበላ በማለት ይጠይቋቸው ከዚያም የመረጡትን በፍራፍሬ የተሰየመውን አካላቸውን በመንካት በድርጊት እያሳዩ እንዲበሉ ያድርጓቸው፡፡ የተበላውን ፍራፍሬ ድምፅ ሳያወጡ ስሙን ብቻ ይጥሩ ጨዋታውን ከጨረሱ በኂላ ወደ ክፍላቸው በመግባት የሚወዱትን የፍርፍሬ አይነት በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ በመሳል እና የሚወክለውን የቀለም አይነት በመቀባት ስንት ፍራፍሬዎች እንደሳሉ የአካል ክፍሎች ምን ምን እንደሚባሉ ለጤናችን ምን ጥቅም እንደሚሰጡ ፅፈው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡በመጨረሻም በጨዋታው ውስጥ የነበሩትን ፍራፍሬዎች እንዲስሉ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የፍራፍሬ ሞዴሎች /የሥዕል ካርዶች/፣ የተለያዩ ቀለማት፣ እርሳስ፣ ...ወዘተ

**የምዘና ስልት:** በምልከታ፣ በተግባር ሲሰሩ መመዘን፣ በፍራፍሬዎች የተሰየመውን የአካል ክፍል የስምምነት መሆኑንና በትክክል ትዕዛዙን መጠበቃቸውን መመዘን፣የቃል ጥያቄ: ምን አይነት ጨዋታ ተጫወትሽ/ትክ፣ምን ሳልክ/ሽ....

# የአውድ ማጠቃለያ ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም________________________________ጾታ_______እድሜ_______ደረጃ_______

**መግለጫ:** ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "✓" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ።

| ተ.ቁ | የመማር ብቃቶች | የምልከታ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | ጥሩ | በ.ጥሩ | እ.በ.ጥሩ |
| 1 | በውይይት በንቃት በመሳተፍ ተገቢ ምላሽ ሰጥተዋል? | | | | |
| 2 | የሰዎችን ስሜት በመገንዘብ ውጤታማ ማኅበራዊ ተግባቦት ፈጥረዋል? | | | | |
| 3 | የመኖሪያ አካባቢያቸውን በተገቢው መንገድ ጠብቀዋል? | | | | |
| 4 | በመቆምና በመንቀሳቀስ የተለያዩ ተግባራትን አከናውነዋል? | | | | |
| 5 | ቁጥሮችን በማወዳደር በቅደም ተከተል አስቀምጠዋል? | | | | |
| 6 | የድግግሞሽ/ቅጥ/ሥርዓት ጥለትን (Pattern) በመገንዘብ፤ቅደም ተከተሉን ይገልጻሉ? | | | | |
| 7 | የተለያዩ ጥበባዊ እሴቶችን ይተገብራሉ? | | | | |
| 8 | ማኅበራዊና ስሜታዊ ክህሎትን አዳብረዋል? | | | | |
| 9 | የግብረገብ እሴቶችን በተግባር አሳይተዋል? | | | | |
| 10 | አናባቢ እና ተነባቢዎችን ማንበብና መፃፍ ችለዋል? | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻም፦________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

# አውድ ሁለት: ሠላም

## አጠቃላይ አውዱ የተቀመጠው ሳምንትና ሰዓት 5 ሳምንት / 75 ሰዓት

## 3.1. መግቢያ

በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚገኙ ሕፃናት ሰላም የሚለው የመማር ዐውድ ሕፃናት የሰላምን ምንነት መሠረታዊነት፣ አስፈላጊነት እና አብሮ ለመኖር ያለውን አስተዋጽኦ በሰፊው እንዲማሩ እና ሰላምን የመኖር ገጽታዎችን እንዲለማመዱ ይረዳቸዋል፡፡ ሰላም ከጓደኛ ጋር አብሮ ለመኖር፣ ለመረዳዳት፣ በጋራ ለመሥራት፣ ፍቅር እንዲኖር ለማድረግ እና ደስተኛ ለመሆን ያለውን ከፍተኛ ሚና በተለያዩ ስልቶች ለመለማመድ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ ዐውድ ማኅበረሰቡ ማኅበራዊ መስተጋብሮችን የሚያከናውነው ሰላም በመኖሩ መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡ በተጨማሪም ሕፃናት የሰላም መገለጫ ተግባራትን እንዲያከናውኑ እና እንዲለማመዱ ሰፊ ዕድል ይሰጣቸዋል:: በሰላም እና ሰላም በሌለበት ሁኔታ ያለውን ልዩነት በተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶች ይማራሉ፡፡ የሰላም መገለጫ ቃላቶችንና ፅንሰ ሐሳቦች ይረዳሉ፡፡

ሕፃናት በዚህ ዐውድ ሰላም ሥራ ሠርቶ ለመብላት፣ ትምህርት ለመማር፣ ልጆችን ወልዶ ለማሳደግ እና መሰል የሕይወት ሂደታዊ ተግባራት መሠረት መሆኑን ያውቃሉ፡፡ በተጨማሪም ስለራሳቸው እንዲያውቁ፤ ስሜታቸውን ከሚረብሹ ተግባራት እንዲቆጠቡ፤ ሰላም እንዴት መፍጠር እንደሚችሉ ግንዛቤን ያዳብራሉ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ዐውድ ለሕፃናት የሚመጥኑ ከሰላም ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር ሕፃናት በዕድሜያቸው ሊያጎለብቱ የሚገባቸውን አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊ፣ አእምሯዊ እና ማኅበራዊ ብቃቶችን ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም አጥጋቢ የመማር ብቃቶችና ዝርዝር የአተገባበር ስልቶች ቀርበዋል፡፡

## የሚጠበቁ ውጤቶች

### ሕፃናት ይህን አውድ ከተማሩ በኋላ:

- ✓ ማኅበራዊ ክህሎት ይኖራቸዋል፤
- ✓ የሰላም መገለጫ ባህሪያቶችን ያዳብራሉ፤
- ✓ ሌሎችን የመዉደድ ስሜታቸዉን ያዳብራሉ፤
- ✓ ቀላል የመደመርና የመቀነስ ስሌቶችን ይሰራሉ፤
- ✓ የሀገር ወዳድነት ስሜትን ያዳብራሉ፤
- ✓ በራስ በመተማመን ስሜት መግባባት ይችላሉ፤
- ✓ በዕለት ተዕለት ተግባራቸዉ የደህንነት እና የንጽሕና አጠባበቅ መርሆዎችን ይተገብራሉ፤
- ✓ ጊዜን መሰረት በማድረግ የዕለትተዕለት ተግባራቸዉን ያቅዳሉ፤
- ✓ ከመማር ይዘቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለያዩ ሥነ ጥበባዊ ተግባራትን በመስራት ይዝናናሉ፤

### አበይት ይዘቶች

ሠላም በሚለው የመማር ዐውድ ውስጥ የሚከተሉት የትምህርት ይዘቶች ተካተዋል፡፡

- ራስን ማስተዋወቅ፣
- ራስን ማወቅ፣
- አካል ክፍሎች፣
- ጤና፣
- ቁጥሮችን መቁጠር፣
- ጥበባዊ ግንዛቤ
- ራስን መቆጣጠር ፣
- ድምፅን መለየት ፣
- ስርአተ ምግብ ፣
- የቅርብ አካባቢ ፣
- ቁጥሮችን መፃፍ፣
- የፈጠራ ስራ
- ራስን መቻል ፣
- የቃላት ክምችት ፣
- የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር ፣
- ቁጥሮችን ማወዳደርና መደርደር ፣
- ባህላዊ ቅርሶች
- ማኅበራዊ ግንዛቤ ፣
- ራስን መግለጽ ፣
- የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር ፣
- ቅጥ/ሥርዓተ ጥለት/ድግግሞሽ
- ጥበባዊ እሴቶች
- የግብረ ገብ እሴቶች ፣
- ተፈጥሯዊ እና ሰውሠራሽ አካባቢ
- የቦታ ግንዛቤ፣
- የፊደላት ድምፅ ግንዛቤ ፣
- መለየትና መመደብ ፣
- ማገናኘት፣ ማያያዝና ተግባራዊነት

# አንደኛ ሳምንት

**ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ: 30 ክፍለ ጊዜ /15 ሰዓት**

**አጥጋቢ የመማር ብቃቶች**

- ✓ ልምዳቸዉን ያካፍላሉ፤
- ✓ እያንዳንዳቸው የተለያየ ዓይነት እምነት ወይም ሐሳብ ሊኖራቸው እንደሚችል ይረዳሉ፤
- ✓ የሰዉነት ክፍሎቻቸዉን በመቆጣጠር ተግባራትን ይሰራሉ፤
- ✓ የግል ንጽሕናቸውን ይጠብቃሉ፤
- ✓ ሰላምን የሚገልጹ ሥዕሎችን በመሣል ይቀባሉ፤
- ✓ ቁጥሮችን በመጠቀም የፈለጉትን ነገር መግለፅ ይችላሉ፤
- ✓ ባህላዊ ዘፈኖችን በማስመሰል ይዘፍናሉ፤

**ንዑስ ይዘቶች :** ራስን ማስተዋወቅ፣ ራስን ማወቅ፣አካል ክፍሎች፣ ጤና፣ ቁጥሮችን መቁጠር፣ ጥበባዊ ግንዛቤ

## ተግባር አንድ: የክፍል ዉጭ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጥበባዊ ግንዛቤ፣ ቁጥር መቁጠር፣ የአካል ክፍሎች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** ጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ይህ የሳምንቱ የመጀመሪያዉ ቀን እንደመሆኑ ህፃናቶች ቅዳሜና እሁድ ምን ምን ተግባራቶችን እንዳከናወኑ ለጓደኞቻቸዉ እንዲያወሩ የተወሰነ ደቂቃ

ይፍቀዱላቸዉ፡፡ ከዚህ አውድ በፊት ስለእፅዋቶች እንደተማሩ በማስታወስ የተረዱትን እንዲናገሩ ይጠይቋቸዉ፤እርስዎም ተጨማሪ ሀሳብ በመጨመር ከክፍል ዉጭ ይዘዋቸዉ ይዉጡ፡፡ ከዚያም በትላልቅ ቡድን በማደራጀት በየቡድናቸዉ በአካባቢያቸዉ የተለመዱ ባህላዊ ዘፈኖችን የምት መሳሪያዎችን ተጠቅመዉ (ከበሮ፣ዋሽንት...) በመዝፈን ባህላዊ ጭፈራዎቻቸዉን እንዲጨፍሩ ያድርጓቸዉ፤እርስዎም በየቡድኑ በመዘዋወር አብረዋቸዉ ይጨፍሩ፡፡ ይህንን የውጭ ጨዋታ በተቀመጠለት ክፍለ ጊዜ አቅደው ይስሩ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** አካባቢያዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የተቀረፀ፣ሺፓስ፣ቴፕ ሪከርደር፣ ስልክ....

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(በጨዋታዉ ሂደት የህፃናቶችን የጨዋታ ንቃት መመዘን)፣ የቃል ጥያቄ (ስንት ዘፈኖችን ዘፈናችሁ? በጨዋታዉ ምን ተሰማችሁ? ለጭፈራዉ የተጠቀማችሁባቸዉ የአካል ክፍሎች ምንምን ናቸዉ? የትኛዉን ዘፈን በይበልጥ ወደዳችሁት?)

## ተግባር ሁለት፡ ዉይይት (2 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ህብረተሰብ፣ ራስን ማወቅ፣ጥበባዊ ግንዛቤ፣እምነት፣አኗኗር፣የስራ መስክ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በዉይይት፣ በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ

**የመምህር ሚና:** መምህር ህፃናቶችን ለማነቃቃት ያስችል ዘንድ ቀድመው ከተለማመዱት መዝሙር መርጠው እንዲዘምሩ እድል ይስጧቸዉ፡፡

ህፃናቶችን በክፍል ዉስጥ በትናንሽ ቡድን (4 6 ቁጥር ባልበለጠ) እንዲቀመጡ በማድረግ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ጎረቤታሞችን የተለያየ አይነት እምነት(ሀይማኖት)፣አኗኗር፣አድሜ፣የስራ መስክ እና ሌሎች ልዩነቶችን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ በትልቅ ወረቀት በማዘጋጀት የሚታይ ቦታ ላይ ይስቀሉላቸዉ፡፡ ከዚያም ህፃናት ከስዕሉ የተረዱትን እንዲናገሩ እድል ከሰጧቸው በኋላ ተጨማሪ ሀሳብ በመጨመር ወደ ሚቀጥለዉ ዉይይት ያስገቧቸዉ። በመቀጠልም በየቡድናቸዉ ህፃናቶች በአካባቢያቸዉ የሚኖሩ ህብረተሰቦች የተለያየ አይነት እምነት፣አኗኗር፣የስራ መስክ እና ሌሎችም አይነት ልዩነቶች እንዳሏቸዉ በማስተዋል ልይነቶቻቸዉን እንዲወያዩባቸዉ በማድረግ በመዘዋወር ድጋፍ ያድርጉላቸዉ፡፡ በመጨረሻም በየቡድናቸው የተወያዩበትን በየተራ እንዲያቀርቡ ማድረግ እርሶም ሰዎች መሰረታዊ ልዩነቶች እንዳሉን በማስገንዘብ ልዩነቶቻችንን በመረዳትና በማክበር አብሮ የመኖር ባህል (ልምዶቻችንን) ማጎልበት እንዳለብን ያስገንዝቧቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የህብረተሰብ መሰረታዊ ልዩነቶችን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ (የምን ሀይማኖት ተከታይ ነህ/ሽ?፣እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ የምን የምን አይነት ሀይማኖት ተከታዮች አሉ?በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ማህበረሰብ በምን አይነት የስራ መስክ የተሰማሩ ናቸዉ? ከምትመለከቷቸዉ ስዕሎች ዉስጥ እናንተ አካባቢ ከሚተገበሩት ጋር ስንቶቹ ይመሳሰላሉ? የትኞቹ ናቸዉ? በዉይይት ጊዜ ስርአት ጠብቆ የመወያየት ስልትን በምልከታ መገምገም

## ተግባር ሶስት፡ መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ራስን ማስተዋወቅ፣ ራስን ማወቅ፣ የሰውነት አካል ክፍሎች፣ ጤና፣ጥበባዊ ግንዛቤ፣ ቁጥር መቁጠር

**የማስተማር ዘዴ ፡** መዝሙር

**የመምህር ሚና፡** መምህር ሕፃናት ከዚህ ቀጥለው የቀረቡ ሦስት መዝሙሮችን እየዘመሩ እንዲማሩ እርስዎ ከክፍለ ጊዜው በፊት አስቀድሞ ጭብጡን፣ ዜማውን እና ግጥሙን ይረዱት:: በመቀጠልም ሕፃናት እንዲዘምሩ ያለማምዷቸዉ፤በመጨረሻም የመለማመጃ ደብተራቸዉ ገፅ ላይ ያለዉን መልመጃ ያሰሯቸዉ::

### መዝሙር አንድ

ወላጆቼ እኔን በጣም ይወዱኛል
ወላጆቼ እኔን በጣም ይወዱኛል ፣
ሁልጊዜ በፍቅር ይንከባከቡኛል::
ትህትና እንዲኖረኝ እውነት እንድናገር ፣
ጥሩ ልጅ እንድሆን ለፍትሕ የምኖር ፣
ሁልጊዜ ይመክሩኛል እንድኖር ለሀገር ::
ትምህርት ቤት ሄጄ እንድማር ትምህርት ፣
ቦርሳ እና ደብተሬን አስይዘው በጧት ፣
ስመው ይልኩኛል በስስት አንጀት
ከጓደኛች ስነጫዋወት
በመከባበር ነው ተራ እየጠበቅን
እኔ ልቆይ እና አንተ ቅደም እያልን ፣
እናድጋለን እኛ ብርቅየ ልጆች ነን ፣
ኢትዮጲያዊ የሚባል ውብ ሀገርም አለን ::

**ቁልፍ ቃላት ፡** ሰላም፣ ቀለማት፣ስሜት

**የማስተማር ዘዴ ፡** በመዝሙር፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር በመዝሙር አዘማመር ቅደም ተከተል እንዲዘምሩ በማድረግ ሲጨርሱ በመለማመጃ ደብተራቸዉ ገፅ ላይ ያለዉን መልመጃ ያሰሯቸዉ::

### መዝሙር ሁለት

**ሰላምን እንኑራት**
አረንጓዴ ቀለም ይሆናል መለምለም ፣
ቢጫ የተስፋ ነው አርቆ የሚያልም ::
ቀይ የመሥዋዕት ሰማያዊ የዕውቀት ፣

ነጭ ነው የሰላም ወይን ጠጅ የምቾት ፡፡
አበባ የፍቅር ወፏ የሰላም ናት፣
ሰላም ሰላም እያልኩ በቃላት ስጠራት፣
መዝሙሮችዋን ጽፌ በጆሮ ስሰማት ፣
ታስደንሰኛለች ሁልጊዜ ደስታ ናት ፣
እናንተም እንደ እኔ አዳምጡና ኑሯት ፡

**ቁልፍ ቃላት ፡** ሰላምታ፣ትህትና፣ስሜት፣ንጽህና፣ሀገር፣ሰላም፣ ፍቅር

**የማስተማር ዘዴ ፡** በመዝሙር፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር በመዝሙር አዘማመር ቅደም ተከተል እንዲዘምሩ በማድረግ ሲጨርሱ በመለማመጃ ደብተራቸዉ ገፅ ላይ ያለዉን መልመጃ /በደብተር የጂኦሜትሪ ቀርፆችን ያሰሯቸዉ፡፡

## መዝሙር ሶስት

### ትምህርት ቤቴን እወዳታለሁ

ትምህርት ቤቴን እኔ እወዳታለሁ፣
በአምስቱን ቀናት እሄድባታለሁ፡፡
ሰላምታንም ስሰጥ እንዲሁም ስቀበል፣
ከአንገት ጎንበስ ነው ከወገብም ዘንበል፡፡
በእጆቼ ሰላም ስል ከፊቴ ፈገግታ፣
ሊኖረኝ ይገባል ሁልጊዜም ደስታ፡፡
ጥርሶቼን ስቦርሽ ፊት ቁርሴን ሳልበላ፣
እጆቼን ታጥቤ ምግቤንም ስበላ፣
አፌን ስታጠበው ከምግብ በኋላ፣
ይኖረኛል ደስታ ንጹሕ እንቡጥ ገላ፡፡
ኢትዮጵያዊነቴን ባህሌን እንዳከብር፣
ታስተምረኛለች ስለ ሰላም ፍቅር፣
ተሳስቦ ተዛዝኖ ስለ አብሮ መኖር፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ቀለማትንና ቅርፃቅርፆችን የያዙ የሥዕል ካርዶች፣ የመለማመጃ ደብተር

**የምዘና ስልት:** የመዝሙሩን ቃላት አጠቃቀማቸውን መገምገም፣ የቃል ጥያቄ መጠየቅ (በመዝሙሩ ውስጥ ስንት ቀለማት አሉ? ስማቸውን ዘርዝሩ፣ ስንት መዝሙሮችን ዘመራችሁ፤ በመለማመጃ ደብተራችሁ ገጽ ላይ ስንት የክብ፣ አራት መዓዘን፣ ሦስት ቅርፆች አሉ፤ እና ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው)፣ ለመዝሙሩ ያላቸዉን ንቃት በምልከታ መመዘን፣ ሐሳብ የማደራጀት አቅማቸውን መመዘን እንዲሁም የፁሁፍ መጠይቆችን ይስጡ...

## ተግባር አራት፡ በስራ መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፤** ራስን ማወቅ፣ጤና ፣የሰውነት አካል ክፍሎች፣ልባዊ ፈገግታ፣ ግብረገብ የስራ አይነት

**የማስተማር ዘዴ:** በስራ ፣ በገለፃ በጥያቄና መልስ ሰርቶ በማሰራት

**የመምህር ሚና :**

መምህር ሕፃናትን የመምህር እና የሐኪም ሥራ ምን እንደሆነ ይጠይቋቸው ከዚያም እርስዎ ተጨማሪ ሐሳብ በመስጠት እውቀታቸውን ያዳብሩ፡፡ ከዚያም “መምህር እና ተማሪ፣ ሐኪም እና ታካሚ በሚል የጨዋታ ርዕስ መስሎ ጨዋታ እንደሚጫወቱ ይንገሯቸው፡፡ ቀጥሎ የቀረበውን የመስሎ ጨዋታ እንደ ሕፃናቱ ብዛት በትናንሽ ቡድን እንዲከፋፈሉ ካደረገ በኋላ ጨዋታዎቹን በዕጣ ያከፋፍሏቸው ከተቻለ ሕፃናቱ የሐኪምና የመምህር አልባሳት ለብሰው እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡

**የመምህር እና ተማሪ:** የተወሰኑ ሕፃናት ተማሪዎች አንድ ሕፃን ደግሞ መምህር በመሆን የዕለቱ የውሎ የትምህርት ይዘትንና ራስን ማስተዋወቅ ይሆናል፡፡

መምህርቷ ወደ ክፍል ስትገባ: “እንደምን አደራችሁ ልጆችዬ” በማለት ሰላምታ ትሰጣለች፤ሕፃናትም ከመቀመጫቸው በመነሣት: “እንደምን አደሩ መምህርት” ይላሉ፡፡

**መምህርት :** “አመሰግናለሁ ተቀመጡ” ትላለች፤

**ሕፃናት :** “እናመሰግናለን” ብለው ይቀመጣሉ፡፡

**መምህርት** “ልጆችዬ ዛሬ የምንማረው ከሰዎች ጋር ሰላምታን እንዴት እንደምንለዋወጥ ነው፡፡ ጎበዞች ልጆችዬ እስኪ ከእኔ ጋር ማነው ሰላምታ የሚለዋወጠው? በማለት ትጠይቃለች፡፡

አንድ ሕፃን ከመቀመጫው ይነሳ እና ከአስተማሪዋ ጋር ሰላምታ ይለዋወጣል፤ የሰላምታው ሂደት መምህርቷ እና ተማሪው ከወገባቸው ጎንበስ ብለው የቀኝ እጃቸውን ክንድ በግራ እጃቸው ይይዙ እና በቀኝ እጃቸው ዓይን ለዓይን በመተያየት በልባዊ ፈገግታ ሰላምታ ይቀያየራሉ፤ በሰላምታ ልውውጥ ሂደት ሕፃናት ጥንድ ጥንድ በመሆን የፊት ፈገግታን፣ የእጅ አጨባበጥ ሥርዓትን፣ ከወገብ ጎንበስ ማለትን፣ የዓይን ለዓይን መተያየትን እንዲለማመዱ እና ለሰላምታ አገልግሎት የሚያገለግሉ የሰውነት ክፍሎችን እንዲያስተውሉ ያድርጓቸው፡፡

**ሐኪም እና ታካሚ:** አንድ ሕፃን ሐኪም፣ ሌላ ሕፃን ታካሚ ሌላ ሕፃን ደግሞ የታካሚ ወላጅ/አሳዳጊ በመሆን ገጸ ባሕርይ ይኑራቸው፤ ሕፃኑ/ኗ አሞት/አሟት ወደ ጤና ተቋም ይሄዳል/ትሄዳለች፤ ሕፃኑ/ኗ ወላጅ/አሳዳጊ ጋር ወደ ሐኪሙ ይገባል፡፡

በመቀጠል ሐኪሙ ከመቀመጫው ተነስተው ታካሚ ሕፃኑን/ኗን እና ወላጅ/አሳዳጊዉን ከወገቡ ጎንበስ ብሎ በፈገግታ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ እንዲቀመጡ ወንበር ሰጥቶ የሕፃኑን/ኗ ስም ይጠይቃል፤ ሕፃኑም/ኗም ስሙን ይነግረዋል፡፡

**ሐኪሙ:** “ምንህን/ሽን አሞህ/ሽ ነው የመጣኸው/ሽዉ?” ብሎ ይጠይቀዋል፤

**ህፃኑ/ኗ :** “ምግብ ስበላ ያስታውከኛል፣ ሆዴን ያመኛል፡፡” በማለት ይናገራል/ትናገራለች፤

በመቀጠል ሐኪሙም፡ “ምግብ ከመበላትህ/ሽ በፊት እጅህን/ሽን በውሃ እና በሳሙና ትታጠባለህ/ቢያለሽ? በማለት ይጠይቃል፡፡

ህፃኑ/ኗ ፡ “የምታጠበው በውሃ ብቻ ነው፡፡” ይላል/ትላለች፡፡

ከዚያም ሐኪሙ ምርመራ ያደርግለት/ላት እና ስሙን/ሟን በመጥራት “ምግብ ከመብላትህ/ትሽ በፊት እና ከሽንት ቤት መልስ እጅህን/ሽን በውሃና በሳሙና በደንብ መታጠብ አለብህ/ሽ:: ሆድህን/ሽን ያመመህ/ሽ ይህን ባለማድረግህ/ሽ ነው፤ ምግብ በደንብ መብላት አለብህ/ሽ፣ በቂ ውሃ ጠጣ/ጭ፤ የግል ንጽሕናህን በሚገባ ጠብቅ/ቂ፡፡ ይህን ካደረግክ/ሽ ጤነኛ እና ደስተኛ ልጅ ትሆናለህ/ኛለሽ፡፡” በማለት ይመክራል፡፡

ሕፃኑ/ኗ ከእናቱ /ከአሳዳጊ ጋር አመስግነው ወደቤታቸው ይሄዳሉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ለሕፃናት የሚመጥን የወላጆች/አሳዳጊዎች አልባሳት፣ ለሕክምና ምርመራ አስመስሎ ለመሥራት አገልግሎት የሚውል አካባቢያዊ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** *የቃል ጥያቄ ምን አይነት ሞያዎች ነበሩ፣የጥኛውን ወደዳችሁ፣ለምን፣ህፃኑ የታመመዉ ምን ሆኖ ነዉ? ሀኪሙ/ሀኪሟ ህፃኑን/ኗን ምን አይነት ምክር መከረዉ? እናንተ ከሰዎች ጋር ሰላምታ ስትለዋወጡ እንዴት ነዉ? በቃል ግለፁት?... ምልከታ፡ ሀላፊነት የመወጣት አስተዉሎታቸዉን መመዘን...*

## ተግባር አምስት: ተረት (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** *ሰው ማክበር፣ መታዘዝ፣ አለመዋሸት፣ መረዳዳት፣ራስን ማወቅ፣ ቁጥር መቁጠር እንስሳት ፣ተራን መጠበቅ*

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት ፣በትረካ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** *መምህር ለሕፃናት አሁን የተረት ጊዜ መሆኑን በመንግር ገተረቱን ያውሩላቸው*

### ጎረቤታሞቹ የዱር እንስሳቶች

በድሮ ጊዜ በአንድ ጫካ ውስጥ የሚኖሩ የዱር እንስሳቶች ነበሩ፤ ስማቸውም አንበሳ፣ ጦጣ እና ጥንቸል ይባሉ ነበር፡፡ ሦስቱም የዱር እንስሳቶች ልጆች አሏቸው፤ ብዛታቸውም አንበሳ ሦስት ልጅ አለው፤ ጦጣ ሁለት ልጅ አለው፤ ጥንቸል ደግሞ አራት ልጆች አሉት፡፡ እነዚህ እንስሳቶች በአንድ የጫካ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ቢሆኑም የልጅ አስተዳደግ ሁኔታቸው ግን የተለያየ ነበር፤ የአንበሳ ልጆች ወላጆቻቸዉ በሚገባ ይንከባከቧቸዋል፤ የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎችን ማለትም ሰው ማክበር፣ መታዘዝ፣ አለመዋሸት፣ መረዳዳት፣ የመሳሰሉትን በተግባር ለልጆቻቸዉ እያስተማሩ ያሳድጋሉ፤ በዚህም ምክንያት ልጆቹ ሰውን አክባሪ ፣ ታዛዥ፣ በመንደሩናበመምህራኖች ተወዳጆች ናቸው ፡፡ በአንፃሩ የጦጣ ልጆች ግን በተቃራኒው ወላጆቻቸዉ ለልጆቹ ግድየለሽ የሆኑ፣ የማይንከባከቧቸው፣ የሚሠሩትን የማይከታተሉ በመሆኑ እና ልጆቹ የሚገስፃቸው ባለመኖሩ መምህራኖች እና ጎረቤት ሲያዛቸው አይታዘዙም፤ ከጓደኞቻቸው ጋር ሁልጊዜ የጣላሉ፤ ውሸት ይዋሻሉ፤ የመጫወቻ እቃዎችን እኛ ብቻ እንጫወትበት የሚሉ ዓይነት ልጆች ናቸው፡፡ የጥንቸል ልጆች ደግሞ እንደ አንበሳ ልጆች ከወላጆቻቸዉ ተገቢ የወላጅ እንክብካቤ እና ፍቅር የሚያገኙ፣ ትህትናን የተላበሱ እና ሰው

ታዛገሮች ናቸው፤ ታዲያ የእነዚህ ጎረቤታም ልጆች የሚማሩት በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ነበር፤ የአንበሳ የጥንቸል እና የጦጣ አንዳንድ ልጆቻቸው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃ ሦስት ተማሪ ናቸው፤ ከዕለታት አንድ ቀን መምህራቸው የውጭ ጨዋታ እንዲጫወቱ የጨዋታውን የአጨዋወት ስልት ትነግራቸው እና ተራበተራ እንዲጫወቱ ታደርጋቸዋለች፤ እነሱም ጨዋታውን መጫወት ላይ እያሉ የጦጣ ልጅ ተራ ደርሷት ጨዋታውን ከጨረሰች በኋላ ሌላውን ተረኛ እንዲገባ ያደርጉታል ፤ ነገር ግን የጦጣ ልጅ ተራውን አለቅም እራሴ ነኝ የምጫወተው በማለት እምቢ ትላቸዋለች ፤ ቀጣዩ ተረኛ የጥንቸል ልጅ ደግሞ ልቀቂ ይላታል ፤ በዚህ ጊዜ የጦጣ ልጅ እንዴት ልቀቂ ይለኛል ብላ ተረኛውን ልጅ ትደበድበዋለች፤ በሃይል እግሩን መትታው ስለነበር ይደማበታል ፤ በዚያን ጊዜ በጨዋታው ላይ የነበሩት ሁሉ ሲንጫጩ መምህሯ ትሰማ እና እየሮጠች ስትመጣ የጥንቸል ልጅ እግሩ ደምቶ እያለቀሰ ታገኘዋለች፤ ወዲያው መምህሯ የተጎዳውን ትንሹን ጢንቸል ወደ ክፍል ወስዳደው ደሙ እንዲቆም እርዳታ በማድረግ በጨርቅ ከጠቀለለች በኋላ በቶሎ ወላጆቹን ጠርታ ወደጤና ተቋም እንዲሄድ ታደርገዋለች፤ ከዚያም የተፈጠረውን ነገር ስትጠይቃቸው የጦጣ ልጅ እኔ ተራዬን ሳልጫወት እኔ ልጫወት ብሎኝ ነው የመታሁት በማለት ትዋሻለች፤ በመቀጠል መምህሯ እየዋሸች መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ ወላጅ እንድታመጣ ታደርጋታለች፤ ወላጅ/ አሳዳጊዋ መጣች መምህሯም ወላጇን/አሳዳጊዋን የልጅቱን ሥነምግባር የሚከታተሉበትን ሁኔታ ከጠየቀች በኋላ ለወላጇ/አሳዳጊዋ ምክር ሰጥታ አሰናበተቻት፡፡ጦጣም ትንሹን ጥንቸል ይቀረታ ጠየቀ የተጎዳው ጥንቸልም ለሁለት ቀን ያክል እንደጓደኞቹ ጨዋታ ሳይጫወት ተቀምጦ በመመልከት ብቻ ከቆየ በኋላ ተሸሎት መጫወት ጀመረ የጦጣም ልጅ ከዚያን ቀን ጀምሮ ፀባዩን አስተካክሎ ከጓደኞቹ ጋር በደስታ እና በፍቅር መጫወትና መኖር ጀመረ ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተረቱን ታሪክ የሚገልፅ ስዕላዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ የትኩረት ዝንባሌያቸዉን መመዘን ፤**የቃል ጥያቄ**

1. በአንድ የጫካ መንደር ውስጥ የሚኖሩ የዱር እንስሳቶች ስንት ናቸው? ስማቸው ማን ማን ይባል ነበር?
2. ልጆቹን በጥሩ ሥነ ምግባር የማያሳድገው የዱር እንስሳት ማን ነበር ?
3. ጨዋታውን የረበሸችው ልጅ የማን ልጅ ነበረች በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር የረበሸችው ?
4. መምህራቸው እየሮጠች የመጣችው ምን ሆና ነበር ? ከዚያስ ምን አደረገች ?

## ተግባር ስድስት: የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት :** የአካል ክፍሎች፣ ቁጥር መቁጠር፣ ጥበባዊ ግንዛቤ

**የማስተማሪያ ዘዴ** በተግባር፣ በገለፃ፣ በተግባር፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናትን ስለግል ንፅህና አጠባበቅ ሂደቶች እንዲናገሩ ይጠይቋቸው:: በተጨማሪም የግል ንፅህናን ለመጠበቅ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ሳይጠቀሙ በምልክት እንዲያሳዩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል ወደውጭ ይዘዋቸው ይውጡ እና ለህፃናቶች የስምምነት ጨዋታ እንደሚጫወቱ ይንገሯቸዉ(ማለትም የስምምነት ጨዋታ ለጨዋታዉ ብቻ የሚያገለግል የመግባቢያ ስምምነት ብቻ እንጅ ለእዉነተኛዉ የእለት ከእለት እንቅስቃሴያችን የምንጠቀምበት

እዉነታ አለመሆኑን በመረዳት ለህፃናቶችም ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡) ጨዋታው በግል የሚከናወን ነው ከዚያም ውሃ እና ሳሙና በመስጠት ተራ በተራ እየታጠቡ ተራ የደረሰው/ሳት ሕፃን ጓደኞቹ/ዋ ሰላም ሲሉት/ሲሏት እጁን/ጇን ይታጠባል/ትታጠባለች፤ ፍቅር ሲሉት/ሲሏት ፊቱዋን/ፊቱን ይታጠባል/ትታጠባለች፤ ትህትና ሲሉት/ሲሏት ጥፍሯን/ሩን የመቁረጥ ናሙና ያሳያል/ታሳያለች፡፡ በዚህ ሂደት ሁሉም ልጅ ጨዋታውን ይቀጥላሉ፡፡

በመጨረሻም ወደ የክፍላቸው ከገቡ በኂላ የመለማመጃ ደብተራቸው/በደብተር/ ገጽ ላይ የሚገኘውን የመልመጃ ጥያቄዎች ማለትም ፍቅር፣ ሰላም፣ ትህትና፣ መታጠብ፣ውሃ ፣ሳሙና እና መሰል ቃላቶችን በመጠቀም አረፍት ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው:: እርስዎ በመዘዋወር ድጋፍ ያድርጉላቸው ፤ ከጨረሱ በኂላ አንድ በአንድ እየወጡ የሰሩትን እንዲያቀርቡ እና ስንት አረፍተ ነገሮችን እንደመሰረቱ እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡

***የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:*** ፡ ሳሙና ፣ ውሃ ፣ ስለንፅህና አጠባበቅ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ፣ የመለማመጃ ደብተር ፣እርሳስ

***የምዘና ስልት:*** ምልከታ፡ ህግና ደንብን የመከተል ሥርአታቸውን በምልከታ መመዘን ፣ የቃል ጥያቄ፡ ፍቅር ስንል የትኛውን የሰውነት አካል ክፍላችንን ነበር የታጠብነው ? ሰላም ስንልስ ?፣ የፁሁፍ ጥያቄ መስጠት ቃላት እንዲመሰርቱ፣ ዓረፍተ ነገር እኒዲሰሩ...

## ተግባር ሰባት: የክፍል ውስጥ ጨዋታ ( 6 ክፍለ ጊዜ )

***ቁልፍ ቃላት:*** ወፎች፣ ፍራፍሬ፣ አበባ ቅርፅ፣ቁጥር፣ባንዲራ፣ ቀለም፣ሰላም ጥበባዊ ግንዛቤ

***የማስተማሪያ ዘዴ:*** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

***የመምህር ሚና:*** መምህር እባክዎትን ለሕፃናት ለማነቃቂያ የሚሆን አንድ መዝሙር መርጠው እንዲዘምሩ ያድርጓቸው ቀጥለው በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድን ይከፋፍሉ እና ብዛት ያላቸው የወፍ ሥዕሎች፣ ፍራፍሬ (ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ሎሚ ) አበባ ፣ የልብ ቅርፅ ሥዕል፣የባንዲራ ሥዕል የያዙ ሥዕሎችን እያንዳንዱ ድግግሞሽ ሊኖረው ይገባል ምሳሌ ባንዲራሶስት፣ የወፍ ስዕል አምስት፣ ሙዝ አስር፣ ... እና እስከ ሃያ የሚደርሱ የቁጥር ፍላሽ ካርድ በየጠረጴዛቸው መስጠት ቁጥሩን አዘበራርቀው/አቀላቅለው በመስጠት ስእሉን በአይነት ከለዩ በኂላ ብዛቱን ቆጥረው ስእልና ቁጥሩን እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡

በመቀጠል ደግሞ ደብተር /ወረቀት፣ እርሳስ እና የተለያዩ ከስእሎቹ ጋ የሚመሳሰሉ ቀለማትን በመስጠጥ ተወስኑትን ዛሬ የቀሩትን ነገ ስለው እንዲቀቡ ያድርጉ በመቀጠል የመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ የሚገኙትን ተመሳሳይ ሥዕላዊ መግለጫዎች እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም በየቡድናቸው ተራበተራ እየተነሱ በጋራ የነጭ እርግብ ሥዕል እያሳዩ የሰላም ልብቅርፅ የፍቅር ፣ ባንዲራ የሰላም እያሉ ይዘምራሉ፡፡

***የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:*** የወፍ ስዕል፣ የተለያዩ ፍራፍሬ፣ የልብ ቅርፅ ፣ የባንዲራ ሥዕሎችን የያዙ የሥዕል ካርዶች፣ ማርከር፣ ቀለም ፣እርሳስ፣ ወረቀቶች፣ የመለማመጃ ደብተር

***የምዘና ስልት:*** የቃል ጥያቄ ስንት ሥዕሎችን ሳላችሁ? የምን የምን ሥዕል ነበሩ ?፣ ወፎቹ ስንት ነቸው፣ ባንዲራውስ .. አስር ቁጥር ፣ሃያ ቁጥር፣ አስራ አንድ ቁጥር... አሳዩኝ/አሳየኝ... ምልከታ(አስመስለዉ የመስራት/የመሳል አቅማቸዉን በምልከታ መገምገም

# ሁለተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክፍለ ጊዜ/ 15 ሰዓት

## አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

- ✓ ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖራቸው የግንኙነት ወቅት የገጠማቸዉን ስሜቶች ይገልፃሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ የድምፅ ዓይነቶችን ያስመስላሉ ፡፡
- ✓ የቦታን ምንነት ፅንሰሀሳብ ይረዳሉ ፡፡
- ✓ ንፅህናውን የጠበቀ ምግብ እና መጠጥ አስፈላጊነትን ይረዳሉ ፡፡
- ✓ ቀላል ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ ይችላሉ፡፡
- ✓ የሰላም መዝሙሮችን ይዘምራሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ ሥዕሎችን በመሣል ቀለም ይቀባሉ ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን መቆጣጠር ፣ ድምፅን መለየት ፣ ስርአተ ምግብ ፣ የቅርብ አካባቢ ፣ ቁጥሮችን መፃፍ፣ የፈጠራ ስራ

## ተግባር አንድ: ዉይይት (6 ክፍለ ጊዜ)

### ዉይይት አንድ ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የስራ ድርሻ፣ስነ ምግባር፣ እሴቶች፣ ሴትና ወንድ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በዉይይት፣በጥያቄና መልስ ፣በገለፃ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ይህ ቀን የሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን እንደመሆኑ ሕፃናት ንፅህናቸውን ጠብቀው የመጡ መሆናቸውን በመዘዋወር ያረጋግጡ፡፡ ህጻናቶችን በትናንሽ ቡድን በመከፋፈል (4 6 ቁጥር በማይበልጥ) ያስቀምጧቸዉ፡፡ ከዚያም የቤተሰብ አባላት የስራ ድርሻን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ በትልቅ ወረቀት በማዘጋጀት የሚታይ ቦታ ላይ ይስቀሉላቸዉ፡፡ በተጨማሪም የቤተሰብ አባላት የስራ ድርሻን በተመለከተ ስራን ተረዳድቶ ከመስራት አንፃር የወንድና የሴት የስራ ድርሻ ልዩነቶችን እንደሌለው ይግለፁላቸው፤ሴቶች እና ወንዶች ማንኛዉንም ስራ በእኩልነት መስራት እንደሚችሉ ያስገንዝቧቸዉ፡፡

- ✓ ህፃናቶች ከስዕሉ ምን እንደተረዱ በቃል ከጠየቁ በኋላ ወደ ዉይይቱ ያስገቧቸዉ
- ✓ በየቡድናቸዉ በየቤታቸዉ የቤተሰብ አባላቶቻቸዉን የስራ ድርሻ እንድያወሩ (እንዲወያዩ) ያድርጓቸዉ
- ✓ እየተወያዩበት ያለዉን ሀሳብ ከተዘጋጀላቸዉ ስዕላዊ መግለጫ ጋር እያዛመዱ እንዲሰሩ ያድርጓቸዉ
- ✓ ከየቡድናቸዉ የተወያዩበትን የየግል ሀሳባቸዉን በራስ የመተማመን ስሜት እንዲያቀርቡ ያድርጓቸዉ
- ✓ ከስነምግባር አኳያ ሊከተሏቸዉ የሚገቡ ስነ ስርዓቶችንና የቤተሰብ አባላት የስራ ድርሻ መረዳዳት ጥሩ ህይወትን ለመምራታ ከፍተኛ ሚና እንዳለዉ ያስገንዝቧቸዉ
- ✓ እነሱ እቤት ውስጥ በምን የስራ ድርሻ አዘውትረው እንደሚሳተፉ እና ለምን በዚያ ስራ

እንደተሳተፉ እንዲገልጹ ያድጉ

- ✓ ይህንን ሁሉም ህፃናት እንዲ ሰሩ እንዲናገሩ በውይይቱ በንቃት እንዲሳተፉ ያበረታቱ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቤተሰብ አባላቶችን የስራ ተግባራት የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(ከንግግራቸዉ አስተዉሎታቸዉን መመዘን)

**የቃል ጥያቄ**

- ✓ በቤታችሁ ዉስጥ ምንምን ስራዎች ይሰራሉ ስንት ናቸው?
- ✓ ከተመለከታችኋቸዉ ስዕላዊ የስራተግባራቶች ዉስጥ የትኞቹ እና ስንቶቹ እናንተ ከዘረዘራችኋቸዉ ጋር ይመሳሰላሉ?
- ✓ የቤተሰብ አባላት የስራ ተግባራቶችን ስናከናዉን የምንከተላቸዉ የስነምግባር እሴቶች(ስነስርአቶች) ምንምን ናቸዉ? የወንድና የሴት ስራ ልዩነት አለው ብላችሁ ታስባላችሁ...

## ዉይይት ሁለት ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ገጠመኞች፣ስሜትን የሚገልፁ ቃላቶች(መደሰት፣መከፋት፣ማልቀስ)

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በዉይይት፣በጥያቄና መልስ ፣በገለፃ

**የመምህር ሚና:** መምህር ለህፃናቶች ለእነሱ በሚመጥን ሁኔታ እርስዎ በሆነ አጋጣሚ የገጠመዎትን አስደሳችም ሆነ አስደንጋጭ ስሜታዊ ገጠመኝ ይንገሯቸዉና ምን እንደተሰማቸዉ ይጠይቋቸዉ፡፡ በመቀጠል የተለያዩ ስሜቶችን(መከፋት፣ማዘን፣ማልቀስ፣መደሰት፣መሳቅ) የሚገልፁ ቃላቶችን የያዙ ቁርጥራጭ ካርዶችን እና ስሜትን የሚገልፁ ስእሎችን ያዘጋጁላቸዉ::

ቀጥሎ ህፃናቱን በትናንሽ ቡድን ያስቀምጧቸዉ፤በየቡድናቸዉ በተለያዩ አጋጣሚዎች የገጠማቸዉን ገጠመኝና በምን ሁኔታ እንዳለፉት ለጓደኞቻቸዉ እንዲያወሩ ያደርጓቸዉ፤ስሜታቸዉን የሚገልፀዉን ካርድ እንዲያሣዩ ያድርጓቸዉ፡፡እርስዎ በመዘዋወር የዉይይቱን አስደሳችነት ይመልከቱ ተነሳሽነታቸዉን በማበረታታት ከየቡድናቸዉ በየተራ ገጠመኞቻቸዉን ለክፍል ጓደኞቻቸዉ ወጥተዉ እንዲያወሩና ስሜታቸዉን የሚገልፅላቸዉን ቃላት የያዘዉን ካርድ እና ስዕል እንዲያሳዩ ያድርጓቸዉ እና ህፃናቶች ባቀረቡት ላይ እንደአስፈላጊነቱ ምክረ ሀሳብ ይስጧቸዉ፡፡ በመጨረሻም እራሳቸውን ከሚሰማቸው ስሜት ጋር( ምሳሌ ደስታ፣ሀዘን...) እንዲሲሉና እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ስሜቶችን ሊገልፁ የሚችሉ ቃላቶችን ፣ስዕሎች የያዙ ቁርጥራጭ ካርዶች፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ ደብተር ፣ቀለም

**የምዘና ስልት:** **ምልከታ**(የተለያዩ ስሜቶችን የመረዳት አቅማቸዉን መገምገም)፣ **የቃል ጥያቄ** (ስንት የገጠመኝ ሰማሽ/ክ፣ ስሜታችሁን የሚገልፅ ካርድ ዐሳዩ /አሳይ፣ውይይቱ እንዴት ነበር ፣የማን ገጠም አሳዛኝ ነበር፣አስደሳችስ ገጠመኝ የቱ ነበር፣ አሳዛኝ ገጠመኝ ሲያጋጥመን ምን ማድረግ አለብን... ምን ተሰማችሁ?

## ተግባር ሁለት: ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ትህትና፣መከባበር፣መረዳዳት ፣ራስን መምራት፣አካባቢን መረዳት፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በትረካ ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና** ፤ መምህር ህፃናቶችን ለማነቃቃት ያስችል ዘንድ ለተወሰነ ደቂቃ ነፃ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ከክፍል ውጭ ያስወጧቸው ቀጥሎጥላ ዛፍ ያለበት ስፍራ በመፈለግ ተረት ለመስማት በሚመች አቀማመጥ አስቀምጠው የተረት ተረት አባባል ባህልና ወግን መሠረት በማድረግ ያንብቡላቸው ፡፡

### ጎረቤታሞቹ

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ የሚዋደዱ ብዙ ጎረቤታሞች ነበሩ፤ ስማቸውም ወ/ሮጫልቱ፣ ወ/ሮአልማዝ ፣ ወ/ሮህሊማ እና ወ/ሮ አብረኸት ይባላሉ ፤ ታዲያ እነዚህ ጎረቤታሞች በአካባቢያቸው ሰው ሲታመም የሚጠይቁ ፤ የተቸገረን በገንዘባቸው እና በጉልበታቸው እርስበርሳቸው የሚረዳዱ፤ አንዷ ስታጠፋ ሌላዋ የሚታገሱ መልከም ሥነ ምግባር ያላቸው ጎረቤታሞች ናቸው፡፡ የእነዚህ ጎረቤታሞች ልጆች አንድ ትምህርትቤት የሚማሩ ሲሆኑ የአራታቸውም ሰዎች ልጆች የቅ/አንደኛ ደረጃ ሦስት ተማሪዎች ናቸው፤ እነዚህ ልጆች ሁልጊዜ ራሳቸውን ችለው በፕሮግራም በጋራ ያጠናሉ፤ የቤትሥራ ይሰራሉ፤ አብረው ይጫወታሉ፤ ወላጆቻቸውን/አሳዳጎዎቻቸዉን በጋራ ይታዘዛሉ ፤በአጠቃላይ የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን አብረው ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸዉ ሳይነግሯቸው ያከናውናሉ፤ በመካከላቸው አለመግባባት ቢፈጠርም እንኳ ሳይጣሉ ወዲያው ይስማማሉ፡፡ በመምህራኖቻቸው ተወዳጆች እና ታዛዦች በመሆናቸው በታማኝነት ሁልጊዜ ያሄቸዋል፤ ወላጆቻቸውም/አሳዳጊዎቻቸዉም ለልጆቻቸው የመልካም ሥነ ምግባር ምሳሌ በመሆናቸው ደስተኞች ናቸው፡፡ ታዲያ አንድ ቀን እነዚህ ልጆች የመመገቢያ ሰዓታቸው ደረሰ እና ወደመመገቢያ ክፍላቸው ከመሄዳቸው በፊት ተራ በተራ ሳይገፋፉ እና ሳይሽቀዳደሙ እጃቸውን በሳሙና በደንብ ሲታጠቡ በአጋጣሚ ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸዉ ትምህርት ቤት መጥተው ስለነበር ልጆቻቸው በፍቅር፣ በትህተና እና በሰላም ተራ በተራ እየታጠቡ ወደ መመገቢያ ክፍላቸው ሲገቡ ተመለከቷቸው፤ ወላጆችም/አሳዳጊዎቻቸዉም በጣም ተደስተው የመጡበትን ተግባር ከመምህራቸው ጋር አከናውነው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡

**መምህር** ይህን ተረት በደንብ ካነበቡላቸው እና ካስገነዘባችኋቸው በኋላ በትናንሽ ቡድን ገፀባህርያቱን በመወከል ተከፋፍለው በተግባር እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታን ይፍጠሩላቸው፡፡ በመጨረሻም የሚና ጨዋታውን ጭብጥ በጥያቄ ያስገንዝቧቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የወላጆች/አሳዳጊዎች አልባሳት፣ ሳሙና ፣ ውሃ፣ የመመገቢያ ክፍል ናሙና፣ ለሚና ጨዋታው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ...

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ ( በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ጎረቤታሞች ብዛታቸው ስንት ነበር? ማን ማን ይባላሉ?፣ እንዴት ይኖሩ ነበር፣ ልጆቻቸው ከነሱ ምን ተማሩ? ፣ ልጆቻቸው በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ምን ተግባራትን ያከናውኑ ነበር?፣.... ምልከታ(የታሪኩን ገጸባህሪይ ወደ ተግባር የመቀየር አቅማቸዉን መገምገም)

## ተግባር ሶስት፡ በሥራ መማር (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ራስን መምራት፣ ቁጥር፣ መጻፍ፣ አካባቢን መረዳት ፣ዕዳት

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር ስራ ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና**

መምህር ልጆችን ለማነቃቃት የሚያስችል አንድ የሚያውቁትን መዝሙር ያስዘምሯቸው

- ✓ በመቀጠል ሕፃናትን በክፍል ውስጥ እንደየብዛታቸው በትናንሽ ቡድን በመከፋፈል የተወሰኑት የተበታተኑ የመማሪያ ቁሳቁሶችን እየተነጋገሩ እንዲያስተካክሉ ያድርጓቸው
- ✓ ሌሎች የመቀመጫ ወንበሮቻቸውንና ጠረንጴዛቸውን፣ የመማሪያ ክፍላቸውን እንዲያፀዱ ያድርጓው፤
- ✓ ተጨማሪ ሕፃናት ደግሞ በተመሳሳይ ሌሎች ተግባራትን በየቡድናቸው ይስጧቸው
- ✓ እርስዎ ሕፃናትን እየተነጋገሩ እና እየተወያዩ መሥራታቸውን ይከታተሏቸው ፤
- ✓ ከጨረሱ በኋላ ያከናወኗቸውን ተግባራት በመቁጠር እና በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፤ በመጨረሻም በጋራ የትምህርትቤት መተዳደሪያ ህግና ደንቦችን እንዲያወጡ እና ወደ ተግባር እንዲቀይሯቸው ያድርጉ
- ✓ ይህንን ተግባር ሁሉም ህፃናት በየተራ በተቀመጠው ክፍለ ጊዜ እንዲያከናውኑ ያድርጉ ሲሰሩ ተግባሩንም በታ ማቀያየቀር አይዘንጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** እስክርቢቶ፣ ወረቀት፣እርሳስ፣መጥረጊያ፣ ፎጣ

**የምዘና ስልት፡** በሥራ ሂደት ላይ ተግባብቶ የመሥራት አቅማቸውን በምልከታ መመዘን ፣ የሥራ ተነሳሽነታቸውን መገምገም፣ የቃልጥያቄ (ምንምን ሥራዎችን ሰራችሁ? ስራዎቻችሁን በቁጥር ግለፁት፣ስትሰሩ ያቃታችሁ ምን ነበር፣ እንዴት ተወጣችሁት…

**ማስታወሻ፡** በእርስዎ ክፍል ዉስጥ በህፃናት አቅም ለሰሩ ወይም ለተገበሩ የሚችሉ ተግባራት ካለዎት አቅማቸዉን በሚመጥንና በማይበዛ መልኩ እየተጫወቱ እንዲሰሩ ያድርጓቸዉ፡፡

## ተግባር አራት፡ መዝሙር (4 ክፍለ ጊዜ )

**ቁልፍ ቃላት፡** ድምፅን መለየት፣ አመጋገብ፣ አካባመረዳት፣ጤና ፣ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር፣በገለፀ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ለሕፃናት ክፍለጊዜው የመዝሙር መሆኑን ይንገሯቸው ፤

- ✓ በመዝሙሩ ውስጥ ያሉትን ገፀ ባህሪርይያቶች በመተወን እንዲዘምሩ ያድርጓቸው
- ✓ ከዚያም የመዝሙሩን ጭብጥ በትናንሽ ቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ
- ✓ እርስዎ በመዘዋወር ድጋፍ እና ፍንጭ ይስጧቸው ፤
- ✓ ከጨረሱ በኋላ የተወያዩበትን እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፤ እርስዎም ተጨማሪ ሐሳብ ይስጧቸው ፤
- ✓ በመጨረሻ የመለማመጃ ደብተር ገጽ የሚገኙትን በመዝሙሩ ውስጥ ያሉትን እንስሳቶች ሥዕል ስማቸውን እና ብዛታቸውን ከፃፉ በኋላ በቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ

- ✓ ቀለም በሚቀቡበት ወቅት የእንስሳቱን ትክክለኛ ቀለም የሚገልፁ ቀለማቶችን እንዲጠቀሙ አቅጣጫ ይሰጧቸው ::

## መዝሙር አንድ

### እንስሳቶቻችን

ወፊቷ በረረች
በሰማይ ላይ ሄደች ፣
ሲው ሲው እያለች ሰላም አበሰረች ::
በሬውም አገሳ እንቧ እያለ ሄደ ፣
ውሻውም በተራው ዋው ሲል ነጎደ ::
ድመቷ ሚያው አለች አይጧም ደነገጠች ፣
ወደመጣችበት ከጉድጓዷ ገባች ::
ዶሮየም ኩክ አለች ፣
እንቁላል ልትጥል ከቦታዋ ገባች ::
ላሟ ትጠቅማለች ወተት ትሰጣለች ፣
እንንከባከባት ለእኛ ትጠቅማለች ::
ስጋ እና ወተትም ለኛ ትሰጣለች ፣
ከተመገብናቸው ጤናማ እንሆናለን::
በሽታ አይዘንም ጤነኛ ነን ሁሌም ፣
በንጹሕ ጠብቀን እንመገብ ዛሬም ፣
ይሄንን ካደረግን ደስተኛ ነን ነገን ::

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቤት እንስሳቶችን የሚያሳይ ሰዕላዊ መግለጫ ፣ ቀለም፣ የመለማመጃ ደብተር/ወረቀት፣ለመዝሙሩ ማጻመጫ የሚሆኑ ኤሌክትሪክ መሳሪያዎች

**የምዘና ስልት: የቃል ጥያቄ:** በሰማይ ላይ በረረችው ማነች ድምፅስ እንዴት ነበር፣ ምን እንስሳትን ለያችሁ፣ እንስሳቶች ለሰው ምን ይጠቅማሉ.በሽታ እንዳይዘን ምን ማድረግ አለብን? በመዝሙሩ ውስጥ ስንት እንስሳቶች አሉ ፣.... **ምልከታ** ሲዘምሩ እና ሲሰሩ በተገቢ መመልከት ፣ **ማህደረ ተግባር** ፡ የሰሩትን በአግባቡ አስቀምጦ ለውጣቸውን መመዘን

## መዝሙር ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት ፡** ቤተሰብ፣ ፍቅር፣ ስነ ምግባር፣ትምህርት ቤት

**የማስተማሪያ ዘዴ ፡** በመዝሙር፣በገለፀ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አዘማመር ቅደም ተከተልን ተከትለው እንዲዘምሩ ያድርጉ

ባለዉለታዬ

የእኔ ቤተሰቦች ናቸዉ ለእኔ ዉዶች ፣
ሁልጊዜ የሚያዩኝ በሚሳሱ አይኖች ፣
እናት እና አባቴ ደብተሬን አሟልተዉ ፣
እህት ወንድሞቼ ትምህርት ቤት ወስደዉ ፡፡
ትምህርት አስጠንተዉ እንዳነብ መክረዉኝ ፣
እስክርቢቶ አያያዝ በእጅ አሳይተዉኝ ፣
ከደብተር ላይ ስፅፍ መስመር አስይዘዉኝ ፣
ጎበዝ ልጅ እንድሆን ሁልጊዜ መክረዉኝ ፣
ጎረቤቶቻችን ምግባር አስይዘዉኝ ፣
ይሄዉ አድጋለሁኝ በፍቅር አጅበዉኝ ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ከመዝሙሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች ፣ለማዳመጫ የሚሆን ኤሌክትሮንክስ መሳሪያ ምሳሌ ስልክ፣ ጂፓስ...

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (የቅንጅት ተግባራቸውን መመዘን) **የቃል ጥያቄ:** በመዝሙሩ ውስጥ እናት እና አባት ለእናንተ ምን ያደርጋሉ ? እናንተስ ምን አይነት ባህሪ ሊኖራችሁ ይገባል ፣ የአካባቢያችሁ ሰዎች ምን ያስተምሯችኋል.....

## ተግባር አምስት: የክፍል ውስጥ ጨዋታ (7 ክፍለ ጊዜ )

**ቁልፍ ቃላት:** ስዕል፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ ቁጥር፣መቁጠር፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ ፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናትን ክፍለጊዜው የክፍል ውስጥ ጨዋታ መሆኑን ይንገሯቸው፡፡ ሕፃናትን በክፍል ውስጥ እንደየብዛታቸው በትናንሽ ቡድን በማደራጀት ስለሠላም እና ፍቅር የሚገልፁ የተለያዩ ሥዕሎችን ያሳዩአቸው

**ለምሳሌ:** አበባ ፣ ባንዲራ ፣ ወፍ ፣ ልብቅርፅ ፣ የመሳሰሉ በመሣል ቀለም ወይም ከለር እንዲቀቡ ያድርጓቸው፤ ከጨረሱ በኋላ የሰሩትን ተራ በተራ እንዲቀቡ ዕድል ይስጧቸው በመቀጠል በየቡድናቸዉ ያዘጋጇቸዉን ተመሳሳይ ስዕሎች ብዛት ምን ያክል እንደሆነ አንድላይ በማድረግ ይቁጠሩ ቀጥሎ አንዱ ቡድን ከሌላዉ ቡድን ያዘጋጇቸዉን ተመሳሳይ ስዕሎች በምን ያክል ብዛት እንደሚበልጥና እንደሚያንስ እንዲናገሩ ያድርጓቸዉ፤ በመጨረሻም በደብተር /ከመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ ያለውን የሰላም ተምሳሌት የነጭ እርግ፣ የባንዲራ፣የሰላምታ ሥዕሎች እንዲያዛምዱ፣እንዲሲሉና እንዲቀቡ ያርጉ፡፡

ይህንን ተግባር በተደጋጋሚ እንዲሰሩ እድሉን ያመቻቹ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ቀለም እርሳስ ፣ እርሳስ ፣ ወረቀት ፣ ላጲስ ፣ ስለሠላም የሚያሳዩ ቁርጥራጭ የሥዕል ካርዶች ፣ የመለማመጃ ደብተር ፣ወረቀት...

**የምዘና ስልት ፥ ምልከታ** የቀለም ምርጫቸውን ተገቢነት ፣ የቀለም አቀባብ ሥርአታቸውን

መመዘን፣ **የቃል ጥያቄ** ስንት ሥዕሎችን ሳላችሁ ? ምንምን ናቸው? ስዕሎቹን በምን በምን አጋጣሚ እናገኛቸዋለን ?

# ሦስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክፍለ ጊዜ/ 15 ሰዓት

## አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ፡

- ✓ የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን በአግባቡ ይመራሉ፤
- ✓ የሰላምን ትርጉም ያዉቃሉ፤
- ✓ በሰላም አብሮ የመኖር ተረቶችን ይናገራሉ፤
- ✓ የሰላም መገለጫ ስዕሎችን ይስላሉ፤
- ✓ ሰላማዊና ሰላማዊ ያልሆኑ አካባቢያቸዉን ይለያሉ፤
- ✓ ባህላዊ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፤
- ✓ በይበልጣል፣ያንሳል እና እኩልይሆናል የማወዳደሪያ ምልክቶችን በመጠቀም ሁለት ቁጥሮችን ያወዳድራሉ፤

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን መቻል፣ የቃላት ክምችት፣ የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር ፣ ቁጥሮችን ማወዳደርናመደርደር፣ ባህላዊ ቅርሶች

## ተግባር አንድ፡ ዉይይት (5 ክፍለ ጊዜ)

### ዉይይት አንድ ( 2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ራስን መቻል፣የቃላት ዕውቀት፣ የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣የነገሮችን ብዛት መቁጠርና ማወዳደር፣ ተግባብቶ በጋራ መስራት፣ሰላም

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በዉይይት፣ በጥያቄና መመልስ፣

**የመምህር ሚና ፡** መምህር ህፃናቶችን ለማነቃቃት ያስችል ዘንድ አንድ የፈለጉትን መዝሙር መርጠዉ እንዲዘምሩ ያድርጓቸዉ

- ✓ ህፃናቶችን በትናንሽ ቡድን ከ4 6 በማይበልጥ ቁጥር ያደራጇቸዉ
- ✓ እርስዎ ለህፃናቶች ቅዳሜና እሁድ ምንምን ተግባራቶችን እንዳከናወኑ ይንገሯቸዉ
- ✓ ለህፃናቶች የህፃናቶችን የእረፍት ጊዜ ተግባራት የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ በማሳየት ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸዉ
- ✓ በየቡድናቸዉ ቅዳሜና እሁድ ምንምን ተግባራቶችን እራሳቸዉን ችለዉና ከቤተሰቦቻቸዉ ጋር እንዳከናወኑ ለተወሰነ ደቂቃ ካሰቡ በኋላ ለጓደኞቻቸዉ እንዲያወሩ ያድርጉ ተግባራትን ሲያከናውኑ የትኛው የሰውነት ክፍላቸው እንደዳበራ ይወያዩ
- ✓ በዉይይት ሰአታቸዉ ከቤተሰቦቻቸዉ ጋር በጋራ በመሆን ያከናወኗቸዉን ተግባራቶች ከስነምግባር/ስርአት አኳያ ምን እንደሚመስል ሂደታዊ በሆነመንገድ እንዲናገሩና በግል እና በጋራ ምን ያክል ተግባራቶችን እንዳከናወኑ ማስታወሻ በመያዝ እንዲወያዩ መነሻ ሀሳብ ይስጧቸዉና በመቀጠል የሰላም መገለጫ ስዕሎችን እንዲስሉ ያድርጓቸዉ፡፡

- ✓ እርስዎ በመዘዋወር ድጋፍ ያድርግላቸዉ
- ✓ መጨረሻ ላይ ተራበተራ የተወያዩበትን የየራሳቸዉን ተግባራት ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እየወጡ እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸዉ
- ✓ እርስዎ ተገቢ የሆኑ የህፃናት ተግባራቶችን በማበረታታት ተገቢ ያልሆኑትን ደግሞ የማስተካከያ ሃሳብ ይስጧቸዉ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የአካባቢ ባህልን መሰረት ያደረገ የህፃናት የእረፍት ጊዜ ተግባራቶች የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ/ፖስተር፣

**የምዘና ስልት: ምልታ** የቃላት አጠቃቀም ዕውቀትንና ተገቢነት መገምገም፣ሀሳብ መስጠት ያላቸዉን ተነሳሽነታቸዉን መመዘን፣ **የቃል ጥያቄ** በእረፍት ቀን ምን አደረግሽ/ አደረክ፣ ስራ ስንሰራ ጡንቻዎቻችን ምን ይሆናሉ፣ስንት ተግባራትን አከናወናችሁ...

**የቃል ጥያቄ**

- ✓ ከስዕሉ ላይ የምትመለከቷቸዉ ህፃናቶች ምን እየሰሩ ነዉ?
- ✓ ስንት የሰላም መገለጫ ስዕሎች ሳላችሁ?
- ✓ ቅዳሜና እሁድ እራሳችሁን ችላችሁ(በግላችሁ) ምን ምን ተግባራትን አከናወናችሁ? በብዛት ግለፁ::
- ✓ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በምን አይነት የመግባባት/የመናበብ ሂደት/ስርአት ተግባራቶችን በጋራ አከናወናችሁ? ስንት ተግባራትን አከናወናችሁ?
- ✓ ከስዕሉ ከተመለከታችኋቸዉ የህፃናት የቅዳሜና እሁድ ተግባራቶች ዉስጥ እናንተ ስንቱን አከናዉናችኋል? የማን ተግባር በብዛት ይበልጣል የእናንተ ወይስ በስዕሉ ዉስጥ የሚገኙት ህፃናቶች?

## ዉይይት ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ራስን መምራት፣እቅድ፣የቃላት ዕውቀት፣ ማወዳደር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በዉይይት፣ በጥያቄና መመልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ለሕጻናቶች ስለ ዕለት ተግባር እቅድ ምንነት ህፃናቶችን ያገናዘበና በሚረዱት መንገድ እንዲሆን አድርገዉ በምሳሌ በማስደገፍ እንዲሁም የህፃናቶችን የእለት ከእለት ዝርዝር ተግባራት የሚያሳይ ዕሁፋዊ መግለጫ በማሳየት በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ያስገንዝቧቸዉ።

- ✓ ህፃናቶችን በትናንሽ ቡድን ከ4 6 በማይበልጥ ቁጥር ያደራጇቸዉ
- ✓ በየቡድናቸዉ ትናንት(ባለፈዉቀን) ከጠዋት ጀምረዉ እስከማታ ድረስ ምን ምን ተግባራቶችን እንዳከናወኑ እንዲወያዩ እና የሚቀጥለዉ ቀን(የነገ) ተግባራትን እቅድ ደግሞ በየግላቸዉ እንዲያቅዱ በማድረግ ተግባር ይስጧቸዉ
- ✓ እርስዎ በመዘዋወር ማበረታቻና ድጋፍ ይስጧቸዉ
- ✓ የተወያዩበትን የቀጣይ ቀን እቅዳቸዉን ጨምረዉ እንዲያቀርቡ ተራበተራ እድል ይስጧቸዉ
- ✓ እቅዳቸዉ ላይ ማስተካከያ ካሉት በመስጠትና ለቀጣይ ቀን በእቅዳቸዉ መሰረት

ተግባራቶቻቸዉን እንዲያከናዉኑ ያሳስቧቸው

- ✓ እቅዳቸዉን አከናዉነዉ ከጨረሱ በኋላ ቀጣይ ቀን ላይ ሕጻናቶችን ያገናዘበ የእቅድ ግምገማ እርስ በርሳቸውና ከእርስዎ ጋር አድርጉ
- ✓ የዕለት እቅድ አስፈላጊነትን ግንዛቤ ያስጨብጧቸዉ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የህፃናቶችን የእለት ከእለት ዝርዝር ተግባራትን የሚያሳይ ፅሁፋዊ መግለጫ፣ ወረቀት ፣እርሳስ፣

**የምዘና ስልት :** ራሳቸዉን የመምራት ብስለታቸዉን በምልከታ መገምገም

**የቃል ጥያቄ**

- ✓ ትምህርት ቤት ከመምጣታችሁ በፊት ምን ምን ስራ ሰራችሁ?
- ✓ ወደ ትምህርት ቤት ስትመጡ ምን ምን ነገሮችን ማሟላት አለባችሁ?
- ✓ ከእንቅልፋችሁ ስትነሱ ጀምሮ እስከ ማታ የመኝታ ሰአታችሁ ድረስ የምታከናዉኑትን ተግባራት ንገሩኝ? በብዛት ስንት ሆኑ? የቅዳሜና እሁድ ተግባራችሁ ከዚህ በምን ይለያል? የእለት ተግባር እቅድ ማቀድ ለምን ይጠቅማል?
- ✓ ያቀዳችሁትን እቅድ እንዴት ተገበራችሁ፣ መተግበር ያቃታችሁ እቅድስ አለ ወይ ካለስ ችግሩን እንዴት ትፈታላችሁ

## ተግባር ሁለት: መዝሙር (8 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የቃላት ክምችት፣የትናንሽ ጡንቻ መዳበር ቁጥሮችን ማወዳደር እና መደርደር፣ባህልን ማወቅ ፣ሰላም

**የማስተማሪያ ዘዴ :** መዝሙር ፣በጥያቄና መልስ ፣

**የመምህር ሚና:** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አዘማመር ስልትን ተከትለው እንዲዘምሩ በማድረግ የመዝሙሩን ጭብጥ እንዲገነዘቡ ያድርጉ

### መዝሙር አንድ ( 4 ክፍለ ጊዜ)

**እኛ ሕፃናት**

እኛ ሕፃናቶች የዛሬ አበባዎች፣
እንሆናለን ዳግም የነገ ተስፋዎች፡፡
ሰባት ከስድስት ትበልጣለች እያልን፣
እንድናወዳድር ቁጥሮችን ተጠቅመን፣
አስተምረውናል ጠጠሮች ሰጥተውን፡፡
ግራ እጅ ሲታጠፍ ይሰጠናል ያንሳል፣
ቀኝ እጃችን ሲሆን ይሆናል ይበልጣል፣
ሁለቱ እኩል ሲሆን መች ይበላለጣል ፣
ቁጥሮች ሳወዳድር እንጠቀማለን ፡፡
ሰላም የራሳችን ምሳሌ እንደሆነች ፣

ፍቅር የልብ ናት በሰዎች ውስጥ ያለች ፡፡
እጃችን የተስፋ እግራችን የአንድነት
ዓይነጣጠሉም እንደ አንድ ሰውነት ፡፡

በመቀጠል የሰውነት የአካል ክፍሎችን እርስዎ ሲጠሩላቸው ለምሳሌ ግራ እጅ ሲታጠፍ ያንሳል፣ ቀኝ እጅ ሲታጠፍ ይበልጣል እና ወደፊት እኩል ሲዘረጉ ደግሞ እኩል ይሆናል፣ ሰላም ሲጠራ ራስ (ጭንቅላት) እንዲነኩ፣ ፍቅር ሲጠራ ልባቸውን እንዲነኩ፣ ተስፋ ሲጠራ እጃቸውን በወኔ ነፀብራቅ እንዲያሳዩ እና የመሳሰሉ ቅንጅታዊ ተግባራትን ክብ በመሥራት እንዲሠሩ ያድርጓቸው:: ምልክቶችን በመጠቀም በደብተር/በወረቀት ቁጥሮችን እንዲያወዳድሩ ያሰሩ::

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ከመዝሙሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስእሎች ፣መዝሙሩን ከፍ አድርጎ ለማሰማት የሚረዳ ኤሌክትሮኒክስ...

**የምዘና ስልት:** **የቃል ጥያቄ** የይበልጣል ምልክት፣የያንሳል ምክት አሳየኝ/አሳዪኝ፣ በመዝሙሩ ውስጥ ፍቅር ከየት ይመነጫል፣ ሲዘምሩ በምልከታ መገምገም

**ቁልፍ ቃላት:** የቃላት ክምችት፣የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣ ቁጥሮችን ማወዳደር እና መደርደር፣ባህልን ማወቅ፣ ሰላም

**የፁሁፍ መጠይቅ:** የመወዳደሪያ ምልክቶችን ተጠቅመው ቁጥሮችን እንዲያወዳድሩ ቁሶችን በመጠን እንዲያወዳድሩ ያድርጉ

## መዝሙር ሁለት ( 4/ክፍለ ጊዜ)

**የማስተማሪያ ዘዴ:** መዝሙር ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አዘማመር ስልትን ተከትለው እንዲዘምሩ በማድረግ የመዝሙሩን ጭብጥ እንዲገነዘቡ ያድርጉ

**ቁልፍ ቃላት:** የቃላት እወቀት፣ቁጥር፣ መደመር፣ማወዳደር፣ ፍቅር፣ሰላም

**የማስተማሪያ ዘዴ :** መዝሙር ፣በጥያቄና መልስ ፣

**የመምህር ሚና:** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አዘማመር ስልትን ተከትለው እንዲዘምሩ በማድረግ የመዝሙሩን ጭብጥ እንዲገነዘቡ ያድርጉ

### መምህራኖቼ አስተምረውኛል

እማራለሁ እኔ እንድጠቅም ለሀገር ፣
በሥነምግባሬ ሆኜ ሰላም ፍቅር
ትምህርት ቤት ሄጄ ስማር አንድ ሁለት ፣
ሦስት አራት ብየ ስጨምር አምስት ፣
ስድስት ሰባት ካልኩ ቀጣይም ስምንት ፣
ዘጠኝ እና አሥርን ቆጠርኩ በቃላት::
ፊደላትም አሉ ሀ ሁ የሚባሉ ፣
የቃላት ምሥረታ አንብቡ የሚሉ::

መምህራኖቼ አስተምረውኛል እንደፍላጎቴ ፣
አመሰግናለሁ ሁልጊዜ በህይወቴ፡፡
ጓደኞቼ ሁሉ አብረን እንኑር ፣
በሰላም በፍቅር እንተባበር፡፡
አይጠቅምም ለብቻ ሁልጊዜ መራመድ ፣
ውጤታማ እንድንሆን ሁልጊዜ እንዋደድ፡፡

**መምህር** መዝሙሩን በሚገባ ከዘመሩ በኋላ የሚከተለውን ተግባር ያሠሯቸው፡፡

1. በመዝሙሩ ውስጥ ያሉትን ስለሰላም እና ስነ ምግባርን የሚገልፁ ቃለቶችን የማወዳደሪያ ምልክቶችን እና የቁጥር ማወዳደሪያ ምልክቶችን በየግላቸው በቃላቸው እየተናገሩ በቁርጥራጭ ወረቀት እንዲፅፉ ያድርጓቸው
2. እርስዎ በመዝሙሩ ውስጥ ያሉ የሰላም ቃላቶችን እና የማወዳደሪያ ምልክቶችን ሲጠሩ ሕፃናት የጠሩላቸውን ቃላት እና የማወዳደሪያ ምልክት የያዘውን ቁርጥራጭ ወረቀት እንዲያሳዩዎት ያድርጉ ፡፡
3. ሕፃናት በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድን እንዲከፋፈሉ በማድረግ የስምምነት ጨዋታ እንዲጫወቱ ያድርጓቸዉ (የስምምነት ጨዋታዉ ለጨዋታዉ ብቻ የሚያገለግል መግባቢያ በመሆን የሚያገለግል ነዉ እንጅ የእለትከእለት እዉነተኛዉን እንቅስቃሴ የሚገልፅ እዉነታ አለመሆኑን ለህፃናቶች ይግለፁላቸዉ፡፡) መዝሙሩን አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ እያሳዩ እንዲዘምሩ ያድርጓቸው፡፡
4. መዝሙሩን ዘምረው ከጨረሱ በኋላ ከመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ የሚገኙትን የማወዳደሪያ ምልክቶች ስማቸውን እንዲፅፉ፣ ምልክቶችን ተጠቅመው ቁጥሮችን እንዲያወዳድሩ ከአንድ እስከ አሥር የተፃፉ ድርብ ቁጥሮችን በቀለም እንዲቀቡ የሚያዛቸውን መልመጃ እንዲሠሩ ያድርጓቸው ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ወረቀት ፣ እርሳስ፣ እስክርቢቶ ፣ ስለሰላም የሚገልፁ ቃላቶችን የያዘ የሥዕል ካርድ ፣ ቀለም እርሳስ ፣ የመለማመጃ ደብተር የማወዳደሪያና የሂሳብ ስሌት

**የምዘና ስልት:** ጥያቄ እና መልስ የይበልጣል ያንሳል እና እኩል ይሆናል የማወዳደሪያ ምልክቶችን ፅፋችሁ እና በሰውነት አካል ክፍላችሁ አሳዩ )፣ **ምልከታ** ቅንጅታዊ ተግባራቸውን መመዘን ፣ የመዝሙር ቃላቶችን በትክክል መናገራቸውን መከታተል

## ተግባር ሶስት: የክፍል ውጭ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ ፣በገለፃ፣በጥያቄና መልስ፣ ሰርቶ በማሳየት

**ቁልፍ ቃላት:** የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር ፣ ባህልን ማወቅ ፣ቅብብሎሽ፣ፃታ፣ ጥንቃቄ፣ የአብሮነት እሴት

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናትን በስርኣት አሰልፈው ከክፍል ውጭ ይዘዋቸው ይውጡ እና ከክፍል ውጭ ስለሚደረጉ የጥንቃቄ መርሆዎች በቅድሚያ ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠል በራሳቸው

በትናንሽ አምስት/ስድት ወነድና ሴት ያሉበት ቡድን እንዲከፋፈሉ ዕድል ይስጧቸው፤ ከዚያም እያንዳንዳቸው ቡድኖች የሚከተሉትን ተግባራት ተከፋፍለው እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡ (በቡድን ድልድል ወቅት የፆታ እና የቁጥር ክፍፍል ንፅፅር እንዲስተካከል ያድርጉ)

የጨዋታ ዓይነቶች ፡ የእግር ኳስ ጨዋታ፣ ኳስ ቅብብሎሽ፣ በአካባቢያቸው የተለመዱ ባህላዊ ዘፈኖችን ከጭፈራዎች ጋር ያሳዩ ፡፡

መምህር የአተገባበር ሂደት የኳስ ተጫዋች ቡድኖች በተመለከተ ፡

- ✓ የእግር ኳስ እና የኳስ ቅብብሎሽ ጨዋታ የሚጫወቱ ቡድኖች ጨዋታ ከመጀመራቸው በፊት ቡድን ስያሜ ይስጡ ፤ ለምሳሌ አብሮ አደግ ቡድን ፣ አንድነት ቡድን ፣ ኢትዮጲያዊነት ቡድን ወዘተ በማለት ይሰየሙ ፤
- ✓ በስምምነት ዳኛ እና የተወዳዳሪ ክፍፍል ያድርጉ፤ ጨዋታው የሰላም፣ የፍቅር፣ የአብሮነት ተምሳሌት ገፀባሕርይያቶችን ተላብሰው እንዲጫወቱ ያድርጓቸው ፡፡
- ✓ በመጨረሻም የሁለቱ ቡድን ተጫዋቾች በዳኞች አማካኝነት አሸናፊ እና ተሸናፊ ይነገር እና በጋራ ባህላዊ ጭፈራጨፍረው ይለያያሉ፡፡

የተወዳዳሪ ቡድኖች ቀጥሎ ያለውን ገፀባህሪ በጨዋታቀወ ወቅት ያሳያሉ

- ✓ አንዱ ቡድን ባሕርይይ ያለው ማኅበረሰብ አካባቢያዊ የአኗኗር ዘይቤ የሚያንፀባርቅ ጭውውት ማለትም የሰላም፣ ፍቅር፣ መተባበር ባህልን የሚኖሩ ማህበረሰቦች ለዕድገት እና ለልማት መሠረት መሆናቸውን የሚያሳይ
- ✓ ሁለተኛው በተቃራኒው ፀብ፣ ጭቅጭቅ፣ አለመረዳዳት፣ እና የመሳሰሉ የአኗኗር ዘይቤዎችን የሚኖሩ ማህበረሰቦች የሚያስከትለውን ችግር እና ፀረ ልማት የሚያሳይ ጭውውት እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ የሁሉም ቡድኖች ጨዋታውን ከጨረሱ በኋላ የባህላዊ ዘፈን በስልክዎ ወይም በቴፕ ሪከርደር በመክፈት ይህን ካላገኙ ደግሞ ሕፃናት ራሳቸው የሚያውቁትን ባህላዊ ዘፈን በመዝፈን እንዲጨፍሩ ያድርጓቸው
- ✓ በመጨረሻም ከጨዋታዎቻቸው ያገኟቸውን ጭብጦች እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው ፤እርስዎም ተጨማሪ ሀሳቦችን ይንገሯቸው፡ ፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ኳስ ፣ ባህላዊ አልባሳትን የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ በስልክ ወይም ቴፕ ሪከርደሮች የተቀረፁ ባህላዊ ዘፈኖች

**የምዘና ስልት:** በየተግባራቶቻቸው ያላቸውን ንቁ ተሳትፎ መመዘን፣ ተግባብቶ የመሥራት ልምዳቸውን መገምገም፣ ሀሳብን አደራጅቶ የመናገር ልምዳቸውን መገምገም፣

**የቃል ጥያቄ:** ከጨዋታው ምን ተማርሽ/ተማርክ፣ የትኛውን ቡድን ወደድክ/ሽ ለምን፣ የጨፈራችሁት በምን አይነት ማህበረሰብ ባህል ነው፣ በጨዋታው የትኛው የአከል ክፍል ይጠነክራል...

## ተግባር አራት፡ በፕሮጀክት መማር (7 ክፍ ለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ራስን መቻል፣ የቃላት ክምችት፣ የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣ ቁጥሮችን መቁጠር እና መደርደር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በፕሮጀክት፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣

**የመምህር ሚና:** መምህርት ህፃናቱወደፕሮጀክት ስራ ከመግባታቸው በፊት ለማነቃቂያ የሚሆን የሚከተሉትን እንካስላንትያ ጨዋታዎች እንዲጫወቱ ያድርጓቸው ፤ ሕፃናት የሚውቋቸው ተጨማሪ ካሉ እንዲጫወቱ ይፍቀዱላቸው:: በመቀጠል ክፍለ ጊዜው የፕሮጀክት ሥራ መሆኑን ይንገሯቸው::

### እንካስላንቲያ አንድ

| | |
|---|---|
| እንካ እንካስላንቲያ | እንካስላንቲያ |
| በምንቲያ | በምንቲያ |
| በወረቀት | በዳኛ ምን አለ በዳኛ |
| ምን አለ በወረቀት | ፍቅርና ሰላም |
| አምስት እና ሁለት ይሆናሉ ሰባት | ይጠቅመናል ለኛ |

- ✓ ቀጥሎ ከ 1 20 ያሉ ቁጥሮችን ከማወዳደሪያ ምልክቶች ጋር በካርቶን ወይም ከወፍራም ወረቀት እንዲያዘጋጁ አስፈላጊውን ቁሳቁስ በመስጠት ያግዟቸው ቀጥሎ የሰሩትን ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻቸው በማቅረብ የማወዳደሪያ ምልክቶችን ተጠቅመው የሰሩትን ቁጥር ያወዳድሩ የመለማመጃ ደብተራቸውን ገጽ በመጠቀም ቁጥሮችን ያወዳድሩ::

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ካርቶን፣ ወፍራም ወረቀት፣ መቀስ(የፕላስቲክ)፣ እንደየአካባቢዎ ለተግባሩ የሚመረጥ አካባቢያዊ ቁሳቁስ ይጠቀሙ፣ የመለማመጃ ደብተር፣ ወረቀት...

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (የማወዳደር እና የመለየት አቅማቸውን መመዘን)፣

**የቃል ጥያቄ** (ከ 1 — 20 ያሉ ቁጥሮችን ከትልቅ ወደ ትንሽ ደርድሩ ፤ የፀረሰላም መገለጫ ቃላቶችን ዘርዝሩ)

**የፅሁፍ መጠይቅ:** ቁጥሮችን በምልክት እንዲጣወዳድሩ መስጠት፣ አሃዞችን በፊደል እንዲጽፉ ማድረግ ( ምሳሌ 1 አንድ...)

## ተግባር አምስት: ተረት(4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማወዳደር፣እቅድ፣አካባቢ፣ስዕል፣ሞዴል፣ እንስሳት፣ቁጥር፣ሽልማት፣ሞራል፣ስሜት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት ፣በትረካ፣በገለፃ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ተግባር:** መምህር ቀጥሎ የቀረበዉን ተረት እርስዎ ካነበቡ በኋላ የተረቱን ጭብጥ በስዕላዊ መግለጫ በትልቅ ወረቀት በመሳል ህፃናቶች የተረዱትን እንዲገልፁ ያድርጓቸዉ:: በመቀጠል ተረቱን ለማዳመጥ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸዉና በፀጥታ እንዲያዳምጡዎት ያድርጉ በመካከል የህፃናቶችን ግምትና እንዳስፈላጊነቱ ማብራሪያ ይስጧቸዉከተረቱ በኋላ ተረቱን በቃል እንዲናገሩ በስዕል እንዲገልጹ የተቀመጠውን ክፍለ ጊዜ ከፋፍለው ይጠቀመ

### ሁለቱ ጓደኛሞች

ጫልቱና ጠይባ በአንድ ሰፈር የሚኖሩ ጓደኛሞች ሲሆኑ ሁለቱም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ሶስት ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ ጫልቱ በጣም ጨዋታ የምትወድ ከትምህርቷ ዉጭ ብዙ ጊዜዋን በጨዋታ የምታሳልፍ ልጅ ናት፤ ጠይባ ደግሞ ከእንቅልፏ ስትነሳ ጀምራ እስከ ማታ ድረስ የምትሰራቸዉን ስራዎች በማቀድ ስታከናዉን ትዉላለች፤ ታዲያ አንድ ቀን መምህራቸዉ የቤትና የዱር እንስሳቶችን በመለየት አካባቢያዊ በሆነ ቁሳቁሶች ተጠቅመዉ ስዕሎችን/ ሞዴሎችን ሰርተዉ እንዲመጡ የፕሮጀክት ስራ ትሰጣቸዋለች፤ ጫልቱ የተሰጣትን የቤት ስራ ሳትሰራ ሙሉ ጊዜዋን ስትጫወት ስለዋለች ማታ ደክሟት ተኛች፤ ጠይባ ግን የተሰጣትን የቤት ስራ ከትምህርትቤት ስትመለስ በመጀመር አስፈላጊ ቁሳቁሶችን እንደየ እንስሳት ፀጉር፣መቀስ፣ከለር፣ካርቶን፣ማጣበቂያ ወዘተ. ከቤቷና ከአካባቢዋ በመሰብሰብ ሶስት የዱር እንስሳቶችን (ነብር፣ አንበሳና ቀጭኔ) ሁለት የቤት እንስሳቶችን(ዶሮና ድመት)በድምሩ አምስት የቤትና የዱር እንስሳቶችን በመስራት በጠዋት ተነስታ ወደት/ቤት ሄደች፤ ጫልቱ ግን ጠዋት ስትነሳ የቤት ስራ እንደተሰጣት በማስታወስ ለመስራት ስትሞክር ረፈደባት ከዚያም እየሮጠች ወደት/ቤት ስትደርስ ዘበኛዉ ረፍዷል አላስገባሽም ሲላት እያዘነች ወደቤቷ ተመለሰች፤ጠይባ የሰራችዉ ስራ ከክፍሉ ህፃናቶች አንደኛ በመሆን ሽልማትና ሞራል ተሰጣት፤ጫልቱ በጣም መሳሳቷ1 ባትና እንደ ጓደኛዋ ጠይባ መሆን እንዳለባት ስለተማረች ከዚያን ቀን ጀምሮ ተግባሯን በፕሮግራም የምታከናዉን ጎበዝ ልጅ ሆነች፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተረቱን ፅንሰሀሳብ የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት:** የቃልጥያቄ(ጓደኛሞቹ ማንናማን ይባላሉ?የዕለት ተግባራቶቿን በእቅድ የምታከናዉነዉ የትኛዋ ናት?ጠይባ ስንት የቤትና የዱር እንስሳቶችን ሞዴል አዘጋጀች? በትኞቹ በቁጥር ይበልጣሉ? ሞደሉን ለመስራት ምንምን ቁሳቁሶችን ተጠቀመች?ጫልቱ ከት/ቤት የቀረችዉ ለምንድን ነዉ? ትክክል ነዉ ወይስ ስህተት?) ሀሳብ የማደራጀት አቅማቸዉን መገምገም

## አራተኛ ሳምንት

### ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ ፡ 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

- ✓ ዉስብስብ ስሜቶችን ይረዳሉ፤
- ✓ ስሜታቸዉን በትህትና ይገልፃሉ፤
- ✓ ከቅርብ አካባቢያቸዉ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ሠላማዊ ግንኙነት ይመሰርታሉ ፤
- ✓ የተለያዩ ነገሮችን በመያዝ ፣ በመምታትና በመወርወር ተግባር ላይ ይሳተፋሉ፤
- ✓ የሙዚቃ ምትን ተከትለዉ ይጨፍራሉ፡፡
- ✓ ድርብ ቅጥን ይሰራሉ፤
- ✓ ሠላምን የሚያንፀባርቅ ጭውውት ይሰራሉ፤

**ንዑስ ይዘቶች:** ማኅበራዊ ግንዛቤ ፣ ራስን መግለጽ ፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር ፣ ቅጥ ፣ ጥበባዊ እሴቶች

## ተግባር አንድ: ወይይት

### ወይይት አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማህበራዊ ግንኙነት፣ጥበባዊ እሴቶች፣ ብሄርብሄረሰቦች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በወይይት፣በጥያቄና መልስ፣በገለፃ

**የመምህር ተግባር:** መምህር ይህ የሳምንቱ የመጀመሪያዉ ቀን ስለሆነ ህፃናቶች ለማነቃቃት ያክል ቅዳሜናእሁድ ምን እንዳከናወኑ ለጓደኞቻቸዉ እንዲያወሩ ያድርጓቸዉ፡፡

- ✓ ህፃናቶችን በትናንሽ ቡድን(4 6 ብዛት) ያደራጇቸዉ
- ✓ የተለያዩ ብሄርብሄረሰቦችን ማህበራዊ ግንኙነት(በለቅሶ፣በሰርግ፣በእድርወዘተ.) የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ የቻሉትን ያክል በትልቅ ስዕል ያዘጋጁ/የሚያገኙ ከሆነ በኮምፒዉተር/ ሌሎች ስክሪኖች ያሣዩአቸዉና የተረዱትን እንዲናገሩ ድርጓቸዉ
- ✓ ህጻናቶች በአካባቢያቸዉ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች(ለቅሶ፣ሰርግ፣ሽምግልና፣ማህበር፣እድር ወዘተ.) የሚከናወኑ የተለያዩ ተግባራቶችን በየቡድናቸዉ አንድ አንድ ማህበራዊ ርዕሶችን በማከፋፈል እንዲወያዩ ያድርጓቸዉ
- ✓ ከጨረሱ በኂላ ከየቡድናቸዉ አንድ ህፃን በመነሳት እንዲያቀርብ እድል ይስጧቸዉ በቀጣይ ሁሉም ህፃናት በየተራ እንዲያቀርቡ ያድርጉ
- ✓ ማህበራዊ ግንኙነትን ለመመስረት በመሰረታዊነት ሰላም አስፈላጊ እንደሆነ፣ህፃናቶች በአብሮነት የሚያከናዉኗቸዉ ተግባራቶች የማህበራዊ ግንኙነት አካል መሆናቸዉንና ተያያዥ ጭብጦችን ያስገንዝቧቸዉ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት: ምልከታ** (የወይይት ስልት ብስለታቸዉን በማዳመጥ መመዘን) ፣የቃል ጥያቄ በአካባቢያቸሁ ህብረተሰቡ በጋራ የሚያከናዉናቸዉ ተግባራች ምንምን ናቸዉ? በስዕሉ ላይ ከምታዩአቸዉ ማህበራዊ ግንኙነቶች ዉስጥ በእናንተ ከእናንተ አካባቢ ህበራዊ ግንኙነት ጋር የሚመሳሰለዉ የትኛዉ ነዉ? ስንቱ ይመሳሰላሉ? እናንተ ከጓደኞቻችሁ ጋር ምንምን ማህበራዊ ግንኙነቶችን(የአብሮነት ተግባራቶችን) ታከናዉናላችሁ?

### ወይይት ሁለት ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማዘን፣መከፋት፣መደሰት፣ ጥበባዊ እሴቶች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በወይይት፣በጥያቄና መልስ፣በገለፃ

**የመምህር ተግባር:** መምህር የተለያዩ ስሜቶችን የሚያሳዩ ስዕላዊ መግለጫ ሂደታዊ ወይም በተረት ገፅታ መልክ (ሳቅ፣ለቅሶ፣ደስታ፣መከፋት/ማዘን ወዘተ.) በትልቅ ወረቀት በማዘጋጀት ለልጆች የሚታይ ቦታ ላይ ይስቀሉላቸዉ፡፡ በመቀጠልበትናንሽ ቡድን በማደራጀት ስዕሎቹን ተመልክተው የስሜቶች ምንነት እና ስሜቶቹ ሰዎች በምን አይነት ሁኔታ ዉስጥ እያሉ እንደሚያንፀባርቋቸዉ እንዲወያዩ ያድርጓቸዉ፡፡ከጨረሱ በኋላ ከየቡድናቸዉ አንድ ህፃን በመነሳት የተወያዩበት ሀሳብ ስዕላዊ መግለጫዉን በመጠቀም እንድታቀርብ/ብ ያድርጉ

ቀጥሎ እንሱ አሳዛኝ እና አስደሳች ታሪክ አዘጋጅተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡና የቃላት ክምችታቸውን እንዲያሰፉ እድሉን ያመቻቹ፣ ሲጨርሱ ሁሉም የራሱን ደስተኛ ቤተሰብና ጓደኛ በስእል እንዲገልጽ ያበረታቱ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የሰዉ የተለያዩ ስሜቶችን የሚያሳይ የትረካ ስዕላዊ መግለጫ፣እርሳስ፣ወረቀት፣ ደብተር ፣ከለር…

**የምዘና ስልት ፡ ምልከታ** (ነገሮችን ተመልክተዉ ትርጉም የመስጠት አቅማቸዉን መመዘን)

**የቃል ጥያቄ** (የስዕሉን የመልዕክት ታሪክ ተርኩ?ምንምን አይነት ስሜቶችን ተመለከታችሁ? በምን በምን አይነት ሁኔታ ይንፀባረቃሉ?) የምንከፋው ምን አይነት ሁኔታ ሲያጋጥመን ነው ፣ አንተ/አንቺ ሰው አስከፍተሽ/ህ ታውቂያለሽ/ታውቃለህ፣ ሰውን ስናስከፋ ምን መጠየቅ አለብን ….

## ተግባር ሁለት: የክፍል ውጭ ጨዋታ

### ጨዋታ አንድ (3 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት** ፡ ራስን መግለጽ ፣ ማኅበራዊ ሕይወትን መገንዘብ ፣የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣ የጥበባት ሥራዎች፣ሰላም፣ፍቅር፣ፀብ፣ይቅርታ

**የማስተማሪያ ዘዴ** በጨዋታ፣ በገለፃ፣በማሳየት፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና: መምህር** ክፍለ ጊዜው የክፍል ውጭ ጨዋታ እደሆነ ይንገሯቸው እና እንደተለመደው በሰልፍ ይዘዋቸው ይውጡ ፤ ከዚያም የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውኑ ፡፡

- ✓ እንደ የብዛታቸው በትላልቅ ቡድን (7 8 ብዛት) በራሳቸው ተስማምተው እንዲመዳደቡ ያድርጉ (በቡድን ምሥረታው ሂደት የፆታ እና የቁጥር ንፅፅሩ እንዲስተካከል ያድርጉ)
- ✓ በየቡድናቸው በአንድ መንደር ውስጥ ስለሚኖሩ ሰዎች የሰላም አለመኖር ሁኔታ የሚያደርጉትን ውይይት ገፀ ባሕርይይ እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎ የሚነገሩቸውን ታሪክ መነሻ በማድረግ ህፃናቱ በየቡድናቸው አንድ መንደር ይሆኑና አንዱ ቡድን ልጆች ሲጫወቱ ሌሎች ሲረብሹ፣ግማሾቹ መሬት ሲያርሱ ሌሎች የተከሉትን ሲነቅሉና ሲጣሉ በመሃል ሰላም ፈላጊዎች ሄደው ለወረዳው ተጥታ አካል አመልክተው ሁሉም ስብሰባ ይቀመጣሉ ችግራቸውን ይወያያሉ ይቅርታ ይጠያየቃሉ ቀጥሎ በሰላም አካባቢያቸውን ያለማሉ ፣አብረው ይጫወታሉ፡፡
- ✓ ለምሳሌ እንዲሆን ይህህንን ታሪክ ይንገሯቸው እና ገፀ ባህሪዎችን ለማግኘት ይረዳቸዋል ይተርኩላቸው በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ሁልጊዜ የሚጣሉ፣ የሚደባደቡ፣ ምንም ዓይነት የጋራ ማኅበራዊ ሕይወት የሌላቸው ሰዎች ነበሩ፡ ታዲያ በመካከላቸው አንዳንድ ሰላምን የሚፈልጉ ሰዎች ይኖሩ ነበር እና ዘወትር እንደተረበሹ ይኖራሉ፤ አካባቢያቸውን በጋራ ስለማያፀዱ፣ የተቸገረን ስለማይረዱ በፅዳት እጥረት ምክንያት ለሚያጋልጡ የተለያዩ በሽታዎች ከልጆቻቸው ጋር ይጋለጣሉ፤ ልጆቻቸውም ከጎረቤት ልጆች ጋር በጋራ አብረው መጫወት እንዳይችሉ ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸዉ ይከለክሏቸዋል ፤ ይህ ሁኔታ የሰለቻቸው ሰላማዊ ሰዎች አንድ ቀን በአካባቢው አስተዳዳሪ አማካኝነት የሰላም አለመኖር ሁኔታውን በተመለከተ እንዲያስተካክልላቸው ስብሰባ እንዲጠራቸው ያደርጋሉ፤ በዚያ ላይ ሁሉም የመንደሩ ነዋሪዎች ይገኛሉ፤ በስብሰባው ላይ አስተዳዳሪው በመንደሩ ውስጥ

የተፈጠረውን የሰላም አለመኖር ምክንያት ተራ በተራ እንዲናገሩ ካደረገ በኋላ ለችግሩ መፍትሄ ነው የሚሏቸውንም ጭምር እንዲናገሩ ዕድል ይሰጣቸዋል፤ በጋራ የማስተካከያ ሀሳብ ከወሰዱ በኋላ ችግሩን በሚፈጥሩ ሰዎች ላይ ለቀጣይ እንዲፈታ በመምከር እና በአብሮነት፣ መረዳዳት፣ መቻቻል፣ ስሜትን የመቆጣጠር ስብዕና መኖር እንዳለባቸው በመምከር እና ጥፋተኞችን ቅጣት በመቅጣት ይለያያሉ። ከዚያን ቀን ጀምረው በሰላም በፍቅር በመተባበር ከልጆቻቸው እና ከጎረቤቶቻቸው ጋር አብረው መኖር ጀመሩ።

መምህር ይህን ከጨረሱ በኋላ የጨዋታውን ጭብጥ ይጠይቋቸው፤ እርስዎም ተጨማሪ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡ በተቀመጠለት ክፍለ ጊዜ ህፃናቱ በተራ በተራ እንዲሰሩ ያርጉ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የትላልቅ ሰዎች አልባሳት፣ የማኅበረሰቡን ስብሰባ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት፡** በጨዋታው ውስጥ የሚኖራቸውን ንቁ ተሳትፎ በምልከታ መመዘን ፣

**የቃልጥያቄ:** (የመንደሩ ሕፃናት ለበሽታ የሚጋለጡት ለምን ነበር? ስብሰባውን ይመራ የነበረው ሰው ሀላፊነቱ ምንድን ነበር ? እናንተ የትኞቹን ሰዎች መሆን ትፈልጋላችሁ ? ለምን ?) ሰዎች በጋራ በሰላም ለመኖር ምን ማድረግ አለባቸው፣ስናጠፋ ምን ማድረግ አለብን…

## የክፍል ውጭ ጨዋታ ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማኅበራዊ ሕይወትን መገንዘብ፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣ራስን መግለጽ ፣ ማሸነፍ ፣ መሸነፍ ፣ መጣላት ፣መታረቅን ፣ መቻቻል ፣በጨዋታ ተራ መጠበቅን

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ ገበለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና:** መምህር ለሕፃናት ክፍለ ጊዜው የክፍል ውጭ ጨዋታ እንደሆነ ይግለፁላቸው

- ✓ ያታን እና የቁጥር ንፅፅርን ግምት ውስጥ አስገብተው በትናንሽ ቡድኖች እንዲከፋፈሉ በማድረግ የሚከተሉትን ጨዋታዎች እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፤
- ✓ የጨዋታው ጭብጥ ሕፃናት ማሸነፍ እና መሸነፍ ፣ መጣላት እና መታረቅን ፣ መቻቻል እና በጨዋታ ተራ መጠበቅን የመሳሰሉትን አወንታዊ ባሕርይ እንዲያጎለብቱ ማስቻል ነው ፡፡

**ጨዋታ ቁጥር አንድ:** የእግር ኳስ ጨዋታ ( በሁለት ቡድኖች ይተገበራል)

**ጨዋታ ቁጥር ሁለት:** መሀረሜን ያያችሁ አተገባበር

- ✓ ሕፃናት ክብ ሠርተው ይቀመጣሉ
- ✓ አንድ ሕፃን መሀረም ይዛ/ዞ በክብ ዙሪያ ትዞራለች
- ✓ መሀረሜን ያያችሁ እያች/የሚዞረው/የምትዞረው ሕፃን ከአንዷ/ዱ ሕፃን ልጅ ከኋላ አስቀምጣባት ትሮጣለች፤
- ✓ የተጣለባት/ችበት ሕፃን አሯሩጣ መሀረም የጣለችባትን ሕፃን በመሀረሙ ከመታቻት የተመታችው ሕፃን መሀል ላይ ትቀመጣለች/ ይቀመጣል፤ ተሸናፊ ትሆናለች / ይሆናል በመሀረሙ ካልመታቻት/ካልመታት ተሸናፊ አይሆንም/አትሆንም እንደሌሎች ተቀምጣ/ጦ ጨዋታውን ይቀጥላል፤

- ✓ በዚህ ሁኔታ መጨረሻ ላይ አሯሩጣ/ጦ የመታች/የመታ ሕፃን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል፡፡

**ጨዋታ ቁጥር ሦስት:** ኳስ ቅብብሎሽ ( በሁለት ቡድኖች ይተገበራል ) ውድ መምህርት/ር እርስዎ በአካባቢዎ በልጆች ዘንድ የተለመዱ ውድድራዊ ጨዋታዎችን በተጨማሪ እንዲጫወቱ በማድረግ በመካከላቸው የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን፣ ግጭቶችን ፣ አለመቻቻልን ፣ በራሳቸው እንዲፈቱ ዕድል ይፍጠሩላቸው ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** መሀረም ፣ ኳስ ፣ ለጨዋታው የሚያስፈልጉ አካባቢያዊ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** በጨዋታው ሂደት የሚኖራቸውን ውጤታማነት ከመዳበር ገጽታዎች አንፃር በምልከታ መመዘን ፣ **የቃል ጥያቄ** ( በጨዋታው ውስጥ ምንምን ቁሳቁሶችን ተጠቀምን፣ ጨዋታውን ለማሸነፍ ምንምን ማድረግ ይጠበቅ ነበር ስንት ጨዋታዎችን ተጫወታችሁ፣ስትሸነፉ ሆነ ስታሸንፉ ምን ተሰማችሁ፣ በጨዋታ ውስጥ ግጭት ሲፈጠር እንዴት መፍታት እንችላለን....

## ተግባር ሶስት: መዝሙር (7 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማኅበራዊ ሕይወትን መገንዘብ ፣ራስን መግለጽ ፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣ የጥበባት ሥራዎች፣ሰላም፣ፍቅር

**የማስተማሪያ ዘዴ** በመዝሙር ፣በገለፃ፣ሰርቶ በማሳት፣በጥያቄነታ መልስ

### የመምህር ሚና

መምህር! ለሕፃናት ክፍለጊዜው የመዝሙር እንደሆን ይንገሯቸው፡፡ በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድን እንዲከፋፈሉ ያድርጓቸው፡፡ ለሚወዷቸው ጓደኞቻቸው የፍቅር ፣ የሰላም እና የመዋደድ መዝሙር በመፃፍ እንዲዘምሩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠል ቀጥሎ የቀረበውን በመዝሙር አጠናን ስልት መሠረት ያስጠኗቸው፡፡ከዚያም በየቡድናቸው ለየጓደኞቻቸው ተራ በተራ በአካላዊ እንቅስቃሴ እየተወኑ/ እያሳዩ እንዲዘምሩላቸው ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም የራሳቸውን ፍቅር፣ ሠላም የሚገልፁ የስጦታ መዝሙሮችን በመፍጠር እንዲዘምሩ ዕድል ይስጧቸው ፡፡

### መዝሙር ቁጥር አንድ ( 4 ክፍለ ጊዜ)

**ጓደኞቼን እኔ እወዳቸዋለሁ**

ጓደኞቼን እኔ እወዳቸዋለሁ፣
ሁሌም ትምህርት ስሄድ እጠራቸዋለሁ፡፡
በዓላት ምርቃት ድግስም ሲኖረን፣
ስጦታ የፍቅር እንሰጣጣለን፡፡
ስንጣላም ወዲያው እንታረቃለን፣
በመካከላችን ማንም ሰው አይገባም፡፡
እኛ ኅበዞች ነን ትጉ እና ታታሪ፣
ለነገ የምንሆን ሀገራችን አኩሪ፡፡

ዘር ቀለምም ቢሆን አይለየንም እኛን፣
የአንድነት ተምሳሌት የኢትዮጲያ ልጆች ነን፡፡
እኔ እሰጥሻለሁ ይሄን ጓደኛዬ፣
ለስጦታ የሚሆን ይድረስልኝ ብዬ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ከመዝሙሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች( ምሳሌ የመህበረሰቡን በጋራ የመኖር እሴት የሚያሳዩ) ለመዝሙር ማዳመጫ የሚሆን ኤልክትሮኒክስ ማሳሪያዎች...

**የምዘና ስልት:** በምልከታ በመዝሙሩ ውስጥ ያላቸውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከት መመዘን፣ **የቃል ጥያቄ** ( ከጓደኞቻችሁ ጋር ያላችሁ ግንኙነት እንዴት ነው፣ ከማህበረሰቡ ጋር ከምንጠራራበት ድግሶች መካካል የትኞቹ ይጠቀሳሉ፣ ስንጣላ ምን ማድረግ አለብን....

## መዝሙር ቁጥር ፡ ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ማኅበራዊ ሕይወትን መገንዘብ ፣ራስን መግለጽ ፣ መዳበር ፣የጥበባት ሥራዎች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር መዝሙሩን በመዝሙር አዘማማር ስልት ተከትላው ለእንቅስቃሴ በሚመች መልኩ እንዲዘምሩ ያድርጉ

### ለውድ ጓደኞቼ

በጧት ተነስቼ ከእንቅልፌ ነቅቼ ፣
ፊቴንም ታጥቤ ቁርሴንም በልቼ ፣
ዩኒፎርም ለብሼ ቦርሳየን አንግቼ ፣
እጠራችኋለሁ ውድ ጓደኞቼ ፡፡
ግራ መስመር ይዘን ልንሄድ ትምህርት ቤት፣
ጉዞ እንጀምራለን ዕውቀት ለመገብየት ፣
በጣም እናምራለን ስንጓዝ ሕፃናት ፡፡
ፍቅር እና ሰላም ሀ ሁ ሆሄ ጭምር ፣
ቁጥሮችን ጨምረን በአንድ ላይ ስንማር ፣
ውለን እንመጣለን ወደ ትውልድ መንደር ፡፡

መምህርት መዝሙሩን ዘምረው ከጨረሱ በኋላ ከመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ ወይም እርሶ ከታች የተዘረዘሩትን ስዕል በትንንሽ ፍላሽ ካርድ/በምስል በማሳየት ( አበባ ፣ ልብቅርፅ ፣ ወፍ ፣ የተለያዩ የልብስ የስጦታ ሥዕሎች) ፣ በመመልከት የምን ሥዕሎች እንደሆኑ እና ብዛታቸው ስንት እንደሆኑ እንዲናገሩ <u>በመጨረሻም እራሳቸው የመረጡትን አስመሥለው በመሣል</u> ቀለም በመቀባት ለቤተሰባቸው፣ጓደኞቻቸው ለጎረቤቶቻቸው እርስበርስ እንዲሰጣጡ ያድርጉ ፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ፊደላት እና ቁጥሮችን የያዙ የሥዕል ካርዶች እርሳስ ፣ ቀለም፣ እርሳስ ፣ ቀለም ወረቀት ፣ የመለማመጃ ደብተር እስክርቢቶ ፣ ወፍራም ወረቀት ፣

ማጣበቂያ/ሙጫ…

**የምዘና ስልት፡ ምልከታ** (የተሰጧቸውን ተግባራት በትክክል ማከናወናቸውን መከታተል፣ **የቃል ጥያቄ** ( በመዝሙሩ ውስጥ ያሉ ፊደላቶች እነማን ናቸው፣እሰቲ ከአንድ እስ ሃያ ያሉትን ቁጥች በቅደም ተከተል ጥራ/ጥሪ፣ለማን ስጦታ ሰራችሁ፣ምን አይነት ስጦታ ነበር

በመዝሙሩ ውስጥ ህፃናት ከእንቅልፋቸው ሲነሱ ጀምረው ከትምህርት ቤት እስከሚመለሱ ድረስ ያለውን ተግባር በቃል ግለፁልኝ)፣ የሐሳብ ጭብጦችን አቀናጅቶ የመናገር አቅማቸውን መመዘን

## ተግባር አራት፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ ( 5 ክፍለ ጊዜ )

**ቁልፍ ቃላት፡** ህግ፣ እና ደንብ ፣ማቀበል፣ መስጠት፣ማኅበራዊ ሕይወትን መገንዘብ ፣ራስን መግለጽ፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር ፣የጥበባት ሥራዎች፣የቃላት እውቀት

**የማስተማሪያ ዘዴ** በጨዋታ፣ በገለፃ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡**

- ✓ መምህር ለሕፃናትን ክፍለጊዜው የክፍል ውስጥ ጨዋታ እንደሆነ ይንገሯቸው
- ✓ ለማነቃቂያ የሚሆን የመረጡትን መዝሙር መርጠው እንዲዘምሩ ያድርጓቸው፤
- ✓ እርሶ በክፍል ውስጥ እና በቤት ውስጥ ስለሚፈፀሙ ህጎች እንዲሁም ህግ ስላላቸው ጨዋታዎች ገለፃ ያርጉላቸው
- ✓ በመቀጠል የሚያውቁትን ነህግና ደንብ እንዲፅፉ ያድርጉ፤
- ✓ ከጨረሱ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ካደረጉ በኋላ ግድግዳ ላይ እንዲለጥፉ ያድርጓቸው ፤
- ✓ ቀጥሎ አራት አባላት የያዘ ቡድን አደራጅተው ቀላል ቁሶችን የመቀበል እና የማቀበል ጨዋታ እንዲጫወቱ ያድርጉ ጨዋታውን ከመጀመራቸው በበፊት እርስ በእርስ ተገቢ የሆነ የሰላምታ አሰጣጥን እንዲያሳዩ ማድረግ ቀጥሎ
- ✓ አራቱ ህፃናት በመደዳ ራቅ ራቅ ብለው ይቆማሉ የሚቆሙበት ክብ ማክበብ ከዚያ ቀላል ኳስ በመስጠት እንዲቀባበሉ ማድረግ ኳስ የወደቀበት ከጨዋታው ይወጣል
- ✓ ህጉ ከክቡ የወጣና ኳሷን የጣለ ከጨዋታው ይወጣል፤በመጨረሻ የቀሩት አሸናፊ ይሆናሉ፡ ፡በዚህ መሰረት በተቀመጠው ክፍለ ጊዜ ጨዋታውን እየቀያየሩና ህግ እየነገሩ ሁሉም ህፃናት እንዲጫወቱ እድል መስጠት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** ለመጫወቻነት የሚያስፈልጉ ቀላል ቁሶች (ኳሽ፣ ሳጥን፣ ቦርሳ…፣ እርሳስ ፣ወረቀት …

**የምዘና ስልት ፡** የቃላት ክምችታቸዉን ከንግግሮቻቸዉ መመዘን፣ ትህትና፣ ፍቅር፣ ሰላምታ አሰጣጥ ሥርአታቸውን መገምገም፣ የቃል ጥያቄ መጠየቅ (ለምሳሌ ስንት የትምህርት ቤት እና የክፍል ውስጥ ህግና ደንቦችን ምንድናቸው፣ ተገቢ ሰላምታ እንዴት እንለዋወጣለን፣ ምን አይነት ጨዋታ ተቻወታቹ ፣ህጉስ ምን ነበር…


## ተግባር አምስት፡ የግል ተግባር (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ቅጥ፣ ብሄርብሄረሰብ፣ ጭፈራ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የክፍል ህግ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር ስራ፣በገለፃ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር ህፃናቶችን ቀጥሎ ያለውን ተግባ ለማሰራት ህፃናቱ በራሳቸው ተነስተው ወረቀት ፣እርሳስ ፣ከለር እና መቀስ በየተራ ከተቀመጠበት በስርኣት እንዲያወጡ ይንገሩ በዚህ ጊዜ የክፍል ህግን መጠበቅ አስፈላጊ ጉዳይ ስለሆነ በአግባቡ ይከታተሉ

- ✓ በመቀጠል እርሶ የተለያየ በሁለት ቅጥ/ንድፍ/ ሰርተው ያሳዩ እና ህፃናቱም የእርሶን ተከትለው እንዲሰሩ ፣በራሳቸው የፈለጉትን ንድፍ ቅ/ንድፍ እንዲሰ ያርጉ ምሳሌ( የሶስት ጎን፣አበባ፣አራት ማዕዘን… ቅርፅ ስለው ከለር መቀባት፣ቅርፁን ጠብቀው መቆራረጥ
- ✓ የተቆራረጡትን በሌላ ነጭ ወረቀት ላይ ንድፉን ጠብቆ መለጠፍ



- ✓ ሲጨርሱ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦችን ሙዚቃ /ዘፈን በስልክዎ /ሪከርዶች ይዘዉ በመምጣትና ለህፃናቶች በማሰማት የየትኛዉ ብሄረሰቦች ሙዚቃ እንደሆኑ ይንገሯቸዉ፤ በመቀጠል ህፃናቶችን ሙዚቃዎችን በማሰማት ተራበተራ የብሄረሰቦቹን ጭፈራ የሙዚቃዉን ምት በመከተል እንዲጨፍሩ ያድርጓቸዉ፤ እርስዎም አብረዋቸዉ ይጨፍሩ በዚህ እንቅስቃሴ በታቻለ መጠን ጡንቻዎቻቸው እንዲጠነክር በሚያስችል ምኩ ሁሉም እንዲሳተፍ ያርጉ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** መቀስ፣ወረቀት ነጭ/በለከለር፣ እርሳስ፣ቀለም፣፣ማጣበቂያ/ ሙጫ ፣በስልክ ወይም ሌሎች ሪከርደሮች የተቀረፀ የብሄርብሄረሰቦች ሙዚቃ

**የምዘና ስልት፤ የቃልጥያቄ** የምን ንድፍ ሰራሽ ፣ስራውን ስሰሩ የተገባራችሁት የክፍል ህግ ምን ነበር፣ ባለስንት ንድፍ ሰራችሁ፣…ስንት አይነት ጭፈራዎችን ጨፈራችሁ? ምን ስሜት ተሰማችሁ?)፣ምልከታ (በእንቅስቃሴዎቻቸዉ የሰዉነት ንቃታቸዉን መገምገም)

## ተግባር ስድስት፡ በስራ መማር (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** መረዳዳት፣ማህበራዊ ግንኙነት፣ሰላም

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣በተግባር ስራ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና ፡ መምህር ለህፃናቶች ስለሰላም የሚገልፁ ቃላቶችን በትልቅ ወረቀት ፅፈዉ ግድግዳ ላይ ይስቀሉላቸዉ፤ ከዚያም ቀጥሎ የቀረበዉን ሰላምን የሚያንፀባርቁ ጭዉዉት ካነበቡላቸዉ በኋላ ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲተዉኑ ያድርጉ፤ በመቀጠል ህፃናቶች ለቀጣይ ቀን ሲመጡ ወላጆቻቸዉን በመጠየቅ ሰላምን የሚያንፀባርቁ ጭዉዉቶችን በየግላቸዉ ይዘዉ እንዲመጡ በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

### ጭዉዉት

**አበበ፡** ጓደኛዬ ሀና የሰላምን ምንነትና ጠቀሜታ የቤትስራ ሰርተን እንድንመጣ መምህራችን ሰጥታን ነበር ምንድን ነዉ?

ሀና፡ ሰላም ማለት አብሮ መጫወት፣መረዳዳት፣ አለመጣላት፣ሲጫወቱ ተራመጠበቅ ማለት ነዉ

አበበ፡ ጓደኛዬ ሀና መረዳዳት ምንድን ነዉ

ሃና፡ መረዳዳት ማለት ከሰፈራችንና ታሞ የነበረዉን ጋሽአለሙን ታዉቀዉ የለም? እሱ ለመታከሚያ የሚሆን ገንዘብ ስላልነበረዉ የእኛ ቤተሰቦችና ሌሎች ጎረቤቶቻችን በጋራ ገንዘብ ሰብስበዉለት ታክሞ ድኗል አይደል? መረዳዳት ማለት ይህ ነዉ ጋሽአለሙ ባይታከም ኖሮ በጠና ይታመም ነበር ስለዚህ ይሄ ተግባር የሰላም መገለጫ ነዉ

አበበ፡ አሁን ገባኝ ሰላም ግን ለምን ይጠቅማል?

ሀና፡ ሰላም ከሌለ ሰዉ ከቤቱ አይወጣም፤ ስራ አይሰራም፤ብር አያገኝም፤ይጨናነቃል፤ጭንቀት ደግሞ በሽታ ያመጣል፤እኛ ትም/ቤት አንሄድም ስለዚህ ነዚህንሁሉእንዳናጣሰላም ይጠቅመናል

አበበ፡ አመሰግናለሁ ጓደኛየ ሀና አሁን ገብቶኛል የቤት ስራየን በሚገባ ሰርቼ እሄዳለሁ፡፡

ሀና፡ እኔም አመሰግናለሁ ጓደኛየ አበበ እኔና አንተም የሰላም መገለጫ መረዳዳትን ስለተገበርን ደስ ብሎኛል

የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡ የቻርትወረቀት፣ማርከር ከሰላምዊ አኗኗር ጋር ተያያዥነት ያላቸው/ ሰላማዊ ህብረተሰብና፣ጦርነት ያለበትን አካባቢ የሚያሳይ ስእል/ተንቀሳቃሽ ምስል….

የምዘና ስልት፡ የቃልጥያቄ(የሰላም መገለጫ ቃላቶች ምንምን ናቸዉ? ከጭዉዉቱ ምን ተማራችሁ? ሰላም ባይኖር ምን እንሆናለን፣ከጓደኞቻችሁ ጋር በሰላም ለመጫወት ምን ማድረግ አለባችሁ…፣ምልከታ፡ ሲጫወቲ/ሲተውኑ በአግባቡ ተመልክቶ እርማት መውሰድ..

# አምስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክፍለ ጊዜ /15 ሰዓት/

## አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ፡

- ✓ ከሌሎች ጋር አወንታዊ ግንኙነት ለማድረግ የግብረ ገብነት እሴቶችን ይተገብራሉ፡፡
- ✓ የፊደላትን በማጣመር ቃላትን ይመሰርታሉ፡፡
- ✓ ስለተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ አካባቢ ያብራራሉ፡፡
- ✓ የነገሮችን መገኛ ቦታ ይናገራሉ፡፡
- ✓ ነገሮችን በቀለም፣ በመጠን እና በቅርፅ ይለያሉ፡፡
- ✓ ባህላዊ ዘፈኖችን ከጭፈራ ጋር ፈጥረዉ ያሳያሉ፡፡

ንዑስ ይዘቶች፡ የግብረ ገብ እሴቶች፣ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ አካባቢ፣ የቦታ ግንዛቤ፣ የፊደላት ድምፅ ግንዛቤ፣ መለየትና መመደብ፣ ማገናኘት፣ ማያያዝና ተግባራዊነት

### ተግባር አንድ፡ መዝሙር (3 ክፍለጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡ የሥነ ምግባር እሴቶች፣ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ አካባቢ፣ አቅጣጫ መለየት፣ እቅድ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣በጥያቄና መለስ፣በገለፃ

**የመምህር ሚና**

መምህር ይህ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንደ መሆኑ ሕፃናት ቅዳሜ እና እሑድ ምን ምን እንደ ሠሩ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ለተወሰነ ደቂቃ ይፍቀዱላቸው፤ በመቀጠል ቀጥሎ የቀረቡትን መዝሙሮች እርስዎ ቀድመው በማንበብ ከተረዱ በኋላ በመዝሙር አዘማመር ሥርዓት መሰረት ያለማምዷቸው

በመጨረሻም ከመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ ወይም በወረቀት በመዝሙሩ ውስጥ የሚገኙ ቃላቶችን ( ንፋስ፣ ብርቅዬ፣ ውሃ፣ አፈር፣ ከላይ፣ ከሥር፣ ብር የመሳሰሉትን ) በመጠቀም ቀላል አረፍተ ነገር እንዲመሠርቱ ያድርጓቸው።

**መዝሙር አንድ**

**ርዕስ ፡ እኔ ጎበዝ ልጅ ነኝ**

እኔ ጎበዝ ልጅ ነኝ ሰው ሁሉ ሚወደኝ ፣
ለጓደኞቼ እና ለመምህራን ታማኝ ፣
ሲመክሩኝ እሺ የምል ሲያዙኝ የምታዘዝ ፣
ለቀኑ ውሎዬ እቅድን የምይዝ ።
አቅጣጫንም የማውቅ ከላይ ከታች ብዬ ፣
እጠቀመዋለሁ ለቀኑ ሥራዬ ።
ተፈጥሯዊ ንፋስ፣ ውሃ እና አፈር ፣
ሰው ሠራሽ መኪና መብራት እና ብር ።
እነሣለሁ እኔ በጠዋት ማልጄ ፣
ይህንን ለመማር ትምህርት ቤት ሄጄ
ቃላትን ለማንበብ ፊደልን ተምሬ ፣
ስሌትን ለማስላት ቁጠሮችን ቆጥሬ ፣
እታነጻለሁኝ በሥነ ምግባሬ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ፊደላትን የያዙ ፍላሽ ካርድ፣ ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካባቢን የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስል/ስእል፣ እርሳስ፣ ደብተር/ወረቀት…

**የምዘና ስልት: የቃል ጥያቄ** ተፈጥሯዊ አካባቢ የሚባሉት ምንምን ናቸው ? ሰው ሠራሽስ? ጎበዟ ተማሪ ጎበዝ የሆነችው ምንምን ስለምታደርግ ነው? እናንተ እንደ እሷ ትሆናላችሁ?

**የፁሁፍ መጠይቅ:** በፊደላቱ ቃላት እንዲመሰርቱ ማድረግ ( ምሳሌ ን ንፋስ፣ ብ ብርቅዬ….)

## መዝሙር ሁለት (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ተፈጥሮ፣ውበት፣እምነት፣እሴቶች፣ ተስፋ፣መንከባከብ

### ርዕስ ኢትዮጲያን እንወቅ

ኢትዮጵያ ምትባል ብዙ ህዝቦች ያሏት ፣
እኛ ህፃናቶች የምንኖርባት፣
ወጣት አዛዉንቱ በእርሷ ሚኮራባት ፣
ተፈጥሯዊ መስህብ ዉበት የደፋባት ፣
እንግዳ ተቀባይ የምታይ በአንድነት ፣
እምነት ዘር ሀይማኖት የማይከፋፍላት ፣
ይልቁንም ይሄ ግርማ ሞገስ ሆኗት ፣
ይሄዉ ትኖራለች አምሮባት የእኛ እናት ፡፡
እነዚህን ካወቅን እኛ ህፃናቶች ፣
ይሆናሉ መርህ የምግባር እሴቶች ፣
እኛ እንድንከተል የእናንተን መንገዶች ፣
በተግባር አሳዩን ወጣት አዛዉንቶች ፣
እንድንሆን እኛ የነገ ፍሬዎች ፣
ነን እና ለእናንተ የዛሬ አበባዎች ፣
ከተንከባከቡን የእናንተ ተስፋዎች ፡፡

መምህር ከብቃቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተጨማሪ መዝሙሮችን ያዘምሯቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** በመዝሙሩ ውስጥ ያሉ አካባቢያዊ ቁሳቁሶች…

**የምዘና ስልት:** **የጥያቄጥያቄ** ( ኢትዮጵያ ምን ዓይነት ሀገር ናት? አቅጣጫ ጠቋሚ ቃላቶችን ዘርዝሩ)፣ **ምልከታ** (ሲዘምሩ በማዳመጥ የመዝሙር አዘማመር ስልት ዕድገታቸውን መመዘን)

**የፁሁፍ መጠይቅ:** በአቅጣጫ ተቋሚ ቃላት ቀላል አረፍተ ነገር መስራት ፣አቅጣጫ እና ስእላዊ መግለጫን ማዛመድ ምሳሌ ከላይ፡ ቦርሳው ከላይ ነው….

## ተግባር ሁለት፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ (4 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የሥነ ምግባር እሴቶች፣ ተጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ነገሮች፣ የቃላት ድምፆችን መለየት፣ ማገናኘት / ማያያዝ

**የማስተማሪያ ዘዴ** በጨዋታ ፣ሰርቶ በማሳየት ፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና**

መምህር ሕፃናትን ለማነቃቃት እነሱንም ሆነ ወንበሩን እንዳይጎዱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በመንገር ከመቀመጫቸው ተነሥተው ባሉበት ቦታ እጃቸውን ወደ ላይ በማድረግ የእጅ ጣታቸውን በማፍታታት ክፍለ ጊዜውን ይጀምሩ፡፡ክፍለ ጊዜው የክፍል ውስጥ ጨዋታ መሆኑን ይንገሯቸው፤ ጸታንና ብዛትን ታሳቢ በማድረግ ሕፃናቱን በትናንሽ ቡድን እንዲከፋፈሉ ዕድል ይስጧቸው፡፡

በመቀጠል በየቡድናቸው ብዛት ያላቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን የመጀመሪያ የፊደል ሆሄያትን የያዙ የሥዕል ካርዶችን ያከፋፍሏቸው፡፡

ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ነገሮችን ሊገልጹ የሚችሉ የቃላቱን የመጀመሪያ ሆሄ የያዙ የሥዕል ካርዶችን ለምሳሌ፡ ሀ ሀገር፣ ለ ለውዝ ፣ መ መኪና፣ ሠ ሰው ... የሚሉ ቃላትን ወዘተ በመጠቀም ከፊት ለፊታቸው ያስቀምጡላቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ቡድን እኩል ብዛት ያላቸውን የሥዕል ካርዶችን ያከፋፍሏቸው፡

ቀጥሎ ሆሄያቱን በድምፃቸው እየጠሩ በየቡድናቸው ይለዩ ቀድሞ በስርአትእርስ በርስ ተረዳድተው እና ተደማምጠው ለይቶ የጨረሰውን ቡድን መዝግበው ደረጃ ይስጡና ያበረታቱ እና በዚህ ዙር አሸናፊን ይለዩ

ቀጥሎ ሁሉንም የሥዕል ካርዶች በመሰብሰብ በጠረጴዛ ላይ አዘበራርቀው ያስቀም ጧቸው ፤ በመቀጠል ሁለት ሁለት ህፃናትን በመጋበዝ ለጨዋታው ህግ በማውጣት አንዳቸው የተፈጥሮ አንዳቸው ሰውሰራሽ ምስሎችን እንዲለዩ ያድርጉ ከዚያም ወረቀቶቹን አንድ በአንድ በማንሣት ስማቸውን እየጠሩ ተፈጥሯዊ ይናገሩ በመጨረሻም ከመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ ወይም በደብተራቸውየተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሚጠቁሙ ፍደላት የመጀመሪያ ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ (ምሳሌ መ መኪና፣አ አበባ፣ ሰ ሰው....)

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የሥዕል ካርዶች ፣ የተለያዩ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ቁሳቁሶችን የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ፣ የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ ፣ወረቀት፣ደብተር...

**የምዘና ስልት ፡ ምልከታ፡** በቢድን ውስጥም ሆና በግል የቸወታውን ህግ ለመጠበቅ የሚደርጉትን ጥረት በመመልከት‹ **የቃል ጥያቄ** ምን ጨዋታ ተጫወትክ/ሽ፣ የተከተልነው ህግ ምን ነበር፣ ስንሸነፍ እንዴት መቀበል አለብን...፣ የፁሁፍ መጠይቅ”መ፣ ሸ፣ አ፣ በ፣ ቀ፣ ሰ... ) በሚሉት ፊደላት የሚጀምሩ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ የሆኑ ቃላቶችን እንዲመሠርቱ መጠየቅ፣ ስንት ቃላቶችን መሠረታችሁ በማለት መጠየቅ )

## የክፍል ውስጥ ጨዋታ ሁለት ( 4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ህግ፣ ማገናኘት ፣ የሥነ ምግባር እሴቶች፣ መመደብ፣መለየት፣ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ ፣በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና**

- ✓ በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድን እንዲከፋፈሉ ያድርጓቸው ፤ በቡድን ሲሰሩ መከተል የሚገባቸውን ስነምግባር እና የክፍል ህግ ከግምት እንዲያስገቡ እና ስለጨዋታው ገለፃ ይድርጉ
- ✓ በመቀጠል የሚከተሉትን ተግባራት ያሠሯቸው ፡፡ በአጠቃላይ የመጠንን፣ የቅርፅን እና የመጠንን ልዩነት መሠረት ያደረጉ ቁሳቁሶች ለመለየት እና ለመመደብ የሚያስችላቸውን ሁኔታ ለመፍጠር ለየቡድኑ የተለያዩ ቀለማትን የሚያሳዩ ብዛት ያላቸው ጎነ ሦስት፣ ጎነ አራትና ክብ ቅርፅ ያላቸው የሥዕል ካርዶች፣ የተለያየ መጠንና ብዛት ያላቸው ትናንሽ ኳሶች አዘጋጅተው ይስጧቸው:: (ለሁሉም ቡድኖች በእኩል መዳረሳቸውን ያረጋግጡ፤ ቁሳቁሶቹን በዓይነት በዓይነታቸው ልዩነታቸውን በምክንያታዊነት እየተናገሩ እንዲመድቡ ይዘዟቸው፤ በየቡድኖቻቸው የሠሯቸውን ተግባራት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ

ዕድል ይፍጠሩላቸው፡፡ በመጨረሻም በደብተር/በወረቀት፣ በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ የሚገኘውን የክብ፣ ጎነ ሦስት፣ ጎነ አራት፣ ኪዩች የመሳሰሉ ቅርፆችን በቀለም እንዲቀቡ እና በዓይነት በዓይነታቸው ምን ያክል ሥዕሎችን እንደቀቡ ቆጥረው እንዲፅፉ ያድርጓቸው

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን የያዙ የሥዕል ካርዶች፣ የተለያዩ ቀለማትን የሚያሳዩ ቁሳቁሶች፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ኳሶች፣ ባለ ቀለም እርሳስ፣ የመለማመጃ ደብተር ፣ወረቀት፣ ደብተር

**የምዘና ስልት: ምልከታ** (የልየታ እና ምደባ አቅማቸውን መመዘን)፣ **የቃል ጥያቄ** ያከናወናችሁት ተግባር ምን ነበር፣ እንዴት አከናወናችሁ፣ ምን ችግር ገጠማችሁ፣ እንዴት ፈታችሁት፣ምንምን ስዕሎች አላሉ ስንት ናቸው?... **የፅሁፍ መጠይቅ** ፡ ቅርፆቹን በደብተራቸው እንዲሰሩ እና ቆጥረው ቁጥርኑ እንዲጽፉ ማድረግ...

## ተግባር ሦስት: የፕሮጀክት ሥራ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የስምግባር እሴቶች፣ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ አካባቢ፣ አቅጣጫን የመለየት ግንዛቤ እና ቅርፃ ቅርፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ** በፕሮጀክት ሥራ ፣በገለፃ፣ በጥያቄና መለስ

**የመምህር ሚና**

- ✓ መምህር ለሕፃናት የፕሮጀክት ሥራ እንደሚሰሩ ይንገሩ ለማነቃቂያ የሚሆን በአካባቢያቸው የተለመደና ሕፃናት የመረጡት አንድ ባህላዊ ዘፈን እንዲዘፍኑ ለተወሰነ ደቂቃ ዕድል ይስጧቸው ቀጥሎ በትናንሽ ቡድን እንዲከፋፈሉ ዕድል ይስጧቸው፤
- ✓ በመቀጠል በየቡድናቸው ለጓደኞቻቸው ተራ በተራ ቅዳሜ እና እሑድ ምን ምን ተግባራትን እያከናወኑ እንዳሳለፉ እንዲወያዩ ምቹ ሁኔታን ይፍጠሩላቸው፤ ነገር ግን ስለ ቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ስለ አመጋገብ እና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን እንዲያወሩ አይፍቀዱላቸው፤
- ✓ እርስዎ ስለ ሕፃናት የዕረፍት ጊዜ ተግባራት የሚያወራ ተረት ወይም መዝሙር ካለዎት ይንገሯቸው፡፡
- ✓ በመጨረሻም ይህ የሳምንቱ የመጨረሻ ቀን እንደ መሆኑ ከቅዳሜ ጠዋት ጀምረው እስከ እሑድ ማታ ድረስ ያከናወኗቸውን ተግባራት በመመዝገብ በወረቀት ላይ ጽፈው እንዲያመጡ፤ እንዲሁም የፈለጉትንና የሚችሉትን ሁለት የአካባቢው ማህበረሰብ የሚገለገልባቸውን /አዲስ ፈጠራ ቅርፃ ቅርፅ በጭቃ ወይም በወረቀት ሠርተው እንዲያመጡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ሰኞ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ ለጓደኞቻቸው ቅዳሜ እና እሑድ ያከናወኑትን እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡ቀጥሎ የሰሩት ቅርጻቅርጽ ምን እንደሆና ፣ለምን እንደሚያገለግል፣ እንዴት እንደሰሩ እንዲያቀርቡ እድል ይስጡ እርስዎም የእያንዳንዱን እንቅስቃሴያቸውን አስፈላጊነት እንዲናገሩ በማድረግ ተጨማሪ ሐሳቦችን ይስጧቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ስለልጆች የዕረፍት ጊዜ ተግባራት የሚያወራ ተረት በስልክዎ ወይም ቴፕ ሪከርደር የተቀረፀ መዝሙር፣ የተቆራረጡ ወረቀቶች፣ የተቦካ ጭቃ ...

ወዘተ ቅርፆችንሲዘጋጁ የሚያሳይ ስእል /ምስል

**የምዘና ስልት:** የዕረፍት ጊዜ እንቅስቃሴያቸውን መገምገም፣ የዘገባ አጻጻፋቸውን መመዘን እና የታዘዙትን የቅርፃ ቅርፅ ሥራ በማየት መመዘን፡፡የቃል ጥያቄ፡ ምን ሰራክ/ሽ/ እንዴት ሰራሽ/ክ/ ከምን ሰራሽ/ክ፣ በእረፍት ቀን ምን አይነት አሳዛኝ /አስደሳች ነገር አጋጠማችሁ…

## ተግባር አራት፡ በሥራ መማር (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ፣ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ፣ መልካም እሴቶች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመስሎ ጨዋታ ማስተማር

**የመምህር ሚና:** መምህር! በመጀመሪያ ክፍለ ጊዜው በመስሎ ጨዋታ እንደሚማሩ እና መስሎ ጨዋታውን ሲጫወቱ እርስዎ በሚሰጧቸው ትዕዛዝ መሠረት መሥራት እንዳለባቸውና የሚጫወቱትን ቅደም ተከተላቸውን በመጠበቅ እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ የሕፃናቱን ብዛት በማየት ቁጥራቸውን እኩል መክፈል ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠልም የሚከተሉትን ተግባራት በመስሎ ጨዋታ እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡

- ✓ ሕፃናትን ስድስት ስድስት በማድረግ በቡድን በመክፈል እንዲዘጋጁ ማድረግ፡፡
- ✓ የተለያዩ ባህልን የሚገልጹ አልባሳትን እንዲለብሱ ማድረግ(ውድ መምህርት/ር ከዚህ ላይ ጥንቃቄ የሚያደርጉት ያላቸውን እንጂ የሌላቸውን እንዲገደዱ አይፈቀድም)፡፡ በመቀጠልም ባህላዊ ዘፈኖችን እንዲያሳዩ ያደርጉ፡፡
- ✓ የተወሰኑትን ቡድን ደግሞ ሱቅ በመክፈት የተለያዩ ሞዴሎችን ወይም ያለቁ ትናንሽ ዕቃዎችን (ለምሳሌ፡ ባዶ ክብሪት ዕቃ፣ ያለቀ የቅባት ዕቃ፣ ያለቀ እስክርቢቶ ወዘተ) የሱቅ ዕቃዎችን በሥርዓት በማስቀመጥ እና ማለትም በዓይነታቸው፣ በመጠናቸው፣ በቅርፃቸው ደርድረው በማስቀመጥ እንዲለዩ ያደርጉ፡፡
- ✓ የብር ኖቶችን ሞዴል (1 ብር፣5 ብር፣10 ብር…ወዘተ) እንደ አቅማቸው የብር ኖቶችን በመጠቀም በመልካም መግባባት መሸጥ እና መለወጥ እንዲያስመስሉ በማድረግ ከሌሎች ጋር ያላቸውን የግብረገብ እሴቶች እንዲያዳብሩና ነገሮችን በቀለም፣ በመጠን እና በቅርፅ መመደብና መለየት እንዲችሉ፣ ቁጥሮችንም በተወከሉባቸው የብር ኖቶች እንዲለዩ ያደርጉ፡፡
- ✓ የቀሩትን ቡድኖች ደግሞ የተለያዩ የሥዕል መሳያ ቁሳቁሶችን በመስጠት የሚችሉትን ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ከሆኑት መካከል በመሣል የሣሉትን ስም በመጻፍና ድምፁን አስመስለው እንዲጮሁ በማድረግና የሚገኙበትን ቦታ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ፡ የውሻ፣ የጅብ፣ የመኪና፣ የበር ድምፅ …ወዘተ የሕፃናትን ዕድሜ እና አቅም ያማከለ መሆኑን በማሰብ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች :**

- ✓ የማን የማን ባህልን ጨፈራችሁ?
- ✓ ስንት ዓይነት ባህላዊ ጭፈራ ታውቃላችሁ?
- ✓ ከሱቅ ውስጥ ምንምንና በስንት ብር ሸጣችሁ ወይም ገዛችሁ?
- ✓ ሥዕል ለመሣል ምንምን ተጠቀማችሁ?

✓ ስንት ዓይነት ሥዕል ሣላችሁ? የሚሉትንና ሌላም ጥያቄዎችን በመጨመር ይጠይቋቸው::

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የሥዕል ካርዶች፣ሞዴል የብር ኖቶች፣ የተለያዩ ያለቁ የሱቅ ዕቃዎች፣ አልባሳት፣ የተለያዩ የሥዕል መሳያ ቁሳቁሶች ...ወዘተ

**የምዘና ስልት:** **የቃል ጥያቄ** (በጨዋታው ምን ተሰማችሁ?)

**ምልከታ** (ሲገዙና ሲሸጡ ንግግራቸውን እንዲሁም የዕቃውን ዓይነት በትክክል መለየታቸውን መመዘን፣ የሣሉትን ሥዕል የሚጀምርበትን ፊደል በመለየት ስሙን መጻፍና ድምፁን አስመስለው በመጮህ ከሥዕሉ ጋር መዛመድ መቻላቸውን መመዘን፡፡)

## ተግባር አምስት፡ እንቆቅልሽ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ተፈጥሮ፣ ሰው ሠራሽ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በእንቆቅልሽ ፣በገለፃ

**የመምህር ሚና:** መምህር ወደ እንቆቅልሽ ከመግባትዎ በፊት ሕፃናት ደስ የሚላቸውን መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

በመቀጠልም እርስዎ እንቆቅልሽ ከጠየቁ በኋላ ሕፃናትም የሚያውቋቸውን እንቆቅልሽ እንዲጠይቁ ያድርጉ፤በመጨረሻም በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ያለውን እንቆቅልሽ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡

እርስዎ፡ እንቆቅልሽ

ሕፃናት፡ ምናውቅልሽ በማለት እንቆቅልሹን በመጀመር በእንቆቅልሽ ምን እንደ ተማሩ ይጠይቋቸው፡፡

**እንቆቅልሽ አንድ**

አራት እግር አለኝ፤ ሥጋዬ ለምግብነት ያገለግላል፤ እርሻም ለማረስ እጠቅማለሁ የስሜ ፊደል የሚጀምረው **በ** ተብሎ ነው፡፡ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** **በሬ**

**እንቆቅልሽ ሁለት**

በተፈጥሮ ከቤት እንስሳት እገኛለሁ፤ ሞላላ ቅርፅ አለኝ፣ ከላይ ነጭ ከውስጤ ቢጫ ቀለም አለኝ፡፡ ለምግብነት አገለግላለሁ፡፡ በቀላሉ ሕፃናት ይሥሉኛል፡፡ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ :** **እንቁላል**

**እንቆቅልሽ ሦስት**

ከሰው ውጫዊ የሰውነት ክፍል ውስጥ ከአንገት በታች እመደባለሁ፡፡ ቁጥሮችና ፊደሎችን ለመጻፍ፣ሥዕሎችን ለመሣል፣ ሸካራና ለስላሳ ነገሮችን ለመለየት አገለግላለሁ፡፡ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** **እጅ**

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የሥዕል ካርዶች፣ የእንቆቅልሽ መጻሕፍትና

በአካባቢ የተለመዱ እንቅቅልሾች

**የምዘና ስልት፡** እንቆቅልሹን ሲመልሱ ማዳመጥና በማየት መመዘን፣ የቃል ጥያቄ እንቆቅልሾችን በተለያየ መልኩ መጠየቅ

## የአውድ ማጠቃለያ ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም________________________________ጾታ_______እድሜ_______ደረጃ_______

**መግለጫ፡** ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "✓" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | የመማር ብቃቶች | የምልከታ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | ጥሩ | በ.ጥሩ | እ.በ.ጥሩ |
| 1 | ማኅበራዊ ክህሎት አላቸው? | | | | |
| 2 | የሰላም መገለጫ ባህሪያቶችን አብረዋል ? | | | | |
| 3 | ሌሎችን የመዉደድ ስሜታቸዉን ዳብሯል? | | | | |
| 4 | ቀላል የመደመርና የመቀነስ ስሌቶችን ይሰራሉ? | | | | |
| 5 | የሀገር ወዳድነት ስሜትን አዳብረዋል? | | | | |
| 6 | በራስ በመተማመን ስሜት መግባባት ይችላሉ? | | | | |
| 7 | በዕለት ተዕለት ተግባራቸዉ የደህንነት እና የንጽሕና አጠባበቅ መርሆዎችን ይተገብራሉ ? | | | | |
| 8 | ጊዜን መሰረት በማድረግ የዕለትተዕለት ተግባራቸዉን ያቅዳሉ ? | | | | |
| 9 | ከመማር ይዘቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለያዩ ሥነ ጥበባዊ ተግባራትን በመስራት ይዝናናሉ? | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻም፦_____________________________________________

_____________________________________________

_____________________________________________

_____________________________________________

# አወድ ሶስት ቴክኖሎጅ

አጠቃላይ ለዐውዱ የተቀመጠው ሳምንትና ክፍለ ጊዜ፡ 5 ሳምንት/150 ክፍለ ጊዜ

## 4.1. መግቢያ

ቴክኖሎጂ የአንድ ሀገር ዕድገት ወይም ስልጣኔ ማሳያ ወይም መገለጫ ነው፡፡ በአለማችን የሚገኙ የተለያዩ ሀገራት እድገት መሰረቱ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ በሀገራችንም በስፋትና በፍጥነት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በርካታ ስራዎችን ወይም ተግባራትን በአጭር ጊዜና በትንሽ የሰው ሀይል ለማከናወን ቴክኖሎጂ በጣም አስፈላጊና መሰረት ነው፡፡ በዚህ ዐውድ ስር ሕፃናትን ከቴክኖሎጂ ጋር ለማስተዋወቅ ይረዳን ዘንድ የተለያዩ መሰረታዊ የሆኑና የሕፃናትን ዕድሜ የሚመጥኑ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ስለሆነም ሕፃናት የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ማህበራዊና የመግባባት ክህሎታቸውን፣ ቁጥሮችን መቁጠር፣ መደመርና መቀነስ፣ የደህንነትና የንፅህና መጠበቂያዎች አጠቃቀም፣ የመገናኛ መሳሪያዎች አጠቃቀም ቃላትን ማንበብና መፃፍ የመሳሰሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ቀርበዋል፡፡ በአጠቃላይ ሕፃናት መሰረታዊ ከሆኑ ቴክኖሎጂዎች ጋር ትውውቅ በማድረግ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

## 4.2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ሕፃናት ይህንን ዐውድ ከተማሩ በኋላ፡

- ✓ ግንዛቤያቸዉንና ማኅበራዊ ክህሎታቸዉን ለማዳበር የተለያዩ ቴክኖሎጅዎችን ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ ለጨዋታ፣ ፊደላትን ለማንበብና ለመፃፍ፣ እንዲሁም የቃላት ክምችታቸውን ለማሳደግ ዲጂታል ቴክኖሎጅን ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ ማህበራዊ እና ተግባቦታዊ ክህሎትን ለማዳበር ዲጂታል ቴክኖሎጅን ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን ለመቁጠር፣ ለመቀነስ እና ለመደመር የተለያዩ ቴክኖሎጅዎችን ይጠቀማሉ፡
- ✓ ዲጅታል ቴክኖሎጅን በመጠቀም በዕለት ከዕለት ተግባሮቻቸዉ ዉስጥ የደህንነትና የንፅህና አጠባበቅ መመሪያዎችን ይተገብራሉ፡፡
- ✓ የዲጅታል ሚዲያን(ዘመናዊ የመገናኛ መሳሪያዎችን) በመጠቀም የተለያዩ ጥበባዊ ተግባራቶችን በማከናወን ይዝናናሉ፡፡
- ✓ የዲጅታል ሚዲያን(ዘመናዊ የመገናኛ መሳሪያዎችን) በመጠቀም ነገሮችን ይመድባሉ፡

## 4.3. አበይት ይዘቶች

ቴክኖሎጂ በሚለው የመማር ዐውድ ስር የሚከተሉት የትምህርት ይዘቶች ተካተዋል፡፡

- ራስን መግለጽ
- ራስን ማወቅ
- የአካል ክፍሎች
- ጤና
- ቁጥርን መቁጠር
- የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር
- የዲጂታል ቴክኖሎጅ አጠቃቀም
- ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
- ባህላዊ ቅርሶች
- ማኅበራዊ ግንዛቤ

- ጥበባዊ ግንዛቤ
- ራስን መቆጣጠር
- ድምፆችን መለየት
- የቅርብ አከባቢ
- ስርአተ ምግብ
- ቁጥሮችን መፃፍ
- የፈጠራ ስራን መግለፅ
- ራስን መቻል
- ቃላት
- የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር
- ቅጥ
- ጥበባዊ እሴት
- የግብረ ገብ እሴት
- የፊደላት ድምፅ ግንዛቤ
- የቦታ መገኛ ግንዛቤ
- ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ አካባቢዎች
- መለየት እና መመደብ

## አንደኛ ሳምንት

### ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክለፍ ጊዜ/15 ሰዓት

### አጥጋቢ መማር ብቃቶች፡

- ✓ ራሳቸዉን ዲጅታል ቴክኖሎጅን በመጠቀም ይገልፃሉ፡፡
- ✓ የቴክኖሎጅ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሰዉነት አካል ክፍሎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ የቴክኖሎጅ ዉጤቶችን በመጠቀም የግል ንፅህናቸዉን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸዉ ይማራሉ፡፡
- ✓ የዲጅታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫዎታሉ፡፡
- ✓ በየአካባቢያቸው የሚገኙ የእርሻ መገልገያ የሆኑ የቴክኖሎጅ ዉጤቶችን ስም ይለያሉ፡፡
- ✓ የቴክኖሎጅ መሳሪያዎችን ተጠቅመዉ ቁጥሮችን በቃል ይቆጥራሉ፡፡
- ✓ የዲጅታል ቴክኖሎጅን በመጠቀም ቁጥሮችን ከትንሹ ወደ ትልቁ እና ከትልቁ ወደ ትንሹ ያስቀምጣሉ፡፡
- ✓ የዲጅታል መሳሪያዎችን በቀለም፣ በመጠንና በቅርፅ ይለያሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን መግለጽ፣ ራስን ማወቅ፣ የአካል ክፍሎች፣ ጤና፣ ቁጥርን መቁጠር፣ ጥበባዊ ግንዛቤ

**ተግባር አንድ፡ የግል ተግባር /8 ክፍለ ጊዜ/**

**የግል ተግባር፡ አንድ /4 ክፍለ ጊዜ/**

**ቁልፍ ቃላት፡** ራስን መግለፅ፣ ቴክኖሎጂ፣ ድምፅ፣ የስራ ድርሻ

**የማስተማሪያ ዘዴ ፡** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና፡** መምህር በመጀመሪያ ራስዎን ሲያስተዋውቁ የራስዎትን ስም፣ ፆታ፣ የመጡበትን አካባቢ፣የስራ ድርሻዎን፣ የሚወዱትንና የሚጠሉትን ምግብ እንዲሁም የቀለም አይነትና የመሳሰሉትን ስልክዎን/ቴፕ ሪከርደር ተጠቅመው ይቅረፁና አዘጋጅተዉ ለህፃናቶች ያሰማቸው ህፃናቱም የእርስዎን መነሻ በማድረግ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁና ሲያስተዋውቁ

ተራ በተራ ድምፃቸውን በመቅረፅ እንዲያዳምጡ ያድርጉ ከዚህ በመነሳት የቴክኖሎጅ ዉጤትን ጠቀሜታ እንዲረዱ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** ስልክ፣ ቴፐሪከርደር ወዘተ.

**የምዘና ስልት፡** ራሳቸዉን ሲገልፁ በማዳመጥ፣ የቴክኖሎጅ ጠቀሜታዎችን መረዳታቸዉን በቃል መጠየቅ ድምፃችሁን በምን ሰማችሁት፣ የቴክኖሎጂ ውጤት ለምን ይጠቅመናል.......

## የግል ተግባር፡ ሁለት /4 ክፍለ ጊዜ/

**ቁልፍ ቃላት፡** ቅደም ተከተል፣ ቴክኖሎጂ፣ ቁጥር፣

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር ፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** ውድ መምህር በመጀመሪያ እርስዎ ታብሌት፣ ኮምፒውተር፣ ሞባይል፣ ቴፕ ይዘው ወደ ክፍል በመግባት ከ1 20 ያሉ ቁጥሮችን በድምፅ ቀድቶ በማሰማት አብረው እንዲቆጥሩ ያለማምዷቸው፡፡

ከ1 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በተለያየ ቀለማት በማዘጋጀት ከትንሽ ወደ ትልቁና ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** ታብሌት፣ ኮምፒውተር፣ ሞባይል፣ ቴፕ፣ የተለያዩ ቀለማትን የያዙ የቁጥሮች ካርድ

**የምዘና ስልት፡** ምልከታ፡ በድምፅ ተቀድቶ የሰሙትን ቁጥር በመቁጠር ሲለማመዱ በማዳመጥና የተለያዩ ቀለማትን የያዙ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ሲያስቀምጡ ማየት የቃል ጥያቄ፡ ትንሻን ቁጥር ጥራኝ፣ ትልቋ ቁጥር ስንት ነች፣ ይህች ቁጥር ስንት ነች.........

## ተግባር ሁለት፡ ውይይት /10 ክፍለ ጊዜ/

### ውይይት አንድ /4 ክፍለ ጊዜ/

**ቁልፍ ቃላት፡** ዲጅታል ቴክኖሎጂ፣ ቀለም፣ መጠን፣ ቅርፅ፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በውይይት ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ በቡድን

**የመምህር ሚና ፡** መምህር የተለያዩ የዲጅታል መሳሪያዎችን በስዕል፣ በካርድ፣ በሞዴል፣ እንዲሁም ዕውነተኛ መሳሪዎችን በክፍል ውስጥ በማዘጋጀት/በማደራጀት ለዚህ አውድ ማስተማሪያ እንዲሆኑ ያስቀምጡ፡፡

መምህር ሕፃናትን በትናንሽ ቡድኖች ያደራጇቸውና እርስዎ አስቀድመው ያደራጁትን እንዲመለከቱና በመቀጠል የሚያውቋቸውን የተለያዩ የዲጅታል ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን እንዲዘረዝሩ ያድርጉ ከዚያም እርስዎ ያዘጋጇዋቸውን ምስሎችና ሞዴሎች ለየቡድኑ ያከፋፍላቸውና በቀለም፣ በመጠንና በቅርፅ እንዲመድቡ እንዲሁም አገልግሎታቸውን በማንሳት እንዲወያዩ ያድርጉ እርስዎም እየተዘዋወሩ ሁሉንም ቡድኖች በመከታተል እገዛና ድጋፍ ያድርጉ ውይይታቸውን ሲጨርሱ ለክፍሉ ሕፃናት በየተራ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የዲጅታል መሳሪያዎችን የያዘ ስዕል፣ ካርድ፣ ሞዴል ወይም ዕውነተኛ ቁሳቁሶች/መሳሪዎች

**የምዘና ስልት:** ምልከታ፡ እየተዘዋወሩ ሕፃናት በየቡድናቸው የዲጅታል ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በመዘርዘር በቀለም፣ በመጠንና በቅርፅ ሲመድቡ በመመልከትና በማዳመጥ፣ የቃል ጥያቄ ፡ የውይይታችሁ ርዕስ ምንድን ነበር፣ ስትመድቡ ምን አይነት ቀለም አገኛችሁ፣ ስንት የስልክ ምስል አገኛችሁ........ስንት የዲጅታል ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ዘረዘራችሁ? ምን ምን ናቸው? ለምን ይጠቅማሉ? ተመሳሳይ ቀለም/መጠን/ቅርፅ ያላቸው የትኞቹ ናቸው?

## ውይይት ሁለት /3 ክፍለ ጊዜ/

**ቁልፍ ቃላት:** ዲጅታል ቴክኖሎጂ፣ ቁጥር፣ የእርሻ መሳሪያ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በውይት፣ በጥያቄና መልስ፣ በቡድን

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናትን በቡድን በማደራጀት በአካባቢያቸው የሚገኙትንና የሚያውቋቸውን የእርሻ መሳሪያዎችን እንዲዘረዝሩ በማድረግ ሲጨርሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡ በመለማጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ የእርሻ መሳሪያዎችን ስም ፃፉ የሚለውን ተግባር ያሰሯቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የእርሻ መሳሪያዎች፣ ቴክኖሎጂ

**የምዘና ስልት:** የእርሻ መሳሪያዎችን በቡድን ሲዘረዝሩ ተዟዙሮ በመመልከትና ውይይታቸውን በማዳመጥ፣ የቃል ጥያቄ ፡ የውይይታችን ርዕስ ምን ነበር፣ የእርሻ መሳሪያ የምንለው ከምን ውስጥ ይመደባል.......ስንት የእርሻ መሳሪያዎችን ዘረዘራችሁ? የትኞቹ ባህላዊ የትኞቹ ደግሞ ዘመናዊ ናቸው? ምክንያቱስ?

## ውይይት ሶስት /3 ክፍለ ጊዜ/

**ቁልፍ ቃላት:** ዲጅታል ቴክኖሎጂ፣ ቁጥር፣ የእርሻ መሳሪያ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በውይት፣ በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ

**የመምህር ሚና :** መምህር ሕፃናትን በቡድን በማደራጀት የሰው የአካል ክፍሎችን የያዘ ምስል/ፖስተር በቪድዮ፣ በፎቶ፣ በስዕል ያሳዩዋቸውና የሰው የአካል ክፍሎችንና ጠቀሜታቸውን በየቡድናቸው በመወያየት እንዲዘረዝሩ እንዲሁም እነዚህን የአካል ክፍሎች ምንን በመጠቀም እንዳሳያቸውውእንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

ሁሉም ቡድኖች ምን ያክል የሰው የአካል ክፍሎች እንዳሉና የእያንዳንዳቸውን ስምና ጠቀሜታ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ የሰው የአካል ክፍሎች ስምና ጠቀሜታ የሚለውን ተግባር እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

**ማስታወሻ:** መምህር የሰው የአካል ክፍሎችን ለህፃናት ሲያስተምሩ ዕድሜያቸውን ታሳቢ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የሰው የአካል ክፍሎችን የያዘ ምስል፣ ቴሌቭዥን፣ ላብቶፕ፣ ታብሌት፣ ፖስተር

**የምዘና ስልት፡** ምልከታ፡ የሰው የአካል ክፍሎች ስምና ጠቀሜታዎች የሚለውን ተግባር በየቡድናቸው ሲወያዩ ተዟዙሮ በመመልከትና ሲጨርሱም የተወያዩበትን ሲያቀርቡ በማዳመጥ የቃል ጥያቄ፡ አይን ለምንይጠቅማል፣ እጅስ፣ ፎቶ በምን እናነሳለን፣ ፎቶ የምን ውጤት ነው......

## ተግባር ሶስት፡ መዝሙር /4 ክፍለ ጊዜ/

**ቁልፍ ቃላት፡** የግል ንፅህና፣ የቴክኖሎጅ ውጤቶች፣ መደሰት፣ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ህፃናቶችን ቀጠሎ የቀረበዉን መዝሙር ያስዘምሯቸዉና የመዝሙሩን ጭብጥ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

**ንፅህናየን እጠብቃለሁ**

ንፅህናየን እኔ እጠብቃለሁኝ፣
በሳሙና እጄንና ፊቴን እታጠባለሁኝ፣
ጥርሴንም በቡርሽ እቦርሻለሁኝ፣
ፀጉሬን በመታጠብ አበጥራለሁኝ፣
ለትምህርት ጊዜ ሰዓት አያለሁኝ፡፡
ቁርሴንም በመብላት ቦርሳየን አንግቼ፣
ትምህርት እሄዳለሁ እንደጓደኞቼ፡፡
ስዕልን በመሳል እደሰታለሁ፣
አንድ ሁለት ብየ ቁጥር እቆጥራለሁ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የጥርስ ቡርሽ፣ ማበጠሪያ፣ ሳሙና፣ ሰዓት

**የምዘና ስልት፡** ንፅህናየን እጠብቃለሁ የሚለውን መዝሙር ሲዘምሩ በማዳመጥ የቃል ጥያቄ፡ ንፅህናችንን በምንእንጠብቃለን፣ ጊዜን የሚያሳየን የቴክኖሎጂ ውጤት ምንድን ነው፣ ቡርሽ የምን ውጤት ነው............

## ተግባር አራት፡ የክፍል ዉጭ ጨዋታ/8 ክፍለ ጊዜ/

**ቁልፍቃላት፡** የቴክኖሎጅ ዉጤቶች፣ ጨዋታ፣ ሸርታቴ፣ ዥዋዥዌ፣ ሽክርክሪት፣ ሚዛን፣ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በተግባር ፣ በቡድን

**የመምህር ሚና፡** መምህር ህፃናቶችን ከክፍል ዉጭ ይዘዋቸዉ በመዉጣት በትናንሽ ቡድኖች ያደራጇቸዉና ከዚያም በትምህርት ቤትዎ ውስጥ ባሉ መጫወቻዎች ላይ ይመድባቸውና የቴክኖሎጅ ዉጤቶችን በመጠቀም ሸርታቴ፣ ዥዋዥዌ፣ ሽክርክሪት፣ ሚዛን ወዘተ. በመጠቀም በየተራ እንዲጫወቱን ተጫውተው ሲጨርሱ እርስ በእርስ በመቀያር እንዲጫወቱ ያድርጓቸዉ፡፡

ሁሉም ቡድኖች ተጫዉተዉ ሲጨርሱ የአካባቢዉን ባህል የሚያንፀባርቅ ዘፈን በሞባይል/በቴፕ/በስፒከር በመክፈት በጋራ እንዲጨፍሩ ያድርጓቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** በትምህርት ቤቱ ዉስጥ የሚገኙ የመጫዎቻ የቴክኖሎጅ ዉጤቶች እሽክርክሮሽ፣ ሽርተቴ፣ ዥዋዥዌ፣ መንሰላል፣ መሹለኪያ

**የምዘና ስልት: ምልከታ:** ሲጫወቱ እየተዟዙ መመልከትና የቃል ጥያቄ፡ በምን ያክል የቴክኖሎጅ ዉጤቶች ምን ያክል ጨዋታዎችን ተጫወታችሁ? ብሎ

# ሁለተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክለፍ ጊዜ/15 ሰዓት

## አጥጋቢ የመማር ብቃቶች:

- ✓ ዲጅታል መሣሪያዎችን በመጠቀም ስለራሳቸው እና ስለ አካባቢያቸው ይማራሉ፡፡
- ✓ የግል ንጽሕናቸውን ለመጠበቅ ከዕድሜያቸው ጋር የሚስማማ ቴክኖሎጂን ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ ለሰው ልጅ ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን ተስማሚ ካልሆኑት ይለያሉ፡፡
- ✓ የጽዳት ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ከሌሎች ጋር በመሆን በጽዳት ሥራ ይሳተፋሉ፡
- ✓ የቤት ውስጥ የቴክኖሎጂ መገልገያ ዕቃዎችን ከተጠቀሙ በኋላ ያፀዳሉ፡፡
- ✓ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ የክፍል ውስጥና የክፍል ውጭ መጫዎቻዎችን ያፀዳሉ፡፡
- ✓ አካባቢያዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም ሀገር በቀል ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡
- ✓ የፈጠራ ሥራ ይሠራሉ፡፡
- ✓ የሙዚቃ መሳሪያ ይጫወታሉ፡፡
- ✓ የዲጅታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ተረቶችን ይናገራሉ፡፡
- ✓ ሀገር በቀል የመጫዎቻ መሣሪያዎችን ከአካባቢው ቁሳቁሶች ይሥራሉ፡፡
- ✓ ለጽሕፈት አገልግሎት የሚያገለግሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይጠቀማሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን መቆጣጠር፣ ድምፆችን መለየት፣ የቅርብ አካባቢ፣ ሥርዓተ ምግብ፣ቁጥሮችን መጻፍ፣ በፈጠራ ሥራ መግለፅ፡፡

### ተግባር አንድ፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ /3 ክፍለ ጊዜ/

**ቁልፍ ቃላት:** ጽዳትን ፣ቴክኖሎጂ ፣ የቅርብ አካባቢ፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጭውውት ፣በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር የጭውውት ክፍለ ጊዜ መሆኑን ለሕፃናት ይንገሯቸው፡፡ የጥርስ ቡርሽ፣ የኮልጌት፣ የመፋቂያ የመሳሰሉትን ሥዕሎችን በማሳየት እነዚህ የንጽሕና መጠበቂያ ዕቃዎች ከየት እንደመጡ/የምን ውጤቶች እንደሆኑ ይጠይቋቸው፡፡ አስቀድመው ያዘጋጇቸውን ወይም ያለማመዷቸውን ሕፃናት ያስወጡ፡፡ ጭውውቱን ለሁሉም ሕፃናት በሚታይ ቦታ ላይ እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡፡ ሌሎቹ ሕፃናት እነሱ ሲሠሩ እንዲያዳምጡና እንዲከታተሉ ይንገራቸው፡፡

በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ የተቀመጡ ሥዕሎችን ቀለም ያስቀቧቸው፡፡

**ጭውውት**

ቲቲ፡ ምን እየሠራሽ ነው?

ሊሊ፡ ጥርሴን እየቦረሽኩ

ቲቲ፡ እኔም እኮ ጠዋት በመፋቂያ ፍቄያለሁ

ሊሊ፡ በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ መፋቅ አለብሽ

ቲቲ፡ በቃ ለእኔም ቡርሽሽን ስጪኝና ልቦርሽ

ሊሊ፡ በሰው ቡርሽ አይፋቅም በሽታ ያስይዛል

ቲቲ፡ በቃ እሺ አባቴን ግዛልኝ እለዋለሁ ግን የት ነው የሚሸጠው?

ሊሊ፡ መድኃኒት መሸጫ መደብር፣ ሱቅም ይሸጣል ወይኔ ጥርሴ ደማ ወይኔ ጉዴ

አባት፡ ምንድነው የምትጮሂው ምን ሆነሻል?

ሊሊ፡ ጥርሴ ደማብኝ አባ

አባት፡ እስኪ ልይልሽ ጥርስሽን እየቦረሽ ወሬ ማውራት የለብሽም፣ እንዲሁም ጥርስሽን ስትፍቂ ድድሽን ቡርሹ እንዳይነካሽ መጠንቀቅ አለብሽ፡፡ ለማንኛውም ተርፈሻል በይ አሁን በውሃ በደንብ ተጉመጥመጪው በቃ አሁን ደኅና ነሽ ወደ ቤት ግቢ መሸቷል አንቺም ወደ ቤትሽ ሂጂ በማለት ጭዉዉቱ ይጠናቀቅና ህፃናቶች በቤታቸዉ ዉስጥ የሚገኙ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የግላቸውን ንፅህና እንዲጠብቁ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸዉ፡፡

በሚቀጥለዉ ቀን ሲመጡ የተጠቀሟቸዉን የቤት ዉስጥ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንዲናገሩ ያድርጓቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** ሥዕል፣ የጥርስ ቡርሽ፣ መፋቂያ፣ ኮልጌት፣ ውሃ

**የምዘና ስልት፡** ጭውውቱን ሲሰሩ መመልከትና የቃል ጥያቄ መጠየቅ

**ጥያቄዎች**

- ጭውውቱ ስለምን ነበር? ጥርሳችንን የምናጸዳባቸው መሣሪያዎች ምን ምን ናቸው? በቀን ስንት ጊዜ መፋቅ አለብን? ዘመናዊዎቹ የትኞቹ ናቸው? ባህላዊዎቹስ?

## ተግባር ሁለት፡ እንቆቅልሽ (5 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ቴክኖሎጂ፣ ምግብ፣ ድምፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ፣

**የመምህር ሚና ፡** ውድ መምህር ክፍለ ጊዜው የእንቆቅልሽ እንደሆነ ይግለጹላቸው፡፡ ከዚያም እርስዎ ጠያቂ በመሆን ሲጠይቁ ሕፃናት እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ካልመለሱ የእንቆቅልሽ ሥርዓትን በመከተል መልሱን ከሥዕል ጋር በማገናኘት ይንገሯቸው፡፡ ምስል በማዘጋጀት ሲመልሱም ምስሉን እያሳዩ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡ እንቆቅልሾቹ ብዙ ስለሆኑ ለክፍለ ጊዜው በመቀነስ ይጠቀሙ፡፡

በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ ያለውን እንቆቅልሽ ያሠሯቸው።

እንቆቅልሽ፡ 1

ለሰዎች የተለያዩ መልዕክቶችን በድምፅ አስተላልፋለው በየሰዓቱ ዜና እናገራለሁ እኔ ማነኝ?

መልሱ ፡ ሬድዮ

እንቆቅልሽ፡ 2

ቁመቴ ረጅም ነው፤ ተቀቅዬ እበላለሁ፤ ለእኔ ማባያ የሚሆን ስልስ በቲማቲም፣ በሥጋና በአትክልት ይሠሩልኛል። እኔ ማነኝ?

መልሱ፡ ፓስታ

እንቆቅልሽ፡ 3

ሕፃናት ይጫወቱብኛል፤ ልክ እንደ ሰው እጅ እግር አለኝ፤ ልብስ እለብሳለሁ፤ ነፍስ ግን የለኝም። እኔ ማነኝ?

መልሱ ፡ አሻንጉሊት

እንቆቅልሽ፡ 4

ሰዎች ከቦታ ቦታ በእጃቸው ይዘውኝ ይዞራሉ፤ ሰዎች ሩቅ ቦታ ካሉ ሰዎችን በድምፅ ያገኛሉ፣ ጌምና ፊልም ያዩብኛል። እኔ ማነኝ?

መልሱ ፡ የእጅ ስልክ

እንቆቅልሽ፡ 5

ሰዎችን ከቦታ ቦታ አጓጉዛለሁ፤ አራት ጎማ አለኝ፤ የተለያየ ቀለም አለኝ፤ መጠኔም ይለያያል እኔ ማነኝ?

መልሱ ፡ መኪና

እንቆቅልሽ፡ 6

ሰዎች እጃቸው ላይ ያስሩኛል፣ ግድግዳ ላይ ይሰቅሉኛል፤ ጊዜን እቆጥራለሁ። እኔ ማነኝ?

መልሱ ፡ ሰዓት

እንቆቅልሽ፡ 7

የቤት ኮርኒስ መሀል ላይ በኤሌክትሪክ ሽቦ እንጠለጠላለሁ፤ ማታ ሲጨልም ብርሃን እሰጣለሁ ማብሪያና ማጥፊያ አለኝ። እኔ ማነኝ?

መልሱ ፡ አምፖል

እንቆቅልሽ፡ 8

ሰዎች ድስት በመጣድ ወጥ ይሠሩብኛል፤ የምሠራው በኤሌክትሪክ ኃይል ነው፤ ጭስ የለኝም። እኔ ማነኝ?

**መልሱ :** እስቶቭ

**እንቆቅልሽ፡** 9

ውሃ አቀዘቅዛለሁ፤ ምግብ እንዳይበላሽ አደርጋለሁ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ሲጠፋ ሥራ አቆማለሁ እኔ ማነኝ?

**መልሱ :** ማቀዝቀዣ/ ፍሪጅ

**እንቆቅልሽ፡** 10

ሰዎችን ፎቶ ሳነሳ ቀጭ የሚል ድምፅ አወጣለሁ፤ በብዛት አራት ማዕዘን ቅርፅ አለኝ፡፡ እኔ ማነኝ?

**መልሱ :** ካሜራ

**እንቆቅልሽ፡** 11

ክብ ነኝ፤ እንጀራ ይጋግሩብኛል፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ሲጠፋ አልሠራም፡፡ እኔ ማነኝ?

**መልሱ፡** የእንጀራ ምጣድ

**እንቆቅልሽ፡** 12

ሰዎች በኤሌክትሪክ ኃይል ውሃ ለማፍላት ይጠቀሙብኛል በጣም ፈጣን ነኝ፡፡ እኔ ማነኝ?

**መልሱ፡** የውሃ ማፈያ/ ቦይለር

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የፓስታ፣ የመኪና፣ የሬድዮ፣ አሻንጉሊት፣ የእጅ ስልክ፣ ሰዓት፣ አምፖል፣ እስቶቭ፣ ማቀዝቀዣ/ ፍሪጅ፣ ካሜራ፣ የእንጀራ ምጣድ፣ የውሃ ማፈያ/ቦይለር ሥዕል

**የምዘና ስልት፡** እንቆቅልሹን ሲመልሱ በማዳመጥና፣ የቃል ጥያቄ፡ በእንቆቅልሹ ላይ የተነሡት ነገሮች ምን ምን ናቸው? ፓስታ የምን ውጤት ነው፣.........

## ተግባር ሶስት፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

### የክፍል ዉጭ ጨዋታ አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት :** የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን፣ አካባቢን ማወቅ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ዕዳት፣ ድምፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በተግባር

**የመምህር ሚና :** መምህር ህፃናትን ከክፍል ዉጭ ይዘዋቸዉ በመዉጣት በትላልቅ ቡድን በመከፋፈል በየቡድናቸዉ ክብ እንዲሰሩ ያድርጉ፤ በመቀጠል በትምህርት ቤትዎ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በየቡድናቸዉ በመስጠት በአካባቢያቸዉ የተለመዱ ዘፈኖችን መሳሪያዎቹን በመጠቀም እንዲጫወቱ ያድርጉ፤ ከጨረሱ በኋላ የተጠቀሙባቸዉን የሙዚቃ መሳሪያዎች በማፅዳት ወደየቦታቸዉ እንዲመልሱ ያድርጉ፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ከበሮ፣ ክራር፣ ማሲንቆ በአጠቃላይ በአካባቢዎ የተለመዱ የሙዚቃ መሳሪያዎች

**የምዘና ስልት:** የህፃናትን የጨዋታ እንቅስቃሴን በመመልከትና የቃል ጥያቄ( ምን ያክል የሙዚቃ መሳሪያዎችን ተጠቀማችሁ? ምን ተሰማችሁ? የትኞቹ የሚዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊ ናቸው የትኞቹስ ዘመናዊ ናቸው......

## የክፍል ዉጭ ጨዋታ ሁለት (4 ክፍለ ጊዜ)

**የማስተማሪያ ዘዴ :** በጨዋታ፣ በገለፃ ፣ በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና :** መምህር ሕፃናትን ወደ ውጪ በማስወጣት ክብ እንዲሠሩ ያድርጓቸውና በክቡ ውስጥ የተለያዩ ቁሶችን ያስገቡ፡፡ እርስዎ ዓይንዎን በጨርቅ አስረው ክቡ ውስጥ ከገቡ በኋላ ካዘጋጁት ቁሳቁሶች ውስጥ በመፈለግ አንዱን በመንካት ምን እንደሆነ ይናገሩ፡፡ በትክክል መመለስዎን ሕፃናቱ እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡

ሕፃናት ተራ በተራ ዓይናቸውን በመሸፈን እርስዎን በመከተል መሀል እየገቡ እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡፡ ዕቃውን ፈልገው እንዲያገኙና በትክክል የቁሱን ስም እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ አንድ ሕፃን በተደጋጋሚ ሁለት ጊዜ ካልመለሰ ከጨዋታ ውጪ ይሆናል፤ ጨዋታው በዚሁ መንገድ ይቀጥላል፤ በመጨረሻም በትምህርት ቤታቸዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ የሚገኙ የቴክኖሎጅ ዉጤቶችን በመጠቀም ነፃ ጨዋታ እንዲጫወቱ ካደረጉ በኋላ የተጫወቱባቸዉን ቁሳቁሶች እንዲያፀዱ ያድርጓቸዉ፡፡ ይህ ጨዋታ በአንድ ክፍለ ጊዜ ስለማያልቅ ከላይ በተቀመጠው መሠረት ደጋግመው ያሠሯቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፣ እስክሪብቶ፣ ማርከር፣ ቁልፍ፣ ወረቀት፣ ትንሽ ኳስ፣ የዓይን መሸፈኛ ጨርቅ

**የምዘና ስልት:** ሲጫወቱ በማየት ጨዋታዉ ስለምን እንደ ነበር፣ እንዲሁም የቁሳቁሶቹን ስም ምን እንደሆነ፤ ቁሳቁሶቹ ከምን ውስጥ እንደሚመደቡ መጠየቅ፣ የቁሳቁሶቹን ብዛት እንዲቆጥሩ ማድረግ

## ተግባር አራት፡ መዝሙር (6 ክፍለ ጊዜ)

## መዝሙር አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ንጽሕና አጠባበቅ፣ የአመጋገብ ሥርዓት፣ ጤና፣ ቴክኖሎጂ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣በገለጻ ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር ለሕፃናቱ ይህ ክፍለ ጊዜ የመዝሙር መሆኑን ይንገሯቸው፡፡ ከአመጋገብ ሥርዓት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሥዕሎች በመጠቀም ስለ አመጋገብ ሥርዓት፣ ስለ ግል ንጽሕና አጠባበቅ፣ ስለ ዘመናዊ ሕክምና አሰጣጥ ለውጥ ያብራሩላቸው፡፡

### ሳይንስ ሳይንስ

ሳይንስ ሳይንስ መድኃኒቴ
ያስተማረኝ ጤንነቴ
ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን ስበላ
እጄን ታጥቤ ምሳ ስበላ
እግሬን ታጥቤ ማታ ስተኛ
በሕልሜ ታየኝ ሳይንስ ሳጠና
ሳይንስ ሳይንስ መድኃኒቴ
ያስተማረኝ ጤንነቴን
ድንገት ታምሜ ስልክ ደውዬ
ዶክተሬን ጠራሁ እቤቴ ሆኜ
በኢንዲስኮፒ ውስጤን ታይቼ
የታዘዘልኝን መድኃኒት ወስጄ
በጣም ተደስትኩኝ ጤናዬን አግኝቼ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የኢንዲስኮፒ ሥዕል፣ የእጅ መታጠብ ሥዕልና ቪዲዮ፣ ወዘተ.

**የምዘና ስልት፡** የቃል ጥያቄ መዝሙሩ ስለምን እንደሆነ መጠየቅ፣ በቀን ስንት ጊዜ እንታጠባለን?፣ ስንታመም እንዴት እንታከማለን? የህክምና መሳሪያዎች የምን ውጤት ነው

## መዝሙር ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ቃላት፣ ቁጥር፣ ቴክኖሎጂ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር ፣በገለጻ ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር ለሕፃናቱ ያዘማመር ስልትን በመከተል ያዘምራቸው፡፡

### ቴክኖሎጂ

ቴክኖሎጂ እኔ እጠቀማለሁ
አላርሜ ሲጮህ እኔ እነሣለሁ
ላፕቶፔን ከፍቼ ቃላት አነባለሁ
ቴ ቴክኖሎጂ ስ ስልክ
ዣ ዣንጥላ ል ልብስ
ቤ ቤት አ አሻንጉሊት
እያልኩኝ ቃላት አነባለሁ
ኀበዝ እንድሆን ቁጥር እቆጥራለሁ
አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ብዬ
አራት አምስት ስድስት ብዬ እጨርሳለሁ
ላፕቶፔን ዘግቼ እደንሳለሁ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የላፕቶፕ፣ የፕሮጀክተር ሥዕል፣ በቪዲዮ

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ መዝሙሩ ስለምን እንደሆነ መጠየቅ፣ ምን ምን ቃላት መሠረትን? ስንት ስንት ቁጥሮችን ጠራን?፣

## ተግባር አምስት: በሥራ መማር (7 ክፍለ ጊዜ)

### በስራ መማር አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የፈጠራ ሥራ፣ ቴክኖሎጂ፣ ቃላት፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና:** መምህር ለሕፃናት ይህ ክፍለ ጊዜ የተግባር ሥራ የሚሠሩበት መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን/ቁሳቁሶችን በማዘጋጀት እያንዳንዳቸው ከተዘጋጁት ቁሳቁሶች ውስጥ አምስት አምስት ነገር እንዲወስዱ የስራውን ሕግ ብቻ በመንገር ነፃነት ይስጧቸው፡፡ ቁሳቁሶች ሲወስዱ እርስ በእርስ ሊነጣጠቁና ዕቃዬን ወሰደብኝ በማለት እንዳይጣሉ ስሜታቸውን እንዲቆጣጠሩና ተከባብረው እንዲሰሩ ይምከሯቸው፡፡ ከዚያም የወሰዱትን ቁሶች አምስት መሆናቸውን በጋራ በመቁጠር ያረጋግጡ፣ ሲሠሩ አደጋ እንዳይደርስባቸው እንዲጠነቀቁ ይንገሯቸው፡፡ በወሰዱት ቁሳቁስ እስከ አሁን ካዩአቸው የቴክኖሎጂ ዓይነቶች ውስጥ የፈለጉትን የፈጠራ ሥራ እንዲሠሩ እርስዎ አንድ ነገር በመሥራት ያሳያቸው፡፡ እርስዎ የሠሩት ቁስ ለሰው ልጅ ምን ጥቅም እንደሚሰጡ ይግለጹላቸው፡፡ እነሱም ከሠሩ በኋላ ስለ ሠሩት ነገር እንዲያብራሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ሲሠሩ እየተዘዋወሩ በመመልከትና ሊሰሩ ያሰቡትን ነገር በመጠየቅ እገዛ በማድረግ ያበረታቷቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ካርቶን፣ ኮላ፣ የውሃ መያዣ ፕላስቲክ (ሀይላንድ) ክዳን፣ ማርከር፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ቆርኪ፣

**የምዘና ስልት:** ሲሠሩ በማየት የቃል ጥያቄ፡ ምን ሠራህ?፣ ይህን ለመሥራት ምን ምን ተጠቀምክ?፣ የሰራኸው ነገር ለሰዎች ምን ዓይነት አገልግሎት ይሰጣል?

### በሥራ መማር ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የፈጠራ ሥራ፣ ቴክኖሎጂ፣ ቁጥር፣ዘር፣ እህል፣ስሜት፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ

**የመምህር ሚና:** መምህር ለሕፃናት ይህ ክፍለ ጊዜ የግል ሥራ የሚሠሩበት መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡ ከዚያም ወረቀት፣ እርሳስ፣ እስክሪፕርቶ፣ ባለ ቀለም እርሳስ፣ የተለያዩ ሥዕሎችንና የእህል ዘሮችን በማዘጋጀት በየመቀመጫቸው ላይ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚያም የፈለጉትን ሥዕል ደብተራቸው ላይ እንዲሥሉና የሣሉትን ሥዕል ቅርፁን ጠብቀው ኮላ ወይም የተለያዩ ማጣበቂያዎችን በመቀባትና የእህል ዘሩን እንዲለጥፉ ያድርጓቸው፡፡ ሕፃናቱ ይህንን ሲሠሩ ምን እንዳስቸገራቸው በመመልከት አንዳንድ ልጆች የእህሉ ዘር ቦታውን ሲለቅ ስለሚናደዱ ይህንን ስሜታቸውን እንዴት መቆጣጠር እንዳለባቸው ይግለጹላቸው፡፡ በመጨረሻም ምን እንደ ሠሩና የሠሩትን ሥዕል ቅርፅ ለመሥራት ምን ዓይነት የእህል ዘር እንደ ተጠቀሙና ስንት ፍሬ እንደ

ፈጀባቸው ለመቁጠር እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡ ሕፃናቱ ቆጥረው ሲናገሩ እርስዎ የሠሩትን ሥዕል በመያዝ ከሕፃናት ጋር አብረው በመቁጠር ትክክለኛነቱን ያረጋግጡላቸው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የወረቀት፣ እርሳስ፣ እስክሪፕርቶ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ጥራጥሬ፣ኮላ

**የምዘና ስልት:** ሕፃናቱ ሲሠሩ በማየት የቃል ጥያቄ፡ ምን ዓይነት ሥዕል ሠራህ/ሽ?፣ ቅርፁን ለማውጣት ምን ዓይነት የእህል ዘር ተጠቀምሽ/ህ?፣ ምን ያህል የእህል ፍሬ ፈጀብሽ/ህ?

## ተግባር ስድስት፡ ተረት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ተግባር:** ሥርዓተ ምግብ፣ ገንዘብ፣ ስሜት፣ ግብይት፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በትረካ፣ በጥያቄና መልስ፣ በቃል ጥያቄ

### እትዬ አለም

እትዬ አለም የሚባሉ አንድ እናት ነበሩ፡፡ እኚህ እናት የሚኖሩት ለብቻቸው ነው፡፡ ቅዳሜና እሑድ ግን የልጅ ልጆቻቸው ሊጠይቋቸው ይመጣሉ፡፡ የልጅ ልጆቻቸው ማርታና አብርሃም ይባላሉ፡፡ እሳቸውም ለልጅ ልጆቻቸው በኤሌክትሪክ ምዳጃ  የተለያዩ የተመጣጣኑ ምግቦችን ሠርተው እንዳይበላሽባቸው በማቀዝቀዣ (ፍሪጅ) ውስጥ ያስቀምጣሉ፡፡ ልጆቹ ሲመጡም አሙቀው ያቀርቡላቸዋል፡፡ እነሱም እጃቸውን በሳሙና በመታጠብ በጣም ደስ ብሏቸው ይበላሉ፡፡ አንድ ቀን እንደ ለመዱት የሠሩላቸውን ምግብ ለማሞቅ ከፍሪጅ ሲያወጡ መብራት ጠፍቶ ስለነበረ ምግቡ ተበላሽቶ አገኙት፡፡ በዚህን ጊዜ በጣም ተናደዱ፡፡ ምግቡን ዐይተው “ድካሜ ከንቱ ቀረ፡፡” እያሉ ጮሁ፡፡ እነ አብርሃምም ዐይተዋቸው “ተይ እናቴ አትናደጂ ስሜትሽ ተቆጣጠሪ እኛ አሁን በልተን ነው የመጣነው፡፡” በማለት አረጋጓቸው፡፡ እትዬ አለምም ሲረጋጉ “ ልጆቹን በሉ ሂዱና ከቤታችን ጀርባ ካለው ሱቅ የ20 ብር ከሰል ገዝታችሁ በቶሎ ኑ፡፡ ቆንጆ ምግብ እሠራላችኋለው፡፡ ታዲያ ስትሄዱ ዳር ዳሩን ሂዱ አሏቸው፡፡ እነሱም የተሰጣቸውን ብር አንድ፣ ሁለት፣..... በማለት እየቆጠሩ ወደ ተላኩበት ሱቅ በመሄድ ገዝተው መጡ ከዚያም ምግባቸውን አብስለው አብረው ተመገቡ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የብር ኖት፣ ሳንቲም፣ ሥዕል

**የምዘና ስልት:** ተረቱን ሲያዳምጡ በመከታተል ከተረቱ ፍሬ ሓሳብ በመነሣት የቃል ጥያቄ፡ “እትዬ ሜሮን ለልጆቻቸው ምግብ በምን ይሠሩላቸው የነበረው በምንድን ነበር?፣ ምን ዓይነት ምግብ ይሰሩላቸው ነበር?፣ ምግቡን የት ያስቀምጡት ነበር?፣ ምግቡ ለምን ተበላሸ?፣ ከሰል እንዲገዙ ስንት ብር ተሰጣቸው?” ሕፃናቱ በየተራ ተረቱን መልሰው እንዲናገሩ ዕድል መስጠት፡፡

# ሦስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክለፍ ጊዜ/15 ሰዓት

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን መቻል፣ ቃላት፣ የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣ የዲጂታል ቴክኖሎጅ አጠቃቀም፣ ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣ ባህላዊ ቅርሶች

**አጥጋቢ መማር ብቃቶች፡**

- ✓ ምርጫቸዉንና ኃላፊነታቸዉን የዲጅታል ቴክኖሎጅን በመጠቀም ይማራሉ፡፡
- ✓ ቁሳቁሶችን ለማወዳደርና በቅደምተከተል ለማስቀመጥ ዲጅታልቴክኖሎጅን ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ የዲጅታል መሳሪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ ድምፆችን በማዳመጥ አስመስለዉ ይናገራሉ፡፡
- ✓ ባህላዊ ልብሶችን፣ የቤት ቁሳቁሶችን፣ የእርሻ መሣሪያዎችን፣ ታሪካዊ ቁሳቁሶችን፣ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ ዲጅታል ቴክኖሎጅን በመጠቀም የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡
- ✓ ለመንሸራተት፣ ለመንጠላጠል፣ ለመዝለል ጨዋታ የሚያገለግሉ የቴክኖሎጅ ዉጤቶችን ይጠቀመቀሉ፡፡
- ✓ የሰዉ የአካል ክፍሎችን ይስላሉ፡፡
- ✓ ለሰዎች ጤናማ የሆኑ ምግቦችን ጤናማ ካልሆኑ ምግቦች ዉስጥ ይለያሉ፡፡
- ✓ ቴክኖሎጅን በመጠቀም የሌሎችን የአካል ክፍሎች ይለያሉ፡፡
- ✓ ቴክኖሎጅን በመጠቀም የቦታዎችን መገኛ ይገልፃሉ፡፡

## ተግባር አንድ፡ እንቆቅልሽ(4 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍቃላት፡** ኮምፒዉተር፣ ሞባይል/ስልክ፣ ባዮ ጋዝ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በእንቆቅልሽ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** ውድ መምህር በመጀመሪያ ሀሳባቸውን ለመሰብሰብ ሕፃናት የፈለጉትን ወይም የሚወዱትን መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም እንቆቅልሹን እንዲጫወቱ ያድጓቸዉ፡፡

### እንቆቅልሽ 1

ቁጥርና ፊደልን ተጠቅመው ከኤሌክትሪክ ጋር በማገናኘትና በማብራት ይፅፉብኛል፣ ስዕሎችን ይስሉብኛል እኔ ማን ነኝ?

**መልስ፡ ኮምፒተር**

### እንቆቅልሽ 2

ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ ሲናፍቁኝ ቁጥሮችን ፅፌ በመደወል ድምፃቸውን እየሰማሁ ሰላምታ በመለዋወጥ ጤናቸውንና ደህንነታቸውን አረጋግጣለሁ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ፡** ሞባይል(ስልክ)

**እንቆቅልሽ 3**

ከቤት ውስጥ እገኛለሁ የቴክኖሎጂ ውጤት ነኝ ለጤና ተስማሚ ምግቦችን አዘጋጃለሁ ከብረት የተሰራሁ ነኝ ሁለት ጆሮ አለኝ በገጠርም በከተማም እገኛለሁ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ፡** ብረት ድስት

**እንቆቅልሽ 4**

በአብዛኛው በገጠር አካባቢ እገኛለሁ መልኬ ባይታይም በድምፄ ቁጥሮችንና ቃላትን ተጠቅሜ መረጃዎችን ሙዚቃዎችን ሁሉ አስተላልፋለሁ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ፡** ሬዲዮ

**እንቆቅልሽ 5**

በአብዛኛው በገጠር አካባቢ እገኛለሁ፤ ጤናማ ምግቦችን ለማዘጋጀት ይጠቀሙብኛል፤ የምዘጋጀው ከእንስሳት ፅዳጅ ነው፤ ለተወሰኑ ቀናት በእቃ(በጀሪካን) በመሆን በአፈር ውስጥ ተደብቄ እንደተሰጠኝ ቀናት ብዛት አቆያለሁ፤ ብረሃንም እሰጣለሁ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ፡** ባዮ ጋዝ

ውድ መምህር እንደዚህ እያሉ እርስዎ ከጠየቁ በኂላ ሁሉም ሕፃናት ቴክኖሎጅን ተጠቅመው እንቆቅልሽ እንዲናገሩ ይፍቀዱላቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** የእንቆቅልሽ መፅሀፍት፣ ሞዴሎች፣ የስዕል ካርድ እና የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች

**የምዘና ስልት፡** ምልከታ እንቆቅልሹን ሲከታተሉ በማየት፣ የቃል ጥያቄ፡ ከእንስሳት እዳሪ የሚገኘው ምንድን ነው፣ ለወጥ መስሪያ የሚያገለግለን እሳት ላይ የሚጣድ የቴክኖሎጂ ውጤት ምንድን ነው፣...... የፅህፈት ምዘና፡ በእንቆቅልሽ ውስጥ የሰማቸውን ቃላት እንዲፅፉ ያድርጉ፣

## ተግባር ሁለት፡ የመስክ ጉብኘት (5 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የቴክኖሎጂ ዉጤቶች፣ ፋብሪካ ፣ህግ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጉብኝት፣ በገለጻ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር በቅድሚያ ደስ የሚላቸውን የማነቃቂያ መዝሙር በማዘመር ወደ ውጭ በማስወጣት በስርአት በቁመታቸው እንዲሰለፉና እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ሕፃናት እገዛ በማድረግ ማሰለፍና ቅርብ ወደ ሆነ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቤተ ሙከራ ክፍሎች፣ የኮምፒዉተር ክፍሎች፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች፣የፋብሪካ መገኛ ቦታዎች በአጠቃላይ በአቅራቢያዎ ወደሚገኙ የቴክኖሎጅ ዉጤት በብዛት ወደሚገኝበት ቦታ በመዉሰድ ያስጎብኟቸዉ፤ ከተመለሱ በኋላ የተመለከቱትን ዘገባ በስዕል እንዲያቀርቡ ያድርጓቸዉ፤ በመጨረሻም እርስዎ ያዘጋጁትን ስለ ቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚያሳይ ስዕል/ሞዴል በመጠቀም ስለቴክኖሎጂ ዉጤቶች ምንነትና አስፈላጊነት ተጨማሪ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ማርከር፣ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ፣ እርሳስ፣የቴክኖሎጅ ዉጤቶችን የሚያሳይ ቻርት

**የምዘና ስልት:** በጉብኝት ወቅት ትዕዛዝን ማክበራቸውን ማየት፣ የቃል ጥያቄ፡ በጉብኝቱ ወቅት ምን መን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተመለከታችሁ

## ተግባር ሶስት፡ መዝሙር (7 ክ/ጊዜ)

### መዝሙር አንድ፡ (2 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የቴክኖሎጅ ጠቀሜታ፣ቁጥር፣ ጊዜ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር የአዘማመር ስርአትን በመከተል ያዘምራቸው፡፡

**የቴክኖሎጂ ጠቀሜታ**

ውድ ሕፃናት ስሙኝ ልገራችሁ፣
አንድ ሁለት ሦሥት ብለን ብንዘረዝራቸው፣
ተቆጥሮ አያልቅም የነሱስ ጥቅማቸው፡፡
ብዙ ጠቀሜታ አለው ቴክኖሎጂ፣
ጊዜንም ቆጥቦ ብዙ ሥራ ሰርቶ ያፋጥናል እንጂ፡፡
ድምፅን በማሰማት፣
ቁጥሮችን ተጠቅሞ እንዲሁም ቃላት፣
ይነጋገራሉ ጤናና ደህንነት፡፡
በቴክኖሎጂ ስዕልን በመሳል ፣
ብዙ ሥራ ሰርቶ ጊዜን ይቆጥባል፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቴክኖሎጂ መሳሪያ፣የቁጥር ካርድ፣

**የምዘና ስልት:** ሁሉም መዘመራቸውን ማየት፣ የቃል ጥያቄ፡ የቴክኖሎጂ ጥቅም ምንድን ነው፣ እናንተ የትኛውን የቴክኖሎጂ አይነት ተጠቅማችሁ ታውቃላችሁ፣.....

### መዝሙር ሁለት፡ ኮምፒተር (3 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የቴክኖሎጂ ጠቀሜታ፣ ስዕል፣ ምግብ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር የአዘማመር ስርአትን በመከተል ያዘምራቸው፡፡

**ኮምፒተር**

ኮምፒተር በመባል የሚጠራው ስሜ፣
ሰውን አስደሰትሁት ጊዜንም ቆጥቤ፡፡

አንዱ ሲፅፍ ቁጥር፣አንዱ ሲፅፍ ፊደል፣
ሌላም ጥቅም አለኝ ስዕልን ለመሳል፡፡
ለጤና ተስማሚ ምግብን ለመምረጥ፣
አስመርጣለሁኝ ሁሉንም በይበልጥ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቴክኖሎጂ መሳሪያ፣የቁጥር ካርድ፣

**የምዘና ስልት:** ሁሉም መዘመራቸውን ማየት፣ የቃል ጥያቄ፡ የቴክኖሎጂ ጥቅም ምንድን ነው፣ እናንተ የትኛውን የቴክኖሎጂ አይነት ተጠቅማችሁ ታውቃላችሁ፣.....

## መዝሙር ሦሥት: የስልክ ሞባይል(2 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የቴክኖሎጂ ጠቀሜታ፣ ቃላት፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር የአዘማመር ስርአትን በመከተል ያዘምራቸው፡፡

### የስልክ ሞባይል

የቴክኖሎጂ ውጤት የሆንሁኝ፣
ድምፅን በመጠቀም አገናኛለሁኝ፡፡
ሀሎ ሀሎ እያሉ ዘመድ ወዳጅ ሁሉ፣
ሰላምታ በመስጠት ይነጋገራሉ፡፡ (2)
እንዴት ነው ጤንነት ይላሉ ቀጥለው፣
ቃላትና ቁጥር ሁሉንም ተጠቅመው፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የሥልክ ፣የኮፒተር መዴል(ስዕል)፣የቃላት ካረድ፣የቁጥር ካርድ፣የተለያዩ ተስማሚ ምግብና መጠጥ የያዙ የስዕል ካረዶች...ወዘተ

**የምዘና ስልት:** ምልክታ ሲዘምሩ ማየትና ማዳመጥ፣የቃል ጥያቄ ፡ ሰው ከሰው ጋር በምን እንገናኛለን፣

## ተግባር አራት: ተረት (4 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የቴክኖሎጅ ዉጤቶች፣ ገጠር፣ ከተማ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በትረካ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** ውድ መምህር ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በመንገር ከተረት ምን እንደተማሩ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡

### የከተማና የገጠር ልጅ

አንድ በከተማ አካባቢ የሚኖር የ6 ዓመት ልጅ እና በገጠር አካባቢ የሚኖር የ6 ዓመት ልጅ ነበሩ፡፡ ሁለቱም ዘመዳሞች ናቸው፡፡ ስለሆነም የከተማው ልጅ ትምህርት ሲዘጋለት ለዕረፍት ገጠር ወዳለው ዘመዱ ከአባቱ ጋር ሔደ፡፡ የገጠሩ ልጅም በጣም ደስ አለው እና እቅፍ በማድረግ ሰላምታ

ከተሰጣጡ በኋላ ወደ ቤት ገቡ። ከዚያም የከተማው ልጅ ያጎቴ ልጅ ቴሌቬዥን፣ኮምፒተርና ታብሌት የላችሁም ብሎ ሲጠይቀ ያክስቴ ልጅ አሁን ያልሃቸውን ነገሮች እኔ አላውቃቸውም ከእኛ ቤትም የሉም ብሎ መለሰለት። የከተማው ልጅም  እና ምንምን ነው ያላችሁ  ሲለው የገጠሩ ልጅም  ከእኛ ቤት ያለው ሶላር፣ ሬዲዮ፣ ባዮ ጋዝና የእጅ ባትሪ አለን አለው ነው ያጎቴ ልጅ በማለት ሁለቱም በአካባቢያቸው የሚገኙ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን  ተነጋግረው ተግባቡ። በመቀጠልም የከተማው ልጅ ስንት በሬ አላችሁ ብሎ ጠየቀው የገጠሩ ልጅም እርሻ የሚያርሱ ሁለት በሬዎች፣ለጤናችንና እንድናድግ ወተት የምሰጠን አንድ ላም  አሉን። የከተማው ልጅም በጣም ደስ ይላል በማለት ሬዲዮውን በመክፈት የተለያዩ መልክቶችን፣ ሙዚቃዎችንና ድራማዎችን ከሰሙ በኋላ አብረው ተጫወቱ።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡** የሁለቱም ዕድሜ ስንት ነው? የማን ዕድሜ ይበልጣል? በገጠር አካባቢ የሚገኙ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

**ምክር፡** ውድ ሕፃናት የቴክኖሎጂ ውጤቶች በከተማ አካባቢ ብቻ የሚገኙ ሳይሆን በገጠር አካባቢ እንደሚገኙና ምን ምን እንደሆኑ ማወቅ እና መረዳት አለባችሁ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የተረት መፅሀፎች፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ሞዴል(ስዕል)፣ የተለያዩ አትክልትና ፍራፈሬ ስዕል

**የምዘና ስልት፡** ተረቱን መልሰው ሲናገሩ በማዳመጥ መመዘን፣ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፡ የገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኘው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ምን ምን ናቸው፣ ከተማ ላይስ የሚገኙት ምን ምን ናቸው፣የሁለቱም ዕድሜ ስንት ነው? የማን ዕድሜ ይበልጣል? በገጠር አካባቢ የሚገኙ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

## ተግባር አምስት: የክፍል ዉጭ ጨዋታ (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የቴክኖሎጂ የመጫወቻ ቁሳቁሶች፣ዕዳት፣ ቃላት፣

**የመማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣በቡድን

**የመምህር ሚና፡** መምህር ህፃናትን ወደ ዉጭ ይዘዉ በመዉጣት ለማነቃቂያ የሚሆን የተወሰነ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲሰሩ ካደረጉ በኋላ ህፃናትን በትላልቅ ቡድን በማደራጀትና የቴክኖሎጂ ዉጤት የሆኑ የመጫወቻ ቁሳቁሶችን በመጠቀም በየቡድናቸዉ ተራበተራ እንዲጫወቱ በማድረግ የቴክኖሎጂ የመጫወቻ ቁሳቁሶችን ስምና ጠቀሜታ በስንት ቁሳቁሶች እንደሚጫወቱና እንዴት በጥንቃቄ መጫወት እንዳለባቸዉ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸዉ፣ በመቀጠልም በየቡድናቸዉ ሸርተቴ፣ ዥዋዥዌ፣ ሚዛን፣ ሽክርክሪት እና የመሳሰሉ በመጠቀም እንዲጫወቱ አድርጉ፡፡ በመጨረሻም የተጠቀሙባቸዉን የመጫወቻ ቁሳቁሶች እንዲያፀዱና እንዲያስተካክሉ ያድርጓቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** ሸርተቴ፣ ዥዋዥዌ፣ ሚዛን፣ ሽክርክሪትና በትምህርት ቤትዎ ቅጥር ጊቢ ዉስጥ የሚገኙ የቴክኖሎጅ ዉጤት የመጫወቻ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት፡** የጨዋታ እንቅስቃሴያቸዉን በምልከታ ማረጋገጥ፣ የቃልጥያቄ (ምንምን የቴክኖሎጅ የመጫወቻ ዉጤቶችን ተጠቅማችሁ ተጫወታችሁ፣

## ተግባር ስድስት፡ ፕሮጀክት (6 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የቴክኖሎጂ ዉጤት፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ልብሶች

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣በገለፃ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር የፕሮጀክት ስራ ከመስጠትዎ በፊት የህፃናት የቀድሞ እውቀት በመጠቀም ስላላቸው የፈጠራ ችሎታ በአካባቢያቸው ያዩትንና የሚያውቁትን የቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ባህላዊ ቅርሶች፣ ተስማሚ ምግብና መጠጦች፣ ቴክኖሎጂን መጠቀም የእርሻ ሥራ ወይም አትክልትና ፍራፍሬዎችን፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ( ለምሳሌ፡ የኤሌክትሪክ ምድጃ፣ሞባይል፣ ኮምፒዉተር፣ ሶላር፣ ባዮ ጋዝ፣ የሸንኩርት መፍጫ፣ የተለያዩ ጁሶችን ፈጭተን የምንጠቅበት የጁስ መፍጫ) እነዚህን እንደ ሕፃናቱ ዕድሜ የሚወዱትንና የሚያደንቁትን ሰዕል ወይም ሞዴል ሰርተው እንደያመጡ፡፡ በመቀጠልም ሁሉም ሕፃናት በተራ እየተነሱ ሰርተው ያመጡትን ሞዴል ወይም ስዕል ለጓደኞቻቸዉ በደንብ እያብራሩ በመጀመሪያ ምን እንደሰሩ፣ እንዴት እንደሰሩት ስንት አይነት የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተጠቅመዉ እንደሰሩ በደንብ በማብራራት የሰሩትን ፕሮጀክት እንዲያቀረቡ ያድርጉ፡፡

የሁሉንም ሕፃናት ፕሮጀክት ከተመለከቱና ከሰሙ በኋላ እርሰዎ ደግሞ የሚከተሉትን ጥያዎች ይጠይቋቸው፡፡በመጀመሪያ የሰሩትን ማድነቅና ምን እንደሰሩ መጠየቅ? ምን ምን ነገሮችን ተጠቅመው እነደሰሩት መጠየቅ? እንዴት እንደሰሩት በቅደም ተከተል እንዲናገሩ ማድረግ? የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተናገሩ? ባህላዊ ልብሶች የሚባሉት ምን ምን ይባላሉ? በመጨረሻም በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ...ላይ የሚፈልጉትን ስዕል በመሳል ቀለም ቀብተው እንዲያመጡ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የተለያዩ የቴክኖሎጂ ስዕሎች.ፎቶዎች፣ ቪድዮ፣ ስዕሎችና ሞዴሎች፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ ካርቶን፣የቁጠር ካረዶች፣ የተለያዩ ምግብና መጠጥ የያዘ ስዕል... ወዘተ

**የምዘና ስልት፡** በቃል መጠየቅ፣ምን አይነት የቴክኖሎጂ ውጤት ሰራሽ/ህ ፣ ይንን ለመስራት ምን ምን ተጠቀምክ፣ ይህ የተሰራው ዕቃ ምን አገልግሎት ይሰጠናል/ የተሰጣቸውን ፕሮጀክት ማየትና መመዘገብ ፡፡

# አራተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክለፍ ጊዜ/15 ሰዓት

### አጥጋቢ መማር ብቃቶች፡

- ✓ ለጓደኞቻቸው ለመደወል እና መልዕክቶችን ለመቀበል የስልክ ሞዴሎችን ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ በስልኮች/ኮምፒውተር ሞዴሎችን በመጠቀም ስለራሳቸውና ስለቤተሰቦቻቸውይናገራሉ፡፡
- ✓ ስልክን በመጠቀም ስለትምህርትቤታቸዉ ይናገራሉ፡፡
- ✓ ስልኮችን በመጠቀም ይናገራሉ፡፡
- ✓ ለመዝለልና ለመለጠጥ የሚያገለግሉ የቴክኖሎጅ መሳሪያዎችን ተጠቅመዉ የአካል እንቅስቃሴ ይሰራሉ፡፡
- ✓ የዲጅታልና የህትመት ቴክኖሎጅን በመጠቀም በቅርብ አካባቢያቸዉ የሚገኙ የተለያዩ እንስሳትን እና ዕፅዋትን ስም ይናገራሉ፡፡
- ✓ የዲጅታል ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም መዝሙሮችን ይዘምራሉ፡፡
- ✓ ቁጥርን ለመቁጠር ዲጅታል ቴክኖሎጅን ይጠቀማሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** ማኅበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን መግለጽ፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣ ቅጥ፣ ጥበባዊ እሴት

## ተግባር አንድ፡ በስራ መማር (7 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ራስን መግለፅ፣ ማህበራዊ ግንዛቤ፣ ጥበባዊ እሴት፣ድምፅ፣

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በስራመማር፣ በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ህፃናትን ለማነቃቃት ያስችል ዘንድ የሚያዉቁትን አንድ መዝሙር እንዲዘምሩ በማድረግ ከክፍል ዉጭ ይዘዋቸዉ ይዉጡ፡፡

በትናንሽ ቡድን በመከፋፈል በየቡድናቸዉ ከቻሉ ሁለት ሁለት የሞባይል ስልክ ካልቻሉ ደግሞ የስልክ ሞዴሎችን በካርቶን ወይም ወፍራም ወረቀት እርስዎ ከህፃናቶች ጋር በጋራ በማዘጋጀት በየቡድናቸዉ በመስጠት ጥንድ ጥንድ በመሆን የስልክ ንግግር ስርአትን ሰላምታ አሰጣጥ፣ ራስን መግለፅ(ስለሚማሩበት ትምህርት ቤት፣ ስለራሳቸዉ)፣ ጥያቄ አጠያየቅ/መልስ አሰጣጥ፣ አክብሮትና መሰል ልዉዉጦችን በሞባይል ስልክ ወይም የስልክ ሞዴሎች እንዲያወሩ ያድርጓቸዉ፡፡ህፃናት ተራ በተራ በአካባቢያቸዉ የሚገኙ የትላልቅ ሰዎችን ድምፅ በማስመሰል በሞባይል/በስልክ እንዲያወሩ ያድርጓቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የሞባይል ስልክ፣ የስልክ ሞዴሎችን ለመስራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች (ካርቶን፣ ወፍራም ወረቀት፣ ከለር እርሳስ፣ መቀስ እና ሌሎች)

**የምዘና ስልት፡** የቃላት እውቀት እድገታቸዉን በቸክ ሊስት መመዘን፣ ምልከታ፣ የፈጠራ ስራቸዉን መመልከት፣ የቃል ጥያቄ፡ በስልክ ከማን ጋር ተነጋገርክለሽ፣ ስለምን አወራችሁ፣ መጀመሪያ የደወለው ማነው፣ አንስተህ/ሽ ምንአልክ/ሽ፣

## ተግባር ሁለት፡ የክፍል ዉስጥ ጨዋታ (5 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ቅጥ፣ ጥበባዊ ግንዛቤ፣ ቀን፣ ወር፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣ቃላት፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ ፣ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣

**መምህር ሚና፡** መምህር ህፃናትን ለማነቃቃት ያስችል ዘንድ በክፍል ዉስጥ በነፃነት እንዲዘሉ እና የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ ያድርጓቸዉ፡፡

ከቻሉ ኮምፒዉተር/ላፕቶፕ በመጠቀም ካልቻሉ ደግሞ በኮምፒዉተር ተፅፈዉ በወፍራም ወረቀት ፕሪንት የሆኑ ብዛት ያላቸዉ የተለያዩ ቀለማትን፣ ቅርፃቅርፆችን(ክብ፣ አራትማእዘን፣ ሞላላ፣ሶስት ማእዘንና ሌሎች ቅርፃቅርፆችን)፣ የተገነጣጠሉ የእንስሳት አካል ክፍሎችን፣ የእያንዳንዱን የቀለማትን እና ቅርፃቅርፆችን የመጀመሪያ ፊደላቶችን የያዙ ወረቀቶችን በማዘጋጀት ህፃናትን በትናንሽ ቡድን በማደራጀት የተዘጋጀዉን ቁሳቁስ እኩል ያከፋፍሏቸዉ፡፡

በየቡድናቸዉ የመጀመሪያ ፊደል የያዙትን የፊደል ካርዶች የሚዛመዳቸዉን ቀለማትና ቅርፃቅርፆች፣ ስም በማሰብ(ለምሳሌ ሶ ሶስት ማእዘን፣ ቀ ቀይ  በማለት) ቃላቶቹን እንዲያሟሉ ያድርጉ፡፡

ተመሳሳይ ቀለማት፣ ቅርፃቅርፆችን፣ ቀለማትን በአይነት በአይነታቸዉ እና በመጠን በመጠናቸዉ እንዲመድቡና የተቆራረጡ የእንስሳት አካል ክፍሎችን ፈልገዉ በመገጣጠም ስማቸዉን እንዲፅፉ ያድርጓቸዉ፡፡የቀለማት አይነቶችን፣ የእንስሳትን ብዛት እንዲቆጥሩና በአይነት በአይነት እንዲመድቡ ይጠይቋቸዉ፡፡የመለማመጃ ደብተራቸዉ ገፅ  ላይ የሚገኙ ቅርፃቅርፆችን በቀለማቸው እንዲመድቡ ስማቸውን  እንዲፅፍ ያድርጓቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የተለያዩ ቅርፃቅርፆች፣ ቀለማት፣ የተለያዩ ፍደላትን የያዘ ካርድና የተለያዩ የእንስሳት አካል ክፍሎችን የያዙ ካርዶች፣ቻርት ወረቀት ላይ የተሳለ የሰውየአካል ክፍሎች፣

**የምዘና ስልት፡** የቃል ጥያቄ(ምን ምን ቀለማትን አገኛችሁ? ብዛታቸዉ ስንት ነዉ? የገጣጠማችኋቸዉ እንስሳቶች ምንምን ናቸዉ?

## ተግባር ሶስት፡ መዝሙር (7 ክፍለጊዜ)

### መዝሙር አንድ (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ማህበራዊ ግንዛቤ፣ ራስንመግለፅ፣ ጥበባዊ እሴት፣ጤና

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ቀጥሎ የተቀመጠውን መዝሙር ያዘማመር ስርዓትን በመከተል ያዘምራቸው፣

## መዝሙር አንድ

ርዕስ ፡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም
ስልክ አይናችንን ብዙ እንዳይጎዳን፣
ለአጭር ጊዜ ቆይታ እንጠቀማለን፡፡
ድምፃችን ለመቅረፅ ለማዳመጥ ተረት፣
ለመዝለል ለመሮጥ ስፖርት ለመስራት፣
አብረን በመከተል በእስክሪን በማየት፣
ቁጥሮችን ለመቁጠር አንድንና ሁለት፣
ስዕልን ለመለየት በአይነት በአይነት፣
ማወቅ ይገባናል አጠቃቀም ከፊት፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** መዝሙሩን ቀርፀው ለማሰማት ቴብ፣ ፍላሽ፣ ሞንታርቦ፣ ሞባይል፣ ቪድዮ፣

**የምዘና ስልት:** የቃልጥያቄ፡ በመዝሙሩ ዉስጥ ያሉ የቴክኖሎጂ ዉጤቶች ምንምን ናቸዉ፣ስልክ ለረጅም ጊዜስናይ አይናችን ምን ይሆናል፣የቃላት ክምችታቸዉን እድገት መመዘን፣ ምልከታ፡ ሲዘምሩ በማየት፣

## መዝሙር ሁለት(3 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ሀላፊነት፣ ቀለማት፣ ቴክኖሎጂ፣ጤና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር ቀጥሎ የተቀመጠውን መዝሙር ያዘማመር ስርዓትን በመከተል ያዘምራቸው፣

ርዕስ ፡ ሄሎ ጓደኛዬ
ሄሎ ጓደኛዬ እንዴት አምሽተሻል፣
ከትምህርት ቤት መልስ ቤት ስራ ሰርተሻል፣
እኔ ሰርቻለሁ እንስሳትን በአይነት መድቤአቸዋለሁ፣
የቤትና የዱር ብዬ አስቀምጫለሁ፣
ቀለማትን በአይነት መድቤአቸዋለሁ፣
ራሴን በራሴ በስልክ ቀርፃለሁ፣
አሁን ልተኛ ስል ጥርሴን ቦርሻለሁ፣
ቴክኖሎጅን እኔ ተጠቅሜዋለሁ፣
አንችም እንደሰራሽ እተማመናለሁ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** መዝሙሩን ቀርፀው ለማሰማት ቴብ፣ ፍላሽ፣ ሞንታርቦ፣ ሞባይል፣ ቪድዮ፣ የጥርስ ቡርሽ ምስል፣
**የምዘና ስልት:** የቃልጥያቄ፡ በመዝሙሩ ዉስጥ ያሉ የቴክኖሎጂ ዉጤቶች ምንምን ናቸዉ፣ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምን ምን ማድረግ እንችላለን፣ የቃላት ክምችታቸዉን እድገት

መመዘን፣ ምልከታ ሲዘምሩ በማየት፣

## ተግባር አራት ፡ የክፍል ዉጭ ጨዋታ (5 ክፍለጊዜ)

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣

**የመምህር ሚና:** መምህር ለህፃናት የክፍል ዉጭ ጨዋታ ክፍለ ጊዜ መሆኑን ይንገሯቸዉና ከክፍል ዉጭ ይዘዋቸዉ ይውጡ። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጨዋታ እንደሚጫወቱ ይንገሯቸዉና በጨዋታዉ ሂደት ስለሚከተሏቸዉ የጥንቃቄ መርሆዎች በሚገባ ያስገንዝቧቸዉ፤በመቀጠል ህፃናቶችን በትናንሽ ቡድኖች በመከፋፈል ለአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያገለግሉ የቴክኖሎጂ ዉጤቶችን ለምሳሌ መንሸራተቻ፣በአንድ እግርና በሁለት እግር ገመድ መዝለያ፣ዥዋዥዌና መሰል መጫወቻዎችን በየቡድናቸዉ በመከፋፈል በዙር በዙር እንዲጫወቱ ያድርጓቸዉ። እርስዎም ተገቢዉን ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸዉ።በመጨረሻም ወደ ክፍል በማስገባት ምንምን ጨዋታዎችን እንደተጫወቱ እና የተጠቀሟቸዉን የመጫወቻ የቴክኖሎጅ ዉጤቶች እንዲናገሩ ያድርጓቸዉ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** መንሸራተቻ፣ ዥዋዥዌ፣ ገመድ እና ሌሎች አካባቢያዊ የመጫወቻ ቁሳቁሶች፣ በቪድዮ የተቀረጸሲጫወቱ የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል፣

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ: ምንምን ጨዋታዎችን ተጫወታችሁ የተጠቀማችኋቸዉ የመጫወቻ የቴክኖሎጂ ዉጤቶች ምንምን ናቸዉ ፣ ምልከታ: ሲጫወቱ በማየት፣

## ተግባር አምስት የፕሮጀክት ስራ (6 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣ ጥበባዊ እሴት፣ ማህበራዊ ግንዛቤ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣

**የመምህር ሚና:** ዉድ መምህር ህፃናትን በትናንሽ ቡድን በመከፋፈል በየቡድናቸዉ ዘመናዊና ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን አካባቢያዊ በሆኑ ቁሳቁሶች ሰርተዉ እንዲያመጡ በእጣ ያከፋፍሏቸዉ፤ይዘዉ ከመጡ በኋላም የሰራቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎች ስማቸውን እንዲናገሩ እድል ይስጣቸው ከዚያም የሰሩትን የሙዚቃ መሳሪያ ይዘው ከክፍል ዉጭ በመዉጣት መሳሪያዎቹን በመጠቀም ዘመናዊና ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎችን እንዲጫወቱ በስልክዎ የተቀረፀ ባህላዊና ዘመናዊ ዘፈን ካሰሟቸዉ በኋላ እነሱ እንዲጫወቱ ያድርጓቸዉ፤ አብረዋቸዉ በምትም ሆነ በጭፈራ ተግባር ይሳተፉ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** አካባቢያዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ መስሪያ ቁሳቁሶች፣ በስልክ በድምፅም ሆነ በቪዲዮ የተቀረፁ ባህላዊና ዘመናዊ የዉዝዋዜ ዘፈኖች፣ፍላሽ፣ ቴብ፣ የሙዚቓ መሳሪያ ምስል፣

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ: ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ የቴክኖሎጅ ዉጤቶች ምንምን ናቸዉ፣ በጨዋታዉ ምን ተሰማችሁ፣ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ የምንላቸው ምን ምን ናቸው፣ዘመናዊስ፣ ምልከታ: የሰሩትን በማየት።

# አምስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክለፍ ጊዜ/15 ሰዓት

### አጥጋቢ መማር ብቃቶች፡

- ✓ የግብረ ገብ እሴቶችን በማዳበር ከሌሎች ጋር አወንታዊ ግንኙነት ያደርጋሉ፡፡
- ✓ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቦታዎች/አካባቢዎችን ይረዳሉ፡፡
- ✓ ነገሮችን በአይነት በአይነታቸዉ በመለየት ያደራጃሉ፡፡
- ✓ የነገሮችን መገኛ ይገልፃሉ፡፡
- ✓ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉን ፊደላት ይለያሉ፡፡+
- ✓ ስልክ በመጠቀም የራሳቸዉን ግንዛቤ ይፈጥራሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** የግብረ ገብ እሴት፣ የፊደላት ድምፅ ግንዛቤ፣ የቦታ መገኛ ግንዛቤ፣ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ አካባቢዎች፣ መለየት እና መመደብ፣ የፈጠራ ስራን መግለፅ

## ተግባር አንድ የክፍል ዉስጥ ጨዋታ (16 ክፍለጊዜ)

### ጨዋታ አንድ፡ (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የግብረገብ እሴቶች፣የቦታ አቅጣጫ፣ ተፈጥሯዊና ሰዉ ሰራሽ ፣ፈጠራን መግለፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ በተግባር

**የመምህር ሚና፡** ዉድ መምህር ይህ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንደመሆኑ ህፃናት ቅዳሜና እሁድ ምንምን ተግባራትን እንዳከናወኑ ለጓደኞቻቸዉ እርስ በርሳቸዉ እንዲነጋገሩ ለተወሰነ ደቂቃ እድል ይፍጠሩላቸዉ፡፡

ህፃናትን በትናንሽ ቡድን በመከፋፈል ካገኙ ለየቡድናቸዉ ሁለት ሁለት ስማርት የሞባይል ስልኮችን ይስጧቸዉ ካላገኙ ደግሞ ወፍራም ወረቀት/ካርቶን፣ መቀስ፣ ከለር እርሳስና ሌሎች አካባቢያዊ ቁሳቁሶችን ተጠቅመዉ የስልክ ሞዴሎችን ከህፃናት ጋር አብረዉ በመሆን ያዘጋጁ፡፡ እርስዎ በቅድሚያ ስልክ በመጠቀም እንዴት ፎቶ ማንሳት እንዳለብን እራስዎን በማንሳት ያሳዩና ቀጥሎ ህፃናቶች ጥንድ ጥንድ በመሆን እርስ በእርስ ፎቶ እንዲነሱና እርስ በእርስ በመተያየት እንዲደናነቁ፣ በአክብሮት፣በፍቅር አገላለፅ፣ እንዲደናነቁና የተሳሳተ ፎቶ ካነሱ በማጥፋት ድጋሚ እንዲያነሱ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** ስማርት የሞባይል ስልኮች/የስልክ ሞዴሎችን ለመስራት የሚያገለግሉ አካባቢያዊ ቁሳቁሶች፣ ሞባይል ስልክ፣ ፎቶ፣

**የምዘና ስልት፡** በቃል ጥያቄ ፎቶ ምንን በመጠቀም አነሳህ/ሽ፣ ፣ ምልከታ፣ እርስ በእርስ ሲነሳሱ በማየት፣

### ጨዋታ ሁለት (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** መምረጥ፣ መመደብ፣ ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ አካባቢ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ

**የመምህር ሚና:** መምህር ህፃናትን ለማነቃቃት ያስችል ዘንድ አንድ የመረጡትን መዝሙር እንዲዘምሩ እድል ይስጧቸዉ።

እርስዎ የቴክኖሎጅ ዉጤቶች ለምሳሌ ለመጓጓዣ የሚያገለግሉ መኪና፣ ጀልባ፣ አዉሮፕላን የፅህፈት አገልግሎት ኮምፒዉተርና ሌሎችን፣ በተመሳሳይ የእነዚህን የቴክኖሎጅ ዉጤቶች ስም የመጀመሪያ/መካከለኛ/መጨረሻ ፊደላትን የያዙ ቁርጥራጭ ካርዶችንና ምስሎችን በማዘጋጀት ህፃናትን በትናንሽ ቡድን ከከፋፈሉ በኋላ በየጠረጴዛቸዉ እኩል እኩል ምስሎችንና ጎደሎ ፊደላት የያዙ ካርዶችን እንዳይታዩ በጀርባ ሸፍኖ ማስቀመጥ እርስዎ በየቡድናቸዉ በየተራ በመዘዋወር የጎደሉ ፊደላቶችን ፅፈዉ እንዲያሳዩና ቃላቶቹን የሚገልፁትን ስእሎች እንዲያዛምዱ ካደረጉ በኋላ ተግባሮቻቸዉን ይጠይቋቸዉ።

እርስዎ ምን ያክል በትክክል እንደተሰራ ማስታወሻ በመያዝ ቡድኑን ከቡድን ያወዳድሯቸዉ።

በመጨረሻ የመለማመጃ ደብተራቸዉ ገፅ ላይ የሚገኘዉን የቴክኖሎጅ ዉጤት የጎደሉ ስሞቻቸዉን በመሙላት ከምስሎቻቸዉ ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸዉ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቴክኖሎጅ ዉጤቶችን የያዙ ካርዶች፣ የጎደሉ ፊደላትን የያዙ ካርዶች፣ የመለማመጃ ደብተር

**የምዘና ስልት:** የቃልጥያቄ: ለመጓጓዣ የሚያገለግሉ የቴክኖሎጅ ዉጤቶች ምንምን ናቸዉ፣ምልከታ: ጨዋታውን ሲጫወቱ በማየት

## ጨዋታ ሶስት: (3 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የፊደላት ድምፅ፣ መምረጥና መመደብ

**የመምህር ሚና:** መምህር እርስዎ የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ( ለምሳሌ የመሬት መልክአ ምድራዊ አቀማመጥን የሚያሳይ ስዕል፣ ጨረቃ፣ ፀሀይ፣ አዉሮፕላን፣ መኪና፣ ዛፎች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች የመሳሰሉትን በወፍራም ቁርጥራጭ ካርድ ፕሪንት አድርገዉ ያዘጋጁ፤የሚያገኙ ከሆነ በኮምፒዉተር/ስልክ ከኢንተርኔት አዉርደዉ ያሣዩአቸዉ፤ ስለተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ነገሮች ምንነትና ልዩነት ግንዛቤ ፍጠሩላቸው።

ህፃናቶችን በትናንሽ ቡድኖች ከከፋፈሉ በኋላ በየቡድናቸዉ ስእሎቹን በመመልከት ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ በማለት እና ስማቸዉን እንዲለዩ በማድረግ ክትትልና ድጋፍ ያድርጉላቸዉ።ከጨረሱ በኋላ ከየቡድናቸዉ አንድ አንድ ህፃን እድል በመስጠት የሰሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

በጨረሻም የመለማመጃ ደብተራቸዉ ገፅ ላይ ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ነገሮችን እንዲፅፉ ያድርጓቸዉ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ነገሮችን የያዙ ካርዶች፣ኮምፒዉተር፣ ስልክ

**የምዘና ስልት:** የቃልጥያቄ(ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽነገሮች ምን ልዩነት አላቸዉ? ምንምን አያችሁ? በቁጥር ስንት ናቸዉ?)ምልከታ: ሲጫወቱ በማየት

## ጨዋታ አራት (3 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** አካላዊ፣ ተፈጥሮአዊ፣ ሰው ሰራሽ፣ቅርፃ ቅርፅ፣

**የመምህር ሚና:** መምህር ህጻናትን ለማነቃቃት ያክል ከመቀመጫቸዉ ተነስተዉ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ያድርጓቸዉ፡፡

እርስዎ ከቻሉ በኮምፒዉተር በኢንተርኔት አዉርደዉ ያሳዩአቸዉ ካልቻሉ ደግሞ ከኮምፒዉተር ፕሪንት የሆኑ የተለያየ ቅርፃቅርፆች(ሶስት ማእዘን፣ ሞላላ፣ ክብ፣ አራት ማእዘን..)የተለያየ ቀለምያላቸዉ ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ነገሮች(ብርቱካን፣ ቀይ አበባ፣አረንጓዴ ካርዶች፣ስልኮች..) በመጠን( የተለያየ መጠን በብዛት ያላቸዉ ጨሌ /ዶቃ/ቁልፍ) የያዙ ቁርጥራጭ ካርዶችን ያዘጋጁ፡፡

ህፃናትን በትናንሽ ቡድን ከከፋፈላችሁ በኋላ ያዘጋጁትን የተለያየ ቅርፅ፣መጠን፣ቀለም የያዙ ካርዶች በየቡድናቸዉ እኩል እኩል ያከፋፍሏቸዉ በመቀጠልም በመጠን፣ በቀለምና በቅርፅ እንዲለዩና እንዲቆጥሯቸዉ በማድረግ ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸዉ፡፡ ከጨረሱ በኋላ አንድ አንድ የቡድን አባል ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ እድል ይስጣቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ኮምፒዉተር/ስማርትስልኮች፣ የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን፣ የተለያዩ መጠኖችንና ቀለማትን የያዙ ፕሪንት የሆኑ ካርዶች

**የምዘና ስልት: የቃልጥያቄ:** ምንምን ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ነገሮችን አያችሁ ስንት አይነት ቅርፃቅርፆች አገኛችሁ? ስንት አይነት መጠን ያላቸዉ ነገሮችን አገኛችሁ? ምንምን አይነት መጠን አላቸዉ?)ምልከታ: ጨዋታውን ሲጫወቱ በማየት፣

## ተግባር ሁለት: ተረት (3 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ፣ እንስሳት፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በትረካ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ በተግባር

**የመምህር ሚና:** መምህር ቀጥሎ የቀረበዉ ተረት ቀድመዉ እርስዎ በማንበብና በስልክዎ/ሪከርደር ተጠቅመዉ ተረቱን ተርተዉ በመቅረፅ ይዘዉ ወደ ት/ቤት ይምጡ፤በመቀጠል ህፃናትን በክፍል ዉስጥ ለማዳመጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ካደረጉ በኋላ ህፃናትን ተረቱን አዳምጠዉ እነሱ ደግሞ በራሳቸዉ አገላለፅ የሰሙትን ደግመዉ እንዲተርቱ ተራ በተራ እድል ይስጧቸዉ፡፡በመስጠት በመጨረሻም የምዘና ጥያቄዎችን ይጠይቋቸዉ፡፡

### ታታሪዋ ሜሮን

ሜሮን የቅ/አንደኛ ደረጃ ሶስት ተማሪ ስትሆን ሁለት ወንድሞችና አንድ እህት አሏት፤ሜሮን በስነምግባሯ ለወላጆቿና ለመምህራኖቿ ታዛዥ፣ታማኝና ጨዋ ልጅ ናት፤የመኖሪያ ቤቷ ከትምህርት ቤቷ የተወሰነ ርቀት ቦታ ላይ የሚገኝ ሲሆን ት/ቤት እንዳይረፍድባት ሁልጊዜ በጧት ተነስታ ከጓደኞቿ ጋር ወደት/ቤት ትሄዳለች፤አንድ ቀን መምህራቸዉ ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ለሚባሉትን ነገሮች ምሳሌ ፅፈዉ እንዲመጡ የቤት ስራ ትሰጣቸዋለች፤እሷም የመኖሪያ ቤታቸዉ በተፈጥሯዊ እፅዋቶችና ተክሎች ለምሳሌ ፅድ፣ባህርዛፍ፣የፍራፍሬ ተክሎች የተሞላ በመሆኑ ቤታቸዉ ዉስጥ የቤት እንስሳቶች ዶሮ፣ድመት፣ዉሻ፣ላም፣በሬ፣አህያ የመሳሰሉትን ያሉ በመሆኑ በፅሁፍ በመፃፍና በስዕል በመሳል፤ሰዉ ሰራሽ ነገሮችን ደግሞ በቤታቸዉ ዉስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችንና

የትምህርት ቤት አገልግሎት መስጫ ቁሳቁሶችን በማስታወስ በሚገባ ፅፋ ወደ ት/ቤት ሄደች፤ መምህርቷም በሜሮን ጎበዝ መሆን ተደስታ በማበረታታት ወደሚቀጥለዉ ክፍለጊዜ ቀጠለች፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የሞባይል ስልክ/ሪከርደር ፣ተፈጥሮአዊና ሰውሰራሽ ነገሮችና እንስሳት ያሉበት ተንቀሳቃሽ ምስል፣

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ: ሜሮን በስነምግባሯ ምን አይነት ልጅ ናት? ምንምን አይነት ተፈጥሯዊ እና ሰዉሰራሽ ነገሮችን ለቤትስራዋ ፃፈች? ተረቱን በምን አዳመጣችሁ ምን ተሰማችሁ?

## ተግባር ሶስት: የክፍል ዉጭ ጨዋታ (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የቦታ አቅጣጫ፣ ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ አካባቢ፣ የፊደላት ድምፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በቡድን፣ በጥያቄና መልስ፣በገለጻ

**የመምህር ሚና:** መምህር ህፃናትን የክፍል ዉጭ ጨዋታ ክፍለ ጊዜ መሆኑን ይንገሯቸዉና በሰልፍ ወደ ዉጭ ይዘዋቸዉ ይዉጡ፡፡

ህፃናትን በትናንሽ ቡድን ይከፋፍሏቸዉና በትምህርት ቤቱ ቅጥርግቢ ዉስጥ የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ምንምን እንደሆኑና የሚገኙበትን አቅጣጫ/ከላይ፣ ከታች፣ ከስር፣ ከዉስጥ፣ግራ፣ ቀኝ፣ ፊት፣ ኋላ የሚባሉትን አቅጣጫዎች፣ በቅጥር ግቢዉ ዉስጥ የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ነገሮችን በመጎብኘት እንዲለዩ በማድረግ እርስዎም በስልክ የምስል ቀረፃ ያድርጉ፡፡

የህፃናትዎ ብዛት ብዙ ከሆነ በመከፋፈል በዙር በዙር እንዲጎበኙ ያድርጓቸዉና ከጨረሱ በኋላ ወደ ክፍል ይዘዋቸዉ ይግቡና የተመለከቷቸዉን ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ነገሮች የቴክኖሎጂ ዉጤቶችን ጨምሮ የመገኛ አቅጣጫዎችን እንዲናገሩ ተራበተራ እድል ይስጧቸዉ፡፡

በመጨረሻም ህፃናትን በየትናንሽ ቡድኖቻቸዉ እርስዎ የቀረፁትን ምስል ተራበተራ በማሳየት እንዲዝናኑና እንዲነጋገሩ ካደረጓቸዉ በኋላ የጨዋታዉን ጭብጥ ያስገንዝቧቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ዉስጥ የሚገኙ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች፣ ተፈጥሯዊና ሰዉሰራሽ ነገሮች፣ የሞባይል ስልክ/ሪከርደር

**የምዘና ስልት: የቃልጥያቄ:** የመመገቢያ ክፍላችሁ ከመማሪያ ክፍላችሁ በየትኛዉ አቅጣጫ ይገኛል? ምንምን ሰዉሰራሽ ነገሮችን አያችሁ? ብዛታቸዉ ስንት ነዉ? ስልኩን/ሪከርደሩን ለምን አገልግሎት ተጠቀማችሁበት?) ምልከታ፣ የቃላት እውቀት እድገታቸዉን መመዘን

## ተግባር አራት: የፕሮጀክት ስራ(4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መምረጥና መመደብ፣ተፈጥሯዊናሰዉሰራሽ አካባቢ

**የማስተማሪያ ዘዴ በፕሮጀክት ስራ መማር**

**የመምህር ሚና:** መምህር እባክዎትን ህፃናትን ለማነቃቀት ያክል አንድ መዝሙር መርጠዉ እንዲዘምሩ ያድርጓቸዉ፡፡ከቻሉ በስልክዎ/ኮምፒዉተር/ሌሎች ስክሪኖች በመጠቀም ካልቻሉ ደግሞ ፕሪንት ሆነዉ /ተቀርፀዉ የወጡ/ይህንም ካልቻሉ የተለያዩ ከለር እርሳሶችን/ ማርከሮችነ እና ወፍራም ወረቀቶችን ተጠቅመዉ በአካባቢዎ የሚገኙና በአብዛኛዉ በመኖሪያ ቤት የሚጠቀሙባቸዉን የተለመዱ የቴክኖሎጅ ዉጤቶችን ስዕሎች ያዘጋጁ፡፡ህፃናትን በትናንሽ

ቡድን እንዲደራጁ ያድርጓቸዉና ሰዉሰራሽ የቴክኖሎጅ ዉጤቶች በመኖሪያቤታችን ለተለያዩ ተግባራቶች የምንጠቀምባቸዉ መሆናቸዉን ለምሳሌ የመብራት አምፖል፣ ካዉያዎች፣ ስቶብ፣ ምጣድ፣ የልብስ ማጠቢያ ማሽን፣ መመገቢያ ሰሀኖች፣የወጥ ማብሰያ ድስቶች፣ የተለያዩ ማሽኖች፣ ቴሌቭዥን፣ ላብቶፕ፣ ስልኮች የመሳሰሉትን በምሳሌነት በመጥቀስ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸዉ፡፡

እርስዎ ያዘጋጁትን የተለየዩ የቴክኖሎጅ ዉጤቶች የያዙ ስዕሎችን ለሁሉም ሕፃናቶች በሚታይ መልኩ ያሳዩአቸዉና ህፃናትን በየቡድናቸዉ የሚያዩአቸዉን የቴክኖሎጅ ዉጤቶች ምንነትና አገልግሎት እንዲሁም ሌሎች የሚያዉቋቸዉን ቁሳቁሶች በመጨመር እንዲወያዩ እድል ይስጧቸዉ፡፡

ከየቡድናቸዉ አንድ ህፃን በመነሳት የተወያዩበትን ብዛትን ጨምሮ እንዲያቀርብ እድል ይስጧቸዉ/የህፃናት ብዛት አነስተኛ ከሆነ ከየቡድኑ ተጨማሪ እድል ይስጡና ዕለትበዕለት የምንጠቀምባቸዉ አብዛኞች ቁሳቁሶች የቴክኖሎጅ ዉጤቶች መሆናቸዉን እና ቴክኖሎጅ ኑሮን ቀላል ለማድረግ ያለዉን ፋይዳ ምሳሌ በመጥቀስ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸዉ፡፡

በመጨረሻም ህፃናት በክፍል ዉስጥ ያዩአቸዉንና የተወያዩባቸዉን የቴክኖሎጅ ዉጤቶች ሞዴል የተለያዩ አካባቢያዊ ቁሳቁሶችን ተጠቅመዉ እንዲሰሩ የፕሮጀክት ስራ ይስጧቸዉና ሰርተዉ ያመጡትን የፕሮጀክት ስራ በማበረታታት ብዛት፣የሰሩባቸዉን ቁሳቁሶች፣የአሰራርቅ/ተከተል፣አገልግሎት/ጠቀሜታና መሰል ጉዳዮችን በኢግዚብሽን መልክ እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸዉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** ወፍራም ወረቀት/ቻርት፣ ባ፤ቀምእርሳሶች፣ሞዴሎችን ለመስራት የሚያስችሉ አካባቢያዊ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** የቃልጥያቄ፡ በቤታችን ዉስጥ የምንጠቀምባቸዉ የቴክኖሎጅ ዉጤቶች ምንምን ናቸዉ? ለምንለምን አገልግሎት እንጠቀምባቸዋለን? የፈጠራ አቅማቸዉንና የቃላት ክምችት እድገታቸዉን መመዘን፣

**ቁልፍ ቃላት:** የፈጠራ ስራን መግለፅ፣ሰዉሰራሽ አካባቢ፣መለየትናመመደብ

**ተግባር አምስት:** እንቆቅልሽ (3 ክፍለጊዜ)

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ህፃናትን ለማነቃቃት ያስችል ዘንድ የሚያዉቁትን መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርጓቸዉ፡፡

መጨረሻ ላይ የቀረበዉን እንቆቅልሽ በትልቅ ወረቀት በማርከር ወይም ሌላ ደማቅ ከለር ተጠቅመዉ በመፃፍ በክፍል ዉስጥ የሚታይ ቦታ ላይ ይስቀሉላቸዉ፡፡ በመቀጠል በትናንሽ ቡድኖች ያደራጁቸዉና ለመልስ መስጫ የሚሆን አንድ ወረቀት እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸዉና የቀረቡትን እንቆቅልሾች በእንቆቅልሽ አባባል ስርአት መሰረት እርስዎ ሲጠይቋቸዉ ህፃናት በየቡድናቸዉ የተስማሙበትን መልስ እንዲፅፉ ያድርጓቸዉ/ ያልተስማሙበት የተለያየ መልስ ካላቸዉ መልሶቻቸዉን በመልስ መስጫ የጋራ ወረቀታቸዉ ላይ ይፃፉ፡፡

ከጨረሱ በኋላ በየቡድናቸዉ እርስዎ ተዘዋዉረዉ መልሶቻቸዉን በማየትና በማበረታታት ስህተት ካገኙ ተጨባጭ ምክንያት በመስጠት ያስተካክሏቸዉ/አንድ እንቆቅልሽ ከአንድ በላይ መልስ

ሊኖረዉ ይችላል፤ እርስዎ የመማር ብቃቱን መሰረት ያደረገ ተጨማሪ እንቆቅልሾች ካሉዎት በመጠየቅ ህፃናት ለክፍል ጓደኞቻቸዉ የሚያዉቋቸዉን እንቆቅልሾች እየወጡ እንዲጠያየቁ ነፃ እድል ይስጧቸዉ፡፡

**እንቆቅልሽ 1**

ህፃናት ይሰበሰቡብኛል ፊደላትን ማንበብና መፃፍ ይችሉብኛል እኔ ማን ነኝ?

**መልስ፡** ትምህርት ቤት

**እንቆቅልሽ 2**

የአየኝን ሁሉ አያለሁ የቴክኖሎጂ ውጤት ነኝ እኔ ማን ነኝ መስታወት

**እንቆቅልሽ 3**

ሰዎች ስዕል ለመሳልና በጣቶቻቸው እየነካኩ ለመፃፍ ይጠቀሙብኛል እኔ ማን ነኝ

**መልስ፡** ኮምፒውተር

**እንቆቅልሽ 4**

አንበሳ፣ጦጣናዝንጀሮ ይኖሩብኛል እኔ ማን ነኝ?

**መልስ፡** ጫካ/ዱር

**እንቆቅልሽ 5**

ትምህርት ቤት አብረን እንሄዳለን አብረን እንጫወታለን እኔ ማን ነኝ?

**መልስ፡** ጓደኛዬ/እህቴ/ወንድሜ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** ማርከር፣ ባለቀም እርሳስ፣ ፊሊፕ ቻረትና የተለመዱ እንቆቅልሾች

**የምዘና ስልት፡** ጥያቄናመልስ፣የመመራመር አቅም ደረጃቸዉን መመዘን

## ተግባር ስድስት፡ መዝሙር (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍቃላት፡** ሰዉሰራሽና ተፈጥሯዊ አካባቢ፣ የግብረገብ እሴት፣ የቦታ መገኛ፣ የፈጠራ ስራ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር ፣ በገለፃ፣በጥያቄና መልስ፣

**የመምህር ሚና፡** መምህር እባክዎትን ህፃናትን ለማነቃቃት ያክል በክፍላቸዉ ዉስጥ ነፃ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ይፍቀዱላቸዉና ቀጥሎ የቀረበዉን መዝሙር ለህፃናት ከማስዘመርዎ በፊት እርስዎ በመዘመር በስልክዎ/ሪከርደር ይቅረፁትና ያሰሟቸዉ፡፡

ለህፃናቶች በመዝሙር አዘማመር ስልት መሰረት መዝሙሩን በማስዘመር ያለማምዷቸዉና በመጨረሻም ከመዝሙሩ ምን እንደተማሩ በመጠየቅ የመዝሙሩን ጭብጥ በጨዋታ መልክ በመግለፅ ከመማር ብቃቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ መዝሙሮች ካሉዎት ያስዘምሯቸዉ፡፡

## ሳራ እባላለሁኝ

ሳራ ጥላሁን እባላለሁኝ፣
ሲጠሩኝ ስሜን አቤት እያልኩኝ፣
የፊደላት ድምፅ እማራለሁኝ፡፡
ነፋስ በአየር ሻሻ እያለ፣
ዝናቡም ወዲያዉ ጠብጠብ አለ፡፡
በመንገድ ስንጓዝ ይዘን ግራ መስመር፣
ላይ ታች በማየት እንዳንደናገር፣
ማወቅ ይገባናል የቦታን ዳርድንበር፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ፡** የሞባይል ስልክ/ሪከርደር፣ፍላሽ፣ ሞንታርቮ

**የምዘና ስልት፡** ጥያቄናመልስ ፡ በመዝሙሩ ውስጥ ያለችዉ ልጅ ስሟማን ይባላል? ሲጠሯት ምን ትላለች? የነፋሱ ድምፅ ምን አይነት ነዉ? በመዝሙሩ ዉስጥ ያሉትን ተፈጥሯዊ ነገሮች ጥቀሱ፣

# የአውድ ማጠቃለያ ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም____________________ጾታ_______እድሜ_______ደረጃ_______

**መግለጫ:** ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "✓" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | የመማር ብቃቶች | የምልከታ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | ጥሩ | በ.ጥሩ | እ.በ.ጥሩ |
| 1 | ግንዛቤያቸዉንና ማኅበራዊ ክህሎታቸዉን ለማዳበር የተለያዩ ቴክኖሎጅዎችን ይጠቀማሉ? | | | | |
| 2 | ለጨዋታ፣ ፊደላትን ለማንበብና ለመፃፍ፣ እንዲሁም የቃላት ክምችታቸውን ለማሳደግ ዲጂታል ቴክኖሎጅን ይጠቀማሉ? | | | | |
| 3 | ማህበራዊ እና ተግባቦታዊ ክህሎትን ለማዳበር ዲጂታል ቴክኖሎጅን ይጠቀማሉ? | | | | |
| 4 | ቁጥሮችን ለመቁጠር፣ ለመቀነስ እና ለመደመር የተለያዩ ቴክኖሎጅዎችን ይጠቀማሉ? | | | | |
| 5 | ዲጅታል ቴክኖሎጅን በመጠቀም በዕለት ከዕለት ተግባሮቻቸዉ ዉስጥ የደህንነትና የንፅህና አጠባበቅ መመሪያዎችን ይተገብራሉ? | | | | |
| 6 | የዲጅታል ሚዲያን(ዘመናዊ የመገናኛ መሳሪያዎችን) በመጠቀም የተለያዩ ጥበባዊ ተግባራቶችን በማከናወን ይዝናናሉ? | | | | |
| 7 | የዲጅታል ሚዲያን(ዘመናዊ የመገናኛ መሳሪያዎችን) በመጠቀም ነገሮችን ይመድባሉ? | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጸም፦____________________

____________________

____________________

____________________

# ዐውድ አራት እርሻ

አጠቃላይ ለአውዱ የጠቀመጠው የሳምንቱ ብዛት 5/የክፍለ ጊዜ ብዛት150

## 5.1. መግቢያ

ውድ መምህር! ከላይ በተሰጠው አውድ ስር በቅድመ አንደኛ ደረጃ ሶስት ህፃናት አርሻ በሚለው አውድ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቦናዊ፣ አካላዊና አምሮአዊ እድገታቸውን ለማጎልበትና አብዛኛው የሀገራችን ክፍል የሚተዳደረው በእርሻ እንደሆነ እና ለእርሻ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ጥራጥሬዎች፣ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች፣ የተለያዩ የቤት እንስሳት፣ የተለያዩ ለእርሻ ስራ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ስም፣ ለእርሻ የሚያገለግሉ የቤት እንስሳትን የሚለዩበትና የሚረዱበት አውድ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ሳምንት አጥጋቢ የመማር ብቃቶችና ዝርዝር የአተገባበር ስልቶች ቀርበዋል፡፡ ስለሆነም ህጻናቱ ሊያሞሏቸው የሚገባቸው የመማር ብቃቶች እንዲያሟሉ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## 5.2. የሚጠበቁ ውጤቶች

- ✓ የሀገር ወዳድነት ስሜትን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ የማህበራዊ ክህሎት ያዳብራሉ፡፡
- ✓ በዕለት ተዕለት ተግባራቸው የደህንነት እና የንፅህና አጠባበቅ መርሆችን ይተገብራሉ፡፡
- ✓ ጊዜን መሰረት በማድረግ የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን ያቅዳሉ፡፡
- ✓ የቃላት እውቀታቸውን ያሳድጋሉ፡፡
- ✓ ከመማር ይዘቶች ጋር ተያያዥ የሆኑ ሥነ ጥበባዊ ተግባራትን በመስራት ይዝናናሉ፡፡
- ✓ ቃላቶችን በማንበብ ይፅፋሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን በመለየት ይቆጥራሉ፡፡
- ✓ የነገሮችን መሰረታዊ ቅርፅ ይናገራሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ ቁሶችን (ነገሮችን) ቅጥን/ሥርዓተ ጥለትን/ መሰረት እድርገው ቀለምን፣ ቅርፅንና ሙዚቃዊ ምትን በመለየት ይከፋፍላሉ፡፡

## 5.3. ዐበይት ይዘቶች

እርሻ ለሚለው የመማር አውድ የሚከተሉት ዐበይት ይዘቶች ተዘርዝረዋል

- ራስንማ
- ስተዋወቅ
- ራስን ማወቅ
- ራስንማ
- ስተዋወቅ
- ራስን ማወቅ
- የትናንሽ ጡንቻወች መዳበር
- ቁጥሮችን ማወዳደርና ማነፃፀር
- ባህላዊ ቅርሶች
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- ራስን መግለፅ
- የትላልቅ

- የአካል ክፍሎች
- ቁጥር መቁጠር
- ጤና
- ጥበባዊ ግንዛቤ
- ራስን መቆጣጠር
- ድምፆችን መለየት
- የቅርብ አካባቢ
- ስርዓተ ምግብ
- ቁጥሮችን መፃፍ
- በፈጠራ ስራ መግለፅ
- ራስን መቻል
- ቃላት
- ጡንቻዎች መዳበር
- ቅጥ /ሥርዓተ ጥለት፣ ድግግሞሽ/
- ጥበባዊ እሴት
- የግብረገብ እሴቶች
- የፊደላት ድምፆች ግንዛቤ
- ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ አካባቢ
- የቦታ መገኛ
- መለየትና መመደብ
- ማንበብና መፃፍ
- መደመርናመቀነስ

# አንደኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃት

- ✓ ስለራሳቸው፣ ቤተሰቦቻቸውና አካባቢያቸው ጓደኞቻቸው ጋር መረጃ ይለዋወጣሉ፤
- ✓ ፍላጎታቸው ያለምንም ፍርሃት ይናገራሉ፤
- ✓ የተለያዩ የእርሻ መሳሪያዎችን የአካል ክፍሎችን ይለያሉ፤
- ✓ መሰረታዊ የንፅህና አጠባበቅ መርሆችን ይተገብራሉ፤
- ✓ ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግብና መጠጦችን ይለያሉ፤
- ✓ ቁጥሮችን ያወዳድራሉ፣ በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ፤
- ✓ የተለያዩ የመማር መሰኮችን በስነ ጥበባዊ ዜደዎች እየተደሰቱ ይማራሉ፤

**ንዑስ ይዘቶች:** ራስን ማስተዋወቅ ፣ ራስን ማወቅ ፣ የአካል ክፍሎች ፣ ቁጥር መቁጠር ጤና እና ጥበባዊ ግንዛቤ

## ተግባር አንድ: ውይይት (4 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጥበባዊ ግንዛቤ፣ ባህላዊናዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የጥራጥሬ አይነቶች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በውይይት ፣በገለፃ ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ይህን ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ በመጀመሪያ ሰላምታ ከህፃናት ጋር ከተለዋወጡ በኋላ እርስዎ በአካባቢያቸው ስለሚያውቁት የእርሻ ቦታ፣ ባህላዊና የዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን በመለየት ቀደምት እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲናገሩ ይጠይቋቸው:: በመቀጠልም እርስዎ ስለአከባቢቸው ስለሚያውቋቸው የእረሻ መሳሪያውች ገለጻ ያድርጉላቸው:: ቀጥለው ህጻናቱ በውይይት እንዲማሩ በቡድን በመክፈል መወያያ ነጥቦችን ለየቡድናቸው ይስጧቸው::

**ቡድን “1”**

ባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎችን ማለትም፡ ሞፈር፣ ቀንበር፣ ማረሻ፣ ወገል፣ ምናር፣ ማነቆ…ወዘተ የሚባሉትን ስማቸውን፣ ብዛታቸውንና ጥቅማቸውን፣ ለምግብና ለመጠጥ የሚሆኑ ጥራጥሬዎችን አይነት መለየት፣ አካባቢንና የግል ንፅህናን እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል በስዕል ወይም መረጃ በመለዋወጥ አንዲወያዩ ያድርጉ ።

**ቡድን “2”**

ለእርሻ ቦታ የሚዘሩ የጥራጥሬ አይነቶችን ለምሳሌ፡ ስንዴ፣ ባቄላ፣ ሽምብራ፣ በቆሎ፣አተር… ወዘተ የያዘ ስዕል በመስጠት ቀለማቸውን፣ ቅርፃቸውን፣ ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን፣ በመለየት አንዲወያዩ ያድርጉ።በመጨረሻም የጥራጥሬ አይነቶችን እንዲያመጡ በማደረግ ለክፍል ጓደኞቻቸው በማሳየት ስማቸውን እንዲናገሩና መጠናቸውን በትናንሽ መስፈሪያዎች በመለካት ምን ያክል እንደሰፈሩ እንዲናገሩ ያድርጉ።

**ቡድን “3”**

ባህላዊ የአስተራረስ ዘዴ በበሬ፣ በአህያ፣በፈረስ…ወዘተ እና ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ በትራክተር የሚታረስ የእርሻ ቦታ የያዘ ስዕል በመስጠት ማወዳደርና ማነፃፀር በየትኛው ሲታረስ ብዛት ያለው ምርት ወይም ሰብል እንደሚገኝ እንዲወያዩ ያድርጉ።

በመጨረሻም የሁሉም ቡድኖች ውይይት ከተጠናቀቀ በኂላ እርስዎ በተቆራረጡ ወረቀቶች/ካርዶች/ ላይ የጥራጥሬ አይነቶችን ስሞች በመፃፍ ለየቡድኑ በመስጠት ቃላቱን እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያድርጉ። በየቡድናቸው እየዞሩ ግልፅ ያልሆነላቸውን እያብራሩ ግለፅ በማድረግና ከየቡድናቸው እየወጡ የተወያዩበትን ለክፍል ጓደኞቻቸው አንዲናገሩ ካደረጉ በኂላ ባህለዊ ለእርሻ ስራ የሚያገለግሉ የቤት አንሰሳትን እንዲስሉ ያድርጉ።በመጨረሻም በእርሻ መሳሪያዎች የመጀመሪያ ፊደላት ቃል ይመስርቱ፣ በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ላይ ያለውን የእርሻ መሳሪያዎች ስዕል በማየት ስማቸውን ከጎናቸው እንዲፅፉ ያድርጉ።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች :** የተለያዩ ጥራጥሬ፣ የጥራጥሬ ምስሎችን የያዙ ካርዶች፣ የእርሻ መሳሪያዎችን የያዘ ስዕል፣ ባህላዊና ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ የሚያሳይ ስዕል፣ የተለያዩ ቁጥሮችን ቃላት የያዘ ካርዶች

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(የወይይት ስርአት ልምድ እድገታቸዉን መመዘን ፣ መመሪያንና ትዕዛዝን መጠበቃቸውን በመከታተል መገምገም) **የቃል ጥያቄ**(ባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎች የሚባሉት ምንምን ናቸዉ? ዘመናዊስ?)፣የፅሁፍ መጠይቅ መስጠት

## ተግባር ሁለት፡ መዝሙር አንድ (8 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍቃላት:** ቁጥር መቁጠር፣ ቀለማት፣ ጥበባዊ ግንዛቤ፣ ተፈጥሯዊ አካባቢ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር ፣በገለፃ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ህፃናት ከዚህ ቀጥለው የቀረቡ አራት መዝሙሮችን እየዘመሩ እንዲማሩ ያድርጉ።

## መዝሙር አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

### በመንገድ ላይ ስንጓዝ

በመንገድ ላይ ስንጓዝ ግራችንን እንያዝ
የእርሻን ቦታ ለመጎብኘት
በመንገድ ላይ ስናቋርጥ
ግራ እና ቀኝ እንመልከት
የትራፊክ አሃዛ ቀለማት
አረንጓዴ አሃዛ ቢጫ ቀይ
ቢጫው ሲበራ ተዘጋጅ ለመኪና
አረንጓዴው ሲበራ እለፍ እለፍ መኪና
ቀዩ ደግሞ ሲበራ አሁን ነው የኛ ተራ(3)
አንድ ሁለት ሶስት አራት
እንጠብቃለን የትራፊክን ስርአት
ከአዳጋ ይጠበቅ ጤናችን ግራና ቀኝ እንመልከት

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች:** የትራፊክ መብራት ስዕሎች

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(መዝሙሩን በንቃት መዘመራቸዉን መመዘን) ፣ **የቃል ጥያቄ** (የመኪና መንገድ የምናቋርጠው ምን ቀለም ሲበራ ነው? ቀይ ቀለም ሲበራ ምን ማድረግ አለብን ?)

## መዝሙር ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

### የአርሶ አደር ውለታ

እንጀምር ቆጥረን አንድ ሁለት ሶስት ብለን፣
ጤናን ለመጠበቅ እንዲሁም ለመኖር፣
ማወቅ ያስፈልጋል የአርሶ አደሩን ተግባር፡፡
እርሻን እያረሱ እንስሳን ሲያረቡ፣
እህል በጎተራ እየሰበሰቡ
የአገሬ አርሶ አደሮች ተከብረው ይኑሩ፣
የገበያው ጥጋብ የከተማው ደስታ፣
ግብርና መሆኑን አንርሳ ለአንዳፍታ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች:** ለመዝሙሩ አጋዥ የሆኑ ስዕሎች ( የገበሬ ስዕሎች፣

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (መዝሙሩን በንቃት መዘመራቸዉን መመዘን)፣ **የቃል ጥያቄ** ( የአርሶ አደር ተግባር ምንድን ነው ?)

## መዝሙር ሦስት ( 2 ክፍለ ጊዜ)

### ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ሀገራችን ኢትዮጵያ መመኪያችን፣
ኢትዮጵያዊ ነን እኛ ኢትዮጵያን የምንወድ፣
አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ፣
አዲስ አበባ ነው ዋና ከተማችን።
የአስራ ሶስት ወር ፀጋ ፀሀይ የማይለያት፣
ታላቋ ሀገራችን ኢትዮጵያ ብቻ ናት፣
ለጤና ተስማሚ ለመኖር ምቹ ናት፣
ፍቅር አስተማሪ የፍቅር እናት ናት፣
አባቶች እናቶች ጠንክረው ያቆሟት።

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች፡** ለመዝሙሩ አጋዥ የሆኑ ስዕሎች

**የምዘና ስልት፡** የቃል ጥያቄ ( የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ማናት?)

## መዝሙር  አራት (2 ክፍለ ጊዜ)

### ርዕስ፡ አምስት ትንሽ ዳክዬዎች

አምስት ትንሽ ዳክዬዎች
ጨዋታ ሔዱ በተራራው ላይ
ወደ ሩቅ ስፍራ
እናትዮዋ ዳክዬ ቋቋ አለች
አንዷ ዳክዬ ወደ እሷ ሮጠች
አራት ትንሽ ዳክዬዎች ጨዋታ ሔዱ
በተራራው ላይ ወደ ሩቅ ስፍራ
እናትየዋ ዳክዬ ቋቋ አለች
አንዷ ዳክዬ ወደ እርሷ ሮጠች
ሦሥት ትንሽ ዳክዬዎች
ጨዋታ ሔዱ በተራራው ላይ
ወደ ሩቅ ስፍራ
እናትዮዋ ዳክዬ ቋቋ አለች
አንዷ ዳክዬ ወደ እርሷ ሮጠች
ሁለት ትንሽ ዳክዬዎች ጨዋታ ሄዱ
በተራራው ላይ ወደ ሩቅ ቦታ
እናትዮዋ ዳክዬ ቋቋ አለች
አንዷ ዳክዬ ወደ እረሷ ሮጠች
( ምንጭ፡ ከኢትዮጵያ ልጆች ቴሌቪዥን የተወሰደ)

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች:** ለመዝሙሩ አጋዥ የሆኑ ስዕሎች

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ ( ስንት ትንንሽ ዳክዬዎች አሉ?፣እናተወ ዳክዬ ምን አለች?)

## ተግባር ሶስት ፡ ተረት (3 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ራስን ማወቅ፣ ጥበባዊ ግንዛቤ፣ ጤና፣ ቁጥር መቁጠር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ሁለት ተረቶች በማንበብ ከተረቱ ምን እንደተማሩ ይጠይቋቸዉ።

### ገበሬና ነብር

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖር አንድ ገበሬ ነበር። አንድ ቀን ሲያርስ ነብር መጣበት፤ ነብሩንም አዳኞቹ ያባርሩት ነበር። ነብሩም "እባክህ አንተ ገበሬ ደብቀህ አድነኝ" አለው። ገበሬውም እሺ ብሎ አምስት የተለያዩ ዘር ያመጣበት ስልቻ ነበሩት ከአምስቶች ስልቻዎች ውስጥ መርጦ በትልቁ ስልቻ ውስጥ ደበቀው። አዳኞቹም ገበሬው አጠገብ ደረሱና አንድ ነብር በዚህ ሲያልፍ አይተሀል? ብለው ጠየቁት ገበሬውም እኔ አላየሁም ብሎ መለሰላቸው ና አዳኞቹ ነብሩን ፍለጋ ወደ ጫካ ሄዱ። በኋላ ገበሬው ነብሩን ሰዎቹ እርቀው ስለሄዱ አያዩህም ከስልቻየ ውጣና ሂድ አለው። ነብሩም አሁን በጣም ስለራበኝ የምበላው ካላገኘሁ አልሄድም አለው። ገበሬውም ታዲያ ምግብ አልያዝኩም ምን ልትበላ ነው አለው። ነብሩም አንተን እበላለሁ አለው፤ ገበሬውም ይህንስ ካልህ ጓደኞችህ ይፍረዱኝ አለው። በዚህ ተስማምተው ፍርድ ጥየቃ ሄዱ። ዝንጀሮ፣ ፍየል፣ ውሻና ጅብ በገበሬው ፈረዱበት። ጦጣ ግን "እንዴት እንዳዳንከው አሳየኝ" ብላ ጠየቀችው ገበሬውም ነብሩን ከስልቻው ውስጥ አግብቶ አሰረውና አሳያት ጦጣም ሰውየው እንዲያመልጥ በምልክት አሳየችው። ሰውየውም እሩጦ ነብሩን በማምለጥ በሰላም በጤና መኖር ጀመረ ይባላል።

**ማሳታወሻ መምህር!** ስልጆች መዋሸት ተገቢ እንዳልሆነና በትክክል መናገር እንዳለባቸው እንዲሁም ታማኝ መሆን እንዳለባቸው ምክር ይስጧቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ:** ተረቱን የሚገልጽ ስእል፣

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ

1. በተረቱ ውስጥ ስንት የቤት እንስሳትና የዱር እንስሳት አሉ?
2. በተረቱ ውስጥ ታማኝ ሁኖ ያልተገኘው ማን ነው?
3. ነብሩ ከገበሬው ስልቻ ውስጥ ለምን ገባ ?
4. ነብሩን ካዳኞቹ ማን አዳነው?
5. ከእንስሳቱ መካከል በትክክል የፈረደው ማን ነው ?
6. ገበሬው ምን ሲሰራ ነበር ?

## የተረቱ ሁለት፡ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት :** ችግኝ፣ እድሜ፣ሃያ አመት፣ ዛፍ፣ ጤንነት፣ጥበባዊ ግንዛቤ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት ፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** የተረት አተራረት ቅደም ተከተልን ተከትሎ ተረቱን ማቅረብ ፣እነሱ እንዲናገሩ ማበረታታት

### ወጣቱ ገበሬና ወጣቱ ሹም

አንድ ቀን ጠዋት አንድ ወጣት ገበሬ የማንጎ ችግኝ ለመትከል ይቆፍር ነበር፡፡ አውሬ ለማደን አንድ ወጣት ሹም በፈረስ እየጋለበ መጣና ከወጣቱ ገበሬ አጠገብ ሲደርስ ቆሞ ይመለከት ጀመር፡ ፡ ቀጥሎም ወንድሜ ዕድሜህ ምን የያህል ነው ሲል ጠየቀው፡፡ ሽማግሌውም ሰማንያ ዓመቴ ነው ብለው መለሱለት ሹሙም “ወደፊት ስንት ዓመት ? ” ትኖራለህ ሲል እንደገና ጠየቀው፡ ፡ ወጣቱም ”ይህ በፈጣሪ እጅ ያለ ነው ” አለው እንደገና ደግሞ ሹሙ ”ይህ የምትተክለው ዛፍ በስንት አመቱ ፍሬ ያፈራል” ሲል ጠየቀወው፡፡ ወጣቱም ”በሃያ ዓመቱ ሳያፈራ አይቀርም ”ሲሉ መለሰለት ፡፡ ሹሙም ”ሃያ ዓመት ! ብሎ ጮኽ ቀጥሎም እየሳቀ፤ እንግዲውማ ሞኝ ሆነህላ! አለው ፡፡ ወጣቱም ለምን ጌታዬ? ሲል ጠየቀው፡፡ ለጤንነትህ በማሰቤና”ፍሬውን ለመብላት ቶሎ የማይደርስ ዛፍ በመትከል መድከምህ ነዋ? ” ሲል መለሰለት፡፡ በዚህ ጊዜ ወጣቱ ገበሬ ”ይህ ሞኝነት አይደለም ጌታዬ! ” አለና ዛፍ መትከሉን ቀጠለ ወጣቱ ሹምም ልክ ብለሀል ወድሜ እኔም አብሬ ላግዝህ በማለት አብረው ተከሉ ፡፡

**ተሬቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ**

**ዳቦ ከሌላችሁ በእጃችሁ አጨብጭቡ**

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች :** የተረት መጽሐፍ ፣ የቁጥር ፍለሽ ካርድ፣ ትንሽ ዛፍ፣ ውሃ፣ መቆፈሪያ ፣ የቤት እንስሳትና የዱር እንስሳትን የያዘ ስዕል ፣ ጥራጥሬ...ወዘተ

**የምዘና ስልት: ምልከታ**(ተረቱን ሲያዳምጡ የሚኖራቸዉን ትኩረት መመዘን)፣ **የቃል ጥያቄ**

1. በተረቱ ውስጥ ማን ማን አሉ?
2. ስንት ሰዎች ናቸው የሚነጋገሩ?
3. ሽማግሌው ምን ይሰራ ነበር ?
4. ወጣቱ ለምን በሽማግሌው ሳቀበት?
5. የሽማግሌው ዕድሜ ስንት ነው?
6. ሽማግሌውና ወጣቱ መጨረሻ ላይ በምን ተስማምተው ተለያዩ?

## ተግባር አራት፡ የመስክ ጉብኝት (6 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጥበባዊ ግንዛቤ፣ አካባቢን መረዳት፣ የጥራጥሬና አትክልትና ፍራፍሬ አይነቶች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመስክ ጉብኝት መማር

**የመምህር ሚና**፡ መምህር! እባክዎ በአካባቢያቸው ወደ ሚገኝ የእርሻ ቦታ ህጻናቱን ከመውሰድዎ በፊት ከዚህ በታች ያለውን የማነቃቂያ መዝሙር ያዘምሯቸው፡፡ ስለእርሻ

እንሂድ እርሻ ቦታ እናምርት(2)፣

ኢትዮጵያን በልማት እንገንባት፡፡

የሚለውን መዘሙር ከክፍል በማስወጣት ተሰልፈው እንዲዘምሩ በማድረግና ወደ እርሻው ቦታ /በትምህርት ቤቱ የአትክልት ቦታ) የመስክ ጉብኝት ምን ምን ማየት ፣ በምን እነደሚታረስ፣ የእርሻ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ምን ምን እነደሆኑና የአካል ክፍሎቻቸው ስንት እንደሆኑ፣ ምን አይነት ጥራጥሬ እንደሚዘራ ብዛታቸው ስንት አይንት ጥራጥሬ ፣ ስንት አይነት የአስተራረስ ዘዴ፣ ለምግብነትና ለጤና ተስማሚ የሆኑ የፍራፍሬና አትክልት አይነቶችን መለየት የሚሉትን በጥንቃቄ በመመልከት ለክፍል ጓደኞቻቸው ከመስክ ጉብኝት ሲመለሱ በክፍል ውስጥ እንደሚያቀርቡ ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡ በመቀጠልም ቅርብ ወደ ሆነ የእርሻ ቦታ ደህንነታቸውን በጠበቀ መልኩ በስርዓት አሰልፈው ይውሰዷቸው፡፡

ከወሰዱ በኋላ ግልፅ ላልሆነላቸው ህፃናት እገዛ እያደረጉ የተለያዩ የፍራፍሬ እና የአትክልት አይነቶችን፣ የጥራጥሬነ አይነቶችን፣ የእርሻ መሳሪያ ቁሳቁሶችን ስም በደንብ እንዲለዩና ብዛታቸውን እንዲቆጥሩ እገዛ ያድርጉ፡፡በመቀጠልም የአትክልትና የፍራፍሬዎች፣ የአካባቢ እንክብካቤና ጤንነት መጠበቅ እንዳለባቸው ያስረዷቸው፡፡ በአጠቃላይ ያዩትን በዘገባ እንዲያቀርቡ በማድረግ አዕምሮአዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ ልቦናዊና አካላዊ እድገታቸውን ያጎልብቱ፡፡

በመጨረሻም መምህር! ሁሉም ህፃናት በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ በቅርበት የሚያገኟቸውን የጥራጥሬ አይነቶችን በእቃ ይዘው እንዲመጡና እየተነሱ ስማቸውን ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ በማድረግ፣ጥራጥሬዎችን ቀላቅለው እንዲለዩ ማድረግ በገጽ......ላይ ያለውን በመለማመጃ ደብተራቸው የጥራጥሬ አይነቶችን ስዕላቸውን ከስማቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡ በደብተራቸው የጥራጥሬ ስሞችን እንዲጽፉ ማድረግ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች :** ጥራጥሬ ፣አትክልት፣ የእርሻ ቦታዎች ፣ በሬ ፣ አህያ፣ ፈረስ ምስሎችን የያዘ ካርድ ...፣እርሳስ፣ደብተር/ወረቀት...ወዘተ

**የምዘና ስልት**፡ ምልከታ(የሚመለከቷቸዉን ነገሮች ለማወቅ የሚጠይቋቸዉን ጥያቄ መመዘን)፣ የቃል ጥያቄ( ምን ተመለከታችሁ) ፣ሪፖርት ሲያደርጉ በማዳመጥ

## ተግባር አምስት፡ በስራ መማር (3 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍቃላት**፡ ጤና፣ መምህር፣ ገበሬ ፣ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ**፡ በስራ ፣በገለፃ፣ሰርቶ በማሳየት፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና**፡ ውድ መምህር! ለህፃናት የተለያዩ ቁጥር ለመቁጠር የሚያገለገሉ፣ቃላትን ለማንበብ የሚያገለገሉ ፣ጤናን ለመጠበቅ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ ፣ በተጨማሪም የተለያዩ ጥራጥሬዎችን በማዘጋጀት ከክፍል ውስጥ ሀኪምን፣ ገበሬን ፣መምህርን በመሆን በቡድን ተከፋፍለው ሀኪሙ የሀኪሙን ስራ በመስራት ስለጤንነታቸው ደህንነትና አጠባበቅ ያሳያል ፣ገበሬው ለእርሻ ቦታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በስዕል እያሳዩ አትክልቶች እንዴት እንደሚተከሉ፣ እንደሚያድጉ እንዲሁም እንክብካቤ እያደረገ ማሳየት፤ መምህሩም ተማሪዎች ከፊቱ በማስቀመጥ

ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ከ1 20 በማስቀመጥ እንደዲፅፉ በማድረግ እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡ ፡ በደብተራቸው ላይ በተራ ቁጥር የሚያውቁትን ፍራፍሬ እና የጓሮ አትክልት እንዲፅፉ ማድረግ

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች:** የሀኪምን፣ የገበሬና የመመህርን ተግባር የሚሳዩ ስእሎች፣ የቁጥር ፍላሽ ካርዶች፣ እርሳስ፣ ደብተር፣

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(የስራ ሀላፊነትን በመረዳት የመወጣት አቅማቸዉን መመዘን) ፣የቃል ጥያቄ (ሀኪሙ ምን ምን ስራዎችን ሲሰራ ተመለከታችሁ? ገበሬዉስ? መምህሩስ? ቁጥሮቹን በቅደም ተከተል ንገረኝ /ንገሪኝ፣ዓፍ/ዓፊ......

## በስራ መማር ሁለት: ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መግዛትና መሸጥ፣የብርኖቶች፣ባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር ስራ በገለፃ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በክፍል ዉስጥ የሱቅ ኮርነር በማዘጋጀት የተወሰኑ ህፃናት አትክልት፣ፍራፍሬዎችና ጥራጥሬዎችን የብር ኖቶችን ሞደል በማዘጋጀት እንዲሸጡና እንዲገዙ በማድረግ አዕምሮዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊና ስሜታዊ መዳበርን እንዲያጎለብቱ ያድርጉ በተጨማሪም፣ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን፣ በራስ መተማመንን እና ሀላፊነትን እንዲለምዱ በመስሎ ጨዋታው እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

በመጨረሻም ውድ መምህርት በመለማመጃ ደብተር ገፅ ላይ ያለውን ባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎችን ለይተው እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች:** የብር ኖቶች ሞደል፣ አትክልተና ፍራፍሬ ሞደሎች፣ የተለያዩ ቁሳቁሶች ሞደሎች

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (የብርኖቶችን የፍራፍሬ አይነቶችን የመለየት አቅማቸዉን መገምገም)፣ የቃል ጥያቄ መጠየቅ( የብር ኖቶችን መጠየቅ፣ የአትክትና የፍራፍሬ ስሞችን መጠየቅ)፡፡

## ተግባር ስድስት፡ የግል ተግባር (2 ክ/ጊዜ)

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በግልስራ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**ቁልፍ ቃላት:** ጤና፣ጥበባዊ ግንዛቤ፣ ጥራጥሬ፣ እንስሳት፣ አትክልቶች፣ ንጽህና ቃልት፣ ቁጥር

**የመምህር ሚና:** መምህር ለህፃናት ባለቀለምእርሳስ(ክራዮን) ፣ እርሳስ እና ወረቀት በመስጠት የተለያዩ የእርሻ መሳሪያ ቁሳቁሶችን፣ በሬ፣ ትራክተር፣ አህያ፣ ፈረስ...ወዘተ ተጠቅመው አቅማቸው የፈቀደውን ስዕል በመሳል ከእንስሳቱ ጋር ተቀራራቢ የሆነ ቀለም እንዲቀቡ በማድረግ፣ በአገልግሎታቸው እና በአይነታቸው እንዲለዩ የለዩትን ስንት እንደሆነ በመጠየቅ ነገሮችን በቅርፅ፣ በመጠንና በአይነት የመመደብ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠልም ጥራጥሬዎችን፣ አትክለቶችንና ፍራፍሬዎችን መመገብ ለጤንንታቸው አጠባበቅ እንደሚጠቅማቸውና በንፅህና መያዝ እንዳለባቸው ስለጤንነታቸው ያስረዷቸው፣በመጨረሻም ህፃናቱ በደብተራቸው ጥራጥሬዎችን፣ ፍራፍሬዎችን፣እንስሳትን ትራክተር ... ወዘተ ቃላት እንዲፅፉ፣ እንዲያዛምዱ..እንዲሁም በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ላይ ያለውን የሚያውቋቸውን

የፍራፍሬ አይነቶች ስማቸውን እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁሶች:** እርሳስ፣ የተለያዩ ቀለም ያላቸው ወረቀቶች፣እርሳስ ጥራጥሬዎች፣ ቁጥሮችን የያየዘ ካርድ፣ የእርሻ መሳሪያ ቁሳቁሶችን የያዙ የቃላት ካርድ፡፡

**የምዘና ስልት: ምልከታ**(የመመደብና የመለየት አቅማቸዉን መገምገም) የቃል ጥያቄ መጠየቅ(ምን ምን ስዕሎችን አያችሁ እናንተ ምንምን ሳላችሁ ለመሳል ምን ምን ተጠቀማችሁ፣የፃፉችሁትን ቃላት ስንት ናቸው፣ አንብቢ/አንብብ...

# ሁለተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ: 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃት :

- ✓ የተለያዩ ድምፆችንበመለየት ያስመስላሉ፤
- ✓ ስሜታቸውን እንዴት መቆጣጠር እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፤
- ✓ በቅርብአካባቢያቸው ስለሚገኙ ቁሳቁሶችይናገራሉ፤
- ✓ የቅርብ አካባቢያቸውን ያውቃሉ፤
- ✓ ጤናማ የሆኑ ምግብና መጠጦችን ጠቀሜታ ያውቃሉ፤
- ✓ በአካባቢያቸው የሚገኙ ጎጅ ነገሮችን ይለያሉ፤
- ✓ ስዕሎችን፣ምልክቶችን፣የታወቁ ፊደላትንና ቃላትን ተጠቅመው በአግባቡ ይግባባሉ፡
- ✓ ለተለያዩ የስነ ጥበብና ዕደ ጥበብ ውጤቶችን ያደንቃሉ፤
- ✓ እስከ ሀያ ያሉ ቁጥሮችን የፅፋሉ፤

**ንዑስ ይዘቶች:** ራስን መቆጣጠር፣ ድምፆችን መለየት፣ የቅርብ አካባቢ፣ ስርዓተ ምግብ፣ ቁጥሮችን መፃፍ፣ በፈጠራ መግለፅ

## ተግባር አንድ: የክፍል ውስጥ ጨዋታ (5 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍቃላት:** ስርአተ ምግብ፣ ራስን መቆጣጠር፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ስራ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ

**የመምህር ሚና:** መምህርት ይህን ክፍል ጊዜ በክፍል ውስጥ በመጀመሪያ ሰላምታ ከህፃናቱ ጋር ከተለዋወጡ በኋላ ወደ ዕለቱ ት/ት ከመግባትዎ በፊት:

ስራ መስራት ያስደስታል(2)
ሀገርን ወገንን እራስን ያኮራል፡፡(2)

የሚለውን የማነቃቂያ መዝሙር ያዘምሯቸው፡፡ በመቀጠልም ህፃናትን የሚወዱትን የስራ ዓይነት በመጠየቅ ና ለምን እንደወደዱት በመጠየቅና ህፃናት ተስማምተው የመረጡትን የስራ ዓይነት እርስዎ በመስማት በቡድን ሆነው የተስማሙበትን የስራ ዓይነት በመስሎ ጨዋታ እንዲያቀርቡ ትዕዛዛትንና መመሪያ ደንብን ለሁሉም ህፃናት በመናገር ና በማስረዳት እርስዎ በሚነግሯቸው ትዕዛዝ መሰረት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ: ህፃናት የእርሻ ተግባራትን ማከናወን ቢፈልጉ

ለእርሻ ተግባራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን፣ የእያንዳነዱን ስምና ጠቀሜታ፣ ገንቢ ምግቦችን፣ በሽታ ተከላካይና ሃይል ሰጭ ምግቦችን የጥራጥሬ ዓይነቶችን፣ ለእርሻ የሚያገለገግሉ የቤት እንሰሳትን በማስረዳት በቡድናቸው እየተጫወቱ እንዲሰሩና እንዲረዱ ያድርጉ፡፡ ለእርሻ ተግባራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ሞፈር፣ ቀንበር፣ እርፍ፣ ድግር፣ ማረሻ፣ ማነቆ፣ መርገጥ፣ ምራን፣ ወገል እነዚህን በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡና ጥቅማቸውን በመናገር በመስሎ ጨዋታ እንዲጫወቱ እድሉን ያመቻቹ፡፡
በመጨረሻ ከላይ ያሉትን ቃላት እንደ ማነቆ፣ መርገጥ... እንዲጽፉ እና እንዲያነቡ ማድረግ

**የመማሪያ እና የመጫዋቻ ቁሳቁሶች:** ጥራጥሬዎች፣ አትክልት ፍራፍሬዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎችን የያዘ ስዕል፣ የቤት እንስሳትን የያዘ ካርድ፣ ባህላዊ (ዘመናዊ) የአስተራረስ ዘዴ የያዘ ስዕል፣ እርሳስ፣ ደብተር/ወረቀት...

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ( የእርሻ መሳሪያዎችን ስም መጠየቅ)ስንት የእርሻ መሳሪያ አያችሁ፣ ለምን ለምን ያገለግላሉ... ፣ **ምልከታ**(መስለው ሲጫወቱ ማየት)

## ተግባር ሁለት ፡ የክፍል ወጭ ጨዋታ (6 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍቃላት:** ድምፆችን መለየት፣ መኖሪያ አካባቢ፣ ራስን መቆጣጠር፣ቃላት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ በገለፃ፣ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ወደ ውጭ ህፃናትን ከማውጣትዎ በፊት የተለያዩ የተቀዱ ድምፆችን፣ ህፃናት የሚያውቋቸውንና የሚሰሟቸውን ድምፆች (ለምሳሌ የተለያዩ የእንስሳት ድምፆችንና በተለያየ የዕድሜ ክልል ያሉትን ሰዎች ድምፅ እርስዎ መጀመሪያ በማሰማትና ህፃናት መልሰው የሰሙትን ድምፅ መልሰው ያሰሙ ቀጥሎ በስርዓት ተሰልፈው ከክፍላቸው ወደ ውጭ በመውጣት መጠነኛ የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ ካደረጉ በኋላ የጨዋታውን ህግና ደንበ በማሳወቅ ጨዋታውን እንዲጫወቱና በጨዋታ ውስጥ የተማሩትን ት/ትና የነበራቸውን ስሜት በመጠየቅ ጨዋታውን ያጠቃሉ፡፡ **"ጓደኛዬን ፍለጋ"** የሚለውን ጨዋታ ለመጫወት የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች በመከለተል ህፃናትን ያጫውቷቸው፡፡

1. ለጨዋታው የሚመችና ንፁህ የሆነ ቦታ መምረጥ፣
2. ህፃናትን እንደብዛታቸው መጠን መመደብ፣
3. ሦስት አንስሳትን ወይም በተለያየ የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን በመምረጥ( ለምሳሌ: እንስሳትን ከመረጡ ውሻ፣ ድመትና ዶሮ) ሰዎቸን ከመረጡ ደግሞ (ለምሳሌ: ህፃን፣ አባትና እናት)፣
4. ለእያንዳዱ ህፃናት የተነገራቸውን በሚስጥር እንዲይዙ ማድረግ፣
5. ሁሉም ህፃናት የደረሳቸውን ስም እንዳይረሱ ማሳሰብ፣
6. ህፃናት ዓይናቸውን እንዲጨፍኑ መጠየቅ፣
7. ህፃናት ጀምሩ ሲባሉ በቀስታ በሚጫወቱበት አካባቢ አይናቸውን እንደተጨፈነ የያዙትን ድምፅ እያሰሙ አንዲቀሳቀሱ ማድረግና ጓደኞቻቸውን ፈልገው በእጅ በመነካካት መገናኘት፡፡

8. ያለጓደኛው ተደርቦ የተገኘ ከጨዋታው ውጭ ይሆናል፡፡

በመቀጠልም እርስዎ አንድ ሁለት ሶስት የጨዋታ ጊዜው አለቋል በማለት ማጠናቀቅ፤ በመጨረሻምበደብተር/በወረቀትአሊያም በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ላይ ያለውን የተለያዩ እንስሳቶችን ጥቅማቸውን እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

### የመመወያያ ጥያቄዎች

- ✓ ጨዋታውን ወደዳችሁት ? ለምን?
- ✓ ከጨዋታው ምን ተረዳችሁ?
- ✓ በጨዋታው ጊዜ ጓደኛችሁን እንዴት መለየት ቻላችሁ?

የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ጨዋታውን እርስዎ ማብራሪያ በመስጠት ያጠቃሉ፡፡

**የመማሪያ እና የመጫዋቻ ቁሳቁሶች:** የተቀዱ የተለያዩ የእንስሳት ድምፆችና በተለያየ የዕድሜ ክልል ያሉ የተቀዱ የሰዎች ድምፅና እርሳስ፣ደብተር/ወረቀት…

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (መመሪያንና ትዕዛዝን መጠበቃቸውን መመዘን) የመወያያጥያቄዎችን በቃል መጠየቅ የፁሁፍ መጠይቅ የእንስሳትና የእርሻ መሳሪያዎችን ስለው ቀለም በመቀባት ስሙን ፅፈው የሰሩትን ደግሞ ለክፍሉ ህፃናት በውጭ ጨዋታ ክፍለ ጊዜ ያቅርቡ፡፡

## ተግባር ሦስት: የመስክ ጉብኝት (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** እርሻ፣ ሞፈር ፣ቀንበር፣እርፍ፣ማነቀ፣መርገጥ፣ድጋፍ፣ እንስሳት፣የመኖሪያ አካባቢ፣ጥራጥሬ አይነቶች፣ ሰብሎችን መንከባከብ

### ቁጥሮችን መለየት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመስክ ጉብኝት፣ በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር እባክዎ ህፃናት ወደመስክ ጉብኝት እንደሚሄዱ ያስተዋውቁ፡፡ በመቀጠልም በአካባቢያቸው በቅርብ ወደ ሚገኝ እርሻ ወደ ሚያርስ ገበሬ ( ገበሬ የሌለበት አካባቢ ከሆነ ደግሞ በምስል በማሳየት) በመውሰድ የተለያዩ ለእርሻ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማለትም: ሞፈር፣ቀምበር፣እርፍ፣ ድግር፣ ማነቀ፣ መርገጥና በምን አንደሚታረስ (ለምሳሌ: በሬ፣ፈረስ፣አህያና ትራክተር) በደንብ እንዲያዩና ወዲያውኑ ያዩት የሚዘራው የጥራጥሬ አይነት (ለምሳሌ: ሽንብራ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ ስንዴ … ወዘተ የሚባሉትን የጥራጥሬ አይነቶች እንዲሁም የአትክልትና የፍራፍሬ አይነቶችን ብዛታቸውንም ስማቸውንና ጥቅማቸውን እንዲለዩ ማብራሪያ መስጠትና በመስክ ጉብኝታቸው ጊዜ የተመለከቱን በሙሉ ለክፍል ጓደኞቻቸው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ጤናቸው እንዲጠበቅ ፣እንክብካቤጥበቃና በማድረግ በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን አንዲገነዘቡ ያድረጉ፡፡በመጨረሻም በመለማመጃ ደብተራቸው በገፅ ላይ የተቀመጠውን የቤት እንስሳትንና የዱር እንስሳትን ለይተው እንዲፅፉ ያድርጉ ወይም በደብተር/በወረቀት እንዲፅፉ እና በቃላቱ አረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያበረታቱ (ምሳሌ እርሻ ገበሩው ትልቅ እርሻ አለው…)

**የመማሪያ እና የመጫዋቻ ቁሳቁሶች:** የግብርና ተግባራት የሚከናወንበት ማሳ፣ቦታ፣/ይህንን የሚያሳይ ተንቀሳቀሽ ምስል፣ እርሳስ፣ደብተር…

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ነገሮችን ለማወቅ የሚኖራቸዉን ተነሳሽነት መመዘን) የቃል

ጥያቄ(በጉብኝታችሁ ምን ተመለከታችሁ፣ ከምስሉ ስለ እርሻ ስራ ምን ተረዳችሁ የግብርና ስራ ምን ምን ይፈልጋል ፣ **የጽሁፍ መጠይቅ** ዘመናዊ እና ባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎችን ቃላት ደግመው ይፃፉ እና ያዘምዱ

## ተግባር አራት፡ እንቆቅልሽ (4ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ፈጠራ ፣ መሳብ፣ መመራመር፣የምግብ አይነት፣ የምግብ ጥቅም፣ቅርፅ ፣የእርሻ መሳሪያ፣ ቁጥር

**የመስተማሪያ ዘዴ:** በእንቆቅልሽ ፣በጥያቄና መልስ፣ በገለፃ

**የመምህር ሚና:** መምህር በመጀመሪያ ሃሳባቸውን ለመሰብሰብ ህፃናት የፈለጉትን ወይም የሚወዱትን መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡በመቀጠልም ሁሉንም ህፃናት እኩል በሚያሳትፍ መልኩ በንቃት ማዳመጥና በደንብ ማሰብ፣መመራመርና የእንቆቅልሹን መልስ ለመመለስ ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ትዕዛዝ ይስጡ፡፡ ቀጥሎ አንድ ህፃን አስነስተው ከጓደኞቹ ፊት ለፊት አንዲቆም/እንድትቆም እንቆቅልሽ ሲል/ስትል እነሱ ደግሞ ምን አውቅልህ/ሽ እያሉ የተለያዩ የምግብ አይነቶችና ጥቅማቸውን ቁጥሮችን የእርሻ መሳሪያ ቁሳቁሶችን በእንቆቅልሽ እንዲማሩ ያድርጉ፡፡

**ለምሳሌ:** እንቆቅልሽ ምን አውቅልሽ

ቅርፄ ሞላላ ፣ መልኬ ነጭ ፣ሰውነት እገነባለሁ፣ እናቴ ዶሮ ፣ እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** እንቁላል

**እንቆቅለሽ** ምን አውቅልሽ/ህ

ቅርፄ ከረዛ እመስላለሁ፣ የአማርኛ ፊደል ስሜ ገ ነው ፣በሂሳብ ቁጥር እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** 7 ቁጥር

**እንቆቅልሽ** ምን አውቅልሽ/ህ

ከእርሻ መሳሪያ ውስጥ አንዱ ነኝ፣ ሁለት አንገት አለኝ፣ ሁለት አንገቴን በሁለት፣ በሬዎች አንገት ላይ አስገብተው፣ በማሰርና የበሬዎችን ደህንነት በመጠበቅ ፣

ስራየን እሰራለሁ እኔ ማን ነኝ ?

**መልስ:** ቀንበር ና ማነቆ

**እንቆቅልሽ** ምን አውቅልሽ/ህ

በህያ ብር ገዙኝ፣ ምግብ ለማዘጋጀት፣ብርድ ለመከላከልናብርሃን ለመስጠት ይጠቀሙብኛል፣ መልኬ ሲገዙኝ ጥቁር ነኝ ፣ሲጠቀሙኝ ቀይ፣ ሲያስወግዱኝ ነጭ

እኔ ማን ነኝ?

**መልስ:** ከሰል

መልሱን ሲሳሳቱ ሀገር እንዲሰጡ መጠየቅ ሀገር የተሰጠው ጠያቂም ቀጥሎ የሚባለውን ካለ በኋላ ጥክክለኛውን መልስ ይናገራሉ፡፡

ኢትዮጵያ ሂጂ ምን አጥቼ

ብዙ ደስ የሚሉ ነገሮችን አይቼ

**ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ** መልሱ ብለው ጠያቂው/ዋ ህፃን መልሱን እንዲናገሩ የተጠየቁት ህፃናት ደግሞ ሀገር መስጠት እንዳለባቸው ያስገንዝቡ፡፡ በመቀጠልም ህፃናት ተራ በተራ እየተነሱ ከጓደኞቻቸው ፊት ለ ፊት በመቆም የሚያውቁትን እንቆቅልሽ እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡

**የመማሪያ እና የመጫዎቻ ቁሳቁሶች:** የበአካባቢ የተለመዱ እንቆቅለሾች በጽሁፍ፣ እንቆቅልሹን የሚገልጹ ስእሎች፣

**የምዘና ስልት:** ምልከታ በማድረግ ፣የቃል ጥያቄ በመጠየቅ...

## ተግባር አምስት ፡ የግል ተግባር (6 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥሮችን መለየት፣ የሳምንቱ ቀናት፣ቅጥ( ሥርዓተ ጥለት)፣ መደርደር፣በቅደም ተከተል፣ የሳምንቱ ቀናት

**የማስተማሪያ ዘዴ :** በግል ስራ ፣በገለፃ፣ በጥያቄ እና መልስ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና:** መምህር! በክፍል ውስጥ ወደ እለቱ ት/ት ከመሄድዎ በፊት የዕለቱን ት/ት የሚዳስስና ማነቃቂያ የሚሆን የሚከተለውን መዝሙር ያዘምሩ፡፡

**የመዝሙሩ ርዕስ: የሳምንቱ ቀናት**

የሳምቱ ቀናት ሲቆጠሩ ሰባት፣
በቅደም ተከተል እንቁጠር ህፃናት፣
1ኛ ሰኞ፣ 2ኛ ማክሰኞ፣ 3ኛ ረቡዕ፣
4ኛ ሀሙስ፣ 5ኛ አርብ፣ 6ኛ ቅዳሜ፣ 7ኛ እሁድ
እነዚህ ናችው የሳምንቱ ቀናት፤
ቅዳሜ እና እሁድ የንፅህና የመዝናናት ቀናት ፣
ሰኞና ማክሰኞ፣ረቡና ሀሙስ እንዲሁም አርብ የትምህርት ቀናት፡፡(2)

**መምህር** ይህን መዝሙር ካዘመሩ በኋላ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ከ1 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በመፃፍና ህፃናት ተራ በተራ እየተነሱ እንዲቆጥሩ ካደረጉ በኋላ ቁጥሮችን የያዘ የተለያዩ ቁርጥራጮችን ለእያንዳንዳቸው በመስጠትና የተለያዩ ፍራፍሬዎችን፣በተቆራረጡ ወረቀቶች ካርድ ያሉ የተለያዩ እንስሳትን የእርሻ መሳሪያ ቁሳቁስ የያዘ ስዕል ጋር ብዛታቸውን እየቆጠሩና እየገጣጠሙ እንዲያወዳድሩ ያድርጉ፣እንዲሁም በቅጥ/ንድፍ ስራ ቁጥሮቹን እና ስእሎችን እንዲደረድሩ ማድረግ፡፡ በመቀጠልም ሁሉም ህጻናት ተራ በተራ ጥቁር ሰሌዳ ላይ እየወጡ ስዕሉን እየሳሉ ብዛቱን እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ: አንድ ህጻን የተሰጠው/ችው 2 ቁጥርን ከ2 ብርቱካን ጋር እያዛመደ/ች እንዲፅፍ/እንድትፅፍ ማደረግና ተገነጣጥለው የተሰጡትን ቁጥር በመገጣጠምና ሲገጣጥሟቸው ያዩትን ቁጥር ወጥተው ተራ በተራ እንዲፅፉ በማድረግ እገዛ ያድርጉ፡፡ መምህርት በደብተራቸው የተለያዩ የቁጥርና ተቆጣሪን መልመጃ መስጠት፣ በመለማጃ ደብተራቸው ላይ በገፅ.................ላይ ያለውን ከ1 እስ ከ 20 ካሉ ቁጥሮች ውስጥ የጎደለውን በመሙላት እንዲፅፉና እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና የመጫዋቻ ቁሳቁሶች:** ኮርኪዎች፣ ጠጠሮች፣ የብርቱካን ስዕል የያዘ ካረድና የተለያዩ እንስሳትን የያዘ ካርድ፣ የተለያዩ ጥራጥሬዎችን ፣የእርሻ መሳሪያዎች፣ የሳምንቱ ቀናትን የያዘ ካርድ፣ አጭርና ረጅም የሆኑ ነገሮች፣ትልቅና ትንሽ የሆኑ ነገሮች...ወዘተ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ( የፃፉትን ማረጋገጥ ማረምና ማስተካከያ መስጠት)፣ ሲገጣጠሙ ማየትና፣ የቃልጥያቄ(የምን የምን ስዕል ሳላችሁ? ምን ምን ተግባር አከናወናችሁ?ከ5 ቀጥሎ ስንት ቁጥር አለ፣ ከአስራ አምስት ቀጥሎስ...

## ተግባር 6: ፕሮጀክት (3 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍቃላት:** የቅርብ አካባቢ፣ ፈጠራን መግለፅ፣ ቁጥሮችን መለየት፣ቤት፣ብርቅዬ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በፕሮጀክት ስራ፣ በገለፃ ፣ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! የፕሮጀክት ስራ ከመስጠትዎ በፊት የህፃናት የቀድሞ እውቀት በመጠቀም ስላላቸው የፈጠራ ችሎታ በአካባያቸው ያዩትንና የሚያውቁትን የቤት እንስሳ ወይም አትክልትና ፍራፍሬዎችን፣ የቤት አይነቶችን (ለምሳሌ ቆርቆሮ ቤት ፣ ሳር ቤት፣ ፎቅ ቤት... ወዘተ) መሳልና መቀባት እንደሚችሉ ከጠየቁ በኋላ ለሁሉም ህፃናት እርሳስ ፣ ፓርከር ፣ ወረቀት፣ መቀስ፣ ሳር፣ አሸዋ ፣ ማጣበቂያ፣ የተቦካ ጭቃ፣ ቁርጥራጭ ወረቀት እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን ተጠቅመው የሚፈልጉትንና የሚያደንቁትን ሞዴል ሰርተው እንዲመጡና ሲሰሩ ግን ደህንነታቸውና ጤንነታቸውን በጠበቀ ሁኔታ መሆን እንዳለባቸው የሳሉትን ብዛት መጠየቅና ዶክመንት አድርጎ ማስቀመጥ ይኖርብዎታል፡፡

**ውድ መምህር!** እባክዎት የፕሮጀክት ስራ ሲሰጡ በቂ ቀናት እንዲሰጡ ካደረጉ በኋላ ሰርተው ካመጡ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

1. በመጀመሪያ የሰሩትን ማድነቅና ምን እንደሰሩ መጠየቅ
2. ምን ምን ነገሮችን ተጠቅመው እነደሰሩት መጠየቅ
3. እንዴት እንደሰሩት በቅደም ተከተል እንዲናገሩ ማድረግ
4. የሰሩትን ለምን እንደሰሩት መጠየቅ
5. ሲሰሩ እገዛ ያደረገላቸው ካለ እና ከሌላ መጠየቅ በመጨረሻም ህጻናት የሰሩትን በማድነቅና በማበረታታት ዶክመንት አድርገው ያስቀምጡላቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ውድ መምህር የሚከተለውን መዝሙር በማዘመር አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ፣ ተፈጥሮን እንዲያደንቁ፣ ሀገር ወዳድነታቸውን እንዲገልፁ በማስረዳት ያዘምሯቸው፡፡

**መማሪያ እና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቤት እንስሳ፣ አትክልትና ፍራፍሬዎችን፣ የቤት አይነቶችን (ለምሳሌ ቆርቆሮ ቤት ፣ ሳር ቤት፣ ፎቅ ቤት...ወዘተ) ስእል /ሞዴል፣ እርሳስ ፣ ፓርከር ፣ ወረቀት፣ መቀስ፣ ሳር፣ አሸዋ ፣ ማጣበቂያ፣ የተቦካ ጭቃ፣ ቁርጥራጭ ወረቀት እንዲሁም ሌሎች
የምዘና ስልት: በምልከታ: ህፃናቱ ሲሰሩ እና ሲናገሩ በአግባቡ መመልከትና ማገዝ፣ የቃል ጥያቄ ምን ነገሮችን እንዳከናወኑ መጠየቅ ፣ የፅሁፍ መጠይቅ መስጠት

**የመዝሙር ርዕስ፡ እናት ሀገሬ ኢትዮጵያ**

እማማ እልሻለሁ ሀገሬ እትዮጵያ
ኑሪልኝ ዘላለም የዓለም መመኪያ፡፡
ጋራ ሸንተረሩ እንዲሁም ሸለቆው ፣
ብርቅዬ እንስሳትን ሁሉንም ሲያዩአቸው፣
ምንኛ ደስ ይላል አቤት ተፈጥሯቸው፡፡
እስኪ እንወቃቸው እስኪ እንቁጠራቸው
አንደ ሁለት ሶስት ብለን እንዘርዝራቸው
ለምሳሌ ያህል ስማቸው ቢጠራ ዋሊያ፣
ምኒልክ ድኩላ፣ አቦ ሸማኔ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ
አረ ብዙ ናቸው እነ ቀይ ቀበሮ

## ሶስተኛ ሳምንት

**ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/**

**አጥጋቢ የመማር ብቃቶች**

- ✓ ቀላል ሥራቸውን በግላቸው አቅደው ያደራጃሉ ፡፡
- ✓ ማህበራዊ ግንዛቢያቸውን በማዳበር ለሌች እንክብካቤ ያደርጋሉ፡፡
- ✓ የተለመዱ ቃላትን ያስታውሳሉ፡፡
- ✓ ነገሮችንና ቁጥሮችን ያወዳድራሉ ፡፡
- ✓ የቁጥሮችንና የቁሶችን ቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ ፡፡
- ✓ ባህላዊ ቅርሶችን ይጠብቃሉ ፡፡
- ✓ የጣት ጨዋታዎችን በእጅና በእግራቸዉ ያሳያሉ ፡፡

**ንዑሳን ይዘቶች ፡** ራስን መቻል ፣ቃላት፣የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣ቁትሮችን ማወዳደር እና ቅደም ተከተል ፣ባህለዊ ቅርሶች

**ተግባር አንድ፡ በስራ መማር (5 ክ/ጊዜ)**

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ቅርሶች

**የማስተማር ዘዴ፡** በስራ መማር

**የመምህር ሚና፡** መምህር! የሚከተሉትን የቡድን ተግባራት ሕፃናት በተነገራቸው መሰረት ያከናውኗቸው

- ✓ ሕፃናቱ በቁመታቸው በማሰለፍ ይዘዋቸው ወደ ውጭ ይውጡ ፡፡
- ✓ እንደ ሕፃናቱ ብዛት በአንድ ቡድን 1 10 ሕፃናት በማድረግ በማመጣጠን (የወንድ እና የሴት ቁጥር) ይመድቡ፡፡
- ✓ ከዚያም በትምህረት ቅጥር ግቢ ውስጥ ያለውን ያለውን የአትክልት ስፍራ በመውሰድ የተወሰኑት ቡድኖች ተክሎችን ውሃ እንዲያጠጡ ሲመድቡ የቀሩት ደግሞ በአትክልት ስፍራ ውሰጥ ቅጠሎችን እንዲያነሱ ያድርጉ ፡፡

- ✓ የተግባር ሥራውን ህግ ይንገሯቸው ይኸውም ውሃ የሚያጠጣው ቡድን ከፊት ካለው አትክልት እንዲጀምርና ከሁለት እስከ አራት ግዜ ውሃ በማጠጣት ለቀጣዩ ሕፃን እንዲሰጥ ሌለኛው ቡድን ደግሞ የሚለቀሙትን ቅጠል በመልክ በመልክ በማድረግ እንዲሰበስቡ (በያዙት ላስቲክ ሲከቱ እያዩ እንዲከቱ) ያደርጉ፡፡
- ✓ ተራቸውን ጠብቀው እንዲሰሩ መከታተልና ማገዝ
- ✓ በዚህ መሰረት የቡድን ሥራውን ከጨረሱ በኋላ ጥላ ሥር እንዲቀመጡ በማድርግ ጥያቄ መጠየቅ
- ✓ ውሃ ስታጠጡ ስንተ ስንት ጊዜ አጠጣችሁ
- ✓ የሰበሰባችሁት ቅጠል ምን ምን ነው? ስንት አይነት ነው? ከሰበሰባችሁት ቅጠል ውሰጥ ለጓደኞቻችሁ ቆጥራችሁ ስጧቸው
- ✓ መምህር! እነዚህን መሰል ጥያቄዎች ከጠየቁ በኋላ ወደ ክፍል ከማስገባትዎ በፊት ሕፃናት እጃቸውን በሳሙና እና በውሃ እንዲታጠቡ በማድረግ ወደ ክፍል ያስገቧቸው

**የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:** የውሃ ማጠጫ፣ የተሰበሰቡትን ቅጠል ማስቀመጫ ፌስታል፣ የስዕል ካርድ ወይም ስለ አትክልት የሚያሳይ ሥዕል ፣ውሃና ሳሙና

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (የተሰጣቸውን ተዕዛዝ ተከትለው መሥራታቸውን በማየት) የቃል ጥያቄ ውሃ ሲያጠጡ ከየት እንደጀመሩ፤ ስንት ስንት ሃይላንድ ውሃ እንዳጠጡ፤ በዕዳት ላይ የተሳተፉት ስንት ዓይንት ቅጠል እንደሰበሰቡ እና ምን ምን ቃላት ተጠቅመው እንደተግባቡ መጠየቅ እንዲሁም ለጓደኞቻቸው ቆጥረው የሰጡትን ቅጠል ትክክል መሆኑን ከሕፃናቱ ጋር በጋራ በመቁጠር ማረጋገጥ፡፡

### ማስታወሻ:

- ሕፃናት ውሃ ሲያጠጡ አቅማቸውን ያማከለ መሆኑን ያረጋግጡ
- ወደ አትክልት ስፍራው ከመሄዳቸው በፊት ምቹ ጫማ ማድረጋቸውንና በደንብ ማሰራቸውን ያረጋግጡ
- ቆሻሻን ሲለቅሙ ስለታማ ነገሮችን በያገኙ በእጃቸው እንዳይነኩ ይንገሯቸው
- ውሃ ሲያጠጡ ልብሳቸው እንዳይበሰብስ መመሪያ ይስጧቸው
- እንዲሁም የልዩ ፍላጎት ሕፃናትን ካላቸው ቁጥር ልክ ከረዳት መምህርዎ ጋር በመሆንና በመከፋፈል ለመራመድ አስቸጋሪ ካልሆነባቸው ይዘዋቸው ይሂዱ የማይቻል ከሆነ ግን እንደ የፍላጎታቸው በማዘጋጀት እንዲሳተፉ ያድርጉ

## ተግባር ሁለት: የውጭ ጨዋታ (6 ክ/ጊዜ)

### ጨዋታ አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ለሕፃናቱ ክፍለ ጊዜው የውጭ ጨዋታ እንደሆነ በመንገር ለወጭ ጨዋታ ያዘጋጇቸው፡፡ በመቀጠልም በቁመታቸው በማሰለፍ ወደ ውጭ በማስወጣት መጠነኛ የሆነ እንቅስቃሴ እንዲሰሩ ካደረጉ በኋላ ክብ በማሰራት "የእንስሳት መያዝ ጨዋታ" የሚለውን

እንዲጫወቱ ያድርጉ ፡፡

## የጨዋታው ቅደም ተከተል

- ✓ አስር ሕፃናትን በክቡ ውስጥ እንዲገቡያድርጉ
- ✓ በመቀጠልም አስሩም ሕፃናት የሚፈልጉትን እንስሳት ስም እንዲጠሩ ያድርጉ አስሩ በክቡ ውስጥ የጠሩትን እንሰሳ በማስመሰል እየተንቀሳቀሱ የእንሰሳውን ድምፅ እንዲያሰሙ ያድርጉ
- ✓ አንድ ልጅ በመጋበዝ እሱም መያዝ የሚፈለገውን እንሰሳ አስሩ ልጆች ከጠሩት ውስጥ እንዲመርጥ እና እንዲናገር በማድረግ ዓይኑን በመሸፈን ድምፃቸውን በመስማት የጠራውን እንሰሳት ተከትሎ እንዲይዝ ማድረግ
- ✓ ከጠራው እንሰሳ ውጭ ከያዘ ከጨዋታ ውጭ እየሆነ ጨዋታው ይቀጥላል
- ✓ መጨረሻ የሚቀረው የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል እንዲህ እያለ ሁሉም ሕፃናት በጨዋታው እንዲሳተፉ ያድርጉ
    - ጨዋታው ሲያበቃ እንድ ላይ በመሰብሰብ ስንት የእንሰሳ ስም ጠራን?
    - ለሰው ልጅ ለምግብነት የሚጠቅሙ የትኞቹ እንሰሳት ናቸው ?
    - ከጠራችኋቸው እንሰሳት መካከል ለእርሻ አገልግሎት የሚጠቅሙ የትኞቹ ናቸው ?
    - የጠራችሁትን የእንሰሳ ድምፅ በሰዕል እንሰሳውን ስላችሁ አሳዩ

በመጨረሻም የተለያዩ መልመጃዎችን መስጠት (ምሳሌ  የእንስሳት፣ለምግብነት ለእርሻ የሚሆኑ እንስሳትን ስም እንዲጽፉ ፣ከተግባራቸው ጋር እንዲያዛምዱ...)  በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ላይ ያለውን በአካባቢያቸው የሚያውቁትን የቤት እንሰሳ ስለው እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡

**የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:** የእንስሳት ሰዕል፣የዓይን መሸፈኛ ንፁህ ጨርቅ፣የተቀረፀ የእንሰሳት ድምፅ፣ቀለምና የመለማመጃ ደብተር፣ እርሳስ...

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(ጨዋታውን ሲጫወቱ በትክክል መጫወታቸውን በማየት /ለምሳሌ በትክክል የጠሩትን የእንሰሳት እንቅስቃሴ እና ድምፅ መጠቀማቸውን )

**የቃል ጥያቄ:** ለግብርና የምንጠቀምባቸው እንሰሳት እነማን ናቸው፣ድምፃቸውን አሰሙ፣ የጠሩትን እንሰሳ ስንት እግር አንዳለው ወይም እንዳላት መጠየቅና የሚደረግላቸው እንክብካቤ ምንድን ነው የሚሉትንና ሌሎችን የምዘና ስልት ተጠቅመው ይመዝኗቸው፡፡

## ማስታወሻ:

- ወደ ውጭ ከመውጣታቸው በፊት አዳጋ ከሚያስከትሉ ነገሮች ነፃ መሆኑን እና የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡
- ዓይናቸው የሚሸፈንበት ጨርቅ ንፁህ መሆኑን እና እንዲሁም ሲታሰር እንዳይጠብቅ በማየት ያረጋግጡ፡፡
- ጨዋታውን ሲጫወቱ ለመያዝ በሚደረግ ጥረት ዕርስ በርስ እንዳይገፋፉ ቀድመው ያስጠንቅቁ፡፡
- ልዩ ድጋፍ እና ክትትል የሚያስፈልጋቸውን ሕፃናት የራስዎትን መንገድ በመጠቀም እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡

## ጨዋታ ሁለት ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** እንስሳት፣ ቁጥር ፣ድምፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ:**

**የመምህር ሚና:** በመምህር! ሕፃናቱን በቁመታቸው በማሰለፍ እና ወደ ውጭ በማስወጣት ትንሽ ቡድን ይመስርቱ ይህም በአንድ ቡድን ቢበዛ አስር ሕፃናት በማድረግ ይመድቡ።

የተለመዱ ቃላት የመጥራት ጨዋታ

- ✓ በመደቡት መሰረት ትንንሽ ክብ እንዲሰሩ ያድርጉ፣
- ✓ የቡድኑን ስም በእንስሳት ፣ በዛፍ እና በአዕዝርት ስም ይወክሉ/ስያሜ ይስጧቸው፣
- ✓ የቡድን አባላት ከ1 10 ባሉ ቁጥሮች ይወክሏቸው፣
- ✓ በመቅረፅ ድምፅ የተዘጋጀውን ባህላዊ ክላሲካል በመክፈት ክባቸው ውስጥ በመሆን እንዲቀሳቀሱ ያድርጉ፣
- ✓ የቡድናቸውን ስም እና ቁጥር ሲጠራ የፈለጉትን የእንስሳት፣ ዛፍ እና የአዕዝርት ስም እንዲጠሩ ያድርጉ ሲጠሩ ማስታውሻ ይያዙ፣
- ✓ የቡድኑ እና የራሱ ስም ተጠርቶ ቃላት መጥራት ያቃተው እና የተጠራውን መልሶ የጠራ ሕፃን ከጨዋታ ውጭ እየሆነ ጨዋታው ይቀጥላል፣
- ✓ በመጨረሻም አብዛኛው የቡድን አባላት የቀረበት ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል፣
- ✓ እባክዎት ውድ መምህር! ከጨዋታው በኋላ በጨዋታው ላይ የጠሩትን ቃላ ት በደብተራቸው በማፃፍና መነሻ በማድረግ አጫጭር ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው።

**የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:** እንስሳት፣ ዛፍ፣ የአዕዝርት ስዕልእና ስም፣ደብተር፣ እርሳስ፣ በመቅረፅ ድምፅ የተቀረፀ የባህላዊ ጭፈራ ክላሲካል

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(በትክክል ቃላት መጥራት መቻላቸውን ሰምቶ በማየት ማረጋገጥ) የቃል ጥያቄ: የቡድናችሁ ስም ምን ነበር? ስንት የእንስሳት ፣ የአዕዝርትእና ዛፎች ስም ጠራችሁ? ድምራቸው ስንት ሆነ?

## ተግባር ሶስት: ውይይት (4 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የግንኙነት ቃላት፣እርባታ፣ ጤፍ፣ ዝግባ፣ መተጋገዝ ፣መተባበር

**የማስተማሪያ ዘዴ:**

**የመምህር ሚና:** መምህር! አሁን ክፈለ ጊዜው የውይይት እንደሆነ በመግለፅ ለውይይቱ ያዘጋጃቸው ለውይይቱ ያመ ዘንድ እንደ አቀማመጣቸው ከ1 6 ሕፃናት በአንድ ቡድን በማድረግ ይመድቡ፣

### አዳዲስ የግንኙነት ቃላት

በቅድሚያ አዳዲስ የግንኙነት ቃላት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይግለፁላቸው

በመቀጠል በግብርና ጊዜ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው ቃላት ምሳሌ በመጥቀስ ይንገሯቸው፣ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በግብርና ጊዜ አካባቢያቸው ላይ ያሉ ሰዎች ሲናገሩ የሰሟቸውን

ከግብርና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቃላት በተመደቡበት ቡድን እንዲናገሩ ማደረግ፤ ለውይይቱ ሰዓት መስጠት፤ ከቡድኑ መሪ የሚሆኑ አንድ አንድ ህጻናትን በመወከል የቡድናቸውን ሃሳብ እንዲያቀርቡ ማድረግ (ሲያቀርቡ በእነሱ ዕድሜ ልክ መሆን አለበት) እራስዎ ያዘጋጁትን አዳዲስ የግንኙነት ቃላት የያዙትን የሰዕል ካርድ በመጠቀም እርሰዎ እያንብቡላቸው፤ እነሱ እንዲደግሙት ያድርጓቸው። ምሳሌ፡ እርባታ፣ ጤፍ፣ ዝግባ፣ መተጋገዝና መተባበር ወዘተ

የተነበበው ቃል ምንን እንደሚያመለክት ይጠይቋቸው (ከመልሳቸው በኂላ መተጋገዝ፣መተባበር የመሳሰሉት ባህላችን እንደሆነና አኛም እርስ በእርሰ መተጋገዝ እና መተባበር እንዳለብን ይንገሯቸው፤በመቀጠልም ያነበቡትን ቃላት ብዛት ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጓቸው

እባክዎ አዳዲስ የግንኙነት ቃላትን ደግመው መፃፍ፣ማዛመድ እንዲሰሩ ማረግ በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ላይ ያለውን የእንሰሳት ሰስዕል በማየት አገልግሎታቸውን እንዲፅፉ ያድርጉ

**ማስታወሻ:** አስቀድመው ከግብርና ጋር ግንኙነት ያላቸውን አዳዲስ ቃላት ያዘጋጁ

**የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:** የግንኙነት ቃላት የተፃፋበት ፍላሽ ካርድ…

**የምዘና ስልት: ምልከታ** የተሰጣቸውን ውይይት በተገቢው ስርአት እያከናወኑ መሆኑን መከታተል ሲመልሱ ፣ሲያቀርቡ…፣ የቃል ጥያቄ፡ መተጋገዝ ምንድን ነው፣ መተባበር ምንድነው በምን ልንተባበር እንችላለን፣ …

## ተግባር 4፡ የግል ተግባር (5 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር ፣ቅደም ተከተል፣ አይነት ፣ መመደብ

**የማስተማር ዘዴ:** በተግባር ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ ፣ ሰርቶ በማሰራት

**የመምህር ሚና:** መምህር ክፍለ ጊዜው የግል ተግባር የሚያከናውኑባቸው መሆኑን በመንገር ለመስራት ያዘጋጇቸው። ይህን ተግባር ለማከናወን አስቀድመው ያዘጋጁትን የመማሪያእና የመጫወቻ ቁሳቁሶችን ይጠቀሙ።

### ቅደም ተከተል ማስያዝ፡

- ✓ ሕፃናት በተቀመጡበት መቀመጫ ላይ የመማሪያ ቁሳቁሶችን መመደብ፣
- ✓ በቅድሚያ እርስዎ ያዘጋጁትን ቁሳቁሶቹን በመጠቀም ቅደም ተከተላቸው በመጠቀም በዓይነታቸው ይመድቧቸው የመደቧቸውን በመቁጠር ቅደም ተከተላቸውን በመጠየቅ ይደርድሩ ከዚያም የደረደሩትን ይህ የዛፍ ስዕል ነው ፤ቀጥሎ ደግሞ የላም፣የሽምብራ ሥዕል ፣ የዛፍ ሥዕል ብዛት 3 ሲሆን የላሞች ብዛት ደግሞ 6 ነው ፣ የሽምብራው ብዛት ደግሞ 8 ስለሆነ በቅደም ተከተላቸው 3፣6፣8 በማድረግ እኔ ደርድሪያለሁ እስኪ ልክ እንደኔ አድርጎ የሚያሳየኝ እርስዎን በመከተል አንድ ሁለት ልጆች እንዲሰሩ ያድርጉ።
- ✓ የሰሩትን ልጆች እና እርስዎን መሰረት በማድረግ በየጠረጴዛቸው የተቀመጠውን ቁሳቁስ በመጠቀም እንዲሰሩ ያድርጉ ውድ መምህር! እነሱ ሲሰሩ እርስዎ በመዟዟር ያስያዙትን ቅደም ተከተል የስዕላቸውን ስም እና መጠናቸውን እንዲነግርዎት ያድርጉ።
- ✓ በትክክል መስራታቸውን ከራሳቸው ጋር በመቁጠር እና የምስሉን ስም አይተው በማረጋገጥ ለተሳሳቱት ማስተካከያ ሲሰጡ በትክክል ለሰሩት ማበረታቻ ይስጧቸው።
- ✓ በመጨረሻም በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ላይ ያለውን ቁጥሮችን ከትንሽ ወደ ትልቅ

ቁጥር በቅደም ተከተል መደርደር ያሰሯቸው፡፡

**ልዩ ማስታወሻ:** ይህንን የግል ተግባር ክፍለ ጊዜው በሚደገምበት ጊዜ ምስሎቹን በእርሻ መሳሪያ በመቀየር ማሰራት ይችላሉ፡፡ ምሳሌ፡ ደማ፣መኮትኮቻ፣ ማረሻ

**የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:** የስዕል ካርድ፣ እርሳስ፣ የመለማመጃ ደብተር

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(ቁሳቁሱን ሲደረድሩ በትክክል ቅደም ተከተል ጠብቀው መደርደራቸውን በማየት መከታተል) ስንት ሽንብራ ነበር፣ የምን ምስሎች ነበሩ...

**የቃል ጥያቄ:** ምን ምን ስዕል ደርሷችሁ ነበር፣ እንዴት አድርጋችሁ በቅደም ተከተል ደረደራችሁት

**ማስታወሻ:** ስቀደመው ከግብርና ጋር ግንኙነት አያላቸውን ብዛት የሚያሳይ የስዕል ካርዶችን ማዘጋጀት እንዳለብዎት አይዘንጉ፣

## ተግባር 5: መዝሙር (5 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** እንስሳቶች፣የጥራጥሬ አይነቶች ፣ቁጥር፣ማረስ

**የመምህር ሚና :** መምህር ክፍለ ጊዜው መዝሙር መሆኑን ያስገንዝቧቸው መዝሙሩን ለመዘመር አሁን አዲስ መዝሙር ይዤላችሁ መጥቻለው እስኪ መዘመር የሚፈልግ ይዘጋጅ በማለት ስሜታቸውን በማነቃቃት ይጀምሩ፣

### የገበሬ ልጅ ነኝ

- ✓ በቅድሚያ ያዘጋጁትን የሥዕል ካርድ በመጠቀም በመዝሙሩ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት ያንቡብላቸው እርስዎም መዝሙሩን በተግባር በማሳየት (ለምሳሌ ያርሳል ሲል ወደመሬት በማጎንበስ እንደመቆፈር እያደረጉ)በመዘመር ያሳዩዋቸው፣
- ✓ ከዚያ ተማሪዎች ከወንበራቸው እንዲነሱ እና በትክክል እንዲቆሙ ማድረግ፣
- ✓ እርስዎ እየዘመሩ እነሱ ከእርስዎ ቀጥሎ እንዲዘምሩ ማድረግ፣
- ✓ ይህንን ተግባራት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ካስደገማችሁ በኋላ ለብቻቸው እንዲዘምሩ ያድርጉ፣
- ✓ ከመዝሙሩ በኋላ በተማሪ መለማመጃ መፅሀፍ ገጽ ላይ ያለውን ምስሎቹን በማየት መጠሪያ ስማቸው እንዲፅፉ ያድርጋቸው

### የገበሬ ልጅ ነኝ

አባቴ ገበሬ ነው ብዙ ከብት ያረባል፤

10 በግ ያረባል፤

20 ዶሮ ያረባል፤

መሬቱን በበሬ አርሶ ዘር ይዘራል፤

ጤፍ ስንዴ በቆሎ ያመርታል፤

በአህያ በመጫን ለገበያ ያቀርባል፤

በገንዘቡ ለእኔ ልብስ ይገዛል፡፡

እኔም በሬውን እወደዋለው፤

ልክ እንደ አባቴ እንከባከበዋለው፤

ሳር እና ድርቆሽ እሰጠዋለው፡፡

*የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:* የእንስሳት ስዕል እና ቁጥር የተጻፈባቸው ካርዶች፤ እርሳስ

*የምዘና ስልት:* ምልከታ (መዝሙሩን ሲዘምሩ ስንኙን በትክክል መጥራታቸውን ) የቃል ጥያቄ (ስንት ከብት ያረባል ነበር? ፣ስንት ዶሮ ነበረው ? ስንት በግ ነበረው ? የሚያርሰው በምን ነበር ?) የፅሁፍ መጠይቅ መስጠት፡ የግብራን ንስሳትና ማሳሪያዎችን እንዲጽፉ እና ስዕል እና ቃላት እኒዲያዛሙ ማድረግ

## ተግባር ስድስት: በስራ መማር (5 ክ/ጊዜ)

*ቁልፍ ቃላት:* ባህላዊ አልባሳት፣ የምግብ አይነቶች፣ ባህላዊ ጭፈራ

*የማስተማሪያ ዘዴ:* በመስሎ ጨዋታ፣ በገለፃ፣በጥያቄና መልስ

*መምህር ሚና:* *መምህር* ክፍለ ጊዜው የድራማ መሆኑን በመግለፅ ያዘጋጇቸው፡፡ በቅድሚያ ድራማውን የሚሰሩ ሕፃናት በመምረጥ ያዘጋጁትን ድራማ ለማቅረብ እንዲዘጋጁ ያድርጉ፣

### ባህልን መጋራት

- ✓ መርጠው ያዘጋጃቸውን ሕፃናት የተለያዩ ባህልን የሚገልጹ አልባሳት እንዲለብሱ ያድርጓቸው፣
- ✓ በመቀጠል የተዘጋጁበትን ድራማ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ እንዲሠሩ ያድርጉ፣
- ✓ የለበሱትን አልባሳት ባህል የሚወክል የምግብ ዐይነቶችን ያዘጋጁ በማስመሰል እርስ በእርሳቸው እንዲገባበዙ ያድርጉ፡፡ እንዲሁም አንድ ህጻን የገበሬ አልባሳትን በማልበስ እርሻ ውሎ እንደመጣና እንደደከመው በመግለጽ ምግብ እንዲሰጡት ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ከብሄር ብሄረሰብ ምግቦች ውስጥ የኔ “ቆጮ” አለ የእኔ ደግሞ “ዶሮ ወጥ” አለ ቅመስ እያሉ ይሰጡታል፡፡ በመጨረሻም የለበሱትን አልባሳት ጭፈራ አብረን እንጨፍር በማለት ጨፍረው ይገባሉ፣

*የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:* የባህል አልባሳት ፣ የባህል የምግብ አይነቶችን የያዘ ሥዕል/ ሞዴል፣ የተቀረፀ የባህል ሙዚቃ እና ማጫወቻ...

*የምዘና ስልት:* ምልከታ (ሲሠሩ በማየት) የቃል ጥያቄ: ስንት ዓይነት የባህል አልባሳት አሳዩን? ስንት ዓይነት የባህል ምግብ አሳዩን? እናንተ ምን ዓይነት የባህል ምግብ ቀምሳችሁ ወይም በልታችሁ ታውቃላችሁ? ይህ ምግብ የየት አከባቢ ባህል ነው? አልባሳቱስ? በምን አይነት ባህላዊ ጭፈራ ጨፈራችሁ....

### ማስታወሻ:

- አስቀድመው ድራማውን የሚሰሩ ህጻናትን በመምረጥ ማስጠናት እንዳለብዎት አይዘንጉ፣ ሁሉም ህፃናት እንዲሰሩ ያድርጉ
- ልዩ ፍላጎት እና እገዛ የሚያስፈልጋቸው ህጻናት ካሉ በድራማው ላይ እንዲሳተፉ ዕድል ይስጧቸው፣

- የድራማውን ሀሳብ በአንድ ጊዜ ለመያዝ ስለማይችሉ የክፍለ ጊዜው ድልድል ላይ ባለው መሠረት ይድገሙላቸው፡፡

# አራተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

- ✓ ከሌሎች ጋር ያላቸዉን የግንኙነት ክህሎት ያዳብራሉ፡፡
- ✓ የዉይይት ተሳትፏቸዉን ያሳድጋሉ፡፡
- ✓ ማኅበራዊ ግንዛቤን በማሳደግ ለሌሎች እንክብካቤ ያደርጋሉ፡፡
- ✓ ማኅበራዊ ግንኙነታቸዉን ያሳድጋሉ፡፡
- ✓ መደበኛ የምት እንቅስቃሴን ያከናውናሉ፡፡
- ✓ የቅጥን ትርጓሜ ይገልፃሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ የኪነ ጥበብ እና ለእደ ጥበብ ሥራዎች ዋጋ ይሰጣሉ

**ንዑሳን ይዘቶች፡** ማኅበራዊ ግንዛቤ ፣ ራስን መግለፅ፣ የትልልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣ ቅጥ/ ሥርዓተ ጥለት፣ ጥበባዊ እሴት

## ተግባር 1፡ የግል ሥራ (6 ክ.ጊዜ)

### የግል ስራ አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ማኅበራዊ ግንዛቤ፣ራስን መገንዘብ፣ ጥበባዊ ግንዛቤ፣እርባታ፣ እርሻ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! አሁን ክፍለ ጊዜው የግል ሥራ የሚሰሩበት መሆኑን በመግለፅ ያዘጋጀዘቸው፡፡ አስቀድመው ለዚሁ ያዘጋጁትን ፖስተር ወይም ሥዕል ይጠቀሙ፣

### ስለ እርሻ እና እርባታ

- ✓ ሕጻናቱን ጥንድ በማድረግ ይመድቦቸው፣
- ✓ ያዘጋጁትን የእርሻ እና የእርባታ ቻርት ወይም ሥዕል ለሕጻናቱ በማሳየት ከስዕሉ ምን እንደተመለከቱ ይጠይቋቸው፣
- ✓ ሕጻናቱ ከተናገሩት በመነሳት እና ምስሉን በመጠቀም (ሁሉም ሕጻናት ማየት በሚችሉበት ቦታ በማስቀመጥ) ሰዎች እንዴት እንደሚያርሱ፣ አንድ ላይ በህብረት እንደሚሰሩ፣ የእርባታ ከብቶች እነማን እንደሆኑ እና እንዴት እንደሚረቡ ቀላል የሆነ ቋንቋ በመጠቀም ይግለፁላቸው፣
- ✓ ከእርስዎ በመቀጠል አንድ ሕጻን በመጋበዝ ከስዕሉ ላይ ምን እንደተመለከተ/ች ወይም ምን እንደተገነዘበ እንዲናገር ያበረታቱት፣
- ✓ ሲጨርስ ምስሉ ላይ ካሉት እንስሳት የቱን እንደሚወድ/ምትወድ እንዲናገር/ እንድትናገር ይጋብዙ/ዟ/ት ለምን እንደሚወደደው/ችው ይጠይቁ መልሰው ሲጨርሱ ከእሱ/እሷ ጋር ጥንድ የሆነው ጓደኛውን በመጋበዝ ልክ እርስዎ እሱን በጠየቁበት መንገድ እንዲቀጥሉ ያድርጉ፣

- ✓ አጠገባቸው በመሆን የሚያቅታቸውን ነገር በማገዝ ሁሉም ሕፃናት በጓደኞቻቸው ሲጋበዙ እየወጡ እንዲናገሩ ያመቻቹላቸው፤
- ✓ ሁሉም ተናግረው ሲጨርሱ እርስዎ ምስሉን በመጠቀም በጥያቄና መልስ ያጠቃሉላቸው ምሳሌ፡ ይህ ሥዕል ምንን አሳያችሁ፣ይህስ፣ በማለት
- ✓ የእርሻ ስራ ሲከናወን የሚያሳይ ስዕል ስለው ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ፣የሳሉትን በማየት እንዲያደንቁ እና እርስ በእርስ እንዲደናነቁ ያድርጉ፤
- ✓ ስለሰሩት ስዕል ለክፍል ህፃናት ገለፃ ጣርጉ

**የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:** ስለ እርሻ በህብረት ሲሠሩ እና የከብት እርባታ እንዴት እንደሚሰራ የሚያሳይ ሥዕል ወይም ፖስተር

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ምስሉን ሲጠቀሙ በማየት) የቃል ጥያቄ (ሥዕሉ ላይ ምን ሲያደርጉ ያሳያል? ከእንስሳቶቹ ዉስጥ የትቹን ትወዳላችሁ? ለምን?

### ማስታወሻ:

- አስቀድመው ስለ እርሻ ሥራ እና ከብት እርባታ የሚያሳይ ሥዕል ወይም ፖስተር ማዘጋጀት እንዳለብዎ አይዘንጉ፣

## የግል ሥራ ሁለት ( 3/ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቀርጻ ቅርጽ፣ትንሽ፣ትልቅ፣ መካከለኛ፣ ማወዳደር፣መመገብ፣ጥራጥሬ

**የማስተማር ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! አሁን ክፍለ ጊዜው የግል ሥራ የሚሰሩበት መሆኑን በመግለፅ ዝግጁ ያድርጓቸው ለዚሁ ያዘጁትን አዝርዕት ወይም ጥራጥሬ ያቅርቡ በመቀጠል

### ቅርፆችን መለየት

- ✓ ሕጻናቱን ጥንድ በማድረግ ይመድቦቸው፤
- ✓ ያዘጋጁትን የጥራጥሬ ዘር በመደባለቅ በየጠረጴዛቸው ያስቀምጡ፤
- ✓ ከዚያ ሶስቱን ጥራጥሬዎች እያሳዩ ስማቸውን ይጠይቋቸው
- ✓ እንዴት እንደሚለዩ እና እንደሚያወዳድሩ( ማወዳደሪያ ቃላቶችን ትንሽ፣ መካከለኛ እና ትልቅ የሚሉትን እርስዎ ሲጠሩ እነሱ ከእርስዎ ቀጥሎ እንዲጠሩ ያድርጉ) እና በተግባር በማሳየት እርስዎን በመከተል ጠረጴዛቸው ላይ የተቀመጡትን ጥራጥሬዎች በመጠቀም እንዲሠሩ ዕድል ይስጧቸው፤
- ✓ ሲጨርሱ በተራ በማስነሳት እና ወደ ፊት በመምጣት ከጥራጥሬዎቹ ስም በመጀመር በመጠናቸው እና በአይነታቸው እንዲደረድሩ እና የማወዳደሪያ ቃላት በመጠቀም እያወዳደሩ እንዲናገሩ ያግዟቸው ፤
- ✓ በዚሁ መሠረት ሁሉም ሕጻናት እንዲሠሩ ያድርጉ፤
- ✓ ሰርተው ሲጨርሱ ከሁሉም ትልቁ ጥራጥሬ ማነው፣ መካከለኛውስ፣ ትንሹስ፣ በማለት ይጠይቁ እና የማወዳደሪያ ቃላትን በመጠቀም እርስዎ ሲሉ እነሱ እንዲደግሙ ያድርጉ፤

- ✓ ከሶስቱ ጥራጥሬዎች የቱን ተመግበው እንደሚያውቁ እና የቱን እንደሚወዱ ይጠይቃቸው፣
- ✓ በመጨረሻም በደብተራቸው የጥራጥሬዎችን ስም እንዲጽፉና አረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያርጉ እንዲሁም በመለማመጃ መፅሀፋቸው ገጽ ላይ ያለውን ተግባር ያሰራቸው፣አረፍተ ነገር መሥራት ባቄላ፣ስንዴ ፣ በቀሎ

**የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:** ጥራጥሬ ባቄላ፣ ስንዴ፣ በቀሎ፣ የቃላት ቻርት የማወዳደሪያ ቃላት

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (ጥራጥሬውን ሲለዩ እና ሲያወዳድሩ በማየት) የቃል ጥያቄ (ይህ ጥራጥሬ ምንድን ነው፣ የቱ ጥራጥሬ ከሁሉም ትልቅ ነው የቱ ትንሽ ነው፣ምን መብላት ትወዳላችሁ፣በቃል አረፍተ ነገር ስሩ ማሳሌ ባቄላ እኔ ባቄ ተቀቅሎ መብላት እወዳለሁ..

## ተግባር 2: የመስክ ጉብኝት (4 ክ.ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማህበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን መገንዘብ፣ ጥበባዊ ግንዛቤ፣ተክል ፣መትከል፣መንከባከብ፣ ማወዳደር

**የመምህር ሚና:** መምህር! አሁን ክፍለ ጊዜው ወደ ውጪ በመውጣት የመስክ ጉብኝት የሚያደርጉበት መሆኑን በመግለፅ ያዘጋጇቸው፡፡ አስቀድመው በግቢ ውስጥ ያለው የአትክልት ስፍራ በሌላ አለመያዙን ያረጋግጡ ፣

### ጉብኝቱ ስለ እርሻ ሥራ ነው

- ✓ ሕጻናቱን በቁመታቸው በማሰለፍ ወደ ውጪ ያስወጣቸውና ጥላ ላይ እንዲቀመጡ ያድርጉ፣
- ✓ ከዚያም ወደ አትክልት ስፍራው ሲገቡ እንዳይገፋፉ፣ አትክልት ወይም ሳር ላይ እንዳይቆሙ፣ እንዳይቆርጡ እና የመሳሰሉትን ህግ ይንገሯቸው፣
- ✓ የአትክልት ስፍራው እንዴት እንደሚቆፈር፣ እንዴት እንደሚጠበቅ፣ ውሃ እንዴት እንደሚጠጣ፣ አጥሩ ሲፈርስ እንዴት እንደሚጠገን፣ እያሄሄሩ እና ገለፃ እያደረጉ ያሳያቸው፣
- ✓ እንደ ትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ የግብርና ክበብ አባላት የሆኑ መምህራንና ሕጻናት በማስጎብኘት እንዲሳተፉ ያድርጉ፣
- ✓ የመስክ ጉብኝቱ ካበቃ በኋላ እጃቸውን በሳሙና እንዲታጠቡ በማድረግ ጥላ ሥር ያስቀምጣቸውና የውይይት ጥያቄዎችን ይጠይቃቸው
- ✓ ምን ምን ነገሮችን ተመለከታችሁ፣ ካያችሁት ተክሎች ሁሉ በጣም ረጅረሙ የቱ ነው፣ አጭሩስ፣ እናንተ በምትኖሩበት ግቢ ውስጥ የተክል ስፋራ አላችሁ ምን ምን ተክል ተክላችኋል፣ ቤተሰቦቻችሁስ የሚያረቡት እንስሳት አለ፣ ካለ ምን ምን ናቸው እናንተስ ትኖቹን እንስሳት ትወዳላችሁ ቤተሰቦቻችሁ ለሚያረቦቸው እንስሳት ምን በማድረግ ታግዛላችሁ በማለት ያወያዮቸው እና ትምህርቱን ያጠቃሉ፣
- ✓ በተማሪ መለማመጃ መፅሀፍ ገጽ ላይ ያለውን ቃላት መመስረት ተግባር ያሰራቸው
- ✓ በመጨረሻ በጉብኝት ያገኙትን ልምድ ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻቸው ይንገሩ

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የተዘጋጀ የእርሻ ስፍራ፣መቆፈሪያ፣ውሃ ማጠጫ፣አካፋ ፣ውሃ፣ሳሙና...

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (በጉብኝቱ ወቅት ያላቸውን ስሜት በማየት)፣ **የቃል ጥያቄ** ጉብኝቱ እንዴት ነበር ምን ምን አያችሁ እናንተስ በግቢያችሁ የግብርና ሥራ ትሰራላችሁ ወላጆቻችሁስ የሚያረቡት እንስሳት አለ ካለ እናንተስ የቱን ትወዳላችሁ ወላጆቻችሁንስ ምን በማድረግ ታግዛላችሁ...

**ማስታወሻ:**

- አስቀድመው የግብርና ስፋራውን ለጉብኝት ምቹ ማድረግዎን አይርሱ፣
- የሕጻናቱ ጫማ መታሰሩን እና ምቹ መሆኑን ያረጋገጡ፣
- ልዩ ፍላጎት እና እገዛ የሚያስፈልጋቸው ልጆች ካሉ በማመቻቸት እንዲሳተፉ ዕድል ይስጧቸው፣
- ሁሉንም አሰርቶ ለመጨረስ ስለማይችሉ የክፍለ ጊዜው ድልድል ላይ ባለው መሠረት ይድገሙላቸው::

## ተግባር 3: በስራ መማር

### ድራማ አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ግብርና ፣እርባታ፣ እርሻ፣አዝመራ፣ አዝእርት፣ፅዳት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመስሎ ጨዋታ፣ በገለፃ ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና:** መምህር! አሁን ክፍለ ጊዜው ወደ ውጪ በመውጣት ድራማ የሚሰሩ መሆኑን በመግለፅ ያዘጋጀዞቸው ፣

### የግብርና ሥራ

- ✓ ውጪ ቪድዮ ለማሳየት የሚቻል ከሆነ ያስወጧቸው ነገር ግን ውጪ ለማሳየት የማይቻል ከሆነ ክፍል ውስጥ ያዘጋጁትን ስለ ግብርና ማለትም ስለ እርሻ፣ ስለ ከብት እርባታ፣ ስለ እረኝነት፣ ስለ አዝርት/አዝመራ ስብሰባ የመሳሰለውን የሚያሳይ ቪድዮ በመክፈት ለሁሉም ሕጻናት በቅርበት እንዲያዩ ያድርጉ፣
- ✓ ሕጻናቱን በቁመታቸው በማሰለፍ ወደ ውጪ ያስወጧቸው፣
- ✓ ከዚያም ከአምስት ባልበለጠ ቡድን በመመደብ ቡድን አንድ አራሽ ገበሬ አንድ ሕጻን ሲሆን ሌሎቹ ሁለቱ በሬ ሊሎቹ ደግሞ አጋዥ በመሆን በቪድዮ እንዳዩት ይተውኑ
- ✓ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ከብት አርቢ በመሆን ግማሹ ሳር እንደሚሰጥ ሌላው ውሃ ሲያጠጣ ሌላው ደግሞ የከብቶቹን ማደሪያ እንደሚያፀዳ በመሆን በቪድዮው መሠረት እንዲተውኑ ያድርጉ፣
- ✓ ሦስተኛው ቡድን ከመካከላቸው አንዱ እረኛ በመሆን ሌሎቹ ደግሞ ከብት ቢሆኑ እረኛው ሲጠብቅ እንደ ቪድዮው እንዲተውኑ ያድርጉ፣
- ✓ አራተኛው አዝመራ ሰብሳቢ በመሆን እየተባበሩ አዝመራን እንደሚሰበስብ እና

እንደሚከምር በማስመሰል እንዲተውኑ ያድርጉ፣

- ✓ ሲጨርሱ በአግባቡ በሳሙና እጃቸውን ታጥበው ወደክፍል ይግቡ በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ያልሰራው ቡድን እየተቀያሩ እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው
- ✓ ተግባሩ ሲጠናቀቅ ወደ ክፍል በማስገባት ምን ሆነህ ነበር የተጫወከው ምን ምን አደረክ የቱን ሥራ ወደደከው ወደ ፊት ምን መሆን ትፈልጋለህ የመሳሰሉትን ይጠይቃቸው፣ መሬት የሚያርስ ምን ይባላል፣ ከብት የሚጠብቅ ምን ይባላል፣ ከብት የሚያረባ ምን ይባላል

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** ስለ ግብርና ማለትም ስለ ከብት እርባታ፣ስለ እረኝነት፣ስለ አዝመራ አሰባሰብ ፣ስለ እርሻ የሚገልጽ ቪድዮ፣ መቆፈሪያ፣ውሃ ማጠጫ፣አካፋ ፣ዶላ፣ከተገኘ የእንስሳት ማስክ፣ ውሃ፣ሳሙና፣ በካርቶን /በእንጨት የከብት ማደሪያ ቤት....

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (በድራማው ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በማየት) የቃል ጥያቄ ምን በመሆን ተጫወታችሁ፣ የቱ ገጸ ባሕርይ ወደዳችሁት፣ ወደ ፊት ምን መሆን ትፈልጋላችሁ፣ የከብት እረኛ ምን ይባላል፣እርሻ የሚያርስ ምን ይባላል፣ከብት የሚያረባስ...

## ድራማ ሁለት ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማኅበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን መገንዘብ፣ ጥበባዊ ግንዛቤ፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመስሎ ጨዋታ፣ በገለፃ ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ቁጥር ቃላት

**የመምህር ሚና:** መምህር አሁን ክፍለ ጊዜው የመስሎ ጨዋታ መሆኑን በመግለፅ ያዘጋጃቸው

### የግብርና ሥራ

- ✓ በተቀመጡበት ወንበር መሠረት ለእርስዎ እንደሚመችዎ በማድረግ ቡድን ይመሥርቱ
- ✓ ከዚያ እንዴት እንደሚጫወቱ እርስዎ እንደ አንድ እንስሳት በመሆን ያሣዩአቸው፣
- ✓ ባዩት መሠረት እንዲጫወቱ ባዘጋጁት ቡድን ልክ የእንስሳትን ስም በማዘጋጀት ለሁሉም ቡድኑ አንድ እንዲያነሱ ያድርጉ፣
- ✓ ስላነሱት እንስሳት ለ5 ደቂቃ እንዲወያዩ ጊዜ ይሥጧቸው፣
- ✓ የመወያያ ጊዜው እንዳበቃ ከፊት ካለው ቡድን በመጀመር ወደ ፊት በመውጣት የደረሳቸውን የእንስሳት እንቅስቃሴ እና ድምፅ እያስመሰሉ እንዲጫወቱ ማድረግ፣
- ✓ እርስዎም የደረሳቸውን እጣ በመቀበል የተቀሩት ሕጻናት የሰሙት ድምፅ እና እንቅስቃሴ የምን እንደሆነ መጠየቅ ከዚያ ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ እጣው ላይ የተፃፈውን ማሳየት ትክክል ከሆኑ ማበረታታት ትክክል ካልሆኑ እዛው ከሌላ ቡድን እንዲያግዛቸው ማድረግ፣
- ✓ ሁሉም ቡድን በዚህ መሠረት እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- ✓ አቅርበው ሲጨርሱ የቀረቡት የእንስሳት ጨዋታ ስንት የእንስሳት ድምፅ ሰማን ከተነሱት እንስሳት ውስጥ በጣም ትልቁ የቱ ነው ትንሹስ እናንተ የቱን እንስሳ ትፈራላችሁ ለምን
- ✓ በመጨረሻም የእንስሳት ስም መፃፍ እና ማንበብ ከስእል ጋርማዛመድ ያሰሯቸው፣

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** የእንስሳት የድምፅ ቅጂ፣ ሥዕል፣ ከተገኘ የእንስሳት

ማስክ፣እርሳስ፣ ደብተር /ወረቀት...

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (በጨዋታ የሰሩትን ተግባር በማየት እንቅስቃሴው እና ድምፁ መጣጣሙን) **የቃል ጥያቄ** (ስንት የእንስሳት ድምፅ ሰማን፣እንቅስቃሴውስ እንዴት ነው፣በጣም ትልቁ እንስሳ የቱ ነው፣በጣም ትንሹስ እንስሳ የቱ ነው፣እናንተ የቱን እንስሳት ትፈራላችሁ።

## ተግባር 4: የተግባር ሥራ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ዘሮችን መዝራት፣ተክሎችን መትከል፣መጠንን ማወዳደር

**የመምህር ሚና:** መምህር! አሁን ክፍለ ጊዜው የተግባር ሥራ የሚሰሩበት መሆኑን በመግለፅ ያዘጋጇቸው

### መትከል እና መዝራት

- ✓ በቁመታቸው በማሰለፍ ወደ ደጅ ያስወጧቸው፣
- ✓ አስቀድመው የታዘዙትን የአዝርዕት ዘር ችግኝ እና ተክል እንዲሁም የሚጠቀሙበትን ቁሳቁስ በማዘጋጀት ይዘው ይውጡ፣
- ✓ ወደ ግብርና ቦታ በመውሰድ ተቆፍሮ በተዘጋጀው ቦታ ያመጡትን ተክል ወይም ዘር እንዴት እንደሚተክሉ በማሳየት እና ለማደግ ምን ምን እንደሚያስፈልጋቸው በመግለጽ፣ የተወሰኑት ለመትከል እና ለመዝራት ሙከራ ሲያደርጉ የቀሩት ደግሞ አፈር በማልበስ፣ውሃ በማጠጣት እና በማስተካከል እንዲሰማሩ ያድርጉ፣
- ✓ ሲተክሉ እርስዎ በመከታተል ያግዟቸው፣
- ✓ ተክለው ከጨረሱ በኋላ እዛው ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮን ማሳየት
- ✓ መሬትን በመቆፈር ለእርሻ ማዘጋጀት በማሳየት ስለተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች ማስረዳት፣
- ✓ ቅጠሎቹን በመጠቀም የትኛው ቅጠል ከየትኛው ቅጠል መጠኑ እንደሚተልቅ እና የቅጠሎቹ ቅርጽ አንዳቸው ከአንዳቸው በምን እንደሚለዩ ማሳየት፣ ወደ ክፍል ከገቡ በኋላ የተለያዩ ቅጠሎችን ቀላቅሎ በመስጠት በቅርፅ እና በመጠናቸው በመለየት ትልቅ፣ መካከለኛ እና ትንሽ በማለት እንዲደለድሉ ማድረግ፣
- ✓ በደብተራቸው፣በወረቀት ወይም በመለማመጃ መጽሀፍ ገጽ ላይ ያውን በቅጠል የህትመት ሥራ ያሰሯቸው፤

**የመማሪያ እና የመጫወቻ ቁሳቁሶች:** ዘር፣ ችግኝ፣ ዶማ፣ አካፋ፣ ቅጠል፣ ቀለም፣ውሃ፣ አፈር፣ መትከያ ባሊዲ፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ ደብተር፣ ቀለም...

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (እንዴት እንደተከሉ በማየት) **የቃል ጥያቄ** የምን የምን ዘር ተከልን፣ የምን ችግኝ ተከልን፣ ለማደግ ምን ምን ያስፈልጋቸዋል፣ የቅጠል ቅርፅና መጠን የሁሉም እኩል ነው...

## የተግባር ስራ 2 ( 3 ክ/ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማኅበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን መገንዘብ፣የትልልቅ ጡንቻዎች ቅንብር ማዳበር፣ በጎ ፍቃድ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በገለፃ፣ በተግባር ፣ሰርቶ በማሳየት፣

**የመምህር ሚና:** መምህር አሁን ክፍለ ጊዜው የተረኝነት ሥራ የሚሰሩበት መሆኑን በመግለፅ ያዘጋጃቸው

**ሀላፊነት መውሰድ**

- ✓ አስቀድመው የተረኝነት ሰሌዳ በማዘጋጀት በተለያዩ በጎ ሥራ ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ ሕጻናትን መመዝገብ ፤
- ✓ ከዚያም እነዚህኑ በጎ ፈቃደኞች በተለያዩ ሥራዎች ላይ መመደብ ለምሳሌ‹ ስነሥርዓት አስከባሪ፣ ደከም ያሉ ሕጻናትን ማገዝ የመሳሰሉትን እንዲሠሩ መመደብ፣
- ✓ ከዚያም በጎ ፈቃደኛ ማለት ያለምንም ግፊት መልካም ሥራ መሥራት እንደሆነ እና ይህም ከፈጣሪ በረከት እንደሚያሰጥ በመግለጽ ለዚህ ፈቃደኛነታቸው እንዲያጨበጭቡላቸው ማድረግ፣
- ✓ ከዚያም ሕፃናቱ የሚፈልጉትን ሥራ እንዲሠሩ ነጻ ዕድል መስጠት እነዚህ ተመረጡት ሕጻናት ደግሞ መሀላቸው በመግባት እንዲያግዛቸው ማድረግ፣
- ✓ የተሰጣቸው የተግባር ጊዜ ሲያልቅ ምን ምን በጎ ሥራ እንደሰሩ እንዲናገሩ በተራ መጋበዝ፣
- ✓ የመጫወቻ ቁሳቁስ ማዋሳቸውን፣ የወደቁ ተማሪዎችን ማንሳታቸውን፣ መሥራት ያቃታቸው ተማሪዎችን ማገዛቸውን ወዘተ እንዲናገሩ ማበረታታት፣ከተናሩ በኋላ ስለመልካም ሥራቸው ማስጨብጨብ ማበረታታት፣
- ✓ ይህንኑ ተግባር በቀጣይ አጠናክረው መሥራት እንዳለባቸው በመንገር ሌላ በዚህ በጎ ሥራ ላይ መሰማራት የሚፈልግ በማለት መቀስቀስ፣
- ✓ በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ደግሞ እናንተም ትሰራላችሁ እስከዚያው ግን በቤተሰብ ወላጆቻችሁን በማገዝ፣ በትምህርት ቤት ልክ እንደነሱ በመሳተፍ፣ በአካባቢያችሁም በመልካም ሥራ ላይ በመሳተፍ መሥራት ትችላላችሁ፣
- ✓ በመጨረሻ ሁሉም ህፃናት በዝህ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ወሳኝ ነው።

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** የተረኝነት ሰሌዳ፣ መጫወቻ ቁሳቁስ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (እንዴት እንደሚያግዙ በማየት) የቃል ጥያቄ የበጎ ፈቃድ ሥራ ማለት ምን ማለት ነው? መልካም ሥራ የምንለውን የት ነው? መሥራት ያለብን?...

## ተግባር 5: መዝሙር (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ማህበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን መገንዘብ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ክፍለ ጊዜው መዝሙር መሆኑን ያስገንዝባቸው መዝሙሩን

ለመዘመር አሁን አዲስ መዝሙር ይገኙላችሁ መጥቻለው እስኪ መዘመር የሚፈልግ ይዘጋጅ በማለት ስሜታቸውን ማነቃቃት፣

## አዝርዕት

- ✓ በቅድሚያ ያዘጋጁትን የሥዕል ካርድ በመጠቀም በመዝሙሩ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት ያንበቡላቸው እርስዎ መዝሙሩን በተግባር በማሳየት (ለምሳሌ እንመገብ ሲል እንደመመገብ፣እናጨብጭብ ሲል በማጨብጨብ)በመዘመር ያሳዩዋቸው፣
- ✓ ከዚያ ተማሪዎች ከወንበራቸው እንዲነሱ እና በትክክል እንዲቆሙ ማድረግ፣
- ✓ እርስዎ እየዘመሩ እነሱ ከእርስዎ ቀጥሎ እንዲዘምሩ ማድረግ፣
- ✓ ይህንን ተግባራት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ካስደገመችሁ በኋላ ለብቻቸው እንዲዘምሩ ያድርጉ፣
- ✓ ከመዝሙሩ በኋላ በተማሪ መለማመጃ መፅሀፍ ገጽ ላይ ያለውን ምስሎቹን በማየት መጠሪያ ስማቸው እንዲፅፉ ያድርጋቸው ወይም የተለያዩ ድሪጊቶችን በማየት ምን እንደሆነ ይፃፉ / እያዩ ይግለጹ

### አዝዕርት

እኔ ሽንብራ አለኝ እያው እያው
ጓደኛዬ ባቄላ አለው እያው እያው
ወንድሜ ስንዴ አለው እያው እያው
እኔ ደግሞ ንፍሮ እወዳለው እያው እያው
እህቴ ደግሞ ንፍሮ ቀቀለች እያው እያው
የባቄላ፣የሽንብራ፣የስንዴ ነው እያው እያው
ልክ እንደኔ ንፍሮ የሚወድ እያው እያው
ኑ በአንድ ላይ እንመገብ እያው እያው
ለመገበችን እህቴ እያው እያው
በአንድ ላይ እናጨብጭብ እያው እያው/2/

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** የአዝርዕት ሥዕል የያዘ ቻርት/ፍላሽ ካርድ፣ መዝሙሩን የሚሰሙበት ቴፕ ረከርደር፣ጂፓስ፣፣ስልክ...፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ደብተር

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (መዝሙሩን ሲዘምሩ ስንኙን በትክክል መጥራታቸውን)፣በአግባቡ መግለጽ መቻላቸውን፣ መፃፍ መቻላቸውን...) **የቃል ጥያቄ** (ንፍሮው የተቀቀለው ከምን ከምን ነበር፣ እንዴት በሉት፣ የቀቀለው ማን ነበር፣ ከስንዴ ከባቄላ እና ከሽንብራ ትልቁ የቱ ነው ትንሹስ ይሄ ስእል ስለምን ያወራል.....

## ተግባር ስድስት: የውጭ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁመት፣ መደርደር፣ ማወዳደር ፣ቅርፃቅርፅ፣ግንባታ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ ፣

**የመምህር ሚና: መምህር** ለሕጻናቱ ክፍለ ጊዜው የውጪ ጨዋታ እንደሆነ ይግለፁላቸው:: ከዚያም ሕጻናቱን በቁመታቸው በማሰለፍ እና ወደ ውጪ በማስወጣት አንድ ትልቅ ክብ እንዲሠሩ

ያድርጋቸው

### የተለመዱ ቃላት የመጥራት ጨዋታ

- ✓ አስቀድመው የተለያየ ቅርፅ ፣ ቀለም እና ቁመት ያላቸውን ቁሳቁሶችን ቢያንስ ለሶስት ተወዳዳሪ እንዲሆን አድርገው ያዘጋጁ እና በሰሩት ክብ ውስጥ ያስቀምጡ
- ✓ በሰሩት ክብ በማስቀም የጨዋታውን ህግ ይንገራቸው ክላሲካሉን በመከተል በመጨፈር በክቡ መዞር፣ማጨብጨብ ሲባል ማጨብጨብ፣መደርደር ሲባል መሀል ላይ የተቀመጠውን የግንባታ እቃ መደርደር ፣ በቀለሙ ሲባል አንድ አይነት ቀለም ያላቸውን ቁሶች በአንድ ላይ ማድረግ ፣ በቁመት ሲባል ዘንጉን በፍጥነት በቁመት መደርደር በቅርጽሲባል አንድ አይነት ቅርጽ ያላቸውን በአንድ ማድረግ
- ✓ የመጀመሪያወቹ ተወዳዳሪዎች ተወዳድረው ሲጨርሱ ለቀጣዮቹ ቀላቅሎ ማዘጋጀት
- ✓ ህጉን በመከተል በመቅረፀ ድምፅ የተዘጋጀውን ባህላዊ ክላሲካል በመክፈት ክባቸው ውስጥ በመሆን እንዲቀሳቀሱ ያድርጉ፣
- ✓ እርስዎ የጠሩትን ተግባር በትክክል የተገበሩ ጨዋታውን ሲቀጥሉ ከሱ በተቃራኒ ያደረጉ ሕጻናት ከጨዋታ ውጪ እየሆኑ ጨዋታው ይቀጥላል፣
- ✓ ከየቡድናቸው እስከመጨረሻው የሚቀሩት ሕጻናት የጨዋታው አሸናፊ ይሆናሉ፣
- ✓ እባክዎትን መምህር ከጨዋታው በኋላ በጨዋታው ላይ የደረደሯቸው ቅርፆች በደብተራቸው በመሣል እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በዚህ መሰረት በተቀመጠው ክፍለ ጊዜ ሁሉም ህፃናት እንዲሰሩ ያድርጉ

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** ደብተር፣እርሳስ፣በመቅረዘ ድምፅ የተቀረፀ የባህላዊ ጭፈራ ክላሲካል ፣ የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆች፣የግንባታ ቁስ፣ ቀይ ዘንግ የተለያየ መጠን ያላቸው…

**የምዘና ስልት:** ምልከታ (በትክክል ህጉን ተከትለው መተግበራቸውን በማየት ማረጋገጥ)

**የቃል ጥያቄ** (የምን የምን ቅርፅ እንደደረደሩ እና ቀለማቸው ምን ዓይነት እንደሆነ መጠየቅ ፣ካዩት ቀለማት ውስጥ የቱን እንደወደዱት መጠየቅ፣ እንዲሁም ደብተራቸው ላይ የሰሩትን በማየት)…

## አምስተኛ ሳምንት

### ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ: 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃቶች :

- ✓ ጥሩ እና መጥፎ ነገሮችን ይለይሉ ፡፡
- ✓ ቀላል የመደመርና የመቀነስ ስሌቶችን ይሰራሉ፡፡
- ✓ ከሌሎች ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችላቸውን የግብረ ገብ እሴቶች ያጎለብታሉ፡፡
- ✓ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉን ፊደላት ቅደም ተከተላቸዉን ይለያሉ፡፡
- ✓ ተረቶችን በራሳቸው አገላለፅ ይናገራሉ ፡፡
- ✓ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ አካባቢዎችን ይረዳሉ፡፡

✓ ቁሳቁሶችን በዓይነት በአይነታቸው በመለየት መደርደር ይችላሉ

**ንዑስ ይዘቶች:** የግብረ ገብ እሴቶች፣ የፊደል ድምፆች ግንዛቤ፣ ሰዉሰራሽ እና ተፈጥሯዊ አካባቢ፣ የቦታ መገኛ፣መለየትና መመደብ፣ ማንበብናመፃፍ፣ መደመርና መቀነስ

## ስድስተኛ ሳምንት

### ተግባር አንድ: መዝሙር ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍቃላት፤** መደመር፣ መቀነስ፣ ቁጠር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** በመዝሙር አዘማመር ቅድም ተከተልመሰረት መዝሙሩን ያዘምሩ

በአንደ ላይ አንድን ጨምሬ
ሁለት አደረግሁት ደምሬ
ሁለት ላይ አንድን ጨምሬ
ሦሥት አደረግሁት ደምሬ
ሦስት ላይ አንድን ጨምሬ
አራት አደረግሁት ደምሬ
ከአራት ላይ አንድን ቀንሼ
ሦስት አገኘሁኘ አንዱን አንስቼ
ከሦስት ላይ  አንድን ቀንሼ
ሁለት አገኘሁ አንዱን አንስቼ
ከሁለት ላይ አንድን ቀንሼ
አንድ አገኘሁኘ አንዱን አንስቼ
ከአንድ ላይ  አንድን ቀንሼ
ባዶ ሆነብኝ አንዱን አንስቼ

ምንጭ: የ "አ" ክፍል መፅሀፍ ቁጥር ሁለት

**መማሪያና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቁጥር ካርድ፣ የማወዳደሪያ ምልክቶች ፍላሽ ካርድ...

**የምዘና ስልት:** በምልከታ ፡ ሲዘምሩ በማየት፣ የቃል ጥያቄ ከ2 ላይ 1 ሲቀነስ ስንት ይቀራል፣ ከ10 ላይ 5 ሲቀነስ ስንት ይቀራል ፣ 4 ላይ 10 ሲደመር ስንት ይሆናል .....

### መዝሙር ሁለት: ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍቃላት:** ተፈጥሮ፣ መልክኣ ምድር፣ፊደል፣ ኑሮ፣ጤና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** በመዝሙር አዘማመር ቅድም ተከተልመሰረት መዝሙሩን ያዘምሩ

**የተፈጥሮ ሀብቶቻችን**

ውብ ተፈጥሮ ያለን እኛ በሀገራችን ፣
የመልክአምድር አቀማመጣችን፣

ተራራ፣ ሸለቆ፣ ሀይቅ ወንዞቻችን፣
የራሳችን ፊደል ሀ ሁ ያልንበት፣
እንዲሁም ቁጥሮችን የቆጠርንበት፣
ለማዝናናትና እኛን ለማስደሰት፣
ለምግብም ቢሆን ኑሮን ለማጎልበት፣
ጤናን ለመጠበቅ ለሀይል ምንጫችን፣
እንጠብቃቸው ሁልጊዜ እንሰሳትን።
ልዩ ናት ሀገሬ ሀገሬ፣
እኔ እወድሻለሁ እጠብቅሻለሁ፣
እማማ ኢትዮጲያ ሁሌ አከብርሻለሁ።

**መማሪያና መጫወቻ ቁሳቁስ:** የቁጥር ካርድ፣ የማወዳደሪያ ምልክቶች ፍላሽ ካርድ…

**የምዘና ስልት: በምልከታ :** ሲዘምሩ በማየት፣ የቃል ጥያቄ መዝሙሩ ስለምን ያወራል፣ጤናችን የሚጠበቀው ምን ስንመገብ፣መልከአ ምድር …..

## መዝሙር ፡ ሶስት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍቃላት:** ተፈጥሮ፣ መልከኣ ምድር፣ፊደል፣ ኑሮ፣ጤና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** በመዝሙር አዘማመር ቅድም ተከተልመሰረት መዝሙሩን ያዘምሩ

### እርሻ ሥራችን

ገበሬው ሲዘራ ዘሩን በክረምት ፣
ዝናቡም ዘነበ ዘሩን ለማፍራት ።
ገበሬው አረሙን ሲያርም በማሳው ፣
ፍሬ እንዲያፈራለት አድጎ ቡቃያው ፣
ይለፋል ሌት ከቀን ሁሌ አይሰለቸው ።
ዘሩም ፍሬ ሁኖ ደረሰ ሊታጨድ
አምስት ማጭዶችን ገበያ በመግዛት፣
ጎረቤት ሰብስቦ ሄደ በአንድ መንገድ ።
ሆ እያሉ ሰብስበው በአንድ ጀንበር ሁሉም ፣
የህብረትን ሥራ ሁሌም በማጣጣም ፣
ፍቅርን ይኖራሉ በአንድነት በሰላም ።
ከማሳው ሰብስበው ጤፍ እና ማሽላ ፣
ምሥር ሽንብራውን እንዲሁም ባቄላ ፣
ለእድገት ያስፈልጋል እንዲሁም ለጤና፣
ወደቤት አምጥተው ካስገቡ በኋላ ፣
ተመራርቀው ሄዱ በፍቅራቸው ጥላ ።

**የመግሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** የግብርና/የማሳ ውስጥ ስራ በህብረት እየሰሩ የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ ፤መዝሙሩን የሚሰሙበት ቴፕ፣ ጂፓስ...

የምዘናስልት: ምልከታ(መዝሙር የመዘመር ስልታቸዉንና አቅም መጎልበት መመዘን) የቃል ጥያቄ( ገበሬዎቹ ምንምን አይነት ሰብሎችን ሰበሰቡ? ገበሬዉ ስንት ማጭዶችን ከገበያ ገዛ?...

## ተግባር ሁለት: ተረት (4 ክፍል ጊዜ )

**ቁልፍ ቃላት:** የእርሻ እቃዎች ፣ የሰብል አይነቶች፣ የግብረገብ እሴቶች

**የማስተማር ዘዴ:** በተረት፣ በጥያቄና መልስ ፣

**የመምህር ሚና :** መምህር! ይህ የሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን እንደመሆኑ ሕፃናቶች ቅዳሜ እና እሁድ ምንምን ተግባራትን እንዳከናወኑ ለጓደኞቻቸው እንዲያወሩ የተወሰነ ደቂቃ ይፍቀዱላቸው፤ በመቀጠል ልጆች ስለ ገበሬ የእርሻ እቃዎች የሚያውቋቸውን እንዲናገሩ ያድርጓቸው ፤ እርስዎም ተረቱን ቀድመው አንብበው በተረቱ ውስጥ የሚገኙ የእርሻ እቃዎችን በማውጣት ምንነታቸውን ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው ፤ ከዚያም ከመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ የሚገኘውን የእርሻ መሳሪያዎች ሥዕል በማሳየት ግንዛቤ፣ እንዲኖራቸው ያድርጓቸው ፤ በመጨረሻም ተረት እንደሚያወሩላቸው እና በጉጉት እንዲያዳምጡዎት በማድረግ ተረት ተረት በማለት ይጀምሩ ፤ ሕፃናቶችም የላምበረት በማለት እንዲቀበሉዎት ያድርጉ ፤ ከተረቱ የወጡ የመወያያ ጥያቄዎችን ያሰሯው ።

### ታታሪው ገበሬ

በድሮ ጊዜ በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖር ቤተሰቦቹን በግብርና ሥራ የሚያስተዳድር አቶለማ የሚባል ሰው ነበር፤ አቶ ለማ የሦስት ልጆች አባት ሲሆን ልጆቹን የሚያሳድጋቸው ከእርሻ የሰብል ምርትን ማለትም ጤፍ ፣ ማሽላ ፣ በቆሎ ፣ ስንዴ ፣ ባቄላ ፣ ምሥር ፣ አተር እና የመሳሰሉትን በማምረት እና የቤት ውስጥ እንስሳቶችን እንደ ላም ፣ በሬ፣ ፍየል ፣ ዶሮ፣ አህያ በማርባት እና በመሸጥ ይተዳደር ነበር፤ ይህ ሰው በመንደሩ ውስጥ የማህበረሰቡን ወግ እና ባህል ጠብቆ በሀዘን ፣ በደስታ ፣ በሰርግ ፣እድር መሰል ማኅበራዊ ተሳትፎዎች ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የሚያገለግል በጎረቤቶች መካከል ግጭት እና አለመግባባት ሲፈጠር በፍጥነት በመፍታት በአካባቢው ማህበረሰብ የመልካም ስነምግባር አርአያ የሆነ ሰው ነበር፣ ከማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ መካከል የግብርና ሥራዎችን በጋራ መሥራት እና የእርሻ ቁሳቁሶችን እንደ ሞፈር ፣ ቀንበር ፣ ማጭድ የመሳሰሉትን በጋራ ይጠቀሙ ነበር ፤ በዚህም ምክንያት ቅርርብነታቸው ቤተሰብ ያክል ነበር፤ አቶ ለማ የቤት እንስሳቶችን የሚንከባከበውን ያክል ከአካባቢው የተወሰነ ራቅ ብለው የሚገኙ የዱር እንስሳቶችንም ሀብቶቻችን ናቸው ብሎ ስለሚያምን የዱር እንስሳት መጠለያ የሆነውን ጫካ እንዳይመነጠር እና የዱር እንስሳቶች እንዳይሰደዱ ከአካባቢው ሰዎች ጋር ፕሮግራም በማውጣት የጥበቃ ተግባራትንም ያከናውናሉ የግብርና ሥራዎቻቸውን በጋራ እየተሳሰቡ በመሥራት የሚኖሩ የጥሩ ማህበረሰብ ምሳሌ በመሆን ኑሯቸውን ይኖራሉ

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. አቶ ለማ ቤተሰቦቹን በምን ሥራ ያስተዳድራል?
2. አቶ ለማ የስንት ልጆች አባት ነው?

3. አቶ ለማ ምንምን የሰብል ምርቶችን ያመርታል?
4. የአቶ ለማ ምንምን የቤት እንስሳቶች አሉት?
5. የአቶ ለማ እርሻ ቁሳቁሶች ምን ምን ይባላሉ?
6. አቶ ለማ ከማህበረሰቡ ጋር እንዴት ይኖራል?

መምህር! አሁን ደግሞ ልጆችን በትናንሽ ቡድኖች በማደራጀት በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ የሚገኘውን የቤት እና የዱር እንስሳቶች ፣ የሰብል ምርቶች ( ምሥር ፣ ጤፍ ፣ በቆሎ፣ ማሽላ ወዘተ ) ፣ የግብርና እቃዎችን የሚያሳየውን ሥዕል ከስሞቻቸው ጋር አዘበራርቀው በማቅረብ እንዲያዛምዱ ፣ ቀለም እንዲቀቡ እና በመጠን በቅርፅ እንዲለዩ ያድርጉ ፡፡

የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ፡ የእርሻ መሳሪያ ቁሳቁሶችን፣ የሰብል ምርቶችን የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ፣ እውነተኛ የሰብል ምርቶች (በቆሎ ፣ ጤፍ ፣ ሽንብራ

የምዘናስልት፡ ምልከታ (ትኩረት የመስጠት አቅማቸውን መመዘን)፣ የቃል ጥያቄ ( የመወያያ ጥያቄዎችን ማሰራት)

## የክፍል ውስጥ ጨዋታ ፡ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡ መለየትና መመደብ፣ መደመርና መቀነስ

የመምህር ሚና፡ መምህር ሕፃናትን በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድን በመከፋፈል በየቡድናቸው ተቆጣሪ ቁሳቁሶችን ለምሳሌ ቆርኪ ፣ ጠጠር ፣ ጨሌ ፣ ሎሚ ፣ አሻንጉሊቶች ወዘተ እኩል እኩል በማከፋፈል ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል በየቡድናቸው በፍለሽ ካርድ የተዘጋጀ የመደመር እና የመቀነስ ሂሳባዊ ስሌቶችን በማዘጋጀት ቁሳቁሶችን ተጠቅመው እንዲሠሩ ያድርጓቸው፤ የቁሳቁሶችን ብዛት በዓይነት እና በመጠን እንዲቆጥሩ ያድርጓቸው ፤ እርስዎ በመዘዋወር ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡ሥራዎቻቸውን ከጨረሱ በኋላ ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ሕፃን እንዲያቀርብ ዕድል ይስጧቸዉ በመጨረሻም ሞራል በመስጠት ማስተካከያ ሀሳብ ይሰጡ፡፡

ቀጥሎ በደብተር ላይ የሒሳብ ስሌት በመስጠት በደመር እና መቀነስ እንዲሰሩ ያለማምዱ

የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ፡ አካባቢያዊ ተቆጣሪ ነገሮች ለምሳሌ ቆርኪ ፣ ጨሌ ፣ ጠጠሮች ፣ ሂሳባዊ ስሌቶችን የያዙ የሥዕል ካርዶች ፣እርሳስ፣ ደብተር፣

የምዘና ስልት፡ ምልከታ(የመለየትና የመመደብ ስልት አቅማቸዉን መመዘን)፤ የቃልጥያቄ ቁሳቁሶችን ተጠቅመዉ ሂሳባዊ ስሌቶችን እንዲሰሩ መጠየቅ

## ተግባር ሁለት ዉይይት (4 ክ/ጊዜ)

የማስተማር ዘዴ፡ በዉይይት ፣በጥያቄና መልስ ፣በገለፃ

ቁልፍ ቃላት፡ የግብረገብ እሴቶች፣ ተፈጥሯዊ አካባቢ‚መለየት ፣ መፃፍ

የመምህር ሚና፡ መምህር ለህፃናቶች በእነሱ ደረጃ ጥሩና መጥፎ ነገሮችን (ማድረግ ያለባቸዉንና የሌለባቸዉን) በይበልጥ በሰብል ምርት ሂደት ላይ የሚገልፁ አጫጭር ፅሁፎች የያዙ በትልቅ ወረቀት በመፃፍ ያዘጋጁላቸዉ

- ✓ በክፍል ዉስጥ በትናንሽ ቡድን እንዲቀመጡ ያድርጓቸዉ
- ✓ በየቡድናቸዉ ህፃናቶች በቤታቸዉ፣ በአካባቢያቸዉና በት/ቤት በግላቸዉና ከሰዎች ጋር ሲሆኑ፣ አትክልቶችና እፅዋቶችን ከመንከባከብ አኳያ ማድረግ ያለባቸዉንና የሌለባቸዉን ጥሩና መጥፎ ነገሮች እርስዎ ፍንጭ በመስጠት እንዲወያዩና በወረቀት እንዲፅፉ ያድርጓቸዉ ( ምሳሌ፡ ስንኮተኩት ስሩን ሳንጎዳ በጥንቃቄ መሆን እንዳለበት፣ ውሃ ስናጠጣ ቀረብ ብለን በአግባቡ ዙሪያውን መሆን እንዳለበት፣ የመኮትኮቻ እና የተለያዩ መሳሪያዎችን በጥንቃቄ መጠቀም እንዳለብን ፣እጥዋቶችን አለመቁረጥ፣ አለማሽተት፣ አለመቅመስ፣...)ወዘተ
- ✓ ከጨረሱ በኋላ ያዘጋጁትን ፅሁፋዊ መግለጫ በማሳየት እነሱ ከተወያዩበት ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸዉ

- ከየቡድናቸዉ ለአንድ ህፃን እድል በመስጠት ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እየወጡ እንዲያቀርቡ ይፍቀዱላቸዉ
- ብቃቱን መሰረት ያደረገ ተጨባጭ ሀሳብ ይንገሯቸዉ

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** ጥሩና መጥፎ ነገሮችን የሚያሳይ ፅሁፋዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት:** ምልከታ( ለእፅዋቶች እንክብካቤ ማድረግ ያለባቸዉንና የሌለባቸዉን ነገሮች ሲናገሩ የማስተዋል ብቃታቸዉን መመዘን)

### የቃል ጥያቄ

- እፅዋቶችን ስትንከባከቡ ማድረግ ያለባችሁንና የሌለባችሁን ነገሮች ዘርዝሩ፡፡
- እናንተ ማድረግ ያለባችሁን ነገሮችና ማድረግ የሌለባችሁን ነገሮች ጥቀሱ፡፡
- ከፅሁፋዊ መግለጫዉ ዉስጥ እናንተ ስንቱን ፃፋችሁ፡፡

## ተግባር አራት፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ )

**ቁልፍ ቃላት:** ፊደል ፣እንቅስቃሴ፣ መሸነፍ እና ማሸነፍ፣ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናቶችን ህፃናቶችን ከክፍል ውጭ ይዘዋቸው ከመውጣቶ በፊት የክፍል ውጭ የጥንቃቄ መርሆዎችን ያገንዝቡ፤ በመቀጠል የሚከተለውን ተግባር ያከናውነው፡፡

- ✓ የአማረኛ የመጀመሪያ ፊደል የያዙ ብዛት ያላቸው የሥዕል ካርዶችን ያዘጋጁ፤
- ✓ በመቀጠል በተወሰነ የቦታ ክፍተት ንጹሕ ቦታ ላይ ደርድረው ያስቀምጡ ( የቦታ ክፍተቱ ልጆችን በአንድ እግራቸው ለመዝለል የሚያስችል መሆን አለበት )
- ✓ ከዚያም ሕፃናቶች በሰልፍ ቅደምተከተል ይሰለፉ፤
- ✓ መጀመሪያ የተሰለፈው ሕፃን ወደተደረደረው የአማርኛ ፊደል በአንድ እግሩ ተራበተራ እየዘለለ በመሄድ በሚዘላቸው ፊደላት የሚጀምር አንዳንድ ቃላቶችን እየመሰረተ ይሄዳል ፤ ነገርግን በፊደላቱ የሚጀምር ቃላቶችን ካልመሰረተ ተሸናፊ ይሆንና ቀጣይ ተረኛ ሕፃን ይቀጥላል ፤ እስከመጨረሻው ቃላቱን በመመስረት ከቀጠለ ግን አሸናፊ ይሆናል ፤ በዚህ ሁኔታ ሁሉም ሕፃናቶች ከጨረሱ በኋላ ጨዋታውን በሚገባ ያጠናቀቁ ልጆች

የጨዋታው አሸናፊ ሲሆኑ ያላጠናቀቁ ደግሞ ተሸናፊ ይሆናሉ ማለት ነው ፡፡

- ✓ ሁሉም ህፃናት ይህንን በተገቢ ያከናውኑ በመጨረሻ ቃላቱን እንዲጽፉ እና እንዲያነቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** የሥዕል ካርዶች፣ የፊደል ካርድ ፣እርሳስ፣ደብተር

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(የጨዋታ ስርአቱን መጠበቃቸዉን መመዘን)፣ የቃልጥያቄ (ስንት ቃላቶችን መሰረታችሁ ምንምን ናቸዉ...

## ተግባር አምስት፡ የመስክ ጉብኝት (5 ክፍለጊዜ )

**ቁልፍ ቃላት:** ተፈጥሮአዊ አካባቢ፣ መለየትና መመደብ

**የመማርማስተማር ዘዴ:** በመስክ ጉብኝት ፣በገለፃ ፣በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! እባክዎትን በአካባቢዎ ወደ ሚገኝ ተፈጥሯዊ እፅዋቶች እና እንስሳቶች ወደ ሚገኙበት አካባቢ የመስክ ጉብኝት ተግባርን ለማከናወን ከሚመለከታቸው አካላቶች ጋር ያመቻቹ ፡፡( ነገር ግን የርህን አይነት ቦታ በከተማ አካባቢ ማግኘት የሚያዳግት ከሆነ በምስል የተቀረፀ በጉብኝት መልክ እንዲመለከቱ ያርጉ)

- ✓ ልጆችን ወደ መስክ ቦታ ይዘዋቸው እንደሚሄዱ ይንገሯቸው ፤
- ✓ በመስክ ቦታ ላይ ስለሚደረጉ የጥንቃቄ መርሆዎች ማለትም እፅዋቶችን አለመቁረጥ፣ አለማሸተት፣ አለመቅመስ፣ እንስሳቶችን እና እፅዋቶችን አለመቅረብ መሰል የጥንቃቄ መርሆዎችን በምክንያታዊነት ያስገንዝቧቸው
- ✓ በመቀጠል በአካባቢዎ ወደሚገኝ ተፈጥሯዊ እንስሳቶች እና እፅዋቶች ወደ አሉበት ቦታ በመውሰድ ያስጎብኟቸው፤ ስለሚመለከቷቸው ነገሮች ጥያቄ እንዲጠይቁዎት ያድርጉ እርስዎም የሚያውቁትን ምላሽ ይስጡ ፤
- ✓ ሕፃናቶች የሚያዩቸውን ነገሮች ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጓቸው ፤
- ✓ ከጨረሱ በኋላ ወደ ክፍል በመውሰድ ስለተመለከቷቸው ነገሮች እንድናገሩ ለእያንዳቸው ሕፃናቶች ዕድል ይስጧቸው

**የመማሪያ እና የመጫወቻ መሳሪያ:** በአካባቢ የሚገኝ ተፈጥሯዊ እንስሳቶችን እና እፅዋቶችን የያዘ ጫካ /የእርሻ ስፍራ፣ ተንቀሳቃሽ ምስል ፣ማስታወሻ መያዣ...

**የምዘና ስልት:** ምልከታ(በጉብኝታቸዉ ወቅት ነገሮችን ለማወቅ ያላቸዉን ተነሳሽነት መመዘን)፣
**የቃል ጥያቄ:** ምን ምን ዕፅዋቶችን አያችሁ ?ምን ምን አይነት ቀለም አላቸዉ? ያደረጋችሁት የጥንቃቄ አይነቶች ምን ነበሩ?፣ ባንጠነቀቅ ምን ይደርስብናል?...

# የአውድ ማጠቃለያ ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም________________________________ጾታ_______እድሜ_______ደረጃ_______

**መግለጫ:** ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሚሉት ብቃት ትይዩ የ "✓" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | የመማር ብቃቶች | የምልከታ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | ጥሩ | በ.ጥሩ | እ.በ.ጥሩ |
| 1 | የሀገር ወዳድነት ስሜትን አዳብረዋል? | | | | |
| 2 | የማህበራዊ ክህሎት አዳብረዋል? | | | | |
| 3 | በዕለት ተዕለት ተግባራቸው የደህንነት እና የንፅህና አጠባበቅ መርሆችን ተግብረዋል? | | | | |
| 4 | ጊዜን መሰረት በማድረግ የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን አቅደዋል? | | | | |
| 5 | የቃላት እውቀታቸውን አሳድገዋል? | | | | |
| 6 | ከመማር ይዘቶች ጋር ተያያዥ የሆኑ ሥነ ጥበባዊ ተግባራትን በመስራት ይዝናናሉ? | | | | |
| 7 | ቃላቶችን በማንበብ ይፅፋሉ? | | | | |
| 8 | ቁጥሮችን በመለየት ይቆጥራሉ? | | | | |
| 9 | የነገሮችን መሰረታዊ ቅርፅ ይናገራሉ? | | | | |
| 10 | የተለያዩ ቁሶችን (ነገሮችን) ቅጥን/ሥርዓት ጥለትን/ መሰረት እድርገው ቀለምን፣ ቅርፅንና ሙዚቃዊ ምትን በመለየት ይከፋፍላሉ? | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፦________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

# ዐውድ አምስት፡ መጓጓዣ

አጠቃላይ ለአዉዱ የተቀመጠዉ ሳምንትና ክ/ጊዜ   6 ሳምንት /180 ክ/ጊዜ

## 6.1. መግቢያ

በቅድመ አንደኛ ደረጃ ሦስት ለሚገኙ ሕፃናት “መጓጓዣ” የሚለው የመማር ዐውድ ሕፃናት ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ የሚጠቀሙበትን የመጓጓዣ ዓይነት እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። መጓጓዣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ እና የተለያዩ ዕቃዎችን ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ ያገለግላል። መጓጓዣ ዘመናዊ እና ባህላዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ሕፃናትም የመጓጓዣ ዓይነቶች ለይተው ለማወቅና ለመጠቀም ይማራሉ፡ ሕፃናት ከቤታቸው ወደ ትምህርት ቤታቸው ሲጓዙ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘው እንዲጓዙና መንገድ ሲያቋርጡ ነጭና ጥቁር ቀለም የተቀባውን (ዜብራ) ማቋረጫ መጠቀም እንዳለባቸው የሚማሩበት ዐውድ ነው። በተጨማሪም ሕፃናት የትራፊክ ሕግ በመማር ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ወይም ሲጓዙ ተገቢ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል።

ሕፃናት በዚህ ዐውድ በየብስ፣ በአየር ላይ እና በውሃ የሚጓዙ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ለይተው ያውቃሉ። በተጨማሪም ሕፃናት ለደኅንነታቸው ራሳቸውን እንዴት ከመኪና አደጋ እንደሚጠብቁ፣ የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶች ሞዴል በመሥራት እና ቀለም በመቀባት ክህሎታቸውን ያዳብራሉ።

በአጠቃላይ በዚህ ዐውድ ለሕፃናት የሚመጥኑ ግንዛቤዎችን ከማስጨበጥ ባሻገር ሕፃናቱ በዕድሜያቸው ሊያጎለብቱ የሚገባቸውን አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ብቃቶች ተካተዋል። ለእያንዳንዱ ሳምንትም አጥጋቢ የመማር ብቃቶችና ዝርዝር የአተገባበር ስልቶች ቀርበዋል።

## 6.2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ሕፃናቱ ይህንን ዐውድ ከተማሩ በኋላ ፡

- ✓ ማኅበራዊ ክህሎት ያጎለብታሉ።
- ✓ የሀገር ወዳድነት ስሜትን ያዳብራሉ።
- ✓ በመንቀሳቀስና በቦታ ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ክህሎት ይኖራቸዋል።
- ✓ ሰዓት ይናገራሉ።
- ✓ ከመማር ይዘቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለያዩ ሥነ ጥበባዊ ተግባራትን
- ✓ በመሥራት ይዝናናሉ።
- ✓ የኢትዮጵያን የብር ኖቶች ይለያሉ።
- ✓ አናባቢና ተነባቢዎችን ማገበብና መፃፍ ይችላሉ።
- ✓ ቁጥሮችን በመለየት ይቆጥራሉ ።
- ✓ የነገሮችን ቅጥ /ሥረዓተ ጥለት/ በመጠበቅና በመለየት ይመድባሉ።
- ✓ የቅርብ አካባቢያቸውን በመለየት ይጠብቃሉ።

## 6.3. ዐበይት ይዘቶች

መጓጓዣ በሚለው የመማር ዐውድ ውስጥ የሚከተሉት የትምህርት ይዘቶች ተካተዋል፡፡

- ራስን ማወቅ፣
- ራስን መግለጽ፣
- የአካል ክፍሎች፣
- ጤና፣
- ቁጥሮችን መቁጠር፣
- ጥበባዊ ግንዛቤ፣
- ራስን መቆጣጠር፣
- ድምፅ መለየት፣
- የቅርብ አካባቢ፣
- ሥርዓተ ምግብ፣
- ቁጥሮች መጻፍ፣
- በፈጠራ ሥራ መግለጽ፣
- ራስን መቻል፣
- የቃላት ክምችት፣
- የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣
- ቁጥሮችን ማወዳደርና ቅደም ተከተል ማስያዝ፣
- ባህላዊ ቅርሶች፣
- ማኅበራዊ ግንዛቤ፣
- የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣
- ቅጥ፣
- ጥበባዊ እሴት፣
- የግብረ ገብ እሴት፣
- የፊደላት ድምፅ ግንዛቤ፣
- የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ አካባቢ፣
- የቦታ መገኛ ግንዛቤ፣
- መለየትና መመደብ፣
- ማገናኘት፣ ማያያዝና መተግበር፣
- የውሳኔ ሰጭነት ክህሎት፣
- ሀገር ወዳድነት፣
- ቅርፆች፣
- የምት እንቅስቃሴዎች፣
- ማንበብና መጻፍ፣
- ደኅንነት እና ጥንቃቄ፣
- መደመር እና መቀነስ፣
- ገንዘብ፣

## 6.4. የማስተማሪያ ዘዴዎች

ይህን ዐውድ ለማስተማር የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች፦

በዚህ ዐውድ ሕፃናትን ለማስተማር የግልና የቡድን ሥራ፣ የክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ተግባራትን እንዲሠሩ ማድረግ፣ በሚና ጨዋታዎች፣ በመስክ ጉብኝት፣ በተረት፣ በመዝሙርና በተለያዩ የጨዋታ ዘዴዎች ከማስተማር በተጨማሪ እንደ ጥያቄና መልስ፣ እንቆቅልሽ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ድራማና የመሳሰሉትን አሳታፊ ዘዴዎች መተግበር ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም በሕፃናት የመለማመጃ ደብተር ውስጥ ያሉትን ተግባራትንና መለማመጃዎችን ማሠራት ተገቢ ነው፡፡

## 6.5. የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁሶች

- ✓ የመጓጓዣ ሥዕሎች፣ ቁጥር መቁጠሪያ (abacus)፣ ትናንሽ ድንጋዮች፣ ቆርኪ፣ ፖስተሮች እና የሥዕል ካርዶች ፣ውሃ፣ ሳሙና (አመድ፣ እንዶድ)
- ✓ ትናንሽ ተቆጣሪ ነገሮች (ለምሳሌ አዝርዕቶች፣ ዶቃዎች፣ ብሎኮች)፣ የቁጥር ገበታ ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ ካርቶን፣
- ✓ ኮላዥ ለመሥራት እና ለማጣበቂያ የሚያገለግሉ አሮጌ ጋዜጦችና መጽሔቶች፣ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች/አይነቶች ሥዕሎች ወይም ሞዴሎች፣ የተቀረጹ ድምፆች፣ ሞዴል

የትራፊክ መብራት፣ ባለቀለም እርሳስ / እርሳስ ፣ የመስክ ጉብኝት፣ የተለያዩ እንስሳት ስም የያዙ የሥዕል ካርዶች (ለመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡ)፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች፣ ቁጥር የተጻፈባቸው ካርዶች፣ የባህል ቅርሶች ያየዙ ስእሎች ፣ ባህላዊ ዘፈኖች ፣ የበዓል አልባሳት፣ የተለያዩ የመጓጓዣ አሻንጉሊቶች ሞዴል፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምልክቶች፣ የተለያዩ የመጓጓዣ መንገዶች እና ተዛማጅ ቃላት ሥዕሎች፣ የኢትዮጵያ ገንዘብ ኖቶችና እና ሳንቲሞችን ሞዴሎች በመጠቀም በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ሕይወት መዝራት ያስፈልጋል፡፡

## 6.6. የምዘና ስልቶች

ሕፃናት በአንድ ተግባር ላይ በቡድን ወይም በጥንድ ሲሠሩ እንቅስቃሴያቸውን በመመልከት በማረጋገጫ ዝርዝር መሠረት መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሕፃናት በመለማመጃ ደብተር ላይ ያሉትን መልመጃዎችና የተግባር ሥራዎችን እንዲሠሩ በማድረግ፣ በማረም፣ ምልከታ እና የቃል ጥያቄ፣ በሥራ ፕሮግራም መሳተፋቸውን መከታተል፤ መጠየቅ፣ የቃል ችሎታቸውን ለመገምገም ቀላል የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ ይገባል፡፡

የግምገማ ማኅደረ ተግባርን (ፖርትፎሊዮ) በመጠቀም የግምገማ ጨዋታዎችን /የጨዋታ እንቅስቃሴዎችን ማጠናቀር፣ የሕፃናትን ዕለታዊ ለውጦችን እና ስኬቶችን መመዝገብ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ደረጃውን የጠበቀ የግምገማ መሣሪያዎችን በመጠቀም ምዘናዎችን የመምህራን እና የወላጆችን ደረጃ አሰጣጥ መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡

## አንደኛ ሳምንት

ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ ፡ 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃት፡

- ✓ ራሳቸውን ማወቅን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ ስለ ግል ፍላጎታቸው በራስ መተማመን ስሜት ይናገራሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን ያወዳድራሉ፡፡
- ✓ የቅርብ አካባቢያቸዉን ይገልፃሉ፡፡
- ✓ ቅርፆችን በማወዳደር በቅደምተከተል ያስቀምጣሉ፡፡
- ✓ ስሜታቸውን ይገልጻሉ፡፡
- ✓ መዝሙሮችና ተረቶችን መዘመርና መናገር ይችላሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን ማወቅ፣ ራስን መግለጽ ፣ የአካል ክፍሎች ፣ ጤና ፣ ቁጥሮችን መቁጠር፣ ጥበባዊ ግንዛቤ

## ተግባር አንድ: የግል ሥራ አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ራስን ማወቅ ፣ራስን መግለጽ፣ መጓጓዣ፣ ቅርፆችን ማወዳደር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** ተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** ውድ መምህር እባክዎትን ይህ ክፍለ ጊዜ ሕፃናት የግል ሥራዎችን የሚሠሩበት መሆኑን በመንገር በትክክል እንዲሠሩ ያግዟቸው፡፡ ስለ መጓጓዣ ዓይነቶች ሥዕል ወይም ቪዲዮ በመጠቀም ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል እርስዎ ወደ ትምህርት ቤት በምን እንደሚመጡ ያብራሩላቸው፡፡ ሕፃናቱም እርስዎን ተከትለው ስማቸውን፣ ጾታቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ የሚጠቀሙበትን የመጓጓዣ ዓይነት እንዲያስተዋውቁ አድርጉ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት በምን እንደ መጡና እስከ ዛሬ በምን በምን ዓይነት መጓጓዣ እንደ ተጠቀሙ ለምሳሌ: ወደ ትምህርት ቤት የመጣሁት በእግር፣ በብስክሌት፣ መኪና፣ ወዘተ በማለት እንዲናገሩ ያበረቷቷቸው፡፡

ሕፃናት ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ምን ዓይነት መጓጓዣ እንደሚወዱና እንደሚጠሉ ይጠይቋቸው፡

**ለምሳሌ:** እኔ በመኪና መጓጓዝ እወዳለሁ፤ መኪና አራት ጎማ አለው፡፡

እኔ በፈረስ መሄድ አልወድም፤ ፈረስ አራት እግር አለው፡፡ በማለት ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡

በሕጻናት መለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን ስም፣ ዕድሜ፣ ጾታ እና የሚያውቋቸውን የመጓጓዣ ዓይነቶች እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ በተጨማሪም የተለያየ ቅርፅ ያላቸዉን ስዕሎች እንዲያወዳድሩና በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ያድርጓቸዉ፡፡

የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦ የመጓጓዣ ሥዕሎች፣ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች ሥዕሎች ወይም ሞዴሎች: የተለያዩ እንስሳት ስም ያላቸው የሥዕል ካርዶች

**የምዘና ስልት:** ሕፃናት ተግባራትን ሲሠሩ መመልከት፣ የቃል ጥያቄ ( በቃል በመጠየቅ ) ምን ምን መጓጓዣ ዐይተው/ተጠቅመው እንደሚያውቁ፣ ከመጓጓዣ ውስጥ የቱን እንደሚወዱና እንደሚጠሉ

## የግል ሥራ: ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር መቁጠር፣ ራስን ማወቅ፣ የመጓጓዣ አይነት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ

የመምህር ሚና : ውድ መምህር ክፍለ ጊዜው የግል ሥራ የሚሠሩበት መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡ በመቀጠል ወረቀትና እርሳስ በመስጠት ከሚወዱት የመጓጓዣ ዓይነት ውስጥ ሦስት ስዕል እንዲሥሉና የሣሏቸው የመጓጓዣ ዓይነቶች ስማቸውን እና ስንት ጎማ እንዳላቸው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ እነሱ ሲሰሩ እርስዎ እየተዘዋወሩ በማየት ያበረታቷቸው፡፡ ተግባራቱን ሠርተው ሲጨርሱ የተወሰኑት ተማሪዎች በማስነሣት ምን እንደሣሉ ለምን እንደሣሉና ስንት ጎማ እንዳላቸው ሥዕላቸውን በማሳየት እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም እርስዎ ያዘጋጁትን ሥዕል ወይም ቪዲዮ በመጠቀም ሕፃናቱ ለመሣል የሞከሩትን ትክክለኛ ሥዕል በማሳየት ስማቸውንና ስንት ጎማ እንዳላቸው ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ: እኔ የሣልኩት መኪና፣ ሳይክልና አውሮፕላን ነው፡፡ መኪና በጣም እወዳለሁ፤ መኪና አራት ጎማ አለው፡፡

በሕጻናት መለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን የመጓጓዣ ሥዕልን ማቅለም የሚለውን ያሠሯቸው)

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የመጓጓዣ ሥዕሎች ወይም ሞዴሎች/ የሥዕል ካርዶች

**የምዘና ስልት:** ሕፃናት ሲሠሩ መመልከት፣ የቃል ጥያቄ ( በቃል በመጠየቅ ) “መኪና ስንት ጎማ አለው?”፣ ሞተርስ?

## ተግባር ሁለት: እንቆቅልሽ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ ጤና፣ የቤት እንስሳት፣መጓጓዣ፣ የአካል ክፍል

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! ከዚህ ቀጥለው የቀረቡትን የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች ሕፃናትን ተራ በተራ ይጠይቋቸው። በእንቆቅልሹ ላይ ያሉትን በሥዕል በማዘጋጀት ሲመልሱ ከሥዕሉ ጋር በማጣመር ያብራሩላቸው። መልስ ካልመለሱ የእንቆቅልሽ አጠያየቅ ስርዓትን በተከተለ መልኩ ይሁን። በመቀጠልም ሕጻናቱ የሚያውቋቸውን እንቆቅልሾች ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጓቸው።

**እንቆቅልሽ! 1**

እኔ የቤት እንስሳት ዓይነት ነኝ፤ ቀኑን ሙሉ ሰዎችን እና ሸቀጦችን ተሸክሜ ከቦታ ቦታ አጓጉዛለሁ። እኔ ማን ነኝ?

**መልሱ:** ግመል፣ ፈረስ፡ አህያ …

**እንቆቅልሽ! 2**

አራት ጎማ አለኝ፤ ከፊት እና ከኋላ ሁለትና ከዚያ በላይ መብራት አለኝ። ሰዎችን ከቦታ ቦታ አጓጉዛለሁ እኔ ማን ነኝ?። መልሱ: መኪና

**እንቆቅልሽ! 3**

ሁለት ጎማ አለኝ፤ በፍጥነት መጓዝ እችላለሁ። እኔ ማን ነኝ?

**መልሱ:** ሞተር ሳይክል

**እንቆቅልሽ! 4**

ከሰውነት ክፍሎች አንዱ ነኝ፤ ሰዎች ለተለያየ አገልግሎት ይጠቀሙብኛል። የመኪና መሪ በመያዝ ለማሽከር አገለግላለሁ እኔ ማነኝ ?

**መልሱ:** እጅ

**እንቆቅልሽ! 5**

ከሰውነት ክፍሎች አንዱ ነኝ፤ ሰዎች ለመራመድና የመኪና መሪ ለመርገጥ ይጠቀሙብኛል። እኔ ማነኝ?

**መልሱ:** እግር

**እንቆቅልሽ! 6**

ሁለት ክንፍ አለኝ፤ በአየር ላይ እበራለሁ፡፡ ሰዎችንና እቃን ከቦታ ቦታ አጓጉዛለሁ እኔ ማነኝ?

**መልሱ፡** አውሮፕላን

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የተሽከርካሪዎች ሥዕሎች፣ የተቀረፀ ቪድዮ፣

**የምዘና ስልት፡** ምልከታ እና የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣የመጓጓዣ አይነቶችን ተናገሩ?/ መኪና ለማሽከርከር ምን ምን የአካል ክፍሎችን እንጠቀማለን?

## ተግባር ሶስት: የክፍል ዉስጥ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ቁጥር፣ የመጓጓዣ አይነቶች

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** ጨዋታ፣ በገለፃ፣ በተግባር፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** ውድ መምህር! ክፍለ ጊዜው የክፍል ውስጥ ጨዋታ መሆኑን ይግለጹላቸው:: የመጓጓዣ ዓይነቶችን ሥዕል ከቁጥር ጋር በማቀናጀት ጽፈው በቃላት ካርድ ያዘጋጁ፡፡ ከዚያም ለሕፃናቱ 1 ቁጥር መኪና፣ 2 ቁጥር አውሮፕላን፣ 3 ቁጥር ሳይክል፣ 4 ቁጥር አህያ፣ 5 ቁጥር ፈረስ፣ 6 ቁጥር ባቡር እንደ ሆነ ይግለጹላቸው፡፡ በመቀጠል ሁሉም ሕፃናት በተቀመጡበት ቦታ ሆነው "1 ቁጥር" ሲባል እንደ መኪና ድምፅ እንዲያወጡና እጃቸውን ዝቅ በማድረግ በመሬት እንደሚሄድ እንዲያሳዩ፣ "2 ቁጥር" ሲባል እንደ አውሮፕላን እጃቸውን ወደ ላይ በማድረግ በሰማይ እንደሚበር እንዲያሳዩ፤ ሌሎቹንም በዚሁ መሠረት እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡

**ለምሳሌ፡** እርስዎ "4 ቁጥር" ሲሉ ሕፃናቱ "ኻ፣ ኻ" እያሉ ድምፅ በማውጣት እጃቸውን ወደ መሬት ያደርጋሉ

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** አሻንጉሊት፣ የመጓጓዣ ዓይነቶች ሥዕል እና ሞዴል

**የምዘና ስልት፡** ምልከታ፣ ቃል ጥያቄ (ከመኪናና ከሳይክል መሽከርከሪያ ጎማ የትኛዉ ይበልጣል ከአህያ እና ከፈረስ እግር የትኛዉ ያንሳል) ምን ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳደረጉ መጠየቅ፣ የቡድን ወይም ጥንድ ሥራ፣ የግምገማ ጨዋታዎችን /የጨዋታ እንቅስቃሴዎችን እና ለውጦችን መቁጠር::

## ተግባር አራት: ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የቅርብ አካባቢ፣የመጓጓዣ አይነቶች

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ በማስመሰል

**የመምህሯ/ሩ ተግባር፡** ወድ መምህር! ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ይተግብሩት፡

### ሀና እና ፋጡማ

ሀና እና ፋጡማ የሚባሉ ሁለት የ6 ዓመት ጓደኛሞች ነበሩ ::የሚኖሩትም በአንድ አካባቢ ነው፤ስለሆነም ወደ ትምህረት ቤት ሲሄዱና ሲጫወቱ በአንድ ላይ ነበር፡፡ ትምህርት ቤታቸውም ከቤታቸው ቅርብ ስለሆነ በእግራቸው ነው የሚሄዱት፡፡ ወደ ትምህርታቸው ሲሄዱም በአካባቢያቸው

የሚገኙ የመጓጓዣ አይነቶችን ማለትም መኪና፣ ባጃጅ፣ ሳይክል፣ አህያ፣ ፈረስ ወዘተ እያዩና ማን ከማን እንደሚፈጥን፣ ስንት እግርና አንዱ ከአንዱ በስንት እግር ወይም ጎማ እንደሚበለጥ፣ የትኛውን እንደሚወዱ እየተነጋገሩ እና ስሜታቸውን እየገለፁ ትምህርት ቤታቸው ደረሱ:: ከዚያም በቅርብ አካባቢያቸው ያዩአቸውን የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን ለመምህራቸው ተናገሩ:: መምህራቸውም ጎበዝ ልጆች በማለት ሌሎችንም እንደነ ሀና እና ፋጡማ በቅርብ አካባቢያቸው የሚያዩትን፣ የሚወዱትን የመጓጓዣ አይነት ወላጆቻቸውን በመጠየቅ በመዝሙርና በተረት እንዲያመጡና እንዲያቀርቡ በማደረግ ሰላምታ ተሰጣጥተው ተለያዩ ::

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ የመጓዛዣ አይነቶችን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ (በተረቱ ውስጥ የሚገኙ የመጓጓዣ አይነቶች ምን ምን ናቸው)፤ ተረቱን ደግመው ሲተርቱ መገምገም

## ተግባር አምስት: ፕሮጀክት ( 6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የመጓጓዣ አይነቶች፣ መገጣጠም፣ ቅርፅ፣ ንፅህና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር ሕፃናትን በትናንሽ ቡድን በማደራጀት በጭቃ ወይም በወረቀት ኮላዥ የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶች ለምሳሌ የመኪና፣ የፈረስ፣ የአውሮፕላን፣ የሞተር ሳይክል፣ የአህያ ሥዕሎችን/ ሞዴሎችን እንዲሠሩ ያድርጓቸው::

በመቀጠል የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ሥዕል በተለያየ ክፍል ለያይቶ በመቁረጥ እና ቀላቅለው ያስቀምጡ:: ከዚያም ለሕፃናት የተቆራረጠውን የመጓጓዣ ዓይነቶችን ሥዕል በመስጠት በመገጣጠም ትክክለኛውን ሥዕል እንዲሠሩ ያድርጓቸው:: ለምሳሌ፦ የተቆራረጡ የመኪና፣ አውሮፕላን፣ ግመል፣ ፈረስ፣ ሞተር ሳይክል ክፍሎችን እንዲገጣጥሙ ያድርጉ::

**ውድ መምህር!** ሕፃናት የተግባር ሥራውን ሠርተው ከጨረሱ በኂላ እጃቸው በውሃና ሳሙና በማድረግ እንዲታጠቡ ያድርጉ::

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ጭቃ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ የተቆራረጡ የመጓጓዣ ዓይነቶች ሥዕሎች፣ ወረቀት ማጣበቂያ ኮላዥ

**የምዘና ስልት:** ሲገጣጥሙ መመልከት፤ የገጣጠማችሁት የትኛው የመጓጓዣ ዓይነት ነው፣ ስንት የመጓጓዣ አይነቶችን ገጣጠማችሁ በማለት የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ፣

## ተግባር ስድስት: መዝሙር( 4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መጓጓዣ፣ ቀናት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህሯ/ሩ ተግባር፦** ውድ መምህር ይህ ክፍለ ጊዜ የመዝሙር መሆኑን ይንገሯቸው:: የመኪና ሥዕል በመጠቀም ለመኪናዋ ሥዕል እንዲዘምሩላት በሚታይ ቦታ ይስቀሏት:: ከዚያም

እርስዎ ስንኝ በስንኝ ሲሉ ሕፃናቱ ደግሞ ከእርስዎ ቀጥሎ ደግመው እንዲናገሩ ያድርጓቸው:: በዚህ ሁኔታ ለሦስት ጊዜ ያህል ካለማመዷቸው በኋላ ከእርስዎ ጋር አብረው እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው:: በቀጣይ ቀን ደግሞ አንድ ጊዜ ካስታወሷቸው በኋላ እንዲዘምሩ ያድርጓቸው:: በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን የመኪና ጎማዎች በመቁጠር መጠናቸውን እንዲጽፉ ያድርጓቸው::

ይቺ መኪና

ይቺ መኪና በጣም ታምራለች
ከቦታ ቦታ ታጓጉዛለች
ቀለማ ቡኒ ሹፌራ መልካም
ተመችቶኛል ለኔ አጠቃቀም
ከሰኞ እስከ አርብ እንማራለን
ቅዳሜ እሁድ ግን እንዞራለን
ስንሽከረከር በመኪናችን
እንቆጥራለን ጎማዎቹን
እኔ የቆምኩት በሁለት እግሬ ነው
መኪና ያለው አራት ጎማ ነው /2/

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የመኪና ሥዕል፣ ጎማዎች ስእሎች፣ የእግር ሥዕል

**የምዘና ስልት:** ሲዘምሩ ማየት ፣የቃል ጥያቄ መጠየቅ( ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁ፣ትምህርት የምትማሩባቸው ቀናቶች ከመቼ እስከ መቼ ነው? ስንት አይነት የመጓጓዣ አይነቶችን ታውቃላችሁ?)

## ሁለተኛ ሳምንት

### ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ ፡ 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃት:

- ✓ ስሜታቸውን ይቆጣጠራሉ::
- ✓ የተለያዩ ድምፆችን በመለየት ያስመስላሉ::
- ✓ በቅርብ አካባቢ ስለሚገኙ ነገሮች በራስ በመተማመን ይናገራሉ::
- ✓ የቅርብ አካባቢን ያውቃሉ::
- ✓ የቅርብ አካባቢያቸውን ተንከባክበው ያሳያሉ::
- ✓ በአካባቢው የሚገኙ ጎጅ ነገሮችን ይለያሉ፣
- ✓ ስለጤናማ ምግብ እና መጠጦች መዝሙር ይዘምራሉ::
- ✓ ሥዕሎችን፣ምልክቶችን፣ የታወቁ ፊደላትን እና ቃላትን በመጠቀም ይግባባሉ::
- ✓ ቁጥሮች ይፅፈሉ::
- ✓ በአከባቢ የሚገኙ ሥነ ጥበባትን ይረዳሉ::
- ✓ የተለያዩ የሥነ ጥበብ እና የዕደ ጥበብ ሥራዎችን ዋጋ ይሰጣሉ፣

**ንዑስ ይዘቶች:** ራስን መቆጣጠር፣ ድምፅ መለየት፣ የቅርብ አካባቢ፣ ሥርዓተ ምግብ፣ ቁጥሮች መጻፍ፣ በፈጠራ ሥራ መግለጽ

## ተግባር አንድ: መዝሙር አንድ ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ድምፅን መለየት፣ መጓጓዣ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር እባክዎትን ክፍለ ጊዜው የመዝሙር እንደሆነ ይግለጹላቸው:: ከዚህ ከታች የተጻፈውን መዝሙር ከእርስዎ በኋላ እንዲዘምሩ በማድረግ ዜማና ስንኞቹን ያለማምዷቸው፤የአውሮፕላኑን ሥዕል በመነካካት እዲዘምሩ ያድርጉ እንዲሁም የተለያዩ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ሥዕል ያሳዩቸው:: በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን አ፣ መ፣ ፈ፣ ሞ፣ ሳ፣ባ፣ በሚሉት ፊደላት ቃላት እንዲመሰርቱ ድርጉ::

**መዝሙር፦ እሆናለሁ**

እሆናለሁ አውሮፕላን
እሆናለሁ አውሮፕላን
በአየር ላይ እበራለሁ
ከደመናው በላይ በላይ
ወደ ላይ ወደ ላይ
መኪናዋን እሆናለሁ
በመሬት ላይ አጓዛለሁ
ጲጵ ጲጵ ጲጵ

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የመጓጓዣሥዕሎች፣ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች ሥዕሎች ወይም ሞዴሎች

**የምዘና ስልት:** ቡድኖችን ወይም ጥንድ ሕፃናት በአንድ መዝሙር ሲዘምሩ መመልከትና በማዳመጥ፤በመሬት የሚጓዝ የመጓጓዣ አይነት የትኛው ነው፣ በአየር የሚበር የመጓጓዣ አይነት የትኛው ነው በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

### መዝሙር ሁለት ( 3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ሥርዓተ ምግቦች፣ መጓጓዣ፣ ንፅህና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህሯ/ሩ ተግባር:** ውድ መምህር እባክዎትን ክፍለ ጊዜው የመዝሙር እንደሆነ ይግለጹላቸው:: ከዚህ ከታች የተጻፈውን መዝሙር ከእርስዎ በኋላ እንዲዘምሩ በማድረግ ዜማና ስንኞቹን ያለማምዷቸው፤ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ካለማመዷቸው በኋላ አብረው እንዲዘምሩ ያድርጉ በመጨረሻም እራሳቸውን ችለው እንዲዘምሩ ያበረታቷቸው:: በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን የምግብ ዓይነቶችን እንዲያዛምዱ ያድርጉ::

መኪናው መጣ

መኪናው መጣ ጲጲጲጲ እያለ
መንገድ እንድንለቅ እየቸኮለ
ቲክ ቲክ ብሎ ስድስት ቆጠረ
አባቴ መጣ እየበረረ
ጲጲ አለ ድምፁ የመኪና
እኔም ሮጥኩኝ ተደሰትኩና
ታጠብን እጃችን ምግቡ ቀረበ/2/
ሁላችን በላን የተመጣጠነ/2/
ስለተመገብኩ ጤናማ ምግብ
እኔ አድጌያለው ሮጣለው በደንብ/2/

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የመጓጓዣሥዕሎች ፣ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች ሥዕሎች ወይም ሞዴሎች፣ የምግብ ዓይነቶች

**የምዘና ስልት፡** መዝሙር ሲዘምሩ መመልከትና በማዳመጥ፣ ምግብ ከመመገባችሁ በፊት ምን አደረጋችሁ፣ የመጣው የመጓጓዣ አይነት ምንድን ነው በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ተግባር ሁለት: እንቆቅልሽ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** መጓጓዣ፣ የሙዚቃ መሳሪያ፣ ስርዓተ ምግብ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** ውድ መምህር ከዚህ ቀጥለው የቀረቡትን የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች ሕፃናትን ተራ በተራ ይጠይቋቸው፡፡ በእንቆቅልሹ ላይ ያሉትን በሥዕል በማዘጋጀት ሲመልሱ ከሥዕሉ ጋር በማጣመር ያብራሩላቸው፡፡መልስ ካልመለሱ የእንቆቅልሽ አጠያየቅ ስርዓትን በተከተለ መልኩ ይሁን፡፡(እንቆቅልሾቹ ብዙ ስለሆኑ ከላይ ለተቀመጡት ክፍለ ጊዜ ያካፍላቸው)

### እንቆቅልሽ . አንድ

ከቤት እንስሳት ዓይነት አንዱ ነኝ ሰዎችን ይጋልቡኛል፣ ጋሪ ያስሩብኛል አራት እግር አለኝ፡፡ እኔ ማን ነኝ፡፡

**መልስ፡** ፈረስ

### እንቆቅልሽ ..ሁለት

ከመጓጓዣ ዓይነቶች ውስጥ እመደባለው በውሃ ላይ እንዛለው ፡፡ እኔ ማን ነኝ፡፡

**መልስ፡** ጀልባ፣ መርከብ

### እንቆቅልሽ... ሶስት

ድቡልቡል ቅርፅ አለኝ ከሚዚቃ መሣሪያ ውስጥ እመደባለው ድም ድም የሚል ድምፅ አወጣለው፡፡ እኔ ማን ነኝ፡፡

**መልስ፡** ከበሮ

**እንቆቅልሽ**

ከሚዚቃ መሣሪያዎች አንዱ ነኝ ከሸንበቆ እዘጋጃለው ቀዳዳዎች እሽሽ የሚል ድምፅ አወጣለው አሉኝ እኔ ማነኝ፡፡

**መልስ፡** ዋሽንት

**እንቆቅልሽ**

ከሙዚያ መሣሪያ መካከል እመደባለው ሦስት መዓዘን ቅርፅ አለኝ ከእንጨትና ከክር እሰራለው ክርክር የሚል ድምፅ አለኝ እኔ ማነኝ፡፡

**መልስ፡** ክራር

**እንቆቅልሽ**

በመሬት ላይ እሁዳለው አራት ጎማ አለኝ ጲጲጲ የሚል ድምፅ አወጣለው እኔ ማነኝ፡፡

**መልስ፡** መኪና

**እንቆቅልሽ**

ከስርዓተ ምግብ ውስጥ እመደባለው ጠዋት ጠዋት ህጻናቶች በሻይ ትበሉኛላችሁ ድቡልቡል ቅርፅ አለኝ ፤ለሰውነት ሀይልና ሙቀት እሰጣለው እኔ ማነኝ፡፡

**መልስ፡** ዳቦ

**እንቆቅልሽ**

ብዙ ውሃ በመጠጣት ከሳምንት በላይ መቆየት የምችል እንስሳ ነኝ፡፡ እኔ ማነኝ?

**መልስ፡** ግመል

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** እንቆቅልሽ ያሉትን ነገሮች በሥዕልና በቪድዮ

**የምዘና ስልት፡** እንቆቅልሹን ሲመልሱ በማዳመጥ፣ ከቤት እንስሳት ውስጥ ለመጓጓዣነት የሚያገለግሉትን ተናገሩ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ዘርዝሩ በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ተግባር ሶስት: የክፍል ውስጥ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የሙዚቃ መሳሪያ፣ ድምፅ፣ የቤት እንስሳት፣ መጓጓዣ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** ውድ መምህር! ሕፃናቱን በተቀመጡበት ያዘጋጃቸውን ቁሳቁሶች ያሳዩአቸው፡፡ የተለያዩ ድምፅ ያላቸውን የእንስሳት ዓይነትና የመጓጓዣ ዓይነቶች እንዲሁም የሙዚቃ መሳሪያዎች ምሳሌ፡ በግ፣ አህያ፣ ላም፣ መኪና፣ ባቡር፣ አውሮፕላን፣ ክራር፣ ከበሮ፣ ግመል እነዚህን ሥዕሎች የት እንደሚኖሩና ምን ዓይነት ድምፅ እንደሚያወጡና ለምን እንደሚጠቀሙ በጋራ ይጠይቋቸው ሲመልሱ እርስዎ ትክክለኛ ድምጻቸውን በማሰማት እንዲደግሙት ያድርጓቸው፡፡ ከዚያ ህጻናቱን በየተራ በማስወጣት ከመጓጓዣ ውስጥ ሁለት፣ ከእንስሳት ውስጥ ሁለት፣ ከሙዚቃ መሣሪያዎች

ውስጥ ሁለት በማድረግ ፊት ለፊት ጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ መጀመሪያ የመረጡትን ሥዕሎች ስድስቱንም በማንሳት ስማቸውን እንዲናገር ያድርጉ ከዚያም ህጻሁን ከክፍል በማስወጣት ወይም አይኑን በማስጨፈን አንዱን ሥዕል በማንሳትና ለተቀመጡት ሕፃናት በማሳየት ይደብቁ ከዚያ የሕፃኑን አይን በመክፈት ወይም ወደ ክፍል በማስገባት ከተደረደሩት ሥዕሎች ውስጥ የጠፋውን አስቦ እንዲናገር ያድርጉ መመለስ ካቃተው ምልክት ይስጡት ለምሳሌ፡ መኪና ከሆነ አራት ጎማ ያለው፣ በመሬት ላይ የሚሄድ፣በትልቅ ግቢ ውስጥ የሚያድር ሰዎችን ከቦታ ቦታ የሚያጓጉዝ ጺ.ጺ. እያለ የሚጮህ በማለት ያኔ ይመልሳል ካልመለሰ ሌሎቹ ህጻናቶች የተደበቀውን ስላዩ በጋራ እረዲመልሱ ያድርጉና ወደ ቀጣይ ሕፃን ይሂዱ፡፡ እንዲህ እያለ ጨዋታው ይቀጥላል፡፡ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን የመጓጓዣ ዓይነቶች ን ከሥዕላቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** እንስሳት፣መጓጓዣ፣የሚዚቃ መሣሪያ በትንንሹ የተሳሉ ሥዕሎች ወይም ሞዴሎች

**የምዘናስልት፡** ጨዋታውን ሲጫወቱ በመመልከት፣ የምታውቋቸውን የቤት እንስሳት በመዘርዘር ድምፃቸውን በማስመሰል አሰሙ፣ የምታውቋቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎችን ተናገሩ በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ ፣

## ተግባር አራት፡ ተረት (4 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ራስን መቆጣጠር፣ ጥንቃቄና ደህንነት፣ የመንገድ አጠቃቀም፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ፣ በማስመሰል

**የመምህር ሚና፦** መምህር እባክዎትን ሕፃናት የቀረበላቸውን ተረት በጥሞና እንድያዳምጡ በማድረግ ያዳመጡት ተረት ፍሬ ሓሳቦችን መልሰው እንዲገልጹ ያግዟቸው፡፡

### ርዕስ፡ አደገኛዉ ጨዋታ

በላይ እና አስቴር የቅድመ አንደኛ ደረጃ ሦስት ጓደኛሞች ናቸው፡፡ ወላጆቻቸው እነሱን ትምህርት ቤት ለማምጣት ስላልቻሉ መንገድ ሲሄዱ የእግረኛ መንገድ ግራ ጠርዝ ይዘው መሄድ እንዳለባቸውና ሲሻገሩ የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አስቀድመው ስላሳያቸው ሁልጊዜ እጅ ለእጅ ተያይዘው ቁጥር መቁጠር ደስ ይላል ደስ ይላል ጎበዝ ያደርጋል 1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 በማለት እየዘመሩ ከቤታቸው ወጡ ልክ አስባልት ላይ ሲደርሱ አስቴር በቃ አሁን የመኪና መንገድ ላይ ስለደረስን መጠንቀቅ አለብን በማለት ተጠንቅቀው መጓዝ ይጀምራሉ፡፡ አንድ ቀን ወደ ትምህርት ቤታቸው እየተጓዙ እያሉ የክፍላቸው ተማሪ መሀመድ መሃል መንገድ ላይ ኳስ እየተጫወተ ተመለከቱት እነሱም ተው መኪና ይገጭኃል ውጣ ሲሉት እሱ ግን ኳሱን ወደነሱ ወርወሮ አስቴርን መታት አስቴርም በጣም ተናዳ ልትመታው ወደ አስባልቱ ስትሄድ በላይ ተይ ራስሽን ተቆጣጠሪ አስባልት ላይ መጣላት ለአደጋ ያጋልጥሻል ትምህርት ቤት ስንደርስ ለሚስ እንናገራለን ብላ አረጋጋቻት ከዚያም መንገዳቸውን ቀጠሉ ትንሽ እንደተጓዙ የሰዎች ጬኸትና የአምቡላንስ ድምፅ ሰሙ ዞር ብለው ሲመለከቱ መሀመድ በመኪና ተገጭቶ አስባልት ላይ ወድቆ ተመለከቱ ሰዎች ተሯሩጠው ወደ አንቡላንስ አስገቡት እነሱም እያለቀሱ ለመምህራቸው ለመንገር ወደ ትምህርት ቤታቸው እሮጡ፡፡ ስለዚህ ሕፃናት ሁል

ጊዜም ቢሆን በመኪና መንገድ ላይ መጫወት የለባችሁም።

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የትራፊክ አደጋ ሥዕል፣የአምቡላንስ ሥዕል፣ የትራፊክ መብራት፣የቁጥር ካርድ

**የምዘና ስልት፡** የተረቱን መልዕክት እንዲናገሩ መጠየቅ፣ መሀመድ በመኪና አደጋ የተገጨው ምን አድርጎ ነው?፣ በመንገድ ላይ ስትጓዙ ምን ማድረግ አለባችሁ በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ተግባር አምስት: የመስክ ጉብኝት (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ድምፆችን መለየት፣ የትራፊክ መብራት፣ የቀለም አይነቶች፣ የእግረኛ ማቋረጫ፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመስክ ጉብኝት፣ በትረካ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፦** ውድ መምህር ወደ ውጭ በማስወጣት ትናንሽ ቡድኖች በማደራጀት ለቡድኑ ቁጥር ይስጧቸው ከዚያም ወደ መኪና መንገድ በመውሰድ

**ቡድን አንድ** ስለ ትራፊክ መብራት ስንት ዓይነት እንደሆኑና ምንምን ቀለም እንዳላቸው

**ቡድን ሁለት** የትራፊክ መብራት ከቀለም ውጪ ምን ዓይነት ምልክቶች እንዳሉት ምሳሌ፡ የሰው ምልክት

**ቡድን ሶስት** የእግረኛ ማቋረጫ ምን ዓይነት ቀለም እንዳለውና ማን ሲጠቀምበት እንዳዩ

**ቡድን አራት** ምን ምን ዓይነት መኪናዎች እንዳዩ

**ቡድን አምስት** መኪናዎች ሲቀጡ ካዩ ማን ቀጣቸው ለምን እንደተቀጡ

**ቡድን ስድስት** ምን ምን ድምፆች እንደሰሙ

**ቡድን ሰባት** በመኪና ታርጋ ላይ ያዩትን ቁጥሮች እንዲጽፉ በማከፋፈል ይስጡ ከዚያም የመስክ ጉብኝቱ አልቆ ወደ ክፍል ሲመለሱ ያዩትን እንደአቀማቸው እንዲናገሩ ያድርጉ የመኪና ታርጋ ቁጥር ሲናገሩ ቁጥሮቹን በመነጣጠል በአንድ ዲጂት ብቻ እንዲናገሩ ያድርጉ።በመጨረሻም ከቻሉ መንገድ ላይ ያዩት ትራፊክን በመጋበዝ ስለ መንገድ አጠቃቀም እንዲያብራራላቸው ያድርጉ ካልተቻለ እርስዎ በተለይ ስለምልክቶቹ ማጠቃለያ ይስጧቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ወረቀት፣ እርሳስ፣የቪድዮ የተቀረፀ የትራፊክ መብራት ምልክቶችና መኪና ፣

**የምዘና ስልት፡** ምልከታ ፣ የትራፊክ መብራት ቀለማትን ተናገሩ፣ የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ ምን አይነት ቀለም ተቀብቷል በማለት ፣ እንዲሁም ስለ መንገድ ደህህነት፣ በመኪኖች ታርጋ ላይ ያዩዋቸውን ዉትሮች እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ተግባር ስድስት: በስራ መማር (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የፈጠራ ሥራ፣ ቅርፅ፣ ድምፅ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ሕፃናቱን ወደ ማበልፀጊያ ክፍል በመውሰድ የራሳቸውን የፈጠራ ሥራ እንዲሠሩ ይንገራቸው እርስዎ አንድ የሆነ ነገር በመሥራት እንደምሳሌ ያሳዩአቸው፡፡ ከዚያም የሚሠሩበትም ቁሳቁሶች በመውሰድ ( እዚህ ላይ ቁሳቁስ ሲወስዱ እርስ በእርሳቸው ሊጣሉና ሊመታቱ ስለሚችሉ ስሜታቸውን እንዲቆጣጠሩ ያድርጉበመገጣጠም በመደርደር የፈለጉትን ነገር እንዲፈጥሩና እንዲሠሩ ያድርጓቸው ከዚያም የሠሩት ነገር ምን እንደሆነ እንዲናገሩና ለመሥራት ስንት ዓይነት ቅርፅ እንደተጠቀሙና የሠሩት ነገር ድምጽ ያለው ከሆነ ምንዓይነት ድምፅ እንደሚያውጣ እንዲናገሩ ይጋብዛቸው፡፡

**ለምሳሌ:** አውሮፕላን ቢሆን አንድ ልጅ የሰራው የሰራውት አውሮፕላን ነው፣አውሮፕላን ለመሥራት 4 ዓይነት ነገር ተጠቅሚያለው 1 ካርቶን 2 ላስቲክ 3 የሃይላንድ ክዳን 4 ወረቀት ድምፁ ሹሽ በማለት እንዲናገሩ ያበረታታቸው ያግዛቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ወረቀት፣ እርሳስ፣ካርቶን፣የየውሃ መያዣ ዕቃዎች ክዳን፣ቆርኪ፣ ፣ማጣበቂያ የመሳሰሉት

**የምዘና ስልት:** ሲሰሩ መመልከት፣ የሰራችሁት የምን ቅርፅ ነው፣ ድምፁን አሰሙ በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ሦስተኛ ሳምንት

### ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ ፡ 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

**አጥጋቢየመማርብቃት:**

- ✓ ራስ መቻልን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ ማኅበራዊ ግንዛቤን በማሳደግ ለሌሎች እንክብካቤ ያደርጋሉ፡፡
- ✓ የተለመዱ ቃላትን ያስታውሳሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን በማወዳደር በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ፡፡
- ✓ የባህል ብዝሀነትን ያደንቃሉ፡፡
- ✓ ባህላዊ ቅርሶችን ይጠብቃሉ፣
- ✓ የጣት ጨዋታዎችን በእጅ እና በጣቶቻቸው ይጫወታሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች:** ራስን መቻል፣ የቃላት ክምችት ፣ የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣ ቁጥሮችን ማወዳደርና ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ ባህላዊ ቅርሶች


### ተግባር አንድ: የግል ተግባር (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ ቅደም ተከተል፣ እንስሳት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህርሚና:** መምህር! በዚህ ክፍለ ጊዜ ሕፃናት የግል ሥራዎቻቸውን በትክክል እንዲሠሩ ያግዟቸው፡፡ የተለያዩ የቤት እንስሳት የያዘ ሥዕል በማዘጋጀትና በአንድ ካርድ ላይ መጠናቸውን በመደጋገም ከ1 20 ያድርጉና በመቀላለል ይስጧቸው፡፡ ከዚያም የቤት እንስሳትን ለብቻ የዱር

እንስሳትን ለብቻ እንዲለዩ ያድርጉ፤ የለዩቸውን ደግሞ እላያቸው ላይ ያሉትን ሥዕሎች በመቁጠር ከትንሽ ቁጥር ወደ ትልቅ ቁጥር በቅደም ተከተል ራሳቸውን ችለው እንዲደረድሩ ያድርጓቸው በመጨረሻም በትክክል መሥራታቸውን በማየት ያረጋግጡ ትክክል ላልሆኑት እንደገና አብረው በመሥራት ያስተካክሉላቸው፡፡ምሳሌ፣



3 ሦስት

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የተለያዩየመጓጓዣሥዕሎች እና ሞዴሎች

**የምዘና ስልት፡** ሲሰሩ በመመልከት፣ የቤት እንስሳትና የዱር እንስሳትን ተናገሩ፣ ቁትሮችን በቅደም ተከተል አስቀምጡ በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ተግባር ሁለት: የክፍል ውስጥ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ ቅርስ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** ውድ መምህር እባክዎትን ሕፃናቱ ሥዕላዊ ካርደ የያዙ ባህላዊ ቅርሶች ለምሳሌ፡ ላሊበላ፣ አክሱም፣ጢያ ትክል ድንግያ፣መካ መዲና፣ሰረገላ፣ ፈረስ፣የሀረር ግንብ፣ የፍሲል ግንብ፣ የመሳሰሉትን የሥዕል ካርዶች ያዘጋጁ ከዚያ ለሕፃናቱ ቢቻል ከቪድዮ ጋር ምስሎቹን በማገናኘት ስማቸውን በመደጋገም ያስተዋውቃቸው ከዚያ ካርዶቹን እጣ እጣ በማለት ጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ ራሳቸውን ችለው አንዱን በመሳብ እላዩ ላይ ያለውን ባህላዊ ቅርስ ምስሉን በማየት ስሙን እንዲናገሩ ያድርጉ ከዚያም ሕፃናቱ ተከትለው እንዲደግሙት ያድርጉ፡፡ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን ባህላዊ ቅርስ መጠሪያ ስሞችን ደግመው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የተለያዩየ ባህላዊ ቅርሶችን የያዙ ካርዶች፣ ቪድዮ

**የምዘና ስልት፡** ጨዋታውን በተግባር ሲጫወቱ መመልከት፣ በካርዶቹ ላይ ያዩዋቸውን ባህላዊ ቅርሶች እንዲናገሩ በቃል መጠየቅ

## ተግባር ሶስት: መዝሙር አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ቁጥር፣ ጣት፣ መቁረጥ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! እባክዎትን ክፍለ ጊዜው የመዝሙር እንደሆነ ይግለጹላቸውና መዝሙሩን ያቅርቡላቸው፡፡ በመጨረሻም በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን ሥዕሎች እንዲያወዳድሩ ያድርጉ፡፡

ዜሮ (0) እንቁላል ናት

0 እንቁላል ናት ማነው የሚበላት?
1 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 4 ፣ ዓሳ አጠመድኩኝ ለአራት
5 ፣ 6 ፣ 7 ጮኬ ለቀቅኩኝ በድንገት
ለምን ለምን ለቀቅሽው
ጣቴን ጣቴን ቆረጠመኝ
የትኛውን ጣትሽን
የቀኝ እጄን ትንሿን ነው / 2x /
የግጥም ምንጭ ፡ የኢትዮጵያ ልጆች

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የቁጥር ካርዶች

**የምዘና ስልት፡** ሲዘምሩ በማዳመጥ፣ የተቆረጠው የትኛው ጣት ነው፣ የእንቁላል ቅርፅ የላት የትኛዋ ቁጥር ናት በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## መዝሙር ሁለት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ ጭፈራ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! እባክዎትን ክፍለ ጊዜው የመዝሙር እንደሆነ ይግለጹላቸውና መዝሙሩን ያቅርቡላቸው፡፡

ተነሡ እንጫወት
ተነሡ እንጫወት
አይገኝም ልጅነት /2/
ስጠብቅ ባህሌን ጉራጌኛ ደስ ይለኛል
እንደዚህ ያስብለኛል
ዕዮ ዕዮ ዕዮ
ተነሡ እንጫወት
አይገኝም ልጅነት /2/
ስጠብቅ ባህሌን ኦሮምኛ ደስ ይለኛል
እንደዚህ ያስብለኛል
እሾ እሾ እሾ
ተነሡ እንጫወት
አይገኝም ልጅነት /2/
ስጠብቅ ባህሌን አማርኛ ደስ ይለኛል
እንደዚህ ያስብለኛል
እስክስ እስክስ እስክስ

ተነሡ እንጫወት
አይገኝም ልጅነት /2/
ስጠብቅ ባህሌን ትግሬኛ ደስ ይለኛል
እንደዚህ ያስብለኛል
ላለይ ላለይ ላለይ

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የባህላዊ ልብሶች፣ ባህላዊ ዘፈኖች

**የምዘና ስልት፡** ሲዘምሩ በማዳመጥ፣ የተለያዩ አካባቢዎችን/ቋንቋዎችን ባህላዊ ጭፈራ በተግባር ሲጨፍሩ መመልከት

## ተግባር አራት: የክፍል ውጭ ጨዋታ አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ማወዳደር፣ ትልቅ፣ ትንሽ፣ እንቅስቃሴ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! ሕፃናቱን ወደ ውጭ በማስወጣት አንድ ትልቅ ክብና 10 ትናንሽ ክብ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ባሉበት ቦታ ቆመው በማጨብጨብ

ንፋሱ ነፈሰ ሆሆሆ
ወደ ሚነፍሰው ሆሆሆ ወደ ሚነፍሰው
እንዴት ያስደስታል! ሆሆሆ አብሮ መጫወቱ
ሆሆሆ አብሮ መጫወቱ ሆሆሆ
ትልቁ ጎማ ተሽከረከረ /4/ ሲሉ
ትልቁን ክብ የሠሩት ሕፃናት ይሽከረከራሉ፡፡
ሌሎቹ ደግሞ ያጨበጭባሉ
ንፋሱ ነፈሰ ሆሆሆ
ወደሚነፍሰው ሆሆሆ ወደ ሚነፍሰው
እንዴት ያስደስታል! ሆሆሆ አብሮ መጫወቱ
ሆሆሆ አብሮ መጫወቱ ሆሆሆ
ትንሹ ጎማ ተሽከረከረ /4/ ሲሉ

ደግሞ ትንሹን ክብ የሠሩት አሥሩ ልጆች እጅ ለእጅ በመያያዝ ይሽከረከራሉ፤ የቀሩት ያጨበጭባሉ:: እንዲህ እያለ ጨዋታውን ይደግማሉ፡፡ መጨረሻ ላይም ለምን ትልቅ ክብና ትንሽ ክብ እንደ ተባለ ይጠይቋቸው፡፡ ከዚያም የክቡ መጠን ትንሽ እና ትልቅ ለመሆን የእነርሱ ቁጥር መቀነስና መጨመር መሆኑን፤ አሥር በሚሆኑ ተማሪዎች ሁለት ቦታ ትንንሽ ክብ በማሠራት የትኛውን ክብ የሠሩት ሕፃናት እንደሚበልጡ እየቆጠሩ “ትንሿ ክብ ውስጥ ስንት ሕፃናት አሉ? ትልቁ ውስጥስ? ስለዚህ የቱ ክብ ይበልጣል?” በማለት እንዲያወዳድሩ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ትልቅና ትንሽ ጎማ፣

**የምዘና ስልት፡** ሲጫወቱ በመመልከት፣ የትልቅና የትንሽን ልዩነት በምሳሌ አስደግፈው እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## የክፍል ውጭ ጨዋታ ሁለት (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ፊደላት፣ ቃላት ምስረታ፣ ቁጥር፣ አካላዊ እንቅስቃሴ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! ሕፃናቱን በቡድን ይክፈሏቸው፡፡ ከዚያም ከባህላዊ ቅርስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የፊደል ካርዶች ለምሳሌ “ኸ ዠ ጀ ጸ ጰ” የሚሉ ሆሄያትን ያዘጋጁ፡፡ ሕፃናቱን ወደ ውጪ በማስወጣት በተመደቡበት ቡድን ክብ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ከየቡድኑ አንድ አንድ ሕፃን መሪ አድርገው ይምረጡ፡፡ ካዘጋጁት የፊደል ካርድ ስድስት ስድስት በማድረግ በየቡድኑ መሐል ያስቀምጡ፡፡ ሕፃናቱ ካርዱን ቆጥረው እንዲረከቡ ያድርጉ፡፡ እርስዎ “ዱብ ዱብ” ሲሉ የፊደል ካርዱን ይዘው በተግባር “ዱብ ዱብ” እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያ “ቁም” ሲባል የተመረጠው ሕፃን አንድ የፊደል ካርድ አንሥቶ ለቡድኑ ሲያሳይ ባዩት ፊደል ቃላት ይመሠርታሉ፡፡ ሕፃናቱ ከተሳሳቱ ካርዳቸው ይወሰዳል፤ ካልተሳሳቱ ካርዱ ከሌሎቹ ተለይቶ እዚያው ይቀመጣል፤ እንዲህ እያለ ስድስቱም የፊደል ካርድ ቃላት ከተመሠረተ በኋላ የቡድኑ መሪ ስንት ካርድ እንደ ቀራቸው ወይም በስንቱ ካርድ በትክክል ቃላት እንደ መሠረቱ እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡ የቡድኑን አባላት የየትኛው ቡድን ብዙ እንደ ሆነና የየትኛው ቡድን ትንሽ እንደሆ ቁጥሩን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም የፊደል ካርዶቹን በማሳየት በጋራ ቃላት እንዲመሠርቱ በማድረግና በመለማመጃ ደብተራቸው ገፅ ላይ ያሉትን ቃላት ቤተሰቦች ያሰራቸው ትምህርቱን ያጠቃልሉላቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የፊደል ካርድ፣ የቁጥር ካርድ፣ የቃላት ካርድ

**የምዘና ስልት፡** ጨዋታውን በተግባር ሲጫወቱ መመልከት፣ ምልከታ፣ ቃላትን መጠየቅ

## ተግባር አምስት: በፕሮጀክት መማር ( 5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፦** መምህር! ወደ ውጭ በማስወጣት ትናንሽ ቡድኖች በማደራጀት የተለያዩ ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ለምሳሌ የመኪና፣ የሞተር ሳይክል፣ የአውሮፕላን፣ የፈረስ፣ የአህያ የጭነት መኪና በሽቦ፣ በካርቶን እና በጭቃ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ከሠሩት ውስጥ የቱ ባህላዊ እንደሆነና የቱ ዘመናዊ እንደሆነ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ ከዚያም ለምን ዘመናዊና ባህላዊ እንደተባሉም እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ከባህላዊና ከዘመናዊ መጓጓዣ የትኛው እንደሚፈጥን ይጠይቋቸው፡፡ በመጨረሻም ቢቻል ቪድዮ በመጠቀም ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችን በማሳየት ፍጥነታቸውን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ካርቶን፣ ማጣበቂያ፣ ወረቀት፣ ሽቦ፣ ጭቃ፣ የውሃ መያዣ ዕቃዎች ክዳን፣ ቆርኪና የመሳሰሉት፣

**የምዘና ስልት፡** በተግባር ሲሰሩ በመመልከት፣ ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ አይነቶችን እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ

# አራተኛ ሳምንት

**ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት/**

**አጥጋቢ የመማር ብቃት፡**

- ✓ ከሌሎች ጋር የመግባባት ክህሎታቸውን ያዳብራሉ።
- ✓ ከሌሎች ጋር የመወያየት ተሳትፏቸውን ያሳድጋሉ።
- ✓ ማኅበራዊ ግንዛቤያቸውን በማሳደግ ለሌሎች እንክብካቤ ያደርጋሉ።
- ✓ የቁጥሮችን ፅንሰሀሳብ ይገልፃሉ።
- ✓ የመዝለልና የመንከባለል ጨዋታዎችን ይጫወታሉ።
- ✓ ቀለማትንና መልክዓምድሮችን ያዉቃሉ።
- ✓ መደበኛ የምት እንቅስቃሴዎችን ይሠራሉ።
- ✓ ቅጦችን በመለየት ይገልጻሉ።
- ✓ የተለያዩ የኪነጥበብ እና የዕደ ጥበብ ሥራዎችን ዋጋ ይሰጣሉ።

**ንዑስ ይዘቶች፦** ማሕበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን መግለጽ፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር ፣ ቅጥ/ሥረዓተ ጥለት/መደርደር/ ፣ ጥበባዊ እሴት

## ተግባር አንድ፡ ውይይት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ እሴቶች

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** ውይይት፣ ገለፃ፣ ጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! ለሕፃናቱ ክፍለ ጊዜው የውይይት እንደ ሆነ በመግለጽ በተቀመጡበት ወንበር መሠረት ቡድን ይክፈሏቸው። ከዚያም ስለ ባህላዊ እሴቶች ሥዕል ወይም ቪዲዮ በመጠቀም መነሻ ይስጧቸው። ለምሳሌ፡ ከማኅበራዊ እሴቶች "ባህልን ማክበር፣ ተካፍሎ መብላት" የሚል ሊሆን ይችላል። ከዚያ በተመደቡበት ቡድን በሚኖሩበት አካባቢና በሰፈራቸው ውስጥ ሲተገበር ስላዩት ባህላዊ እሴትና ባህሉ ሲከበር ምን ምን ነገሮች እንደሚደረጉ እንዲወያዩ ይንገሯቸው፤ ሕፃናቱ ሲወያዩ እየተዘዋወሩ በማየት ያበረታቷቸው። ተወያይተው ሲጨርሱ አንድ ልጅ በማስነሣት ሐሳባቸውን እንዲናገር ይጋበዙ። ሁሉም ቡድን አቅርበው ከጨረሱ በኋላ ስለ ጥበባዊ እሴቶች ዘርዝረው ይንገሩቸው። በዚህም ላይ የባህላዊ ሙዚቃ በመክፈት በአቅማቸው እንዲሳተፉ ያድርጓቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የተለያዩ ባህላዊ እሴቶችን የሚያሳዩ ስዕላዊ መግለጫዎች፣ የተቀረፀ ባህላዊ ሙዚቃ

**የምዘና ስልት፡** ሲወያዩ በመመልከት፣ በየአካባቢያቸውየሚያውቋቸውን ባህላዊ እሴቶች እንዲገልፁ፣ ይቅምና ጉዳታቸውን እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ተግባር ሁለት: ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ልደት፣ ማህበራዊ ግንኙነት፣ ጎረቤት፣ ጓደኛ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! እባክዎትን ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በአሻንጉሊት/ በስእል በማስደገፍ ይንገሯቸው።

### ልደት

ስሜ ሜላት ይባላል፤ የደረጃ ሦስት ተማሪ ነኝ። ዛሬ ከተወለድኩ 6 አመት ሞላኝ። ልደቴን ከእናንተ ከጓደኞቼ ጋር ላከብር ተዘጋጅቻለሁ። የጎረቤታችን ልጅ ካሊድ ግን ከእኅቱ ጋር በመሆን በጠዋቱ "እንኳን ተወለድሽ" በማለት ካሊድ ይህን አበባ ሰጠኝ፤ እኅቱ ደግሞ መኪና ሰጠችኝ፤ አበባ የዕፅዋት ዓይነት ነው። አበባ ለስጦታና ስሜትን ለመግለጽ ያገለግላል። አበባ በጣም እወዳለሁ። እኔም አመስግኜ ኩኪስ ጋበዝኳቸው። እናቴም "እንደዚህ ዓይነት ጥሩ ጎረቤት ስላሉን ልንደሰት ይገባል፤ ማታ ቡና አፍልተን እንጠራቸዋለን።" በማለት ቃል ገባችልኝ። እናንተስ "እንኳን ተወለድሽ፤ መልካም ልደት አትሉኝም?" ስትል ጓደኞቿ ሕፃናቱ " መልካም ልደት ለሜላት" እያሉ ከአሻንጉሊቷ ጋር አብረው በመጨፈር ያከብራሉ።

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡** የተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ አበባ፣ አሻንጉሊት፣ የልደት መዝሙር

**የምዘና ስልት:** ተረቱን በአጭሩ ደግመው እንዲናገሩ መጠየቅ፣ ሜላት ስንት ዓመቷ ነው?፣ የነሜላት ጎረቤት ልጅ ማን ይባላል በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ተግባር ሶስት: መዝሙር አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ደስታ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ስሜትን መግለጽ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ክፍለ ጊዜው የመዝሙር እንደ ሆነ ይግለጹላቸውና መዝሙሩን ያቅርቡላቸው። በመጨረሻም በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን የባህላዊ መጓጓዣ ሥዕሎች እንዲያቀልሙ ያድርጓቸው።

### ደስተኛ የሆነ

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ /2/
ደስተኛ የሆነ ደስታውን እያሳየ ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ
ደስተኛ የሆነ ይሳቅ
ደስተኛ የሆነ ይዝለል /2/
ደስተኛ የሆነ ደስታውን እያሳየ ደስተኛ ይዝለል
ደስተኛ የሆነ ይዝለል
ደስተኛ የሆነ ይተቃቀፍ /2/
ደስተኛ የሆነ ደስታውን እያሳየ ደስተኛ የሆነ ይተቃቀፍ

ደስተኛ የሆነ ይተቃቀፍ
ደስተኛ የሆነ ይደንስ /2/
ደስተኛ የሆነ ደስታውን እያሳየ ደስተኛ የሆነ ይደንስ
ደስተኛ የሆነ ይደንስ

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** መሳቅን፣ መዝለልን፣ መደነስንና ማቀፍን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ/የቪድዮ ምስል

**የምዘና ስልት፡** ሲዘምሩ ዜማውን ጠበቀው መዘመራቸውን መመልከት፣ ሲደሰቱ እንዴት ደስታቸውን እንደሚገልጹ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፣ ስቀው፣ዘለው፣ አቅፈውና ደንሰው እንዲያሳዩ ማድረግ

## መዝሙር ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ኢትጵያዊ፣ ባህል

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** ውድ መምህር! ክፍለ ጊዜው የመዝሙር እንደሆነ ይግለጹላቸው፡፡ የሚቀጥለውን መዝሙር ከእርስዎ ቀጥሎ እንዲዘምሩ ለማድረግ ስንኞቹንና ዜማውን ያለማምዷቸው፡፡

ኢትዮጵያዊ ነኝ
እኔ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ነኝ
የራሴ ምለው በዓላት ያለኝ
ከጎረቤት ጋር እኖራለሁ
ባህሌን አከብራለሁ
ከጓደኛዬ ጋር እጫወታለሁ
ያለኝን ነገር አካፍላለሁ
አብረን አልቅሰን ደግሞም ጨፍረን
እንኖራለን በጋራ ሆነን /2/

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የተለያዩ ባህልን የሚሳዩ ስእሎች/ ፎቶዎች

**የምዘና ስልት፡** ሲዘምሩ መመልት፣ የሚወቋቸውን የተለያዩ ባህሎችን ( አለባበስ፣አመጋገብ ወዘተ. እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## ተግባር አራት: የክፍል ውጭ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ አልባሳትና ጭፈራ፣ መለከዓምድር፣ ምት

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! ሕፃናቱን ወደ ውጭ በማስወጣት የተለያየ ባህላዊ ሙዚቃ በመክፈት ክብ ሠርተው የሙዚቃውን ምት ተከትለው እንዲንቀሳቀሱ ያድርጉ፡፡ ወደ ቀጣዩ ተግባር ከመሸጋገርዎ በፊት አሁን የተወዛወዙበት ባህላዊ ጭፈራ የማን ባህል መገለጫ እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ እነርሱ ሲናገሩ እርስዎ ከሥዕል ጋር ወይም ከቪድዮ ጋር በማገናኘት ስለ

አልባሳቶቹም ያብራሩላቸውና ወደ ቀጣዩ ውዝዋዜ ይሂዱ፡፡ እንዲህ እያሉ የሁሉንም ባህላዊ ውዝዋዜ ለመዳሰስ ይሞክሩ፡፡ ከዚያም ያዩትን ባህላዊ ጭፈራ ወይም አልባሳት እንዲያደንቁ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የጉራጌ ባህላዊ ጭፈራ እንቅስቃሴ ካደረጉ በኋላ ስለ ጭፈራውና አለባበሳቸው እንዲሁም የተለያዩ መልክ አምድራዊ አቀማመጦችን የሚያሳዩ ገፅታዎችን በሥዕል ወይም በቪድዮ ያሳዩአቸው፤ በመጨረሻም ያዩትን ባህላዊ አልባሳትና የመልክአምድራዊ አቀማመጥ ምንነት እንዲለዩና የተሰማቸዉን ስሜት እንዲገልፁ ያድርጓቸዉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ሥዕሎች ወይም አልባሳት፣ ቪድዮ፣ የተቀረጸ ሙዚቃ፣ ቴፕ ሪከርደር ፍላሽ፣ የተለያዩ መለከአ ምድርን የሚያሳዩ ምስሎች

**የምዘና ስልት:** የተለያዩ ባህሎችን መገለጫዎች በቃል መጠየቅ?፣ ባህላዊ ጭፈራዎችን ሲጨፍሩ መመልት

## ተግባር አምስት፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መጓጓዣ፣ ቁጥር፣ ገንዘብ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር ሕፃናቱን ወደ ማዕዘን/ጥግ ክፍል ይውሰዷቸው፡፡ ከዚያም በአንድ ቡድን ውስጥ 10 ሕፃናትን ይመድቡ፡፡ ለየቡድኑ የተለያዩ ቅርፅ ያላቸው ፕላስቲክ የግንባታ ዕቃዎች እኩል በመክፈል ይስጧቸው፡፡ በተሰጣቸው የግንባታ ዕቃዎች በመጠቀም ከመጓጓዣ ዓይነቶች ውስጥ የፈለጉትን ገንብተው እንዲሠሩ ያድርጉና የሠሯቸዉ መጓጓዣ አይነቶች ስንት የግንባታ የፕላስቲክ እቃዎችን እንደተጠቀሙ እንዲቆጥሩ ካደረጉ በኋላ የተዘጋጁትን ቁሳቁሶች አንዱ አሽከርካሪ፣ አንድ ሂሳብ ተቀባይ ወይም ትኬት ቆራጭ ( ከወረቀት ትኬት በማዘጋጀት ይስጧቸው)፣ ሌሎቹ ደግሞ ተሳፋሪ በመሆን ትኬት እየቆረጡ (የወረቀት ገንዘብ ይስጧቸው) እንዲሳፈሩና እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡ ጨዋታውን ሲጨርሱ የሠሩበትን ገንዘብ አብረው በጋራ እንዲቆጥሩና ስንት እንደ ሠሩ በየቡድናቸው ከተናገሩ በኋላ የሠሩትን መጫወቻ እንዳያፈርሱት በመንገር አንዱ ቡድን ሌላው የሠራውን እንዲያይና እርስ በእርስ እንዲደናነቁ ዕድል ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም ከተሠራው የመጓጓዣ ዓይነት ውስጥ የቱን እንዳደነቁ ይጠይቋቸው፡፡ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ካለው የመጓጓዣ ዓይነት ውስጥ የሚፈልጉትን ሁለት ሥዕል እንዲሥሉና ከአንድ እስከ ሀያ ካሉት ቁጥሮች ዉስጥ የጎደሉ ቁጥሮችን እንዲሰሩ ያድርጓቸዉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** ወረቀት፣ የተለያዩ የግንባታ ፕላስቲክ ዕቃዎች፣

**የምዘና ስልት:** ሲሰሩና ሲጫወቱ በመመልከት፣ የሚወዱትን መጓጓዣ አይነት፣ የሰሩትን የመጓጓዣ አይነት፣ ብዛት እንዲናገሩ በቃል መጠየቅ፣

## ተግባር ስድስት: በሥራ መማር (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቅርፅ፣ ቅጥ፣ ማድነቅ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡-** መምህር! ለሕፃናቱ በክፍል ሥራ ደብተራቸው ላይ የተለያዩ ቅርፆችን ለምሳሌ ክቦችን አስቀድመው ሥለው ያዘጋጁ፡፡ ለእያንዳንዳቸው እርሳስና ባለ ቀለም እርሳስ በመስጠት

የተሣለውን ቅርፅ በመደጋገም የመኪና ሥዕል፣ ሞተር ሳይክል እንዲሥሉና እንዲያቀልሙት ያድርጉ፡፡ ከዚያም ቅርፁን ደጋግመው በመሥራት የሥዕሉን ስም እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ከዚያ በኋላ አጠገባቸው ካለው ሕፃን ጋር እንዲቀያየሩና እርስ በእርስ የሠሩትን ሥነ ጥበብ እየተያዩ እንዲደናነቁ ያድርጉ፡፡ ( በሌላ ቀን ደግመው ሲያሠሯቸው የሚያዘጋጁትን ቅርፅ በአራት ማዕዘን፣ በሞላላ እያደረጉ በመቀያየር ያሠሯቸው፡፡)

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡-** በደብተር ላይ ተሰርቶ የተዘጋጀ ቅጥ/ቅርፅ፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

**የምዘና ስልት፡** ሲሰሩ መመልከት፣ የሰሩትን ስእል ምን እንደሆነ እና ስንት ስእል እንደሳሉ እንዲናገሩ በቃል መጠየቅ)

# አምስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ ፡ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃት፡

- ✓ ጥሩ እና መጥፎ ነገሮችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር የግብረ ገብ እሴቶችን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ፊደላት በቅደም ተከተል ይለያሉ፡፡
- ✓ ተረቶችን በራሳቸው አገላለጽ ያዘጋጃሉ፡፡
- ✓ የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ አካባቢን ይረዳሉ፡፡
- ✓ የቦታ መገኛ ግንዛቤአቸውን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ ነገሮችን በዓይነት በዓይነታቸው ይመድባሉ፡፡
- ✓ ከትምህርቱ ጋር የተገናኙ ሥነ ጥበቦችን ይተገብራሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡-** የግብረ ገብ እሴት፣ የፊደላት ድምፅ ግንዛቤ፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ አካባቢ፣ የቦታ መገኛ ግንዛቤ፣ መለየትና መመደብ፣ ማገናኘት፣ ማያያዝና መተግበር

### ተግባር አንድ: የግል ስራ አንድ (7 ክፍለጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ፊደል፣ ድምፅ መለየት፣ ቃላት ምስረታ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፐ | የ | ጩ | ፕ | ኀ |

**የመምህር ሚና ፡** ውድ መምህር እባክዎትን ይህ ክፍለ ጊዜ ሕፃናት የግል ሥራዎቻቸውን የሚሠሩበት መሆኑን ይግለጹላቸው ከዚያም ፊደላትን በፊደል ካርድ ያዘጋጁ ለምሳሌ፡

በምሳሌ መሠረት የ "ፐ" ፣ የ "ፕ"፣ የ "ኀ" እና የ "ጩ" እና "የ" ቤተሰቦችን በሙሉ ከላይ ባለው የፊደል ካርድ መሠረት ያዘጋጁ፡፡ ያዘጋጁትን የፊደል ካርድ በመቀላቀል ከተቻለ በየወንበራቸው ላይ በማስቀመጥ ካልተቻለ ደግሞ ከተማሪዎቹ ፊት ለፊት በማስቀመጥ አንድ አንድ ሕፃን በየተራ በማስወጣት ተመሳሳይ ፊደላትን ከነቤተሰቦቻቸው እንዲለዩና እንዲመድቡ ያድርጉ፡፡ ከዚያም

የመደባቸውን ፊደላት በማንሣት ፊደላቱን እያሳዩ ድምፃቸውን እንዲጠሩ ሌሎቹ ሕፃናት ደግሞ እነርሱን በመከተል ፊደላቱን እያዩ ድምፃቹን እንዲደግሙት ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ፊደላቱን ወደ ቦታው ሲመልሱ ፊደላቱን የት እንደ ተቀመጡ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም የፊደላቱን ድምፅ አንድ ጊዜ ካስባሏቸው በኋላ ፊደላቱ ከጠረጴዛው ላይ እንደተ ቀመጡ በማሳየት ይግለጹላቸው፡፡ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን በተሰጣቸው ፊደላት መነሻነት ቃላት እንዲመሠርቱ ያድርጉ፡፡( ፈ፣ መ፣ አ፣ ገ፣ ጀ፣) በሌሎቹ ክፍለ ጊዜ ፊደላቱን በመቀያየር ያሠሯቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ፊደላትን የያዘ ሥዕላዊ ካርድ

**የምዘና ስልት፡** የተሰጣቸውን ፊደላት በትክክል መስራታቸውን ክትትል ማድረግ ፣ የቃል ጥያቄ ( ቃላትን እንዲመሰርቱ ማድረግ )

## የግል ስራ ሁለት: (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮች

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** ውድ መምህር! አስቀድመው ሁለት የቁስ ማስቀመጫ ዕቃ ያዘጋጁ፡፡ አንዱ ላይ ሰው ሠራሽ አንዱ ላይ ደግሞ ተፈጥሮ ብለው ይጻፉበትና ያሳዩአቸው፡፡ ሰው ሠራሽ ማለት ሰዎች የሠሩት እንደሆነ፣ ተፈጥሮ ማለት ደግሞ ሰው ያልሠራው አስቀድሞ የነበረ መሆኑን በመግለጽ ካዘጋጁት ቁስ ውስጥ ምሳሌ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ቁሱን ሲያዘጋጁ ዐውዱ መጓጓዣ ስለሆነ ቁሶቹን መጓጓዣ ለማድረግ ይሞክሩ፡፡ ያዘጋጁት ቁሳቁስ በየመቀመጫቸው ለመበተን ጥቂት ከሆነ በየተራ በማስወጣት ያሠሯቸው፤ ነገር ግን ቁሳቁሱ በቂ ከሆነ ለሁሉም ሕፃናት በየመቀመጫቸው ይስጧቸው፡፡ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ነገሮችን በማቀላቀል ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጡላቸው፡፡ ከዚያ ተፈጥሮአዊ ተፈጥሮ በሚለው ሳጥን/ፌስታል ውስጥ እንዲከቱ ሰው ሠራሽ ነገሮችን ደግሞ ሰው ሠራሽ በሚለው ሳጥን/ ፌስታል ውስጥ እንዲከቱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ሰው ሠራሽ ነገሮችን ምን ምን እንደሆኑና ከየት አንሥተው የት እንደከተቱ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠልም ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ምን ምን እንደሆኑና ከየት አንሥተው የት እንደከተቱ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ሲያሠሯቸው በሌላ ቁሳቁስ ያሠሯቸው በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን ቁሶችን በማየት ተፈጥሮአዊ ከሆኑ ከተፈጥሮ ጋር፤ ሰው ሠራሽ ከሆኑ ከሰው ሠራሽ ጋር ማገናኘትን ያሠሯቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ነገሮች በሥዕል የተዘጋጀ ወይም ሞዴል፣ የዕቃ መያዣ ፌስታል ወይም ከካርቶን የተዘጋጀ ሳጥን

**የምዘና ስልት፡** ሲሰሩ መመልከት፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሆኑ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በቃል መጠየቅ

## ተግባር ሁለት: ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ግብረ ገብነት

**የማስተማሪያ ዘዴ፦** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህሩ ተግባር ፦** ውድ መምህር! ሕፃናት የቀረበላቸውን ተረት በጥሞና እንዲያዳምጡ

በማድረግ ያዳመጡት ተረት ፍሬ ሐሳቦችን መልሰው እንዲገልጹ ያግዟቸው፡፡

**የተረቱ ርዕስ፡** የኤታ

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ የኤታ የተባሉ የዕድሜ ባለጸጋ አባት ነበሩ፡፡ ሁል ጊዜ በፈረስ በመምጣት የመንደሩን ሕፃናት በመሰብሰብ ፊደል ማስተማር ይወዳሉ፡፡ አንድ ቀን እንደ ለመዱት ፈረሳቸውን ዛፍ ላይ በማሰር ከዛፉ ሥር ሕፃናትን ሰብስበው እንዲህ እያሉ ማስተማር ጀመሩ፡፡

የኤታን ይማርን ሀጥሺ /2/
የኤታ/2/ ፊደል ሲያስቆጥሩን
ወዉ ፈፉፌፋ ሲሉ
የኤታን ይማርን ሀጥሺ /2/
የኤታ/2/ ጋቢያቸውን ለብሰው
ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው ፊደል ሲያስቆጥሩን
የኤታን ይማርን ሀጥሺ /2/

በማለት አስተምረው ሲጨርሱ በሉ “ፈጣሪ ወደ ቤታችሁ በሰላም ያግባችሁ ዕደጉ” በማለት መርቀው ሲጨርሱ ሕፃናቱ አሜን እያሉ ጉልበታቸውን ተሻምተው ስመው፤ ወደ ቤታቸው መሮጥ ጀመሩ፡፡ ሰላም ግን ሁልጊዜ የኤታ ፈረሳቸው ላይ ወጥተው እስከሚሄዱ ድረስ ትጠብቅ ነበር፡፡ የኤታ ፈረሳቸው ላይ ሲወጡ ከዘራቸው ከእጃቸው አምልጦአቸው መሬት ላይ ወደቀ፡፡ ከዘራውን ለማንሣት ሲያጎነብሱ ኮፍያቸው ከድንጋዩ ሥር ወደቀ፡፡ የኤታ አዘኑ ሰላም ሮጣ ከዘራቸውንና ኮፍያቸውን አውጥታ ሰጠቻቸው፡፡ የኤታም “መልካም ልጅ ነሽ እደጊ” ብለው መረቋትና አብረው ወደ መንደራቸው ጉዞ ጀመሩ፡፡ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን የግብረ ገብ መገለጫ ቃላትን ከሥዕላቸው ጋር ማያያዝን ያሠሯቸው፡፡ቀጥሎ በገፅ ላይ ያለውን የወ፣ የፈ፣ ቤተሰቦችን እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የፊደል ካርድ፣ ሥዕል

**የምዘና ስልት፡** ተረቱን በአጭሩ እንደገና እንዲናገሩ ማድረግ፣ የቃል ጥያቄ ( የፊደለትን ዘሮች መጠየቅ)

## ተግባር ሶስት: የክፍል ውስጥ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** አቅጣጫ፣ መረዳዳት፣ ተፈጥሯዊና ሰውሰራሽ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! ለሕፃናቱ ለምሳሌ ጠረጴዛና ወንበር የመሳሰሉት ስንገፋቸውና ስንጎትታቸው ወደፊት እና ወደኋላ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በዚህ መሠረት ክፍል ውስጥ ያሉ ቁሶችን በመጠቀም ወደ ተለያዩ ቦታዎች በማንቀሳቀስ አቅጣጫዎቹን እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡ ጠረጴዛና ወንበር ሲገፉ የክፍል ጓደኞቻቸውን እግር ወይም እጅ እንዳይቀረጥፉ መንገር፤ ተሳስተው ግን ከገፏቸው ወይም ከነኳቸው ይቅርታ እንዲጠይቁ፤ እንዲሁም መግፋት ያቃታቸውን ሕፃናት እንዲያግዟቸው ሌሎች ሕፃናትን መመደብ፤ ካገዟቸው በኋላ የምስጋና ቃላትን በመጠቀም እንዲያመሰግኑ ያድርጉ፡፡ የሚገፏቸውን ቁሶች “ሰው ሠራሽ” ወይም “ተፈጥሮ” እያሉ እንዲመድቡ ይዘዟቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ወንበርና ጠረጴዛ፣

**የምዘና ስልት:** ተግባሩን በትክክል መስራታቸውን መመልከትና የቦታን አቅጣጫ በቃል መጠየቅ

## ተግባር አራት: የክፍል ውጭ ጨዋታ አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** አቅጣጫ፣ ግብረ ገብነት፣ ተፈጥሯዊና ሰውሰራሽ ነገሮች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! በሕፃናቶቹ ልክ ትናንሽ የመኪና ጎማዎችን ያዘጋጁ፡፡ ከዚያም ወደ ውጭ በማስወጣት ጎማውን እንደ መኪና እየነዱ ወደ ፊትና ወደ ኋላ በመንዳት አካባቢያቸውን እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ ሲነዱ ጎማቸው ከሌላ ሕፃን ጋር ከተገጫጨ ይቅርታ እንዲጠያየቁ ያለማምዷቸው፡፡ ከዚያም አንድ ቦታ ላይ በመሰብሰብ ምን ምን ዓይነት ቦታ እንዳዩ፤ ከተቀመጡበት ቦታ አንጻር በየትኛው አቅጣጫ እንዳዩና ያዩት ነገር ተፈጥሮአዊ ወይስ ሰው ሠራሽ እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ተፈጥራዊና ሰው ሠራሽ ቦታዎችን በመለየት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ሥዕል ወይም ቪድዮ በመጠቀም ተፈጥሯዊ የሚባሉት ገዳማት፣ ተራሮች፣ ትላልቅ ጫካዎች፣ ትላልቅ ሐይቆችና የመሳሰሉት መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ያድርጉ፡፡ ሰው ሠራሽ የሚባሉት ደግሞ የተለያዩ መዝናኛ ቦታዎችን፣ የተለያዩ ሐውልቶች፣ ሕንጻዎችና የመሳሰሉት መሆናቸውን በማሳየት እነሱን ደግመው እንዲሥሉት ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ሰው ሠራሽ እና ተፈጥራዊ ቦታዎች የሚያሳይ ሥዕሎች እና ሞዴሎች፣ ቪዲዮ፣ ትናንሽ የመኪና/የባጃጅ ጎማዎች

**የምዘና ስልት:** ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ ቦታዎችን በቃል መጠየቅ፣ ተግባራቱን ሲሰሩ ምልከታ ማድረግ

### የክፍል ውጭ ጨዋታ ሁለት (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ግብረ ገብ፣ ቃላት መመስረት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናቱን ወደ ደጅ በማስወጣት አንድ ትልቅ ክብ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የግብረ ገብ እሴት መገለጫ የሆኑ ቃላት የመጀመሪያ ሆሄያትን እና ቃላቱን በካርድ ላይ በመጻፍ ያዘጋጁ፡፡ ከክፍል ውጪ ሜዳ ላይ ሦስት ትልልቅ ክብ/ጎማ ያዘጋጁ፡፡ ከዚያም 6 ሕፃናት በመምረጥ ካዘጋጁት ፊደል አንድ አንድ ይስጧቸው፡፡ በአንድ ክብ/ጎማ ሁለት ሕፃናት በመመደብ ከክቡ/ከጎማው አጠገብ ፊደሉን ይዘው ይቁሙ፤ አንዱ ሕፃን እንዲጀምር ያድርጉ፤ የሚጀምረው ሕፃን ክብ ለሠሩት ሕፃናት ፊደሉን ከፍ አድርጎ ሲያሳዩአቸው፡፡ እነሱም በዜማ "መ" ፊደል "መ" ፊደል ወደዚህ መጣች/2/ ሲሉ (መ "መፋቀር"፣ መ "መፋቀር") እያለ ሕፃኑ ዘሎ ይገባል፡፡ ቀጥሎ ያለው ሕፃንም ፊደሉን ያሳያል፤ አሁንም ክብ የሠሩት ሕፃናት "መ" ፊደል "መ" ፊደል ወደዚህ መጣች/2/ ሲሉ (መ "መከባበር" መ "መከባበር") እያለ ሕፃኑ ዘሎ ይገባል፣ ቀጥሎ ያለው ሕፃንም ፊደሉን ያሳያል፡፡ አሁንም ክብ የሠሩት ሕፃናት "መ" ፊደል "መ" ፊደል ወደዚህ መጣች/2/ ሲሉ (መ "መዋደድ" መ "መዋደድ" ) እያለ ሕፃኑ ዘሎ ይገባል፣ ቀጥሎ ያለው ሕፃንም ፊደሉን ያሳያል

አሁንም ክብ የሠሩት ሕፃናት “መ” ፊደል “መ” ፊደል ወደዚህ መጣች/2/ ሲሉ (መ “መተጋገዝ” መ “መተጋገዝ” )እያለ ሕፃኑ ዘሎ ይገባል፣ ቀጥሎ ያለው ሕፃንም ፊደሉን ያሳያል አሁንም ክብ የሠሩት ሕፃናት “መ” ፊደል “መ” ፊደል ወደዚህ መጣች/2/ ሲሉ (መ “መካፈል” መ “መካፈል” )እያለ ሕፃኑ ዘሎ ይገባል፣ ቀጥሎ ያለው ሕፃንም ፊደሉን ያሳያል አሁንም ክብ የሠሩት ሕፃናት “መ” ፊደል “መ” ፊደል ወደዚህ መጣች/2/ ሲሉ (መ “መወያየት” መ “መወያየት”) እያለ ሕፃኑ ዘሎ ክቡ ውስጥ ይገባል፡፡ ከዚያም እነዚህ ፊደላት “ከክቡ በየት በኩል ይገኛሉ?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡ በክቡ ውስጥ ካሉ በመቀጠል እነሱ ይወጡና ሌላ ተማሪ ደግሞ እንዲሁ እያሉ ጨዋታው ይቀጥላል፡፡ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያሉትን ሠ፣ዐ፣ፀ፣ ፊደላት ተጠቅመው ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የፊደልና የቃላት ካርድ

**የምዘና ስልት፡** ቃላት በትክክል መመስረታቸውን መከታተል፣ ቃላት እንዲመሰርቱ በቃል መጠየቅ

### ተግባር አምስ: በፕሮጀክት መማር ( 2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፦** መምህር! ለሕፃናት ስለ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ያስታውሷቸው፡፡ ከዚያም በቡድን በመሆን ወደ ውጪ በማስወጣት አካባቢያቸውን እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ ያዩትን ነገር አስመስለው እንዲሠሩና የሣሉትን ነገሮች ስያሜ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለ ቀለም እርሳስ

**የምዘና ስልት፡** በትክክል ስዕሉን መሳላቸውን መከታተል፣ በአካባቢያቸው ያዩትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮዊ ነገሮችን መጠየቅ

## ስድስተኛ ሳምንት

### ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ ፡ 30 ክ/ጊዜ /15 ሰዓት/

### አጥጋቢ የመማር ብቃት፡

- ✓ የውሳኔ ሰጭነት ችሎታቸውን ያሳያሉ፡፡
- ✓ በእለት ተእለት ተግባራቸው ቀላል ችግሮችን ይፈታሉ፡፡
- ✓ የሀገር ወዳድነት ስሜትን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ ፊደላትን በቅደምተከተል ማንበብና መፃፍ ይችላሉ፡፡
- ✓ ባህላዊ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ ቅርፆችን ይለያሉ፡፡
- ✓ የደኅንነትና ጥበቃ መርሆዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮች በመጠቀም መሠረታዊ የሂሳብ ስሌቶችን ያሰላሉ፡፡

- ✓ የኢትዮጵያን ገንዘብ ኖት ዋጋ ያውቃሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፦** የውሳኔ ሰጭነት ክህሎት፣ ሀገር ወዳድነት፣ ቅርፆች፣ ማኅበራዊ ግንዛቤ፣ የምት እንቅስቃሴዎች፣ ማንበብና መጻፍ፣ ደኅንነት እና ጥንቃቄ፣ መደመር እና መቀነስ፣ ገንዘብ፣


## ተግባር አንድ: የግል ተግባር (8 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቅርፅ፣ ሰንደቅ አላማ፣ ቀለም

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ይህ ክፍለ ጊዜ ሕፃናት የግል ሥራ የሚሠሩበት መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡ ለሕፃናት እርሳስ፣ ወረቀት፣ ባለ ቀለም ወረቀት በማዘጋጀት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ፊት ለፊታቸው በመስቀል እያዩ እንዲሥሉና እንዲያቀልሙ ያድርጉ፡፡ ከዚያም በሰንደቅ ዓላማዋ ላይ ያሉት ቅርፆችን በመለየት እንዲሥሉና የቅርጻቸውን ዓይነት እንዲጽፉ ያሳዩአቸው፡፡

**ምሳሌ:** ሰንደቅ ዓላማዋ አራት ማዕዘን ነች፤ መሀል ላይ ደግሞ የኮከብ ቅርፅና ኮከቡ ያረፈበት ደግሞ ክብ ቅርፅ አለው፡፡ ስለዚህ ሦስቱን ቅርፆች በመሣል ስማቸውን እንዲጽፉና የጻፉትን ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡



ኮከብ ቅርፅ ጎነ አራት ክብ

በመጨረሻም የሣሉትን ሰንደቅ ዓላማ እያሳዩ ሀገራቸው ማን እንደሆነች፣ የት እንደሚኖሩ፣ እነሱ የኢትዮጵያ እንደሆኑ፤ ኢትዮጵያ ደግሞ የሁላችንም እንደሆነች፤ ኢትዮጵያ ሀገራቸውን እንዴት እንደሚወዷት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ኢትዮጵያን የሚወዳት ይነሣና እንዘምርላት በማለት

ባንዲራችን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ
አርማችን ነው መለያችን
የኢትዮጵያ ሀገራችን
ባንዲራችን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም ወረቀት፣ የሰንደቅ ዓላማ ምስል፣ የኢትዮጵያ ካርታ ሥዕል

**የምዘና ስልት:** ሲሰሩ በመመልከት፣ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማትን፣ ቅርፅን እንዲናገሩ በቃል መጠየቅ

## ተግባር ሁለት: መዝሙር አንድ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መደመር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር! ክፍለ ጊዜው የመዝሙር እንደሆነ ይግለጹላቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን መዝሙር ምቱን ተከትለው ከእርስዎ በኋላ እንዲዘምሩ በማድረግ ስንኞቹንና ዜማውን ያለማምዷቸው፡፡

**መኪና**

ሁለት መኪና ነበረኝ፣
አንድ ስጨምር ይሆናል ሦስት፣
ሦስት መኪና ነበረኝ፣
አንድ ስጨምር ይሆናል አራት፣
አራት መኪና ነበረኝ፣
አንድ ስጨምር ይሆናል አምስት፣
አምስት መኪና ነበረኝ፣
አንድ ስጨምር ይሆናል ስድስት፣
ስድስት መኪና ነበረኝ፣
አንድ ስጨምር ይሆናል ሰባት፣
ሰባት መኪና ለኔ ብዙ ነው
አብረን እንንዳ ተከፋፍለነው

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የተለያዩ የመኪና ብዛቶችን የያዘ ምስል፣ የቁጥር ካርድ
**የምዘና ስልት፡** መዝሙሩን ሲዘምሩ መመልከት፣ ቀላል ቁጥሮችን እንዲደምሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ

## መዝሙር ሁለት (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** መቀነስ
**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ
**የመምህር ሚና ፡** መምህር! እባክዎትን ክፍለ ጊዜው የመዝሙር እንደሆነ ይግለጹላቸው:: ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን መዝሙር ምቱን ተከትለው ከእርስዎ በኋላ እንዲዘምሩ በማድረግ ዜማና ስንኞቹን ያለማምዷቸው፤

**ክብ ሲኒዎች**

ሰባት ክብ ሲኒዎች ጠረጴዛ ላይ፣
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ስድስት ይቀራል?
ስድስት ክብ ሲኒዎች ጠረጴዛ ላይ፣
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አምስት ይቀራል?
አምስት ክብ ሲኒዎች ጠረጴዛ ላይ፣
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አራት ይቀራል?
አራት ክብ ሲኒዎች ጠረጴዛ ላይ፣
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሦስት ይቀራል?
ሦስት ክብ ሲኒዎች ጠረጴዛ ላይ፣
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሁለት ይቀራል?
ሁለት ክብ ሲኒዎች ጠረጴዛ ላይ፣
ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አንድ ይቀራል?

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡** የሲኒ ስዕል/ሞዴል፣ የተለያዩ ቆርኪዎች፣ ጠጠር ወይም ትናንሽ ድንጋዮች፣ የቁጥር ካርድ

**የምዘና ስልት:** ሲዘምሩ መመልከት፣ ቀላል ቁጥሮችን እንዲቀንሱ በቃል መጠየቅ

## ተግባር ሶስት: የክፍል ውስጥ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት :** ቅርፅ፣ የብር ኖት፣ መገበያየት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናትን በክፍላቸው ውስጥ በቡድን በመከፋፈል ያስቀምጧቸው፡፡ በተቀመጡበት ጠረጴዛ ላይ እርስ በእርስ ገዥና ሻጭ በመሆን እንዲጫወቱ የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ቁሳቁስ፣ እስከ ሃያ ብር ድረስ የመገበያያ ሞዴል የብር ኖት ፣ ሞዴል ዕቃ መጫኛ መኪና ይስጧቸው፡፡ ከዚያ ሻጭ ሆኖ የሚሠራው ዕቃውን በመኪናው እንደ መጫን አድርጎ ይገለብጣል፡ መኪናው እንዳይገጫቸውና ዕቃው ሲገለበጥ እጃቸውን እንዳይመታቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይንገሯቸው፡፡ ከተገለበጠ በኂላ ሌሎቹ ከተገለበጠው ቁስ ውስጥ የፈለጉትን በመምረጥ ዋጋውን እንዲጠይቁና እንዲከፍሉ መልስ ካላቸው መልሳቸውን አስበው እንዲቀበሉ ዕቃው ተሸጦ ካለቀ በኂላ የገዙትን ዕቃዎች ስም ዝርዝር በደብተራቸው እንዲመዘግቡና ምን ዓይነት ቅርፅ እንዳላቸው እንዲሥሉ ያድርጉ፡፡ ሲጨርሱ የጻፉትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ጮክ ብለው እንዲያነቡና የቅርጾቹን ሥዕሎችን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡ በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ሻጭ የነበረው ገዥ እንዲሆን እንዲቀያየሩ ድርጉ፡፡ በመጨረሻም ለመገበያት ስንት የገንዘብ መጠን እንደ ተጠቀሙ፤ የነበራቸው ገንዘብ ስንት እንደ ነበር ከነበራቸው ገንዘብ ውስጥ ምን ያህሉን ተጠቅመው ስንት እንደቀራቸው ይጠይቋቸው፡፡ የወረቀቱ ብር ምን ዓይነት ቅርፅ እንዳለው የሳንቲሙ አንድ ብር ምን ዓይነት ቅርፅ እንዳለው በማሳየት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም መሠረታዊ ቅርፆችን በሥዕል በማሳየት ያላቸውን ቅርፅ ደጋግመው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በመለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን ቁጥሮችን መቀነስ ያሠሯቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፡** የተለያዩ ቁሳቁሶች፣ የመኪና ሞዴል፣ እርሳስ፣ ባለ ቀለም እርሳስ፣ የተለያዩ መሠረታዊ ቅርፆች ሥዕል/ቪድዮ/ሞዴል፣ የመገበያ ገንዘብ

**የምዘና ስልት:** ሲጫወቱ መመልከት፣ ምንእንደሸጡና እንደገዙ በቃል መጠየቅ

## ተግባር አራት: የክፍል ውጭ ጨዋታ (5 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ዘፈኖች፣ ቅርፆችን መለየት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናቱን ወደ ውጭ በማስወጣትና በመጀመሪያ በአካባቢዎ የተለመዱ ባህላዊ ዘፈኖችን በስልክዎ በመክፈት በማሰማት እንዲጨፍሩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠልም ቀላል የተሽርካሪ ቅርፃችን ለምሳሌ ለመኪናዎች አራት መዓዘን፣ ለአውሮፕላን ሦስት መዓዘን፤ ለሞተር ክብ ቅርፃች መነሻ መሆናቸውን እንዲረዱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ጠመኔ በመጠቀም እነዚህን ቅርፃች መሬት ላይ ይሣሉ፡፡ ሕፃናቱን በቡድን በመክፈል አንዳንድ ዳኛ በመምረጥ የክፍያ ካርድና ገንዘብ በማዘጋጀትና ገንዘብ ተቀባይ፣ አሽከርካሪ በመምረጥ ወደ መኪናው፣ አውሮፕላኑ፣ ወደ

ሞተሩ ቅርፅ ለመግባት እንዲከፍሉና ትኬት በመቀበል እንዲሳፈሩ ያድርጉ፡፡ ነገር ግን ሲሳፈሩ የቅርፆቹን መስመር ከረገጡ አደጋ ውስጥ ስለሚገቡ እንዲጠነቀቁ ይንገሯቸው፡፡ ሕጎቹን በደንብ ካሳወቁ በኋላ እርስዎ ለዳኞቹ በመተው በዝምታ በመከታተል እርስ በእርሳቸው እንዲጫወቱ ያድርጉ:: ዳኞቹም ሕጉን ተከትለው ከጨዋታው እንዲወጡ ወይም እንዲቀጥሉ ውሳኔ እንዲሰጡና የእርስ በእርስ ችግራቸውን በመነጋገር እንዲፈቱ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ከጨዋታው ፍጻሜ በኋላ በጨዋታው ውስጥ ያጋጠማቸው ችግር ምን እንደሆና እንዴት እንደ ፈቱት፤ ምን ዓይነት ቅርፅ ባለው መጓጓዣ እንደ ተሳፈሩ፣ ስንት እንደከፈሉና ወደ መጓጓዣው ሲገቡና ሲወጡ ምን ዓይነት ጥንቃቄ እንዳደረጉ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** ጠመኔ፣ ትኬት፣ ገንዘብ

**የምዘና ስልት:** ሲጫወቱ መመልከት፣ የቃል ጥያቄ (ችግሮች ሲያጋጥሙ በምን መልኩ መፍታት እንዳለባቸው ይጠይቆቸው)

## ተግባር አምስት: ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ሀገርን መውደድ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፦** ውድ መምህር! ለሕፃናቱ በሥዕል በማስደገፍ የሚቀጥለውን ተረት ይንገሯቸው::

**የተረቱ ርዕስ:** ትንሻ ቡጡ

ትንሻ ቡጡ ዕድሜዋ 7 ሲሆን የደረጃ ሦስት ተማሪ ነች፡፡ ሀገሯን በጣም ትወዳለች፡፡ “ተምሬ አውሮፕላን አብራሪ በመሆን ሀገሬን በታማኝነት አገለግላለሁ፡፡” እያለች ለክፍል ጓደኞቻ ትነግራቸዋለች፡፡ የክፍል ጓደኞቻም በጣም ይገረማሉ፡፡ አንድ ቀን ቡጡ አዲስ ሰንደቅ ዓላማ ይዛ ወደ ትምህርት ቤት መጣች፡፡ ጓደኞቿም ከየት እንዳመጣችው ጠየቋት፡፡ እሷም “አጎቴ ለልደቴ አምስት ብር ሰጠኝ፣ አክስቴ ደግሞ ሌላ አምስት ብር ሰጠችኝ፡፡ አሥር ብር ሲሆንልኝ ከእናቴ ጋር ሄጄ ይህችን ሰንደቅ ዓላማ ገዛሁ፡፡” አለቻቸው፡፡ እነሱም “አስነኪን፣ አስነኪን” አሏት፡፡ ቡጡም እንዲነኩት ፈቀደችላቸው፡፡ እርስ በእርስ ሰንደቅ ዓላማዋን ሲነጣጠቁ ቡጡ ተመለከተች፡፡ ድምጿን ጮክ አድርጋ እንዲህ አለቻቸው፡፡ “ይህች ሰንደቅ ዓላማ የሁላችንም ነች፤ ልንጠብቃትና ልንከባከባት ይገባል፡፡ አልያ ግን ልትቀደድና ልትበላሽብን ትችላለች፡፡ ስለዚህ ለመምህርት እንስጣት እሷ ክፍላችን ውስጥ ትሰቅልልናለች፡፡” አለቻቸው፡፡ እነሱም “እሺ እሺ” በማለት ሰንደቅ ዓላማዋን ይዘው ወደ መምህርታቸው ሄዱ፡፡ መምህርቷም ሰንደቅ ዓላማዋን እጅ ነስታ ተቀብላ ክፍላቸው ውስጥ በመስቀል “ውቧ ሀገሬን” የሚለውን በከፍታ ድምፅ እንዲዘምሩ አደረገቻቸው፡፡ እነሱም በታላቅ ስሜት ከሙዚቃው እኩል በመንቀሳቀስ ዘመሩ፡፡ መምህር በመማመጃ ደብተር ገጽ ላይ ያለውን የብር ኖቶችን ከመጠናቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫወቻ ቁሳቁስ፦** የኢትዮጵያ ብር ኖቶች፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ውብ ሀገሬ ዜማ፣ ፍላሽ

**የምዘና ስልት:** ተረቱን እንደገና በአጭሩ እንዲናገሩ ማድረግ፣ ቡጡ ምን ገዛች፣ በስንት ብር በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

# የአውድ ማጠቃለያ ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም_________________________________ጾታ_______እድሜ_______ደረጃ_______

**መግለጫ:** ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "✓" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ።

| ተ.ቁ. | የመማር ውጤቶች | የምልከታ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | ጥሩ | በ.ጥሩ | እ.በ.ጥሩ |
| 1 | ማኀበራዊ ክህሎት አጎልብተዋል። | | | | |
| 2 | የሀገር ወዳድነት ስሜትን አዳብረዋል። | | | | |
| 3 | በመንቀሳቀስና በቦታ ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ክህሎት አዳብረዋል። | | | | |
| 4 | ሰዓት ለይተው መናገር ችለዋል። | | | | |
| 5 | ከመማር ይዘቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለያዩ ሥነ ጥበባዊ ተግባራትን በመሥራት ይዝናናሉ። | | | | |
| 6 | የኢትዮጵያን የብር ኖቶች ለይተዋል። | | | | |
| 7 | አናባቢና ተነባቢዎችን ማንበብና መፃፍ ችለዋል። | | | | |
| 8 | ቁጥሮችን በመለየት መቁጠር ችለዋል ። | | | | |
| 9 | የነገሮችን ቅጥ /ሥረዓተ ጥለት/ በመጠበቅና በመለየት መመደብ ችለዋል። | | | | |
| 10 | የቅርብ አካባቢያቸውን በመለየት ይጠብቃሉ። | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻም፦_________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

# ዐውድ ሰድስት፡ ባህል

አጠቃላይ ለዐውዱ የተቀመጠው ሳምንትና ሰዓት፡ 5 ሳምንት/ 150 ክፍል ጊዜ

## 7.1. መግቢያ

ባህል የአንድ ሀገር ወይም የአንድ አካከቢ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች መኖሪያ ከመሆኗም በላይ የተለያዩ ባህሎች ያሏት ሀገር ናት፡፡ በሀገራችን ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች የየራሳቸው መገለጫ የሆነ ባህላዊ ክዋኔ፣ ጭፈራ፣ ሽለላ፣ ቀረርቶ፣ አልባሳት/አለባበስ፣ ቁሳቁስ፣ ምግብ፣ ቅርሶችና ሌሎችም በስፋት ይገኛሉ፡፡ ይህ የባህል ልዩነትም የውበታችን መገለጫ ነው፡፡ በመሆኑም በእየአንዳንዱ ባህል ውስጥ ማህበረሰቦች ማድረግ ያለባቸውና የሌለባቸው ነገሮች፣ ማኅበራዊ ግንኙነታቸው ምን መምሰል እንዳለበት፣ እንዴት መረዳት እንዳለባቸው፣ ጎጅና ጠቃሚ ልማዶች፣ ወዘተ. የመሳሰሉ ሁኔታዎችን ያካተተ ነው፡፡ ስለሆነም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ሦስት ሕፃናት ይህንን መማራቸው በደረጃቸው ስለሀገራቸው እንዲያውቁ፣ የሀገር ፍቅር እንዲያጎለብቱ፣ በመካከላቸው ልዩነት መኖሩን ተገንዝበው የሌሎችን ማንነት እንዲያከብሩ፣ ማድረግ ያለባቸውንና የሌለባቸውን እንዲለዩና ከባህል ጋር ተያያዥ ሆኑ ሌሎች ሁኔታዎችን ተረድተው ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲዘጋጁ ያስችላቸዋል፡፡

## 7.2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ሕፃናት ይህንን ዐውድ ከተማሩ በኋላ፡

- ✓ ማኅበራዊ ክህሎት ይኖራቸዋል፡፡
- ✓ ስሜታቸዉንና ፍላጎታቸዉን በራስ መተማመን ይናገራሉ፡፡
- ✓ ጤናንና ደህንነትን ለመጠበቅ መሰረታዊ የግል ንፅህና መመሪያዎችንና የደህንነት ክህሎቶችን ይተገብራሉ፡፡
- ✓ የቅርብ አካባቢያቸዉን መጠበቅ ይችላሉ፡፡
- ✓ ከመማር ይዘቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለያዩ ሥነጥበባዊ ተግባራትን በመስራት ይዝናናሉ፡፡
- ✓ ቃላቶችን ያነባሉ፣ ይፅፋሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

## 7.3. አበይት ይዘቶች

ባህል በሚለው የመማር ዐውድ ስር የሚከተሉት የትምህርት ይዘቶች ተካተዋል፡፡

- ራስን ማስተዋወቅ፣
- ራስን ማወቅ፣
- የአካል ክፍሎች፣
- ጤና፣
- ቁጥር መቁጠር፣
- የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣
- ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣
- ባህላዊ ቅርሶች፣
- ማኅበራዊ ግንዛቤ፣
- ራስን መግለፅ፣

- ጥበባዊ ገለፃ/አገላለፅ፣
- ራስን መቆጣጠር፣
- ድምፅ መለየት፣
- የቅርብ አካባቢ፣
- ስርዓተ ምግብ፣
- ቁጥሮችን መፃፍ፣
- በፈጠራ ስራ መግለፅ/ በፈጠራ መግለጽ/፣
- ራስን መቻል፣
- ቃላት፣
- የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣
- ቅጥ፣
- ጥበባዊ እሴት፣
- የግንኙነት ክህሎት፣
- የግብረ ገብ እሴት፣
- የፊደላት ድምፅ ግንዛቤ፣
- ሰውሰራሽና ተፈጥሯዊ አካባቢ፣
- የቦታ ግንዛቤ፣
- መመደብና መደርደር/ማስቀመጥ

## 7.4. የማስተማሪያ ዘዴዎች

በዚህ ዐውድ ሥር የግልና የቡድን ተግባር/ሥራ፣ የክፍል ውስጥና ውጭ ጨዋታ፣ መዝሙር፣ ተረት፣ የመስሎ ጨዋታ፣ የፕሮጀክት ሥራ፣ የመስክ ጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ፣ ወዘተ. ዘዴዎችና በተጨማሪም የመለማመጃ ደብተር ተግባራት ተመራጭ ዘዴዎች ተደርገው የተካተቱ ናቸው፡፡

## 7.5. የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁሶች

ይህንን ዐውድ ግልፅ፣ ቀላል፣ አይረሴና የማይሰለች አድርጎ ለህፃናት ለማቅረብ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን፣ አልባሳትን፣ ቁሳቁሶችን፣ ምግቦችን፣ ጭፈራዎችን፣ መዝሙሮችንና ሌሎችንም የያዙ ሥዕሎች፣ ፖስተሮች፣ ፍለሽ ካርዶች፣ የድምፅ ቅጅዎች፣ የቪድዮ ምስሎች፣ ሞዴሎች፣ እውነተኛ ቁሳቁሶች፣ ሙዚየሞች፣ እንዲሁም ካርቶን፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ላፒስ፣ ማስመሪያ፣ ቀለም፣ ጠጠር፣ ብይ፣ ትናንሽ እንጨቶች፣ የጫማ ሶል፣ ትንንሽ ድንጋዮች፣ የእንሥራ ስባሪ፣ ገመድ፣ ሳሙና፣ ውሃ፣ የብር ኖቶች፣ ኳስ፣ ገበጣ የመሳሰሉት ተካተዋል፡፡

## 7.6. የምዘና ስልቶች

ሕፃናት ይህንን ዐውድ በትክክል መረዳታቸውን/መገንዘባቸውን ለማረጋገጥ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ፣ ሪፖርት/ዘገባ በማስቀረብ፣ በተግባር ሲሠሩ በማየት/በመመልከት፣ ዕለታዊ የባሕርይና የምልከታ ቅጾችን በመጠቀምና በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ የተቀመጠውን ተግባር መሥራታቸውን በመከታተልና ደብተራቸውን በማረም ወዘተ. ስልቶች የተካተቱ ቢሆንም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡

# አንደኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፣ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት

## አጥጋቢ የመማር ብቃት:

- ✓ ስለባህል የሚያውቁትን/ያላቸውን ልምድ ለጓደኞቻቸው ያካፍላሉ፡፡
- ✓ በራስ የመተማመን ስሜታቸዉን ያዳብራሉ፡፡
- ✓ የግልና የአካባቢ ንፅህናቸዉን ይጠብቃሉ፡፡
- ✓ ስለ ግል ፍላጎታቸዉ በራስ መተማመን ስሜት ይናገራሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ስሜታቸውን በስነ ጥበብ አማካኝነት ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ትምህርትን በስነ ጥበብ በመማር ይደሰታሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች:** ራስን ማስተዋወቅ፣ ራስን ማወቅ፣ የአካል ክፍሎች፣ ጤና፣ ቁጥር መቁጠር፣ ጥበባዊ ገለፃ/አገላለፅ

## ተግባር አንድ: ውይይት አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ራስን ማስተዋወቅ፣ የባህል ትውውቅ፣ ቁጥር መለየት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በውይይት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር፣ ባህል የሚለውን ዐውድ ከማስተማርዎ በፊት የተለያዩ ባህላዊ ክንዋኔዎችን፣ አልባሳትን፣ ቁሳቁሶችንና ሌሎች ባህልን የሚገልፁ ነገሮችን በሥዕል፣ በፖስተር፣ በሞዴልና እውነተኛ ቁሳቁሶችን በማዘጋጀትና በመሰብሰብ የመማሪያ ክፍሉን ሳቢና ማራኪ ያድርጉት፡፡

በመጀመሪያም ከዚህ በፊት የተማሩትን ዐውድ ማለትም ትራንስፖርትን ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ ሕፃናትን የቃል ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡

### የቃል ጥያቄዎች

- ➢ የምታውቋቸውን የትራንስፖርት ዓይነቶች ተናገሩ?
- ➢ በአከባቢያችሁ የሚገኙ የትራንስፖርት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

በመቀጠል ሕፃናትን በትናንሽ ቡድን ማለትም (ከ4 6) በማድረግ ያደራጇቸውና እያንዳንዳቸው እራሳቸውንና ባህላቸውን እንዲያስተዋውቁ ያድርጓቸው፡፡

**ምሳሌ:** ስም፣ ዕድሜ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን ባህላዊ ቁሳቁሶች፣ አልባሳት፣ ምግቦች፣ ክዋኔዎች፣ ቁጥሮች፣ ወዘተ. በመቀጠልም ያስተዋወቋቸውን ባህላዊ ሁኔታዎች በክፍል ውስጥ ከተደራጁት ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም በየቡድናቸው የተወያዩትን ለክፍሉ ሕፃናት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን፣ አልባሳትን፣ ምግቦችንና ቁሳቁሶችን የያዘ ሥዕል፣ ሞዴል፣ ፖስተር፣ እውነተኛ ቁሳቁስ፣ ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** በየቡድናቸው እራሳቸውን ሲያስተዋውቁ መመልከት፣ የውይይት ሂደት ብስለታቸዉን መመዘን፣ የቃልጥያቄ መጠየቅ ለምሳሌ: ስማቸውን፣ ዕድሜአቸውን፣ የቤተሰባቸውን ብዛት፣ ወዘተ.

### ውይይት ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ዘፈን፣ ጭፈራ፣ መዝሙር፣ የባህል ትውውቅ፣ ቁጥር መለየት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በውይይት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር ሕፃናትን በትናንሽ ቡድኖች በማደራጀት (ከ4 6) አባላትን የያዘ በማድረግ በአካባቢያቸው የሚያውቁትን ባህላዊ ዘፈን፣ ሙዚቃ፣ መዝሙር በየቡድናቸው እንዲወያዩና በቁጥር ስንት እንደሆኑ እንዲናገሩ ያድርጉ። በመቀጠልም በየቡድናቸው የተወያዩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸውና በየትኛው ባህላዊ ክዋኔ ጊዜ የሚዘፈን ወይም የሚዘመር እንደሆነ፣ በቡድናቸው ውስጥ ስንት ባህላዊ ዘፈኖች/መዝሙሮች እንዳቀረቡ እንዲናገሩና በክፍል ውስጥ ከተለጠፉት/ከተዘጋጁት ባህላዊ ክዋኔዎች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን፣ አልባሳትን፣ ምግቦችንና ቁሳቁሶችን የያዘ ሥዕል፣ ሞዴል፣ ፖስተር፣ እውነተኛ ቁሳቁስ፣ ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** በየቡድናቸው ተዟዙሮ ሲወያዩ መመልከት፣ ማዳመጥና የቃል ጥያቄ መጠየቅ

**የቃል ጥያቄዎች**

- በቡድናችሁ ውስጥ ስንት ባህላዊ ዘፈኖች/መዝሙሮች ቀረቡ?
- የቀረቡት ባህላዊ ዘፈኖች/መዝሙሮች በየትኛው ባህላዊ ክዋኔ ጊዜ የሚቀርብ ነው?

## ተግባር ሁለት: የክፍል ውጭ ጨዋታ አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ስሜትን መግለፅ፣ ራስን ማወቅ፣ ባህላዊ ዘፈን፣ በራስ መተማመን

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር እርስዎ የሚያውቁትን አንድ ባህላዊ ዘፈን/መዝሙር በመዝፈን/በመዘመር ሕፃናትን ካነቃቋቸው በኂላ አሰልፈው ወደ ውጭ ይዘዋቸው በመውጣት በትናንሽ ቡድኖች ይክፈሏቸው። በመቀጠልም ሕፃናቱ በየቡድናቸው ሆነው የሚያውቁትን ባህላዊ ጭፈራዎች፣ ዘፈኖች/መዝሙሮች እንዲጫወቱ በማድረግ እርስዎም እየተዘዋወሩ ድጋፍና ክትትል በማድረግ አብረዋቸው ይጫወቱ፤ በመጨረሻም ምን እንደተሰማቸው ስሜታቸውን እንዲናገሩ ያድርጓቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን የሚገልፁ ጭፈራዎች፣ ዘፈኖች/መዝሙሮች

**የምዘና ስልት:** ሕፃናት በየቡድናቸው ሲጫወቱ ተዟዙሮ መመልከት፣የቃልጥያቄ(ምንምን ባህላዊ ዘፈኖችን ዘፈናችሁ የትኛዉን ወደዳችሁት)

## የክፍል ውጭ ጨዋታ ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ራስን ማወቅ፣ ባህላዊ አለባበስ፣ በራስ መተማመን፣ ባህላዊ ክዋኔ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በዚህ ተግባር ሕፃናትን ከክፍል ውጭ ይዞ በመውጣትና በቡድን በማደራጀት የየራሳቸውን ባህል የሚያስተዋውቁ ባህላዊ አለባበሶችን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም በየቡድናቸው ያቀረቧቸውን ባህላዊ አለባበሶች አጠቃላይ ለክፍል ሕፃናት ተራ በተራ እየወጡ እንዲያሳዩ ያድርጓቸውና ስንት ዓይነት ባህላዊ አለባበሶችን እንዳቀረቡ፣ በየትኛው ባህላዊ ክዋኔ ጊዜ የሚለበስ እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም ከሕፃናት መለማመጃ ደብተር ገጽ ላይ የተቀመጠውን ባህላዊ አልባሳት ስም ይጻፉ የሚለውን ተግባር ቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን የሚገልፁ አልባሳት

**የምዘና ስልት:** ባህላዊ አለባበሶችን ሲያቀርቡ መመልከት፣ ቀል ጥያቄ መጠየቅ

**የቃል ጥያቄዎች**

- ስንት ዓይነት ባህላዊ አለባበሶችን ተመለከታችሁ?
- በየትኛው ባህላዊ ክዋኔ ጊዜ ይለበሳል?

## ተግባር ሦስት: በሥራ መማር አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ምግብ፣ ቁጥር፣ ንፅህና

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናትን ከክፍል ውጭ ይዞ በመውጣት የተለያዩ ባህላዊ ምግቦችን እንዲያዘጋጁ በቡድን ያደራጇቸውና እርስዎም እየተዘዋወሩ ለሁሉም ቡድን እገዛ ያድርጉላቸው:: በመቀጠልም ሁሉም ቡድኖች ያዘጋጇቸውን ባህላዊ ምግቦች ቁጥር/ተራ ቁጥር/ በመስጠት እንዲያስቀምጧቸው ያድርጉና ሁሉም ቡድኖች ቁጥር ሲጠራ በቁጥሩ ውክልና የሰጡትን ባህላዊ ምግብ ለክፍሉ ሕፃናት እንዲያሳዩ በማድረግ በየትኛው ባህላዊ ክዋኔ እንደሚቀርብ እንዲናገሩ/ እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም አመጋገቡ እንዴት እንደሆነ ማለትም ምግብ ከመመገባቸው በፊትና በኋላ እጃቸውን እንዴት እንደሚታጠቡ፣ የመመገቢያ ዕቃዎችንና የመመገቢያ ክፍሎችን እንዴት እንደሚያፀዱ በተግባር እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ለተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎች የሚውሉ ምግቦችን ለማዘጋጀት የሚረዱ ጥሬ እቃዎች

**የምዘና ስልት:** ባህላዊ ምግቦችን ሲያዘጋጁ፣ በተራ ቁጥር ውክልና የሰጡዋቸውን ባህላዊ ምግቦች ቁጥሩ ሲጠራ ማሳየታቸውንና በተግባር እጃቸውን ሲታጠቡ መመልከት፣

## በሥራ መማር ሁለት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ጭፈራ፣ ቁጥር፣ ባህላዊ ክዋኔ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ለሕፃናት ቀላል የሆኑ የተለያዩ የሀገራችንን ማህበረሰቦች/ ብሄር ብሄረሰቦች ባህላዊ ጭፈራዎች በተግባር፣ በቪድዮ፣ በሞባይል በማሳየት አስመሥለው እንዲጨፍሩ በተግባር ያለማምዳቸውና አጨፋፈራቸውንም ተሂዙረው በመመልከት ማስተካከያ ይስጧቸው:: ስንት ባህላዊ ጭፈራዎች እንዳቀረቡ፣ የየትኛው ማህበረሰብ/ብሄርበሄረሰብ እንደሆኑ፣ በየትኛው ባህላዊ ክዋኔ ጊዜ እንደሚቀርቡ፣ ከራሳቸው ባህል ጋር በምን እንደሚመሳሰሉ/እንደሚለያዩ እንዲናገሩ ያድርጓቸው:: በመጨረሻም ሀገራችን የብዙ ባህል ባለቤት እንደሆነች ጭምር ያስገንዝቧቸው::

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችንና ማህበረሰቦችን የሚገልፁ ጭፈራዎችን የያዘ ቪድዮ

**የምዘና ስልት:** ሲጨፍሩ በመመልከት ንቃታቸዉን መዘን፣ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ

### የቃል ጥያቄዎች

- ያቀረባችሁት ባህላዊ ጭፈራ የየትኛው ማህበረሰብ/ብሄርበሄረሰብ ነው?
- በየትኛው ባህላዊ ክዋኔ ጊዜ ይቀርባል?
- በጠቅላላ ያቀረባችሁት ባህላዊ ጭፈራ ስንት ነው?
- ከናንተ ባህል ጋር በምን ይመሳሰላል/ይለያያል?

## ተግባር አራት: ተረት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ጨዋታ፣ ባህላዊ አለባበስ፣ ማህበራዊነት፣ ሩር፣ የገና ዱላ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ለሕፃናት ክፍለ ጊዜው የተረት መሆኑንና ተረቱን በፀጥታ እንዲያዳምጡ በማስታወስ ተረቱን ያንብቡላቸው::

### የተረቱ ርዕስ: ገና ጨዋታ

በድሮው ጊዜ በአንድ ትንሽ ሰፈር ውስጥ የሚኖሩ ዘጠኝ ወንድና ሦስት ሴት ሕፃናት ነበሩ:: ከነዚህም ውስጥ ሁለቱ ወንድ ሕፃናት መንታ ወንድማማች ናቸው:: ሁሉም ሕፃናት ዕድሜአቸው የተቀራረበ ነው:: የገና በዓል ከመድረሱ አራት ቀን በፊት ሁሉም የሰፈሩ ወንድ ሕፃናት ተሰባስበው የገና ዱላ ለማዘጋጀት የየራሳቸውን ጥረት በማድረግ ከአካባቢያቸው በሚገኙ ዕፅዋት እንደየአቅማቸው ቆልመም ያለ ዱላ አዘጋጁ:: ከዚያም የተለያዩ ፕላስቲኮችን አሰባስበው በመቅለል የክብ ቅርፅ እንዲይዝ በማድረግ ሩር ሰሩ:: ከዚያም በኋላ ከዚያን ቀን ጀምረው በቡድን እየተከፋፈሉ የገና ጨዋታ መጫወት ጀመሩ:: በመጨረሻም የገና በዓል በሚከበርበት ዕለት የየራሳቸውን የበዓል ልብስ ለብሰው በመውጣት በቡድን በመከፋፈል የገና ጨዋታቸውን ተጫውተው ካጠናቀቁ በኋላ በጋራ አንድ ላይ ሆነው አሲና በል አሲና ገናየ እያሉ በመጨፈር ወደ ሰፈራቸው ተመለሱ::

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የገና ዱላና ኳስ/ሞዴል

**የምዘና ስልት:** ተረቱንና መልዕክቱን/ጭብጡን በአጭሩ ሲናገሩ በማዳመጥ፣ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ

**ጥያቄዎች**

- በሰፈሩ ውስጥ ስንት ወንድና ሴት ሕፃናት አሉ? መንታ ወድማማቾችስ ስንት ናቸው? ሕፃናቱ ያዘጋጁት ምንድን ነው? ያከበሩት በዓልስ ምንድን ነው? ሕፃናቱ ምን ለብሰው ወጡ? ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ምን በማለት ጨፈሩ?

## ተግባር አምስት፡ የግል ተግባር (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ ባህላዊ አለባበስ፣ቁሳቁስ፣ክዋኔ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ለሕፃናት የተለያዩ የሥዕል መሳያ ቁሳቁሶችን በማቅረብ የመረጡትን ባህላዊ ቁሳቁስ፣ አለባበስ፣ ባህላዊ ክዋኔ እንዲሠሩ ዕድሉን በመስጠት ያበረታቷቸው። ሰርተው ሲጨርሱም ስንት ሥዕል እንደሳሉ፣ የሳሉት ሥዕል ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደሰሩት እንዲገልፁ ያድርጓቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፣ ቀለም፣ ወረቀት፣ ማስመሪያ፣ ላፒስ ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** ስዕሉን ሲስሉ በመመልከት፣ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ

**የቃል ጥያቄዎች**

- ስንት ስዕል ሳላችሁ? የሳላችሁት ስዕል ምንድን ነው? ስዕሉን ስንትና ምን ምን ዓይነት ቀለም ቀባችሁ?

## ተግባር ስድስት፡ የፕሮጀክት ሥራ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ቁሳቁስ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! በመጀመሪያ ሕፃናትን በቡድን ይክፈሏቸውና የተለያየ መስሪያ ቁሳቁሶችን በክፍል ውስጥ በማቅረብ የፈለጉትን አንድ ሞዴል ባህላዊ ቁሳቁስ ሕፃናት እንዲያዘጋጁና ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ። እርስዎም እየተዘዋወሩ እገዛና ድጋፍ ያድርጉላቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ካርቶን፣ የተቦካ ጭቃ፣ ማጣበቂያ፣ ትንንሽ እንጨቶች፣ ኮርኪ፣ ጠጠር፣ መቀስ፣ ወረቀት፣ ውሃ፣ የተለያ ቀለሞች/ቀለማት ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** የሰሯቸውን ሞዴልና አሰራራቸውን በመመልከት፣ በቃል ለምን አገልግሎት እንደሚውል በመጠየቅ

# ሁለተኛ ሳምንት

**ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት**

**አጥጋቢ የመማር ብቃት፡**

- ✓ ስሜታቸውን ይቆጣጠራሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ ድምፆችን ይለያሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ ድምፆችን ያስመስላሉ፡፡
- ✓ በቅርብ አካባቢ ስለሚገኙ ነገሮች በራስ በመተማመን ይናገራሉ፡፡
- ✓ የቅርብ አካባቢያቸውን ይጠብቃሉ፡፡
- ✓ በአካባቢያቸው የሚገኙ ጎጅ/መጥፎ ሁኔታዎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ጤናማ ስለሆኑ ምግብና መጠጦች አስፈላጊነት ይወያያሉ፡፡
- ✓ ሥዕሎችን፣ ምልክቶችን፣ የታወቁ ፊደላትንና ቃላትን ተጠቅመው ይግባባሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን ይፅፋሉ፡፡
- ✓ በአካባቢያቸው ያሉ ስነ ውበቶችን/ስነ ጥበባትን ይረዳሉ፡፡
- ✓ ለተለያዩ የስነ ጥበብና የእደ ጥበብ ስራዎች ዋጋ ይሰጣሉ፡፡

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን መቆጣጠር፣ ድምፅ መለየት፣ የቅርብ አካባቢ፣ ስርዓተ ምግብ፣ ቁጥሮችን መፃፍ፣ በፈጠራ ስራ መግለፅ/በፈጠራ መግለጽ/

## ተግባር አንድ፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የአካል እንቅስቃሴ፣ ህግ፣ ቅደም ተከተል፣

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! በመጀመሪያ ሕፃናትን ከክፍል ውጭ አሰልፈው በመውጣት ደህንነቱ ወደ ተጠበቀ የመጫዎቻ ቦታ ይዘዋቸው ይሂዱ፡፡ ከዚያም እንደቁጥራቸው ብዛት በተለያየ ቡድን ይከፋፍሏቸውና የተለያዩ ጨዋታዎችን ያጫውቷቸው፡፡

**ለምሳሌ፡** ሰኞ ማክሰኞ፣ ገመድ ዝላይ፣ የገበጣ ጨዋታ ወዘተ.

ሕፃናቱ ጨዋታውን በመጀመሪያ በራሳቸው እንዲጫወቱ በማድረግ እንዴት የጨዋታውን ህግና ቅደም ተከተል እያከናወኑ እንደሆነ ይመልከቷቸው፤ ከዚያም ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ማስተካከያ በመስጠት ተከባብረውና ተራቸውን ጠብቀው በትክክል እንዲጫወቱ ያድርጓቸውና ስንት ዓይነት ጨዋታ እንደተጫወቱና ምን እንደሚባል እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም እየተዘዋወሩ ሕፃናቱን የተለያየ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** ገመድ፣ የዕንሥራ ስባሪ፣ ትንሽ ጠፍጣፋ ድንጋይ፣ የጫማ ሶል ቁራጭ፣ ገበታ፣ ጠጠር፣ ብይ

**የምዘና ስልት፡** ሲጫወቱ መመልከትና የቃል ጥያቄ መጠየቅ

### የቃል ጥያቄዎች

- ስንት ዓይነት ጨዋታ ተጫወታችሁ? የተጫወታችሁት ጨዋታ ምን ይባላል? ማን በትክክል በህጉ መሠረት ተጫወተ? ማንስ ህጉን አላከበረም?

## የክፍል ውጭ ጨዋታ ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የአካል እንቅስቃሴ፣ ፉከራ፣ ሽለላ፣ ቀረርቶ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናትን ከክፍል ውጭ ይዘው በመውጣት በቡድን ከከፋፈሏቸው በኋላ ወላጆቻቸውን/ቤተሰቦቻቸውን ጠይቀው ያመጡዋቸውን የተለያዩ ፉከራዎች፣ ሽለላዎች፣ ቀረርቶዎች፣ ወዘተ. ተራ በተራ በየቡድናቸው እንዲለማመዱና በኋላም ለሁሉም የክፍሉ ሕፃናት እንዲያቀርቡ በማድርግ ስንት እንዳቀረቡና መቸ እንደሚቀርቡ ይጠይቋቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ፉከራዎች፣ ሽለላዎች፣ ቀረርቶዎች

**የምዘና ስልት:** ፉከራዎች፣ ሽለላዎች፣ ቀረርቶዎች፣ ወዘተ. ሲያቀርቡ በመመልከት፣ መቸ የሚቀርብ ፉከራ፣ ሽለላ፣ ቀረርቶ እንደሆነ የቃል ጥያቄ ይጠይቋቸው

## ተግባር ሁለት: መዝሙር አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ንፅህና፣ ወንድም፣ እህት፣ ትምህርት ቤት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናትን ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን መዝሙሮች እየዘመሩ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

**መዝሙር: ወንድሜ ያቆብ**

ወንዴሜ ያዕቆብ ወንድሜ ያዕቆብ ተኛህ ወይ ተኛህ ወይ
ደወል ተደወለ ተነሳ ተነሳ
እሽ እነሳለሁ እሽ እነሳለሁ
ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን በልቸ
ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ
መልካም እውቀትን እገበያለሁ
እህቴ የሺ እህቴ የሺ ተኛሽ ወይ ተኛሽ ወይ
ደወል ተደወለ ተነሽ ተነሽ
እሽ እነሳለሁ እሽ እነሳለሁ
እጄን ታጥቤ ቁርሴን በልቼ
ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን በልቸ
ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ
መልካም እውቀትን እገበያለሁ
ምንጭ: ከኢትዮጵያ ልጆች የተወሰደ

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ቴፕ፣ ሞባይል፣ ቴሌቭዥን

**የምዘና ስልት:** ሲዘምሩ በማዳመጥ፣ የቃል ጥያቄ( ቁርሳችሁን ከመብላታችሁ በፊት ምን ታደርጋላችሁ፣ ከበላችሁ በኋላ ወደ የት ትሄዳላችሁ)

## መዝሙር ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** አካባቢን መንከባከብ፣ መጠበቅ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ሕፃናትን ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን መዝሙሮች እየዘመሩ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

### መዝሙር: አካባቢያችን

አካባቢያችንን አካባቢያችንን
እንጠብቅ ሁላችን የመኖሪያችን
ጤናችን ተጠብቆ እንድንኖር ሁላችን
ትኩረት እንስጠው ሁሌም ለአካባቢያችን
ዕፅዋትና እንስሳት አምረው ደምቀው በሰፈር
ሲኖሩ ለማየት ሁሌም በመንደር
እንከባከበው አካባቢያችን
መሠረት ነውና ሁሌም ለኑራችን
ባህልና ወጉን በደንብ ለማወቅ
አካባቢያችንን ሁሌም እንጠብቅ
ስለዚህ ሕፃናት ተነሱ እንነሳ
አካባቢያችንን እንጠብቅ ሳንሳሳ

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ቴፕ፣ ሞባይል፣ ቴሌቭዥን

**የምዘና ስልት:** ሲዘምሩ በማዳመጥ፣ የቃል ጥያቄ( አካባቢያችንን መጠበቅና መንከባከብ ለምን ይጠቅመናል)

## ተግባር ሦስት: በሥራ መማር አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጎጅ ሁኔታዎች፣ ራስን መጠበቅ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በክፍል ውስጥ/ውጭ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የአንድ ቤተሰብ አባላትን የያዘ ማለትም እናት፣ አባት፣ ወንድና ሴት ልጆችና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎችንም የቤተሰብ አባላት የያዘ ቤተሰብ የተለያየ ሀላፊነቶችን

**ለምሳሌ:** ባህላቸውንና አካባቢያቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ እንዲሁም በአካባቢያቸው የሚገኙ ጎጅ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑና እንዴት ራሳቸውን እንደሚጠብቁ እንዲያካትት በማድረግ

የመስሎ ጨዋታ በራሳቸው ፍላጎት እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ከዚያም ሁሉም ቡድኖች የየራሳቸውን ተለማምደው ከጨረሱ በኋላ ለክፍሉ ሕፃናት ተራ በተራ እንዲያቀርቡ በማድረግ በእያንዳንዱ ቡድን የተነሱትን የቤተሰብ ሀላፊነቶች እንዲናገሩ በማድረግ ልምድ እንዲለዋወጡ ያድርጉ።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ለመስሎ ጨዋታው መስሪያ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** የመስሎ ጨዋታውን ሲያቀርቡ በመመልከት፣ የቃል ጥያቄ(በአካባቢያችሁ የሚገኙ ጎጅ ነገሮች ምንምን ናቸዉ እንዴት እራሳችሁን ትጠብቃላችሁ)

## በሥራ መማር ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጤናማ ምግብና መጠጦች፣ የስነ ጥበብ ስራዎች፣ የዕደ ጥበብ ስራዎች፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ ሰር በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር በክፍል ውስጥ/ውጭ ሕፃናትን በተለያየ ቡድን በማደራጀት የተለያየ ቤተሰብ እንዲመሰርቱ በማድረግ የተለያዩ በአላትን እንዴት በጋራ እንደሚያከብሩና ጤናማ የሆኑ ምግብና መጠጦች አስፈላጊነት የመስሎ ጨዋታ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የመስሎ ጨዋታው የተለያዩ ነገሮችን እንዲያካትት ያድርጉ። **ለምሳሌ:** በአላትን በተለያየ ቤተሰብ እንዴት እንደሚያከብሩ፣ የበአል ጊዜ ምርቃትን፣ በበአል ጊዜ የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን፣ በበአል ጊዜ ቤታቸውን እንዴት እንደሚያስውቡ ወዘተ.

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ለመስሎ ጨዋታው የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** የመስሎ ጨዋታውን በመመልከት፣ የቃል ጥያቄ (በበአላት ቀን የምንጠቀማቸዉ የምግብ እና የመጠጥ አይነቶችን ዘርዝሩ፣ በበአላት ቀን ከቤተሰቦቻችን ጋር በአላትን እንዴት እናከብራለን)

## በሥራ መማር ሦስት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ሽምግልና፣ ምስክር፣ አለባበስ፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ ሰር በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናትን በቡድን በማደራጀት በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች ሲጣሉ እንዴት በአካባቢው በሚገኙ ማህበረሰቦች እንደሚዳኙ/እንደሚሸመገሉ የመስሎ ጨዋታ ሰርተው በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ያድርጉ። ሕፃናት የመስሎ ጨዋታውን ሲሠሩ ቢያንስ የሚከተሉትን ነገሮች ማካተታቸውን እየተዘዋወሩ ክትትልና ድጋፍ ያድርጉ።

**ምሳሌ:** አለባበስ፣ አነጋገር/የድምፅ አወጣጥ፣ አቀማመጥ፣ ምስክር ወዘተ.

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ለመስሎ ጨዋታው የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** የመስሎ ጨዋታውን ሲያቀርቡ በመመልከት፣ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ (ስንት ሽማግሌዎች/ አባገዳዎች አሉ? ስንት ምስክሮች አሉ?)

## ተግባር አራት፡ ተረት አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ጎጅ ልማዶች

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና ፡** መምህር በመጀመሪያ ሕፃናት ተረቱን ለማዳመጥና የተረቱን ዋና ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት እንዲዘጋጁ ያድርጉ ከዚያም ተረቱ በቀስታ ለሕፃናት ያንብቡላቸው፡፡

### ተረት፡ እንጥል ቆራጩ

በድሮ ጊዜ አንድ በሰፈሩ እጅግ የተከበሩና በሕፃናት ዘንድ በጣም የሚፈሩ አቶ አድነው የሚባሉ ሰው ነበሩ፡፡ እኒህ ሰው በሚኖሩበት ሰፈርና በአካካቢያቸው እየተዘዋወሩ ሕፃናትን እንደተወለዱ/ ካደጉም በኋላ እንጥል በመቁረጥ የሚኖሩ ሰው ነበሩ፡፡ አቶ አድነው ሁልጊዜም የሕፃናቱን እንጥል የሚቆርጡት አንድ ጊዜ ባዘጋጁት፣ በየጊዜው በማይቀየር፣ በማይታጠብ/በማይቀቀልና ሁሌም ከኪሳቸው በማይለያቸው መቁረጫ ነው፡፡ ታድያ አንድ ቀን ከጓደኞቻቸው ጋር እድር ቁጭ ባሉበት አንድ የጤና ባለሙያ/ሀኪም መጥቶ ትምህርት ለመስጠት የእድሩን ሀላፊዎች አስፈቅዶ በመነሳት እንጥል መቁረጥም ሆነ ማስቀረጥ ትክክል እንዳልሆነና ጎጅ ባህል እንደሆነ፤ እንጥል የሚቆርጡ ሰዎች ሁሌም ተመሳሳይ መቁረጫ ስለሚጠቀሙ የተለያዩ በሽታዎች በቀላሉ እንደሚተላለፉ፤ በተጨማሪም እንጥላቸው የተቆረጡ ሕፃናት የድምፅ አወጣጥ ችግርና ሎሌች የተለያዩ ችግሮች እንደሚገጥማቸው በሰፊት አስረዳቸው፡፡ በመጨረሻም አቶ አድነው እጃን በማውጣት እስከዛሬ ለሰራሁት ሥራ ተፀፅቻለሁ ሕፃናት፣ ወላጆችና የጤና ባለሙያዎች ይቅርታ አድርጉልኝ በማለት ከዛሬ ጀምሮ ማልቆርጥና መቁረጫየም ይኸው በማለት ከኪሱ አውጥቶ ጣለው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** የዕንጥል መቁረጥ የሚያሳይ ስዕል/የቪድዮ ምስል

**የምዘና ስልት፡** ተረቱንና መልዕክቱን/ጭብጡን በአጭሩ ሲናገሩ በማዳመጥ፣ የቃል ጥያቄ

(እንጥል ቆራጩ ማን ይባላል? እንጥል መቁረጡን ለምን አቆመ? እንጥል መቁረጥ ለምን ጎጅ ባህል ተባለ?)

### ተረት ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ጎጅ ሁኔታዎች፣ ማህበራዊ ግንኙነት፣ ደግነት

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተረት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር በመጀመሪያ ሕፃናት ተረቱን ለማዳመጥና የተረቱን ዋና ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት እንዲዘጋጁ ያድርጉ ከዚያም ተረቱ በቀስታ ለሕፃናት ያንብቡላቸው፡፡

### ተረት፡ ባለ ፀጋው

በድሮው ጊዜ በአንድ ሰፈር ውስጥ የሚኖር አንድ ባለጸጋ/ሀብታም አቶ ለምለሙ የሚባል ሰው ነበረ፡፡ እኒህ ሰውየ የሚኖሩበት በጣም ትልቅና የሚያምር ግቢ እንዲሁም መኪና አላቸው፡፡ ታዲያ ይህ ቤተሰብ ከጎረቤቶቻቸውና ከሚኖሩበት አካባቢ ማህበረሰብ ጋር በፍፁም መገናኘት አይፈልጉም፡፡ በመሆኑም በዚህ ቤተሰብ ድርጊት ጎረቤቶቹ ሁልጊዜ ይበሳጫሉ፡፡ ነገር ግን ከዕለታት አንድ ቀን የባለፀጋ ቤት በእሳት ይያያዛል/ይቃጠላል፡፡ በዚህ ጊዜም ባለፀጋው፣ ባለቤቱና ልጆቹ ጩኸታቸውን

ያቀልጡታል። ጎረቤቶቹና የሰፈሩ ሰዎችም ጩኸቱን ሰምተው ወጠው በየቤታቸው በር ላይ ሆነው የባለፀጋው ቤት ሲቃጠል መመልከት ጀመሩ። በዚህ አጋጣሚ በሰፈሩ የሚኖሩ አንድ በዕድሜ ገፋ ያሉ፣ በጣም የተከበሩና ተሰሚነት ያለቸው ሰው ወጥተው እሳቱን በመመልከት ወደ ባለፀጋው ቤት በማምራት ላይ ሳሉ ሁሉም የሰፈሩ ሰው በየቤታቸው በር ቆመው ሲመለከቱ አዩና እናንተ ምን ሆናችኋል ኑ እንጅ እሳቱን እናጥፋ ቢሏቸው አባታችን ብቻውን እንደኖረ ብቻውን ያጥፋው አሏቸው። ቢሆንም እኚህ አባት ተቆጥተውና ገስፀው ልጆቼ ደግነትንና የሰውን ጥቅም እሳቱን አጥፍተን እናሳየው በማለት የሰፈሩን ሰው አስተባብረው እሳቱን አጠፉት። ባለፀጋውም ምንም ሀብት ቢኖረው ካለሰው ዋጋ እንደሌለው በመረዳት በድርጊቱ ተፀፅቶ ጎረቤቶቹንና የሰፈሩን ሰዎች ይቅርታ ጠይቆ በጋራ መኖር ጀመረ።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ቤት ሲቃጠል የሚያሳይ ስዕል/የቪድዮ ምስል

**የምዘና ስልት:** ተረቱንና መልዕክቱን/ጭብጡን በአጭሩ ሲናገሩ በማዳመጥ፣ የቃል ጥያቄ ( ባለፀጋው ማን ይባላል? የሰፈሩ ሰዎች ለምን እሳቱን አናጠፋም አሉ? የሰፈሩን ሰዎች እሳቱን እንዲያጠፉ ያደረጋቸው ማን ናቸው? ባለፀጋው ለምን ተፀፀቱ?)

## ተግባር አምስት: የግል ተግባር አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ ባህላዊ ቁሳቁሶች፣ መሰበር፣ መበላሸት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በመጀመሪያ ባህላዊ የሆኑ የቤት እቃዎችን በተራ ቁጥር እንዲዘረዝሩ ያድርጓቸውና በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ____ላይ እንዲፅፉ ያድርጓቸው። በመቀጠልም እያንዳንዱን ቁሳቁሶች እንዴት ሳይሰበሩ/ሳይበላሹ መያዝ እንዳለባቸው እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው። በመጨረሻም የመረጡትን ቁሳቁስ በመሣል የሚመሳሰለውን ቀለም እንዲቀቡ ያበረታቷቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፣ ወረቀት፣ቀ ለም/ቀለማት፣ ላፒስ፣ ማስመሪያ ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** ደብተራቸውን በማረም፣ ተዟዙሮ ስዕል ሲስሉና ቀለም ሲቀቡ በመመልከት፣ የቃልጥያቄ(ባህላዊ የቤት እቃዎች ምንምን ናቸዉ፣ ሳይበላሹ/ሳይሰበሩ ለማቆየት ምን ማድረግ አለብን)።

### የግል ተግባር ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ ባህል፣ ቀለማት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎችን የሚያሳይ ሥዕል፣ ቪድዮ፣ ሙዚየም ያሳዩዋቸውና ሕፃናትም ያዩዋቸውን ነገሮች በክፍል ውስጥ ተራ በተራ እየተነሱ እንዲገልፁ፣ ስንት ነገሮች እንደተመለከቱና ቀለማቸው እንዲናገሩ ካደረጓቸው በኋላ በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ____ላይ ያዩዋቸውን ነገሮች እንዲፅፉ ያድርጓቸው።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ሥዕሎች፣ ቪድዮዎች፣ ሙዚየም ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** ያዩዋቸውን ነገሮች ምንነት፣ብዛትና ቀለም ሲናገሩ በማዳመጥ፣ በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ ሲፅፉ ተዟዙሮ በመመልከት፡፡

## የግል ተግባር ሦስት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ ባህላዊ አልባሳት፣ ጭፈራ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናት የተለያዩ የኢትዮጵያን ባህል የሚያሳዩ ጭፈራዎችንና አለባበሶችን አዘጋጅተው ተራ በተራ እየወጡ እንዲያሳዩ በማድረግ ያሳዩት ጭፈራም ሆነ አለባበስ የየት አካባቢ እንደሆነና ያሳዩዋቸውን ብዛት እንዲናገሩ አድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** አልባሳት

**የምዘና ስልት:** ጭፈራዎችንና አለባበሶችን አዘጋጅተው ሲያቀርቡ በመመልከትና የየት አካባቢ እንደሆነና ብዛታቸውን ሲናገሩ በማዳመጥ፣ የቃልጥያቄ(ስንት አይነት ባህላዊ አለባበሶችንና ጭፈራዎችን አሳያችሁ ምን ምን ናቸዉ)

## ተግባር ስድስት: የፕሮጀክት ሥራ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የስነ ጥበብ ስራዎች፣ ዋጋ መስጠት፣ ቀለም፣ ባህል

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር! ለሕጻናቱን ለማነቃቃት የሚከተለውን ያዘፍኗቸው:

ማሲንቋችን ዝ ዝ ዝ

ክራራችን ክር ክር ክር

ከበሮአችን ቡም ቡም ቡም

በመቀጠልም ሕፃናት በጋራ የመማርና የመሥራት ባህላቸውን እንዲያዳብሩ በአነስተኛ ቡድን በመከፋፈል /4 6/ የሚፈልጉትን አካባቢ ባህላዊ ክዋኔ የሚገልፅ ሥዕል ሰርተው እንዲያቀርቡ ያድርጉና ስንት ስዕል እንደሳሉ፣ ምን እንደሆነ፣ ምን ዓይነት ቀለም እንደቀቡ፣ ወዘተ. እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ወረቀት፣ እርሳስ፣ ቀለም/ቀለም፣ ላፒስ ማስመሪያ ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** ስዕሉን ሲስሉ ተዟዙሮ መመልከት፣ የየት አካባቢ ባህል ነው?፣ ስንትና ምን ምን ዓይነት ቀለም ተጠቀማችሁ? ወዘተ. በማለት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

# ሦስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ፡ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት

**ንዑስ ይዘቶች፡** ራስን መቻል፣ ቃላት፣ የትናንሽ ጡንቻዎች መዳበር፣ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣ ባህላዊ ቅርሶች

## አጥጋቢ የመማር ብቃት፡

- ✓ በራስ የመመራት ችሎታቸውንና በራስ መተማመንን ዳብራሉ፡፡
- ✓ የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን በአግባቡ ይመራሉ፡፡
- ✓ መሠረታዊ የህይወት ክህሎት ተግባራትን ራሳቸውን ችለው ያከናውናሉ፡፡
- ✓ በትናንሽ ዕሁፎች ውስጥ የሚገኙ የታወቁ ቃላትን ያስታውሳሉ፡፡
- ✓ የጣት ጨዋታዎችን እጆቻቸውንና ጣቶቻቸውን በመጠቀም ተጫውተው ያሳያሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን ወይም ነገሮችን ያወዳድራሉ፡፡
- ✓ ቁጥሮችን ወይም ነገሮችን በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ፡፡
- ✓ የባህል ብዝሃነትን ያደንቃሉ፡፡
- ✓ ባህላዊ ቅርሶችን ይጠብቃሉ፡፡

## ተግባር አንድ፡ የግል ተግባር አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ቁጥር፣ በቅደም ተከተል፣ መጠን፣ ባህላዊ ቁሳቁስ፣ በራስ መመራት፣

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር! በመጀመሪያ ለማነቃቂያ እንዲሆን የሚከተለውን አጭር መዝሙር ያዘምሯቸው፡፡

**መዝሙር፡ ባህል**

ባህሌን ባህሌን ያደግሁበትን
እኔ ወደዋለሁ የኖርሁበትን/2 ጊዜ/

በመቀጠል በክፍል ውስጥ ካደራጇቸው ባህላዊ ቁሳቁሶች የፈለጉትን መርጠው በተመሳሳይ እንዲሠሩ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በማደራጀት ያስቀምጡላቸው፡፡ ቀጥሎም እየተዘዋወሩ ለእያንዳንዳቸው እገዛ ያድርጉላቸው ሲጨርሱም በአዘጋጁት ልክ ቁጥሮችን አብረው እንዲሠሩ/ እንዲጽፉ ድርጓቸው፡፡ ለምሳሌ፡ አምስት የሰራ ከ1 5 ቁጥሮችን እንዲያዘጋጅና ለእያንዳንዱ ሥራ ተራ ቁጥር በመስጠት ሁሉም ሕፃናት ሰርተው ሲጨርሱ ለክፍሉ ሕፃናት ተራ በተራ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** ካርቶን፣ እርሳስ፣ወረቀት ፣ቀለም/ቀለማት፣ ላፒስ፣ ማስመሪያ ወዘተ.

**የምዘና ስልት፡** ስራውን ሲሰሩ ተዟዙሮ በመመልከት፣ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ

**የቃል ጥያቄዎች**

- የሰራችሁትን በተራ ቁጥር ቅደም ተከተል መሠረት ተናገሩ? የሰራችሁት ምን ይባላል? ጥቅሙስ? ማን ብዙ ሰራ/ማንስ ትንሽ ሰራ? ከተመለከታችሁት ውስጥ ማን በትልቁ ሰራ/በትንሹ ሰራ?

### የግል ተግባር ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቁጥር፣ ባህል

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በክፍል ውስጥ ከተቀመጡት ባህልን ከሚገልፁ ፍለሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ ሥዕሎች መካከል እያንዳንዳቸው ሕፃናት የመረጡትን በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ ላይ ተራ ቁጥር በመስጠት እንዲፅፉ ያድርጉና ደብተራቸውን ያርሙላቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ባለቀለምእርሳስ(ክራዮን)፣ወረቀት፣ ላፒስ፣ ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** ደብተራቸውን በማረም፣ ተዟዙሮ በመመልከት

### ተግባር ሁለት: ውይይት አንድ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ምግቦች፣ ቁጥር፣ ቅደም ተከተል፣ ጤንነት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በውይይት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** ሕፃናትን በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድኖች ያደራጇቸውና በየቡድናቸው የፈለጉትን ባህላዊ ምግቦች በዝርዝር እንዲፅፉ በማድረግ ለእያንዳንዳቸው የቁጥር ውክልና/ኮድ/ በመስጠት ከትንሹ ወደ ትልቁ/ከትልቁ ወደ ትንሹ በመጥራት ለጤና ስለሚሰጡት ጥቅም፣ ስለአዘገጃጀታቸውና የየት አካባቢ ማህበረሰብ የሚጠቀምበት እንደሆነ ሪፖርት እንዲያቀርቡ/እንዲናገሩ ያበረታቷቸውና ሲጨርሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፣ ወረቀት፣ ላፒስ፣ ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** ተዟዙሮ በመመልከት፣ ሪፖርቱን ሲያቀርቡ በማዳመጥ፣ የቃል ጥያቄ(ምን ምን አይነት ባህላዊ ምግቦችን ዘረዘራችሁ ለጤና የሚኖራቸዉን ጠቀሜታ ግለፁ፡፡)

### ውይይት ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ቁሳቁሶች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ መጠን፣ ቁጥር፣ ቅደም ተከተል፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በውይይት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ሕፃናትን ለሦስት ለሦስት በማደራጀት በየተራ የሚያውቋቸውን ባህላዊ ቁሳቁሶችና ክዋኔዎች እንዲሁም ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች እንዲዘረዝሩ በማድረግ ማን ብዙ እንደዘረዘረና የማን ትንሽ እንደሆነ እንዲያወዳድሩ ያበረታቷቸውና በመጨረሻም ለክፍሉ ሕፃናት እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፣ወረቀት፣ ላፒስ፣ ወዘተ.

**የምዘና ስልት:** ተዟዙሮ በመመልከት፣ ሲያቀርቡ በማዳመጥየምታውቋቸውን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ቁሳቁሶች ተናገሩ በማለት በቃል መጠየቅ

## ተግባር ሦስት: የክፍል ውጭ ጨዋታ አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የሙዚቃ መሳሪያ፣ የጣት ጨዋታዎች፣ የባህል ብዝሃነት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ከክፍል ውጭ ይዘዋቸው በመውጣትና በቡድን በማደራጀት የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለምሳሌ: ክራር፣ ማሲንቆ፣ ከበሮ… ወዘተ. ለሕፃናት በማቅረብ መሳሪያውን በመጠቀም ባህላዊ ጨዋታዎችን/ጭፈራዎችን እንዲጫውቱ /እንዲጨፍሩ በማድረግ ተዟዙረው አብረዋቸው በመጫወት ክትትልና ድጋፍ ያድርጉ።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች

**የምዘና ስልት:** ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ሲጫወቱ ተዟዙሮ በመመልከት፣ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን እንዲዘረዝሩ እንዲሁም ጣቶቻቸውን/ እጆቻውን በመጠቃም የሚጫወቷቸው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን እንዲናገሩ በቃል መጠየቅ

### የክፍል ውጭ ጨዋታ ሁለት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ጨዋታዎች፣ የባህል ብዝሃነት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ተማሪዎችን ከክፍል ውጭ ይዞ በመውጣት በቡድን በማደራጀት በተለያየ አካባቢ/ብሄር ብሄረሰብ የሚገኙ ባህላዊ ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ዕድል ይስጧቸው። እርስዎም በመጀመሪያ ሕፃናት የመረጡትን ጨዋታ ባህላዊ መሆኑን ያረጋግጡና አጨዋወቱን በትክክል ተግበራዊ ማድረጋቸውን ይከታተሉ። ባህላዊ ጨዋታውን ሲጫወቱም መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄና ደኅንነቶች በደንብ ያስገንዝቧቸው።

ባህላዊ ጨዋታዎች ለምሳሌ: የገበጣ ጨዋታ፣ ትግል፣ የገና ጨዋታ፣ ቡብ፣ ሻህ፣ ቀስት. ወዘተ.

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የባህላዊ ጨዋታ መጫወቻ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** ሲጫወቱ ተዟዙሮ በመመልከት፣ ባህላዊ የጨዋታ አይነቶችን እንዲዘረዝሩ በቃል መጠየቅ

## ተግባር አራት በሥራ መማር (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የቤት እንስሳት፣ ባህል

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር ሕፃናትን በቡድን በማደራጀት የቤት እንስሳትን በመጠቀም ከባህል ጋር ያላቸውን ቁርኝት የሚያሳይ የመስሎ ጨዋታ ሰርተው እንዲያቀርቡ ለማድረግ ሻጭና ገዥ አድርገው ይክፈሏቸው። መስሎ ጨዋታ **ምሳሌ:** ሕፃናት ከቤታቸው ጠዋት ተነስተው፣ ልብሳቸውን ለብሰው፣ ፊታቸውን ታጥበው፣ ቁርሳቸውን በልተው የተለያዩ እንስሳትን /ፈረስ፣

አህያ፣ በቅሎ፣ በሬ፣ ግመል ወይም ሌሎች ቁሳቁሶች/ ይዘው እንዲሄዱና ገበያ ውስጥ እንዲሸጡ በማድረግ ሌሎች የቡድን አባላት ደግሞ የብር ኖቶችን በመጠቀም በመግዛት ለተለያዩ የእርሻ፣ የትራንስፖርትና ለባህላዊ ጨዋታ አገልግሎት እንዲያውሉ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የብር ኖቶች፣ ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** የመስሎ ጨዋታውን ሲያቀርቡ መመልከት፣ የቃል ጥያቄ መጠየቅ

(ማን ምን ሸጠ/ገዛ? በስንት ብር? ባለስንት ብር ኖት ተጠቀመ? የተገዛው እንስሳ ምን ይመገባል? የገዛችኋቸውን እንስሳት ለምን አገልግሎት ተጠቀማችኋቸው?)

## ተግባር አምስት: የመስክ ጉብኝት (6 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህላዊ ቅርሶች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጉብኝት፣ በተግባር፣ በዘገባ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናትን በአካባቢው ወደሚገኝ ሙዚየም በመውሰድ ሙዚየም ከሌለ በቪድዮ የተለያዩ ባህላዊ ቅርሶችን እንዲያዩ ያድርጉና የተመለከቱትን እያንዳንዱ ሕፃን ያዩትን እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡ ሲያቅርቡ የሚከተሉትን ጉዳዮች እንዲያካትቱ ያድርጉ: በያይነታቸው መመደብ፣ የሚገኙበትን አካባቢ፣ አገልግሎታቸውን፣ የተሰሩባቸው ሁኔታዎች፣ ሊደረግላቸው ስለሚገባ ጥንቃቄና ደህንነት፡፡ በመጨረሻም የመረጧቸውንና የወደዱትን ቅርስ አስመሥለው ሰርተው እንዲያመጡ ያበረታቷቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ሙዚየም፣ የቪድዮ ሥዕል

**የምዘና ስልት:** የተመለከቱትን በሪፖርት መልክ ሲያቀርቡ በማዳመጥ፣ ያያችሁት ቅርስ የት አካባቢ ይገኛል፣ አገልግሎቱስ፣ የሚደረግለትን ጥንቃቄና ደህንነት ጭምር እንዲናገሩ በቃል መጠየቅ

# አራተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ 30 ክፍለ ጊዜ/15 ሰዓት

**ንዑስ ይዘቶች:** ማኅበራዊ ግንዛቤ፣ ራስን መግለፅ፣ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳበር፣ ቅጥ፣ ጥበባዊ እሴት

## አጥጋቢ የመማር ብቃት:

- ✓ ሌሎች የተለያየ አመለካከት/እምነት ያላቸው መሆኑን ይረዳሉ፡፡
- ✓ አካባቢን የመንከባከብ ሀላፊነትን ይለማመዳሉ፡፡
- ✓ የቤተሰብ፣ የጓደኞቻቸውንና የትምህርት ቤት ማህበረሰቦችን ደህንነት ይጠብቃሉ/ እንክብካቤ ያደርጋሉ፡፡
- ✓ የምት እንቅስቃሴዎችን ያከናውናሉ፡፡
- ✓ ለተለያዩ የስነ ጥበብና የእደ ጥበብ ውጤቶች ዋጋ ይሰጣሉ፡፡

## ተግባር አንድ፡ ውይይት አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ ዘፈን፣ ዋጋ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በውይይት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ከዚህ በፊት የመማሪያ ክፍሉን በተለያዩ ባህላዊ ሥዕሎች፣ ሞዴሎች፣ ቁሳቁሶች ወዘተ. ማሳመርዎ ይታወሳል፡፡ ይህን ተግባር አሁንም በመቀጠል የበለጠ በማሳመርና በማስዋብ ሕፃናትን በቡድን በማደራጀት የሚወዱትን ባህላዊ ሙዚቃ፣ ዘፈን፣ መዝሙር በየቡድናቸው እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸውና በክፍል ውስጥ የሚመለከቷቸውን የባህል መገለጫዎች ተራ በተራ ለቡድን ጓደኞቻቸው ስለጥቅማቸውና አገልግሎታቸው ገለፃ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ እርስዎም ውይይታቸውን እየተዘዋወሩ በመመልከት እገዛና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ቡድኖች የተወያዩባቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** ባህልን የሚገልፁ ሥዕሎች፣ ፍለሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ እውነተኛ ቁሶች፣ ባህላዊ ዘፈኖች

**የምዘና ስልት፡** ውይይታቸውን በመዘዋወር በመመልከትና በቡድን የተወያዩበትን ለክፍሉ ሕፃናት ሲያቀርቡ በማዳመጥ፣የቃል ጥያቄ(ምንምን አይነት ባህላዊ ዘፈኖችን ዘረዘራችሁ የትኛዉን በይበልጥ ወደዳችሁት ስንት ዘረዘራችሁ

### ውይይት ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ መድሀኒት፣ ዕፅዋት፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በውይይት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህሩ ተግባር፡** መምህር ሕፃናትን በክፍል ውስጥ በቡድን በማደራጀት ወላጆቻቸውን/ ቤተሰቦቻቸውን ጠይቀው የመጡትን ለባህላዊ መድሀኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን በቁጥር በመዘርዘር አገልግሎታቸውን እንዲያስረዱ ያድርጓቸው፡፡ በየአካባቢያቸው የሚገኙ ለባህላዊ መድሃኒት የሚያገግሉ ዕፅዋትን እንዴት እንደሚንከባከቡ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ካደረጉ በኋላ ዕፅዋቱ ለባህላዊ መድሀኒት መቀመሚያ እንደሚያገለግሉና በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው ከተለየዩ በሽታዎች እንደሚጠብቁ ግንዛቤ ያስጨብጧቸው፡፡

በመጨረሻም የመለማመጃ ደብተራቸውን በማውጣት ገጽ ላይ የተቀመጠውን ለባህላዋ መድሀኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት ስሞችን ፃፉ የሚለውን ተግባር እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** የመለማመጃ ደብተር

**የምዘና ስልት፡** ተዟዙሮ የቡድን ውይይታቸውንና ሲጨርሱም ለክፍሉ ሕፃናት ሲያቀርቡ በማዳመጥ፣ ለባህላዊ መድሀኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን ዘርዝሩ በማለት በቃል መጠየቅ፣ በመለማመጃ ደብተራቸውንላይ የፃፉትን በመመልከትና በማረም

## ተግባር ሁለት፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ አንድ (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ምት፣ እንቅስቃሴ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ሕፃናትን ወደ ውጭ በማውጣት ከሚፈልጉት ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የተለያዩ ምቶችን እየፈጠሩ እንዲጫወቱ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ለምሳሌ፡ በሀይላንድ ውስጥ ጠጠር/አሸዋ በመጨመርና በማወዛወዝ፣ የተለያዩ ቁሶችን በማጋጨት፣ ቅል በመጠቀም፣ የተለያዩ ነገሮችን በመወጠር/በማላላት በማንቀጥቀጥ ... ወዘተ. ስልቶችን በመጠቀም የየራሳቸውን ዜማ/ ድምፅ ተጠቅመው እንዲጫወቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ያበረታቷቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** ሀይላንድ፣ ቅል፣ ጠጠር፣ አሸዋ፣ወዘተ.

**የምዘና ስልት፡** ተዟዙሮ ጨዋታቸውን በመመልከትና በማዳመጥ፣ የፈጠሯቸውን የምት ድምፆች በእንቅስቃሴ እንዲያሳዩ ማድረግ

### የክፍል ውጭ ጨዋታ ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ ዘፈን፣ ማስመሰል

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በጨዋታ፣ በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ሕፃናትን ከክፍል ውጭ በማውጣትና በትናንሽ ቡድኖች በማደራጀት ወላጆቻቸውን/አሳዳጊዎቻቸዉን /የቤተሰቦቻቸውን/የሌላ የሚያውቁትን ሰውን ድምፅ፣ አጓጓዝ / አረማመድ፣ አለባበስ፣ አጨፋፈር፣ አመካከት/እምነትና ሌሎች ሁኔታዎችን በማስመሰል የተለያ ባህላዊ ዘፈኖችን፣መዝሙሮችን፣ወዘተ በጋራ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** አልባሳትና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት፡** ተዟዙሮ ጨዋታቸውን በመመልከትና በማዳመጥ፣ አስመስለውን በተግባር እንዲዘፍኑ በማድረግ መመልከት

## ተግባር ሦስት፡ የግል ተግባር (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ፣ ቅጥ፣ ቀለም

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ሕፃናት የመለማመጃ ደብተራቸውን እንዲያወጡ በማድረግ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማን እንዲሥሉ ያግዟቸው፡፡ በመቀጠልም ሁሉንም ቀለማት እንዲቀቡ ቀለም ይስጧቸውና እንዲቀቡ በማድረግ እየተዘዋወሩ ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡ በመጨረሻም ስለባንዲራ ያላቸውን አመለካከት/እምነት ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጓቸውና የቀቡትን ቀለም በቅደም ተከተል ከታች ወደ ላይና ከላይ ወደ ታች እንዲሁም የቀቡትን ቀለም ብዛት በደብተራቸው እንዲፅፉ በማድረግ ያርሙላቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፣ ወረቀት፣ ላፒስ፣ ቀለሞች፣

**የምዘና ስልት:** ተዟዙሮ ስራቸውን በመመልከት፣ ደብተራቸውን በማረም፣የቃልጥያቄ(የኢትዮጲያ ሰንደቅአላማ ምን ምን ቀለማቶችን ይዟል? መካከል ላይ ያለዉ ኮኮብ ምንን ያመለክታል?)

## ተግባር አራት: የፕሮጀክት ሥራ (7 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የምት የሙዚቃ መሳሪያ፣ ስነ ጥበብ፣ ዕደ ጥበብ፣

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በክፍል ውስጥ/ውጭ በትናንሽ ቡድኖች በመክፈል ከባህላዊ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች ውስጥ የመረጡትን ሞዴል፣ ሥዕል፣ ቅርፅ እንዲሠሩ በማድረግ እየተዘዋወሩ እገዛና ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡ ሲጨርሱም የሰሩት ምን እንደሆነ፣ ከምን እንደተዘጋጀ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውል እንዲያስረዱ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ካርቶን፣ እንጨት፣ ጭቃ፣ ክር/ሲር…

**የምዘና ስልት:** ተዟዙሮ ሲሠሩ በመመልከት፣ የቃል ጥያቄ (የሰራችሁት ስራ ምንድን ነው? ከምን ተዘጋጀ? ለምን አገልግሎት ይውላል?)

## ተግባር አምስት: በሥራ መማር አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** አመለካከት/እምነት፣ መዳኘት፣ መንከባከብ፣ መረዳዳት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና :** መምህር በመጀመሪያ የክፍሉን ሕፃናት ለሁለት ቡድን በመክፈል አንደኛው ቡድን ባህል ጠቃሚ ነው የሚለውን ሀሳብ ሌላኛው ቡድን ደግሞ ባህል ጠቃሚ አይደለም የሚለውን ሀሳብ ይዘው በየተራ እየተነሱ እንዲከራከሩ ያድርጓቸው፡፡ ይህንን ክርክር የሚዳኙ ሶስት ሕፃናትን በመምረጥ የሁለቱ ቡድን አባላት የሚያቀርቡትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ አሸናፊውን እንዲያሳውቁ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ሁለት ቡድኖች በመከራከር ሲዳኙ የሚያሳይ ስዕል፣ የቪድዮ ምስል

**የምዘና ስልት:** የሁለቱን ቡድኖች ክርክርና የዳኞችን ውሳኔ በማዳመጥ፣ ስለባህል ጠቀሜታና ጉዳት የየራሳቸውን አመለካከት/እምነት እንዲገልፁ በቃል መጠየቅ

### በስራ መማር ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የሙዚቃ መሳሪያ፣ መዳኘት

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ሕፃናትን በክፍል ውስጥ በቡድን በማደራጀት የተለያዩ ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎችን እንዲጫወቱ ያድርጓቸውና ይህንን ተግባር በክፍል ውስጥ ለመዳኘት በመጀመሪያ ሦስት ሕፃናትን እንዲመርጡና ውድድሩን እዲዳኙ ያድርጉ፡፡ ውድድሩን የሚዳኙ ዳኞችን ተግባርና ሀላፊነት ግንዛቤ ይፍጠሩላቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች

**የምዘና ስልት:** የመስሎ ጨዋታውን በመመልከትና የዳኞችን ሀሳብ በማዳመጥ፣ ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን ሲጫወቱ በመመልከትና በማዳመጥ

## በሥራ መማር ሶስት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** መንከባከብ፣ መረዳዳት፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**መምህር ተግባር:** መምህር የክፍሉ ሕፃናትን በትናንሽ ቡድኖች ይክፈሏቸውና የመስሎ ጨዋታ እንዲጫወቱ ያድርጓቸው። በመስሎ ጨዋታው አንድ ሕፃን የመምህርን ተግባር (ተማሪዎችን ማስተማር፣ መንከባከብ፣ መርዳት ወዘተ.) እንድታከናውን/እንዲያከናውን ሌሎች ደግሞ ተማሪ በመሆን መምህር በመሆን ከ1 20 ያሉ ቁጥሮችን በደብተራቸው እንዲፅፉ የክፍል ስራ መስጠትና ተማሪዎች ደግሞ እንዲሰሩ ማድረግ። ነገር ግን አንድ ሕፃን እርሳስ ሳይዝ የመጣ ስለሆነ ሌሎች እንዲያውሱት እንዲጠይቅና ከመካከላቸው አንደኛው በራሱ በጎ ፈቃድ እንዲሰጠውና እንዲሠራ በማድረግ እርስ በርሳቸው መረዳዳት የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ እንዲረዱ ያድርጉ።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** እርሳስ፣ ጋወን፣ ደብተር

**የምዘና ስልት:** የመስሎ ጨዋታውን ሲያቀርቡ በመከታተል/በመመልከት

# አምስተኛ ሳምንት

## ለሳምንቱ የተሰጠው ጊዜ 30 ክፍል ጊዜ/5 ሰዓት

## አጥጋቢ የመማር ብቃት:

- ✓ ደንቦችንና ስምንነቶችን በመከተል ከሌሎች ጋር በአክብሮት ይጫወታሉ።
- ✓ በባህላቸው ውስጥ ያሉ ጥሩና መጥፎ ሁኔታዎችን/ነገሮችን ይለያሉ።
- ✓ ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችላቸውን የግብረ ገብ እሴቶች ያጎለብታሉ ።
- ✓ የፊደላትን ድምፆችና ምስሎች/ሥዕሎችን በማዛመድ ቃላትን ይወክላሉ።
- ✓ ተረቶችና እንቆቅልሾችን እርስ በእርሳቸው በማውራት ትርጉማቸውን ይገልጻሉ።
- ✓ ከላይ ከታች፣ ከግራ ከቀኝ፣ ከፊት ከኋላ የሚሉትን የቦታ መገኛ ፅንሰ ሀሳቦች ይናገራሉ።
- ✓ ባህላዊ ቁሳቁሶችን በተለያየ ምድብ ይመድባሉ።
- ✓ ጥበባዊ ገለፃዎችን ይለማመዳሉ።

**ንዑስ ይዘቶች:** የግንኙነት ክህሎት፣ የግብረ ገብ እሴት፣ የፊደላት ድምፅ ግንዛቤ፣ ሰውሰራሽና ተፈጥሯዊ አካባቢዎ፣ የቦታ ግንዛቤ፣ መመደብና መደርደር/ማስቀመጥ

## ተግባር አንድ፡ ውይይት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ ቁሳቁስ፣ ቃል፣ ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በውይይት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር በመጀመሪያ ሕፃናትን ለማነቃቃት ያክል እርስዎ ከሚያውቁት አንድ እንቆቅልሽ ወይም ቀልድ ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠልም አንድ አንድ ሕፃን በተራ እየተነሱ የባህላዊ ቁሳቁሶችን ስም የመጀመሪያ ፊደል ብቻ እንዲጠሩ በማድረግ ሌሎች ደግሞ አሟልተው ትክክለኛውን ቃል ከጠሩ በኋላ ባለስንት ሆሄ ቃል እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ፡ “ጋ” ን በመጥራት “ን”ን ጨምረው ጋን እንዲሉና ባለ ሁለት ሆሄ ቃል እንደሆነ እንዲናገሩ ካደረጉ በኋላ የጠሯቸውን የባህላዊ ቁሳቁሶች ስዕል ስለው ቀለም እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ___ላይ ያልተሟሉ ፊደላትን አሟሉ የሚለውን ተግባር እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡** ፊደላትንና ቃላትን የያዘ ፍለሽ ካርድ፣ እርሳስ፣ ላፐስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት

**የምዘና ስልት፡** ውይይት ሲያደርጉ ተዟዙሮ በመመልከት፣ የቃል ጥያቄ (ለተጠራው የመጀመሪያ ፊደል አሟልተው ቃሉን እንዲጠሩ፣ ባለስንት ሆሄ ቃል እንደሆነ እንዲናገሩ በማድረግ)፣ የጠሯቸውን የባህላዊ ቁሳቁሶች ስዕል ስለው ቀለም ሲቀቡ በመመልከት

## ተግባር ሁለት፡ የግል ተግባር አንድ (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ አልባሳት

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር በመጀመሪያ ለሕፃናት ለመስሪያ የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ያቅርቡላቸው፡፡ በመቀጠልም ሁሉም ሕፃናት የሚያስታውሷቸውን ባህላዊ አልባሳት ስማቸውን መዘርዘርና ከጎን ደግሞ ምስላቸውን በመሣል ተስማሚ ቀለም እንዲቀቡ በማድረግ እርስዎም እየተዘዋወሩ ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው ሲጨርሱም የየት አካባቢና በምን ጊዜ የሚለበስ ባህላዊ አልባሳት እንደሀነ እንዲናገሩ በማድረግ የሰሩትን ሥራ ያርሙላቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁሶች፡** ወረቀት፣ እርሳስ፣ ላፒስ፣ ማስመሪያ፣ ቀለም

**የምዘና ስልት፡** የባህላዊ አልባሳትንና ቁሳቁሶችን ስም ፅፈው ከምስላቸው ጋር ሲያዛምዱ በመመልከት፣ የየት አካባቢና በምን ጊዜ የሚለበስ ባህላዊ አልባሳት እንደሆነ ሲናገሩ ማዳመጥና የሰሩትን ስራ ማረም

## የግል ተግባር፡ ሁለት (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት፡** ባህላዊ ምግብ፣ የዘወትር ምግብ

**የማስተማሪያ ዘዴ፡** በተግባር፣ በጨዋታ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና፡** መምህር ሕፃናት ባህላዊ ምግቦችንና የዘወትር/የተለመዱ ምግቦችን እንዲለዩና

ጤናችንን ለመጠበቅ ያላቸውን ፋይዳ እንዲረዱ ለማድረግ የተለያዩ ባህላዊና የዘወትር ምግቦችን የያዙ የመጫዎቻ ካርዶች በማዘጋጀት የተለያዩ ካርዶችን እርስዎ እያሳዩ ሕፃናት ተራ በተራ እየተነሱ ያሳዩዋቸው ካርድ ምን እንደሆነ እንዲናገሩና ለጤናቸው ያለውን ጥቅምና ከየትኛው የምግብ ምድብ ውስጥ እንደሚመደብ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዳቸው ስንት ስንት እንደመለሱ መዝግበው በመያዝ በመካከላቸው የውድድር ስሜት እንዲያዳብሩ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የተለያዩ ባህላዊና የዘወትር ምግቦችን የያዙ የመጫዎቻ ካርዶች

**የምዘና ስልት:** የመጫዎች ካርዶችን ሲያሳዩ መመልከት፣ ላሳዩት የመጫዎቻ ካርድ የሚሰጡትን ማብራሪያ ማዳመጥ፣ ባህላዊና የተለመዱ/የዘወትር ምግቦችን እንዲዘረዝሩ በቃል መጠየቅ

## ተግባር ሦስት፡ ተረት (4 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጥሩና መጥፎ ሁኔታዎች፣ የግብረ ገብ እሴቶች

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በተረት፣ በገለፃ፣ በማስመሰል፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** ውድ መምህር ለሕፃናት ተረቱን ያንብቡላቸው፡፡

**የተረቱ ርዕስ:** ጓደኛሞች

በድሮው ጊዜ በአንድ ሰፈር ውስጥ የሚኖሩ አራት ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ስማቸውም እሌኒ፣ ማንደፍሮ፣ ተስፋሁንና ናታን ይባላሉ፡፡ እነዚህ ጓደኛሞች የሚማሩት በአንድ ትምህርት ቤት ይሁን እንጅ ክፍላቸው የተለያየ ነበር፡፡ እሌኒና ተስፋሁን ወደ ትምህርት ቤት በሚሄዱበትና በሚመለሱበት ጊዜ በመንገድ ላይ ትልቅ ሰው ሲያዩ መንገድ ቆመው ያሳልፋሉ፡፡ ማንደፍሮና ናታን ግን ሰዎችን ሳይጠብቁ ቀድመው በማለፍ እነዚህ ሽማግሌዎች ተጎትተው እስኪያልፉ ትጠብቃላችሁ ብለው እሌኒና ተስፋሁንን ያሾፉባቸዋል፡፡ እነሱም ትላልቅ ሰዎችን ማክበር እንዳለባቸው ለማስረዳት ይሞክራሉ፡፡ በጣም ይገርማችኋል ማንደፍሮና ናታን ወላጆቻቸውን አያከብሩም ሥራም ሲታዘዙ ለመሥራት ፈቃደኛ አይሆኑም እንዲሁም ሰፈር ውስጥ ከሌሎች ሕፃናት ጋር ይደባደባሉ በተጨማሪም ትምህርት ቤት ውስጥ የሌሎች ሕፃናትን ደብተር፣ መፃፍና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመቀማትና በመስረቅ ይታወቃሉ፡፡ በመሆኑም የዓመቱ ትምህርት ሲጠናቀቅ እሌኒና ተስፋሁን ትምህርታቸውን ያጠኑ ስለነበር በጣም ጥሩ ውጤት ሲያስመዘግቡ ማንደፍሮና ናታን ግን ወደ ሚቀጥለው ክፍል ማለፍ ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** የግብረ ገብ እሴቶችን የሚያሳይ ቻርት/ስዕል

**የምዘና ስልት:** የቃል ጥያቄ (አራቱ የአንድ ሰፈር ልጆች እነማን ናቸው? በጣም ጎበዝና ጨዋ የሆኑት እነማን ናቸው ምንስ አደረጉ? ሰነፍ፣ ለወላጆቻቸው ማይታዘዙና ታላላቆቻቸውን የማያከብሩት እነማን ናቸው? ከዚህ ተረት ምን ተረዳችሁ/ተማራችሁ?)

## ተግባር አራት፡ መዝሙር አንድ (1 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ባህል፣ ጥበባዊ ገለፃ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በመጀመሪያ ተማሪዎች መዝሙሩን ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ በማድረግ ያዘጋጁትን መዝሙር እርስዎ በመዘመር/በቴፕ፣ በሞባይል ወይም በሌላ ነገር ቀርፀው ያሰሟቸውና ሕፃናትም ስንኝ በስንኝ እየዘመሩ እንዲለማመዱና በመጨረሻም ብቻቸውን በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉ።

**መዝሙር: ውብ ባህላችን**

በሸለቆ ላይ ሰንጓዝ
ወንዙ ተራራው ሚያፈዝ
አቤቱ ጌታ የአምላክ ሥራ
ስንቱ ይወራ ስንቱ ያውራ
ሴቶች ልበሱ ያገር ልብስ
ወኔ ደስታችን ይቀስቀስ
ወንዶች ልበሱ ያገር ልብስ
ማፈሩ ይቅር መወቀስ
ውብ ባህላችን ያኮራናል
ልዩነታችን ያምርብናል።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ቴፕ፣ ሞባይል

**የምዘና ስልት:** መዝሙሩን ሲዘምሩ በማዳመጥና ፣የቃል ጥያቄ (የመዝሙሩ መልዕክት ምንድን ነው? በመዝሙሩ የተገለፁ ውብ ባህሎችን ተናገሩ?)

## መዝሙር ሁለት (2 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ኢትዮጵያ፣ ጥበባዊ ገለፃ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በመጀመሪያ ተማሪዎች መዝሙሩን ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ በማድረግ ያዘጋጁትን መዝሙር እርስዎ በመዘመር/በቴፕ፣ በሞባይል ወይም በሌላ ነገር ቀርፀው ያሰሟቸውና ሕፃናትም ስንኝ በስንኝ እየዘመሩ እንዲለማመዱና በመጨረሻም ብቻቸውን በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉ።

**መዝሙር: ኢትዮጵያ**

ኢትዮጵያ ማለት ጥበብ ናት
ሁሉም ሊለብሳት ሚጓጓት ሚጓጓት
የብዙ ሺ ዓመት ታሪክ ያላት
የብዙ ቅርሶች ባለቤት ናት
ኢትዮጵያ ማለት ውበት ናት
ሁሉም ሰው ሊያያት ሚጓጓት ሚጓጓት
ጀግኖች ልጆችሽ የሚያኮሩሽ
ከጠላት ሁሉ ሚጠብቁሽ

ኢትዮጵያ ማለት ጀግና ናት
ሁሉም ሊሆናት ሚጓጓት ሚጓጓት
አንች ሀገራችን ኢትዮጵያ
አንች ነሽና ባለሙያ
እንማራለን ጠንክረን
እንድናኮራሽ ኩሪልን ኩሪልን።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ቴፕ፣ ሞባይል

**የምዘና ስልት:** መዝሙሩን ሲዘምሩ በማዳመጥና ፣የቃል ጥያቄ (የመዝሙሩ መልዕክት ምንድን ነው? በመዝሙሩ ስለኢትዮጵያ የተገለፁ ነገሮችን ተናገሩ?)

### መዝሙር ሶስት (1 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ቅርስ፣ ጥበባዊ ገለፃ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በመዝሙር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በመጀመሪያ ተማሪዎች መዝሙሩን ለማዳመጥ እንዲዘጋጁ በማድረግ ያዘጋጁትን መዝሙር እርስዎ በመዘመር/በቴፕ፣ በሞባይል ወይም በሌላ ነገር ቀርፀው ያሰሟቸውና ሕፃናትም ስንኝ በስንኝ እየዘመሩ እንዲለማመዱና በመጨረሻም ብቻቸውን በጋራ እንዲዘምሩ ያድርጉ።

**መዝሙር: ቅርሶቻችን**

ዳሸን ተራራ፣ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ሶፎሞር
ጎንደር ቤተ መንግስት፣ ጅማ አባጅፋር
የጀጎል ግንብ፣ የሉሲ ሀገር
ለትውልድ እንዲሸጋገሩልን
እንክባከባቸው የታሪክ መዳረሻዎቻችን
የትናንት፣ የዛሬ፣ የነገ ኢትዮጵያ የታሪክ ምሳሌዎቻችን።

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ቴፕ፣ ሞባይል

**የምዘና ስልት:** መዝሙሩን ሲዘምሩ በማዳመጥና ፣የቃል ጥያቄ (የመዝሙሩ መልዕክት ምንድን ነው? በመዝሙሩ የተገለፁ ቅርሶችን ተናገሩ?)

## ተግባር አምስት: የክፍል ውስጥ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** የቦታ መገኛ፣ ባህላዊ ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ ምግብ፣ የሙዚቃ መሳሪያ፣ቁጥር

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር በመጀመሪያ ሕፃናትን በትናንሽ ቡድኖች ይከፋፏቸውና በየቡድናቸው እንዲቀመጡ ያድርጉ። በመቀጠልም እያንዳንዱ ቡድን በመካከላቸው አንድ አንድ ጠረጴዛ እንዲያስቀምጡ ያድርጉና የተለያዩ ባህላዊ ቁሳቁሶችን፣ አልባሳትን፣ ምግቦችንና የሙዚቃ

መሳሪያዎችን የያዙ ካርዶችን ከጠረጴዛው ከላይ ወይም ከታች፣ ከፊት ወይም ከኋላ፣ ከግራ ወይም ከቀኝ በማስቀመጥ ያስቀመጡት ካርድ የሚገኝበትን ቦታና ብዛቱን ተራ በተራ በመናገር እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁስ:** ባህላዊ ቁሳቁሶችን፣ አልባሳትን፣ ምግቦችንና የሙዚቃ መሳሪያዎችን የያዙ ካርዶች

**የምዘና ስልት:** እየተዘዋወሩ በየቡድናቸው የነገሮችን መገኛ ቦታ በመናገር ሲጫወቱ መመልከት፣ የቃል ጥያቄ (ካርዱ ከጠረጴዛው የት ይገኛል? የተቀመጠው ካርድ ምንን ይወክላል? ስንት ካርድ ተቀምጧል?)

## ተግባር ስድስት፡ የፕሮጀክት ሥራ (11 ክፍለ ጊዜ)

**ቁልፍ ቃላት:** ጥበባዊ ገለፃ፣ ባህልዊ አልባሳት፣ ጭፈራ፣ ምግብ፣ ቁሳቁስ

**የማስተማሪያ ዘዴ:** በጨዋታ፣ በተግባር፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

**የመምህር ሚና:** መምህር ይህ ወቅት የዓመቱ የትምህርት መጠናቀቂያ በመሆኑና የአውዳችንም የመጨረሻ ሳምንት የመጨረሻ ተግባር ስለሆነ ሕፃናት በዚህ ዐውድ የተለያዩ የሀገራቸውን ባህል ያወቁ በመሆናቸው ባህላቸውን የበለጠ እንዲወዱና እንዲያደንቁ ለማድረግ ሕፃናት ፌስቲቫል ለማዘጋጀት በቡድን ይከፋፍሏቸውና የተለያየ ተግባራትን ይስጧቸው፡፡

**ለምሳሌ:** የተለያዩ የሀገራችን ባህላዊ አለባበሶች፣ ጭፈራዎች፣ ቁሳቁሶች፣ ምግቦች ወዘተ.

በመጨረሻም ሕፃናት በደንብ እንዲያዘጋጁ፣ እንዲለማመዱና እንዲዘጋጁ በመከታተልና በመደገፍ በማድረግ ሌሎች እንግዶችን በመጋበዝ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

**የመማር ማስተማርና የመጫዎቻ ቁሳቁሶች:** ፌስቲቫሉን ለማቅረብ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

**የምዘና ስልት:** በየቡድናቸው የተሰጣቸውን ስራ ሲለማመዱና ፌስትባሉን ሲያቀርቡ መመልከት፣ በፌስቲቫሉ ያላቸዉን ስሜት በመመልከት

# የአውድ ማጠቃለያ ምዘና ቅጽ

የተማሪ ስም____________________ጾታ_______እድሜ_______ደረጃ_______

**መግለጫ:** ከተቀመጡት አማራጮች መካከል ሕፃናቱ ባሟሉት ብቃት ትይዩ የ "✓" ምልክት በማድረግና ዝቅተኛ በሆኑት ብቃቶች ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | የመማር ውጤቶች | የምልከታ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | ጥሩ | በ.ጥሩ | እ.በ.ጥሩ |
| 1 | ማኅበራዊ ክህሎት አዳብረዋል፡፡ | | | | |
| 2 | ስሜታቸዉንና ፍላጎታቸዉን በራስ በመተማመን መናገር ችለዋል፡፡ | | | | |
| 3 | ጤናንና ደህንነትን ለመጠበቅ መሰረታዊ የግል ንፅህና መመሪያዎችንና የደህንነት ክህሎቶችን ተግብረዋል፡፡ | | | | |
| 4 | የቅርብ አካባቢያቸዉን መጠበቅ ችለዋል፡፡ | | | | |
| 5 | ከመማር ይዘቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለያዩ ሥነጥበባዊ ተግባራትን በመስራት ይዝናናሉ፡፡ | | | | |
| 6 | ቃላቶችን ያነባሉ፣ ይፅፋሉ፡፡ | | | | |
| 7 | ቁጥሮችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ | | | | |

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻም፦______________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION